# የዮሐንስ ወንጌል

*መግቢያ*

*አስተዋፅኦ*

የሎጎስ (ቃል) መቅድም (1፥1-18)

I. ክርስቶስን ከእስራኤል ጋር ማስተዋወቂያ (1፥19-51)
   (ሀ) በመጥምቁ ዮሐንስ (1፥19-39)
   (ለ) ለመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት (1፥37-51)

II. ክርስቶስ ለእስራኤል ያሳያቸው ምልክቶች፣ ያደረጋቸው ንግግሮችና የደረሰበት ተቃውሞ (2፥1—12፥50)
   (ሀ) የክርስቶስ ለእስራኤል መገለጥ (2፥1—11፥46)
      1. የመጀመሪያ ምልክት፤ ውሃን ወደ ወይን ጠጅ መለወጡ (2፥1-11)
         አፍታ (2፥12)
      2. በኢየሩሳሌም ለነበሩ አይሁድ የመጀመሪያው ምስክርነት (2፥13-25)
         የፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም (2፥23-25)
      3. የመጀመሪያ ንግግር፤ ስለ አዲስ ልደትና አዲስ ሕይወት (3፥1-21)
         አፍታ፥ ስለመጥምቁ ዮሐንስና ስለ ኢየሱስ (3፥22—4፥3)
      4. ሁለተኛው ንግግር፤ የሕይወት ውሃ (4፥4-22)
         አፍታ፤ በገሊላ (4፥43-45)
      5. ሁለተኛው ምልክት፥ የሹሙ ልጅ መፈወስ (4፥46-54)
         በዓል በኢየሩሳሌም (5፥1)
      6. ሦስተኛው ምልክት፥ በሰንበት ቀን በቤተሳይዳ የሽባው ሰው መፈወስ (5፥2-18)
      7. ሦስተኛው ንግግር፥ የክርስቶስ የመለኮት ልጅነት (5፥19-47)
      8. አራተኛው ምልክት፤ የአምስት ሺህ ሰዎች መመገብ (6፥1-15)
      9. አምስተኛው ምልክት፥ በውሃ ላይ መራመድ (6፥16-21)
      10. አራተኛው ንግግር፤ የሕይወት እንጀራ (6፥22-59)
      11. የደቀ መዛሙርቱ መፈተን (6፥60-71)
         አፍታ (7፥1)
      12. የዳስ በዓል በኢየሩሳሌም (7፥2-36)
      13. አምስተኛው ንግግር፤ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ (7፥37-52)
         ስታመነዝር የተያዘችው ሴት (7፥53—8፥11)
      14. ስድስተኛው ንግግር፤ የዓለም ብርሃን (8፥12-30)
      15. ከአይሁድ ጋር የተደረገ ክርክር (8፥31-59)
      16. ስድስተኛው ምልክት፥ ዕውር ሆኖ የተወለደው ሰው መፈወስ (9፥1-41)
      17. ሰባተኛው ንግግር፤ መልካሙ እረኛ (10፥1-21)
         የቤተመቅደስ መታደስ በዓል በኢየሩሳሌም (10፥22-42)
      18. ሰባተኛው ምልክት፥ የአልዓዛር ከሞት መነሣት (11፥1-46)
   (ለ) እስራኤላውያን ክርስቶስን መቃወማቸው (11፥47—12፥50)

III. ክርስቶስና የአዲስ ኪዳን ሕዝብ መጀመሪያ (13፥1—20፥29)
   (ሀ) የመጨረሻው እራት (13፥1—14፥31)
      1. የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠብና ከዚያም በኋላ የተደረጉ ንግግሮች (13፥1-38)
      2. ኢየሱስ፥ ወደ አብ የሚያደርሰው መንገድ (14፥1-31)
   (ለ) ስለ እውነተኛው የወይን ግንድና ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ማድረግ ስለሚያስገኘው ውጤት የተደረገ ንግግር (15፥1—16፥33)።
   (ሐ) ኢየሱስ ስለ ራሱና ስለ አዲስ ኪዳን ሕዝብ መቀደስ የጸለየው ጸሎት (17፥1-26)
   (መ) መከራን የሚቀበለው አገልጋይ (18፥1—19፥42)

1. *መያዙ* (18፥1-12)
2. *የአይሁድ ፍርድ* (18፥13-27)
3. *የሮማውያን ፍርድ* (18፥28—19፥16)
4. *ስቅለቱ* (19፥17-37)
5. *ቀብሩ* (19፥38-42)

(*ሠ*) *ከሞት የተነሣው ጌታ* (20፥1-29)

*የወንጌሉ ጸሐፊ ዐላማ መግለጫ* (20፥30-31)

*መደምደሚያ* (21፥1-25)

**ጸሐፊው፤** *ዮሐንስ*

**ዐቢይ ሐሳብ፤** *ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *80—95 ዓ.ም.*

### *ታሪካዊ ዳራ*

ከአራቱ ወንጌሎች ውስጥ የዮሐንስ ወንጌል የተለየ ነው። ሌሎቹ ሦስቱ ወንጌሎች ያልጠቀሱትን ኢየሱስ በይሁዳና በኢየሩሳሌም የፈጸመውን አገልግሎት የዮሐንስ ወንጌል ይዞአል፤ በተጨማሪም የክርስቶስን የማንነት ምስጢር በስፋት ገልጦአል። ጸሐፊው፣ "ኢየሱስ ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር" በመባል በተዘዋዋሪ መንገድ ተጠቅሶአል (13፥23፤ 19፥26፤ 20፥2፤ 21፥7:20)። ከራሱ ከወንጌሉ ማስረጃነትና ከጥንቱ የክርስትና ትምህርት በመነሣት፣ ይህ ወንጌል ከመጀመሪያዎቹ ዐሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ለኢየሱስ በጣም ከሚቀርቡት (ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ) አንዱ በሆነው በዘብዴዎስ ልጅ በዮሐንስ እንደ ተጻፈ መረዳት ይቻላል።

በርካታ ጥንታዊ የመረጃ ምንጮች እንደሚያመለክቱት፣ ሐዋርያው ዮሐንስ በሸመገለበት ወቅት በኤፌሶን በሚኖርበት ጊዜ በእስያ የሚኖሩ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ይህን ወንጌል ይጽፍ ዘንድ ጠየቁት። ይህም የሆነው፣ አንድ ሴሪንተስ የተባለ አይሁድ የኢየሱስን መለኮትነትና ማንነት በሚመለከት ሕዝቡን ለማሳመን የነዛውን አደገኛ ኑፋቄ ለመከላከልና ለመቃወም ነው። የዮሐንስ ወንጌል ቤተክርስቲያን፣ እውነተ በክርስቶስ ትሥጉት መገለጡን የምታበሥርበት ጥልቅ ሥነ መለኮታዊ መግለጫ ሆኖ ያገለግላል።

### ዐላማ

ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈበትን ዐላማ በምዕ 20፥31 ላይ፤ "ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ ሆነ እንድታምኑ፣ አምናችሁም በስሙ ሕይወት እንዲኖራችሁ ይህ ተጽፎአል" ሲል ይገልጻል። የወንጌሉ ጥንታዊ የግሪክ ጽሑፎች ሰዋሰው፣ ጊዜን በሚመለከት "እንድታምኑ" (20፥31) ተብሎ የተተረጐመውን ቃል በአንድ ወይም በሁለት መንገድ ተጠቅሞበታል፤ ይህም ይሁንታዊ ምኞትን ገላጭ በሆነ መልኩ ("ማመን ትጀምሩ ዘንድ") በሚልና አሁን እየቀጠለ ስላለ ነገር ምኞትን ገላጭ በሆነ መልኩ ("ማመናችሁን ትቀጥሉ ዘንድ") በሚለው ነው። ዮሐንስ ለማለት የፈለገው የመጀመሪያውን አባባል ከሆነ፣ ወንጌልን የጻፈው ያላመኑ ሰዎች በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ይድኑ ዘንድ ነው፤ ነገር ግን ለማለት የፈለገው ሁለተኛውን አባባል ከሆነ፣ ወንጌሉን የጻፈው የሐሰት ትምህርት ቢስፋፋም እንኳ አማኞች ወደ አብና ወደ ልጁ ኅብረት በሙላት ይገቡና የእምነት መሠረታቸውንም ያጠናክሩ ዘንድ ነው (ከ17፥3 ጋር ያነጻጽሩ)። ምንም እንኳ እነዚህ ሁለት ዐላማዎች ከወንጌሉ ድጋፍ የሚያገኙ ቢሆንም፣ የወንጌሉ ጠቅላላ ይዘት የኋለኛውን ሐሳብ እንደ ዋነኛ ዐላማ አድርጎ አጽንዖት ይሰጠዋል።

### ቅኝት

ይህ አራተኛ ወንጌል ኢየሱስ ክርስቶስ የእስራኤል መሲሕና ሥጋ የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ስለ መሆኑ ልዩ የሆነ ማስረጃን በጥንቃቄ ያቀርባል። ማስረጃውም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤ (1) ሰባት ምልክቶች (2፥1-11፤ 4፥46-54፤ 5፥2-18፤ 6፥1-15፤ 6፥16-21፤ 9፥1-41፤ 11፥1-46) እና ኢየሱስ እውነተኛ ማንነቱን ቁልጭ አድርጎ የገለጠባቸው ሰባት ንግግሮች (3፥1-21፤ 4፥4-42፤ 5፥19-47፤ 6፥22-59፤ 7፥37-44፤ 8፥12-30፤ 10፥1-21)። (2) ሰባት "እኔ" (እኔታዊ) መግለጫዎች (6፥35፤ 8፥12፤ 10፥7፤ 10፥11፤ 11፥25፤ 14፥6፤ 15፥1)፤ ክርስቶስ በእነዚህ ዘይቤአዊ ንግግሮችም እርሱ ለሰው ዘር ቤዛ ለመሆን

ያለውን ዐላማ ገልጾአል፡፡ (3) የኢየሱስ የሥጋ ትንሣኤ፥ ይህ፣ "ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔርም ልጅ" (20፥31) ለመሆኑ የመጨረሻው ምልክትና የፍጻሜው ማስረጃ ነው፡፡

ወንጌሉ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፤ (1) ምዕራፍ 1—12 የክርስቶስን ትምህርትና የይፋ አገልግሎት የሚናገር ክፍል ነው፡፡ ምንም እንኳ ኢየሱስ ሰባት አሳማኝ ምልክቶች፣ ግልጽ የሆኑ ሰባት ንግግሮችና ሰባት አስገራሚ እኔታዊ ("እኔ") መግለጫዎች ቢያቀርብም አይሁድ መሲሕነቱን አልተቀበሉትም፡፡ (2) ኢየሱስ በብሉይ መጻሕፍት የኪዳኑ ሕዝብ በሆኑት እስራኤላውያን ስለተገፋ ለአዲስ ኪዳን ሕዝብ (ለመሠረታት ቤተክርስቲያን) ትንሰስ ወደሆኑት ደቀ መዛሙርት ዘወር አለ (ምዕ 13፥21)፡፡ እነዚህ ምዕራፎች የጌታን እራት (ምዕ 13)፣ የመጨረሻ ንግግሮችና (ምዕ 14—16) የመጨረሻ ጸሎት ያጠቃልላሉ (ምዕ 17)፡፡ ስለዚህ አዲስ ኪዳን የተጀመረውና የተመሠረተው በክርስቶስ ሞትና (ምዕ 18—19) ትንሣኤ (ምዕ 20—21) ነው፡፡

## ልዩ ገጽታ

የዮሐንስ ወንጌልን ልዩ የሚያደርጉት ስምንት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) የኢየሱስን መለኮትነት ለመግለጽ፣ "የእግዚአብሔር ልጅ ነው" በማለት አጽንዖት ይሰጥበታል፡፡ "የአንድያ ልጅን ክብር አየን" (1፥14) ከሚለው የዮሐንስ ወንጌል የመክፈቻ ታላቅ ዐዋጅ አንሥቶ ቶማስ፣ "ጌታዬ አምላኬም" (20፥28) ብሎ እስከመሰከረበት የወንጌሉ መደምደሚያ ድረስ ኢየሱስ በሥጋ የመጣው እግዚአብሔር ወልድ እንደሆነ ተገልጾአል፡፡ (2) "ማመን" የሚለው ቃል በተደጋጋሚ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ክርስቶስን መቀበል ከሚለው ጋርም ተመሳሳይ ነው (1፥12)፤ ይህ ደግሞ የአእምሮ እምነትን ሳይሆን፣ ባለማቋረጥ ሙሉ ሕይወትን ለክርስቶስ መስጠትን የሚያስችል ልባዊ ምላሽን የሚጠይቅ ነው፡፡ (3) "የዘላለም ሕይወት" የሚለው ቃል የዮሐንስ ወንጌል ቍልፍ ሐሳብ ሲሆን፥ የሚያመለክተውም የማያልቅ ሕልውናን ሳይሆን በመዳናችን የተነሣ ከክርስቶስ ጋር በምንፈጥረው አንድነት ከኀጢአትና ከሰይጣን ባርነት ነጻ ወጥተን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በማድረግና እርሱንም በማወቅ እያደግን የምናገኘውን የላቀ ሕይወት ነው፡፡ (4) ሰዎች ከኢየሱስ ጋር ያደረጓቸው የግል ግንኙነቶች (ኒቆዲሞስ፣ ሳምራዊቷ ሴት፣ የቤተ መንግሥቱ ጥም ወዘተ) በወንጌሉ ውስጥ ከ27 ጊዜ ያላነሰ ተጠቅሰዋል፡፡ (5) ከኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኋላ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ አማኞች የኢየሱስን ሕይወትና ኀይል በቀጣይነት እንዲለማመዱ አስችሎአቸዋል፡፡ (6) ይህ ወንጌል "እውነት" ለሚለው ቃል አጽንዖት ይሰጣል፤ ኢየሱስ እውነት ነው፤ የእግዚአብሔርም ቃል እውነት ነው፡፡ እውነት ሰዎችን ነጻ ያወጣል (8፥32)፤ ንጹሕ ያደርጋቸዋል (15፥3)፤ የሰይጣን ባሕርይና ሥራ ተጻራሪ ነው (8፥44-47:51)፡፡ (7) በወንጌሉ ውስጥ ሰባት ቁጥር ዋና ቍጥር ነው፤ ሰባት ምልክቶች፣ ሰባት ንግግሮች፣ የማንነቱ መግለጫ የሆኑ ሰባት "እኔ" ዎች (በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ የሰባት ቍጥርን ዋነኛነት ያነጻጽሩ)፡፡ (8) ሌሎች በዮሐንስ ወንጌል የሚገኙ ቍልፍ ቃሎችና ሐሳቦች፣ "ብርሃን"፣ "ቃል"፣ "ሥጋ"፣ "ፍቅር"፣ "ምስክር"፥ "ማወቅ"፣ "ጨለማ" እና "ዓለም" የሚሉ ናቸው፡፡

## ወንጌሉን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የዮሐንስ ወንጌልን በ37 ቀናት መነበብ ይኖርበታል፤

❑ 1፥1-18 ❑ 1፥19-51 ❑ 2 ❑ 3፥1-21 ❑ 3፥22-36 ❑ 4፥1-26 ❑ 4፥27-54 ❑ 5፥1-30 ❑ 5፥31-47 ❑ 6፥1-24 ❑ 6፥25-59 ❑ ❑ 6፥60-71 ❑ 7፥1-24 ❑ 7፥25—8፥11 ❑ 8፥12-30 ❑ 8፥31-47 ❑ 8፥48-59 ❑ 9 ❑ 10፥1-21 ❑ 10፥22-42 ❑ 11፥1-16 ❑ 11፥17-57 ❑ 12፥1-19 ❑ 12፥20-50 ❑ 13፥1-30 ❑ 13፥31—14፥14 ❑ 14፥15-31 ❑ 15፥1-17 ❑ 15፥18—16፥16 ❑ 16፥17-33 ❑ 17 ❑ 18፥1-27 ❑ 18፥28—19፥16 ❑ 19፥17-42 ❑ 20፥1-18 ❑ 20፥19-31 ❑ 21

### ማስታወሻ

## ቃል ሥጋ ሆነ

1 በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም
ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፤ ቃልም እግዚአብሔር
ነበረ። [2]እርሱም በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር
ጋር ነበረ።
[3]ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሮአል፤
ከተፈጠረው ሁሉ ያለ እርሱ የተፈጠረ
ምንም የለም። [4]ሕይወት በእርሱ ነበረች፤
ይህች ሕይወት የሰው ብርሃን ነበረች።
[5]ብርሃንም በጨለማ ያበራል፤ ጨለማውም
አላሸነፈውም።[υ]
[6]ከእግዚአብሔር የተላከ ዮሐንስ የተባለ
እንድ ሰው ነበረ። [7]ሰዎች ሁሉ በእርሱ
በኩል እንዲያምኑ፣ ስለ ብርሃን ምስክር
ሆኖ ለመቆም መጣ፤ [8]ስለ ብርሃን
ሊመሰክር መጣ እንጂ እርሱ ራሱ ብርሃን
(ዮሐ 4፥7-30)
አልነበረም። [9]ለሰው ሁሉ ብርሃን ሰጪ
የሆነው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም
እየመጣ ነበር።[ለ]
[10]እርሱ በዓለም ውስጥ ነበረ፤ ዓለም
የተፈጠረው በእርሱ ቢሆንም እንኳ፣
ዓለም አላወቀውም። [11]ወደ ራሱ ወገኖች
መጣ፤ የገዛ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም፤
[12]ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ
ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት

1፥1 ኢሳ55፥11፤ ዮሐ17፥5፤ ፊል2፥6፤ 1ዮሐ1፥2፤ ራእ19፥13 1፥2 ዘፍ1፥1፤ ዮሐ8፥58፤ 17፥5፡24፤ 1ዮሐ1፥1፤ ራእ1፥8 1፥3 ቍ10፤ 1ቆሮ8፥6፤ ቈላ1፥16፤ ዕብ1፥2 1፥4 መዝ36፥9፤ ዮሐ3፥19፤ 5፥26፤ 6፥57፤ 8፥12፤ 9፥5፤ 11፥25፤ 12፥46፤ ሐሥ3፥15፤ ዕብ7፥16፤

1፥4 1ዮሐ1፥1፡2፤ 5፥20፤ ራእ1፥18 1፥5 መዝ18፥28፤ ዮሐ3፥19 1፥6 ማቴ3፥1 1፥7 ቍ12፡15፡19፡32 ዮሐ3፥15፡26፤ 5፥33 1፥9 ኢሳ49፥6፤ 1ዮሐ2፥8 1፥10 ቍ 3 1፥11 ኢሳ53፥3 1፥12 ቍ7፤ ዘጸ14፥1፤ ዮሐ3፥15፤ ሮሜ8፥14፡21፤ ኤፌ5፥1፤ 1ዮሐ3፥1፡2፤ 3፥23

*[υ]1፥5 ወይም ጨለማው ግን አላወቀውም*
*[ለ]1፥9 ወይም ይህ ወደ ዓለም ለሚመጣ ሰው ብርሃን የሚሰጥ እውነተኛው ብርሃን ነበረ*

1፥1 **ቃል**፤ ዮሐንስ ኢየሱስን "ቃል" (የግሪኩ ትርጒም "ሎጎስ" ይለዋል) ብሎ በመጥራት ወንጌሉን ይጀምራል። ዮሐንስ ይህን ስያሜ ለክርስቶስ በማዋል እርሱ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ አድርጎ አቅርቦታል። ይህ የዮሐንስ ስያሜ በዚህ በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር በልጁ እንደተናገረን ያመለክታል (ዕብ 1፥1-3 ይመ)። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ጥበብ (1ቆሮ 1፥30፤ ኤፌ 3፥10-11፤ ቈላ 2፥2-3)፣ የማንነቱና የእኔነቱ ፍጹም መገለጫ (ዮሐ 1፥3-5፡14፡18፤ ቈላ 2፥9) እንደ ሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ያውጃሉ። አንድ ሰው የሚናገራቸው ቃላት የሰውየውን ልብና አስተሳሰብ እንደሚገልጹ ሁሉ፣ ክርስቶስም፣ "ቃል" እንደ መሆኑ የእግዚአብሔርን ልብና አስተሳሰብ ይገልጻል (14፥9፤ በገጽ 1080 ላይ፣ "*የእግዚአብሔር ቃል*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ኢየሱስ ክርስቶስ፥ "ቃል" ከመሆኑ ጋር የተያያዙ የእርሱ የሆኑትን ሦስት ዋና ዋና ገላጭ ባሕርያትን ዮሐንስ እንደሚከተለው ያቀርብልናል፤

(1) "ቃል" ከአብ ጋር ያለው ግንኙነት፤ (ሀ) ክርስቶስ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በቅድመ ሕልውናው ከእግዚአብሔር አብ ጋር ነበር (ቈላ 1፥15ን ይመ)። ክርስቶስ እግዚአብሔር ወልድ ስለሆነ ከእግዚአብሔር አብ ጋር በዘላለማዊ አንድነት ያለና ከዘላለም ጀምሮ የኖረ ነው። (ለ) ክርስቶስ እንደ እግዚአብሔር አብ አንድ ዐይነት ባሕርይና ማንነት ያለው መለኮት ("ቃልም ሥጋ ሆነ") ነው (ቈላ 2፥9፤ የማር 1፥11 ማብ ይመ)።

(2) "ቃል" ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት፤ እግዚአብሔር አብ ዓለምን የፈጠረውና አሁንም አጽንቶ የያዘው በክርስቶስ አማካይነት ነው (ቍ 3፤ ቈላ 1፥16፤ ዕብ 1፥2)።

(3) "ቃል" ከሰው ጋር ያለው ግንኙነት፤ "ቃልም ሥጋ ሆነ" (ቍ 14)። ከኀጢአት በስተቀር ከሰው ልጆች ጋር ተመሳሳይ ማንነት በመያዝ እግዚአብሔር በኢየሱስ የሰው ልጅ ሆነ። ክርስቶስ መንግሥተ ሰማይን ትቶ ሰው ሆኖ በመወለድ በሰዎች የአኗኗር ሁኔታ ውስጥ መግባቱ የትሥጉት መሠረታዊ ዐላማ ነው (የማቴ 1፥23 ማብ ይመ)።

1፥2 **በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ**፤ ክርስቶስ ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይደለም፤ ዘላለማዊ እንደመሆኑ ከእግዚአብሔር አብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ምን ጊዜም በፍቅር ኅብረት ይኖራል (በማር 1፥11 ላይ ስለ "ሥላሴ" የቀረበውን ማብ ይመ)።

1፥4 **ሕይወት የሰው ብርሃን ነበረች**፤ በእርግጥ እውነተኛ ሕይወት በክርስቶስ ታይቶአል (ከ14፥6፤ 17፥3 ጋር ያነጻጽሩ)። የእርሱ ሕይወት ለሰው ሁሉ ብርሃን ነበረች፤ ይህም የእግዚአብሔርን እውነት፣ ማንነትና ኀይል ሰዎች ሁሉ በእርሱ በኩል ማግኘት እንደሚችሉ ያመለክታል (8፥12፤ 12፥35-36፡46)።

1፥5 **ብርሃንም በጨለማ ያበራል**፤ የክርስቶስ ብርሃን በሰይጣን ቍጥጥር ሥር ባለችው ክፉና ኀጢአተኛ ዓለም ያበራል። ከዓለም ሕዝብ ብዙኀኑ የእርሱን ሕይወት ወይም ብርሃን አልተቀበለም፤ ሆኖም "ጨለማው አላሸነፈውም"፤ (ማለትም ጨለማው አላየለበትም)።

1፥9 **ለሰው ሁሉ ብርሃን ሰጪ የሆነው**፤ ወንጌልን ለሚሰሙ ሁሉ ክርስቶስ ብሩህ መረዳት ይሰጣቸዋል። ይህንንም የሚያደርገው በነጻነት መልእክቱን መቀበል ይችሉ ዘንድ ጸጋንና ማስተዋልን በመስጠት ነው። ከዚህ ከክርስቶስ ብርሃን ውጭ እውነቱን ልናይና ልንድን የምንችልበት ሌላ ብርሃን የለም።

1፥10 **ዓለም አላወቀውም**፤ "ዓለም" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ከእግዚአብሔር፣ ከቃሉና ከትእዛዙ ተጻራሪ ሆኖ የተደራጀውንና በተግባራዊ ሁኔታ እየተንቀሳቀሰ ያለውን ሥርዐት ነው። ዓለም ክርስቶስን ሊረዳ አይችልም፤ እስከ ዘመኑ ፍጻሜ ድረስ ለክርስቶስና ለወንጌሉ በግድየለሽነት ወይም በጠላትነት እንደጸና ይዘልቃል (ያዕ 4፥4 ይመ)። ዮሐንስ እንዳስተዋለው በድነት ታሪክ ውስጥ የአዳኙ ዋና ጠላት ዓለም ነው (ከያዕ 4፥4፤ ከ1ዮሐ 2፥15-17፤ 4፥5 ጋር ያነጻጽሩ)።

1፥12 **ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት**፤ ለድነት የሚያበቃ እምነት በቅጽበት የሚፈጸም ተግባርና በሕይወት ዘመን ሁሉ ቀጣይ የሆነ አቋም ሊሆን እንደሚችል ይህ ጥቅስ በግልጽ ያመለክታል፤ (1) አንድ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ክርስቶስን "ሊቀበል" (በግሪክ ቃሉ "ኤላቦን" የሚል ሲሆን የተገኘውም "ላምባኖ" ከሚለው ግስ ነው) ይገባዋል። (2) ያመነ ሰው እምነቱን በሥራ ሳያቋርጥ ይገልጻል። "ላመኑት" የሚለው ቃል (በግሪክ ቃሉ "ፒስቱሲን" የሚል ሲሆን የተገኘውም "ፒስቲዎ" ከሚለው ግስ ነው) ስዋስዋዊ አገባብ ቀጣይነት ያለውን ድርጊት የሚገልጽና በእምነት የመጽናትን አስፈላጊነት የሚያመለክት ነው። አንድ ሰው በድነቱ እስከመጨረሻ ይጸና ዘንድ በጅማሬው ላይ ክርስቶስን ሲቀበል የወሰደው እውነተኛ የእምነት እርምጃ ሊቀጥል ይገባል (ማቴ 10፥22፤ 24፥12-13፤ ቈላ 1፥21-23፤ ዕብ 3፥6፡12-15)።

1፥12 **ላመኑት**፤ ዮሐንስ በስም ደረጃ ያለውን

ሰጣቸው። 13እነዚህም ከእግዚአብሔር ተወለዱ
እንጂ፣ ከደም[ሀ] ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም
ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።
14ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም አደረ፤
እኛም ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ ከአባቱ ዘንድ
የመጣውን የአንድያ[ለ] ልጅን ክብር አየን።
15ዮሐንስም፣ " 'ከእኔ በኋላ የሚመጣው
ከእኔ በፊት ስለ ነበረ ከእኔ ይልቃል' ብዬ
የመሰከርሁለት እርሱ ነው" በማለት ጮኾ
ስለ እርሱ መሰከረ። 16ከእርሱ ሙላት
ሁላችንም በጸጋ ላይ ጸጋ ተቀብለናል፤ 17ሕግ
በሙሴ በኩል ተሰጥቶ ነበር፤ ጸጋና እውነት
ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መጣ።
18ከቶውንም እግዚአብሔርን ያየ ማንም
የለም፤ ነገር ግን በአብ እቅፍ ያለው አንድያ
ልጁ[ሐ] የሆነው አምላክ እርሱ ገለጠው።

## መጥምቁ ዮሐንስ ራሱ ክርስቶስ እንዳልሆነ ተናገረ

19አይሁድ፣ ማንነቱን እንዲጠይቁት
ካህናትንና ሌዋውያንን ከኢየሩሳሌም ወደ
እርሱ ሲልኩ፣ ዮሐንስ የሰጠው ምስክርነት
ይህ ነበር።
20ከመመስከርም ወደ ኋላ አላለም፤
"እኔ ክርስቶስ[መ] አይደለሁም" ብሎ በግልጽ
መሰከረ።
21እነርሱም፣ "ታዲያ አንተ ማን ነህ?
ኤልያስ ነህ?" ብለው ጠየቁት።
እርሱም፣ "አይደለሁም" አለ።
እነርሱም፣ "ታዲያ ነቢዩ ነህ?"
አሉት።
እርሱም፣ "አይደለሁም" ሲል መለሰ።
22በመጨረሻም፣ "እንግዲያስ ማን ነህ?
ለላኩን ሰዎች መልስ እንድንሰጥ ስለ ራስህ
ምን ትላለህ?" አሉት።
23ዮሐንስም በነቢዩ በኢሳይያስ
እንደ ተነገረው፣ "'ለጌታ መንገድ አቅኑለት'
እያለ በምድረ በዳ የሚጮኸ ድምፅ እኔ ነኝ"
ሲል መለሰ።
24ከተላኩትም ፈሪሳውያን አንዳንዶቹ፣
25"ታዲያ፣ ክርስቶስ ወይም ኤልያስ ወይም
ነቢዩ ካልሆንህ፤ ለምን ታጠምቃለህ?"
ብለው ጠየቁት።
26ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፤
"እኔ በውሃ[ሠ] አጠምቃለሁ፤ እናንተ
የማታውቁት ግን በመካከላችሁ ቆሟል፤
27ከእኔ በኋላ የሚመጣው፣ የጫማውን
ማሰሪያ ለመፍታት እንኳ የማልበቃ እርሱ
ነው።"
28ይህ ሁሉ የሆነው ዮሐንስ ሲያጠምቅ በነ
በረበት ከዮርዳኖስ ማዶ በቢታንያ ነበር።

## የእግዚአብሔር በግ

29ዮሐንስ በማግሥቱ፣ ኢየሱስ ወደ

1፥13 ዮሐ3፥6፤ ቲቶ3፥5፤ 1ጴጥ1፥23፤ 1ዮሐ3፥9፤ 4፥7፤ 5፥1፡4፤ ያዕ1፥18
1፥14 ዘፀ33፥18፤ 40፥34፤ ማቴ3፥11፤ ዮሐ14፥6፤ ሮሜ3፥24፤ ገላ4፥4፤ ፊል2፥7፡8፤ 1ጢሞ3፥16፤ ዕብ2፥14፤ 1ዮሐ1፥1፡2፤ 4፥2
1፥15 ቍ7፡30፤ ማቴ3፥11
1፥16 ሮሜ3፥24፤ ኤፌ1፥23፤ ቈላ1፥19፤ 2፥9
1፥17 ቍ14፤ ዘዳ32፥46፤ ዮሐ7፥19
1፥18 ዘፀ33፥20፤ ዮሐ3፥16፡18፤ 6፥46፤ ቈላ1፥15፤ 1ጢሞ6፥16፤ 1ዮሐ4፥9፡12
1፥19 ማቴ3፥1፤ ዮሐ2፥18፤ 5፥10፡16፤ 6፥41፡52፤ 7፥1፤ 10፥24
1፥20 ሉቃ3፥15፡16፤ ዮሐ3፥28
1፥21 ዘዳ18፥15፤ ማቴ11፥14
1፥23 ማቴ3፥1፤ ኢሳ40፥3 1፥26 ማር1፥4 1፥27 ቍ15፡30፤ ማር1፥7 1፥28 ዮሐ3፥26፤ 10፥40 1፥29 ቍ36፤ ዘፍ22፥8፤ ዮሐ3፥17፤ ኢሳ53፥7፤ 1ጴጥ1፥19 ራእ5፥6፤ 13፥8

*ሀ 1፥13 ወይም ከሰው ውሳኔ*
*ለ 1፥14 ወይም አንድ ልጁ የሆነው*
*ሐ 1፥18 አንዳንድ ቅጆች አንድ ልጁ ይላሉ*
*መ 1፥20 ወይም መሲሕ* «ክርስቶስ» (በግሪኩ ቋንቋ) እና «መሲሁ» በዕብራይስጡ ሁለቱም የተቀባ የሚል ትርጉም አላቸው፤ ቍ 25 ይመ::
*ሠ 1፥26 ወይም በውሃ ውስጥ ቍ 31 እና 33 ይመ*

---

«እምነት» (በግሪኩ «ፒስቲስ») የሚለውን ቃል ተጠቅሞ እንደማያውቅ ልብ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ሆኖም «ማመን» (በግሪክ «ፒስቴኦ») የሚለውን ግስ በተደጋጋሚ ጊዜ በወንጌሉ አስገብቶታል:: ዮሐንስ እንደሰተዋለው ወደ ድነት የሚያደርስ እምነት ሰዎች በስራ የሚገልጹት ድርጊት ነው:: እውነተኛ እምነት በኢየሱስና በእርሱ ቤዛነት ሥራ ላይ የሚኖረን ልል እምነት ወይም መተማመን አይደለም፤ ነገር ግን እርሱን ጌታና አዳኝ አድርገን ወደ ክርስቶስ ምን ጊዜም የሚያቀርበንና በፍቅርና ራስን በመካድ ራሳችንን የምንሰጥበት ሁኔታ ነው (ከዕብ 7፥25 ጋር ያነጻጽሩ)::

**1፥12 የእግዚአብሔር ልጆች፤** ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ የልጅነት መብት ሊያገኙ የሚችሉት በክርስቶስ ስም ሲያምኑ ብቻ ነው:: ክርስቶስን ሲቀበሉት ዳግም ይወለዳሉ፤ የእግዚአብሔር ልጆችም ይሆናሉ (3፥1-21):: ነገር ግን ሰዎች ሁሉ «የእግዚአብሔር ልጆች» አይደሉም::

**1፥13 ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም፤** በክርስቶስ ሞት አማካይነት ለእኛ ድነትን ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር ምንም ግዴታ አልነበረበትም፤ ነገር ግን ግድ ያለው የራሱ ፍቅርና ርኅራኄ ብቻ ነው:: የድነትን ሐሳብ ያመነጨው እግዚአብሔር ራሱ ነው::

**1፥14 ቃልም ሥጋ ሆነ፤** የዘላለም አምላክ የሆነው ክርስቶስ ሰው ሆነ (ፊል 2፥5-9):: ስብእናና መለኮት በእርሱ ውስጥ ተዋሐዱ:: የሰብእና ውስንነት ሁሉ በሚገኝበት የሰው ልጅ ማንነት ውስጥ ራሱን ዝቅ አድርጎ ገብቶአል (ከ3፥17፤ 6፥38-42፤ 7፥29፤ 9፥5፤ 10፥36 ጋር ያነጻጽሩ)::

**1፥17 ጸጋና እውነት፤** ከጥንቶቹ እምነትና (ዘፍ 5፥24፤ 7፥1፤ 15፥6) ለኀጢአት ይቅርታ ከተሰጠው ተስፋ (ዘፀ 34፥6-7፤ ዘሌ 5፥17-18) ማየት እንደሚቻለው በብሉይ ኪዳን ለነበሩ ሰዎች የተሰጠው ጸጋ የተወሰነ ነበር:: አሁን ግን በክርስቶስ አማካይነት ጸጋንና እውነትን በሙላት መቀበል ይቻላል (ሮሜ 5፥17-21):: እውነት መሥዋዕት ማቅረብን በመሳሰሉ አምሳያዎች ከእንግዲህ ተጋርዶ አይቀርም:: «በጸጋ ላይ ጸጋ ተቀብለናል» (ቍ 16) የሚለው ሐረግ፣ የቀረበላቸውን ጸጋ የተቀበሉ አማኞች የማያቋርጥ ጸጋና ኀይል እንደሚሰጣቸው ያስገነዝባል:: ጸጋ ክርስቶስን የተቀበሉ አማኞች የሚለማመዱት የእግዚአብሔር ኀይል፣ ህልውትና ባርከት ነው (በገጽ 1746 ላይ፤ *«እምነትና ጸጋ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ):: ሕግን ለመጠበቅ በምናደርገው ጥረት ድነትን ማግኘት አንችልም፤ ነገር ግን ድነት ማግኘት የምንችለው ወደ ሕይወታችን ገብተው መንፈሳችንን ለማደስና በክርስቶስ አምሳል አኗኗራችንን ለመቅረጽ መንፈስ ቅዱስና የክርስቶስ ጸጋ ወደ እኛ ሲመጡ ነው::

**1፥29 የእግዚአብሔር በግ፤** ኢየሱስ በኀጢአተኞች ምትክ እንዲሠዋ በእግዚአብሔር የቀረበ በግ ነው (ከዘፀ 12፥3-17 እና ከኢሳ 53፥7 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 129 ላይ፣ *«የፋሲካ በዓል»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ):: ኢየሱስ በሞቱ የበደል ሸክምና የኀጢአት ኀይል እንዲወገድ አደረገ፤ በዓለም የሚኖሩ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡበትንም መንገድ ከፈተ::

እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፤ "እነሆ!
የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር
በግ፤ 30ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ በፊት
ስለ ነበር ከእኔ ይልቃል' ያልሁት እርሱ
ነው፤ 31እኔ ራሴ አላወቅሁትም ነበር፤
በውሃ እያጠመቅሁ የመጣሁትም እርሱ
በእስራኤል ዘንድ እንዲገለጥ ነው።"
32ከዚያም ዮሐንስ እንዲህ ሲል
ምስክርነቱን ሰጠ፤ "መንፈስ እንደ ርግብ
ከሰማይ ወርዶ በእርሱ ላይ ሲያርፍ አየሁ፤
33በውሃ እንዳጠምቅ የላከኝም፣ 'በመንፈስ
ቅዱስ የሚያጠምቀው፣ መንፈስ ሲወርድና
በርሱ ላይ ሲያርፍ የምታየው እርሱ ነው'
ብሎ እስኪ ነገረኝ ድረስ እኔም አላወቅሁትም
ነበር፤ 34አይቻለሁ፣ እርሱ የእግዚአብሔር
ልጅ እንደ ሆነ እመሰክራለሁ።"

ዮሐ 7፥38-39

## የመጀመሪያዎቹ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት

*1፥40-42 ተጓ ምብ — ማቴ 4፥18-22፤ ማር 1፥16-20፤ ሉቃ 5፥2-11*

35በማግሥቱ፣ ዮሐንስ ከሁለቱ ደቀ
መዛሙርቱ ጋር እንደ ገና እዚያው ቆሞ
ነበር፤ 36ኢየሱስንም በዚያ ሲያልፍ አይቶ፣
"እነሆ! የእግዚአብሔር በግ" አለ።
37ሁለቱ ደቀ መዛሙርትም ይህን ሲናገር
ሰምተው ኢየሱስን ተከተሉት። 38ኢየሱስም
ዘወር ብሎ ሲከተሉት አየና፣ "ምን
ትፈልጋላችሁ?" ብሎ ጠየቃቸው።
እነርሱም፣ "ረቢ፣ የት ትኖራለህ?"
አሉት፤ 'ረቢ' ማለት መምህር ማለት ነው።
39እርሱም፣ "ኑና እዩ" አላቸው።
ስለዚህ ሄደው የት እንደሚኖር አዩ፤
በዚያም ዕለት አብረውትዋሉ፤ ከቀኑም
ዐሥር ሰዓት ያህል ነበር።
40ዮሐንስ የተናገረውን ሰምተው
ኢየሱስን ከተከተሉት ከሁለቱ አንዱ የስምዖን
ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበር። 41እንድር
ያስ በመጀመሪያ ያደረገው ወንድሙን
ስምዖንን ፈልጎ፣ "መሲሑን አገኘነው" ብሎ
መንገር ነው፤ 'መሲሕ' ማለት ክርስቶስ
ማለት ነው። 42ወደ ኢየሱስም አመጣው።
ኢየሱስም ተመለከተውና፣ "አንተ የዮና
ልጅ ስምዖን ነህ፤ ኬፋ ተብለህ ትጠራለህ"
አለው፤ 'ኬፋ' ማለት ጴጥሮስ ማለት ነው።[a]

1፥30 ቍ15፥27
1፥32 ማቴ3፥16
1፥33 ማር1፥4፡8
1፥34 ቍ49፤ ማቴ4፥3
1፥35 ማቴ3፥1
1፥36 ቍ29
1፥38 ቍ49፤ ማቴ3፥7
1፥41 ዮሐ4፥25
1፥42 ዘፍ17፥5፡15፤ 32፥28፤ 35፥10፤ ማቴ16፥18
1፥43 ማቴ4፥19፤ 10፥3፤ ዮሐ6፥5-7፤ 12፥21፡22፤ 14፥8፡9
1፥44 ማቴ11፥21
1፥45 ማር1፥24፤ ሉቃ3፥23፤ 24፥27፤ ዮሐ21፥2
1፥46 ዮሐ7፥41፡42፡52
1፥47 መዝ32፥2፤ ሮሜ9፥4፡6
1፥49 ቍ34፡38፤ ዘፍ28፥12፤ ማቴ2፥2፤ 4፥3፤ 23፥7፤ 27፥42፤ ዮሐ12፥13
1፥51 ማቴ3፥16፤ 8፥20
2፥1 ማቴ12፥46፤ ዮሐ4፥46፤ 21፥2

## ኢየሱስ ፊልጶስንና ናትናኤልን ጠራቸው

43በማግሥቱ፣ ኢየሱስ ወደ ገሊላ ለመሄድ
ፈለገ፤ ፊልጶስንም አግኝቶ፣ "ተከተለኝ"
አለው።
44ፊልጶስም እንደ እንድርያስና እንደ
ጴጥሮስ ሁሉ የቤተ ሳይዳ ከተማ ሰው
ነበረ። 45ፊልጶስ ናትናኤልን አግኝቶ፣
"ሙሴ በሕግ መጻሕፍት፣ ነቢያትም ስለ
እርሱ የጻፉለትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱ
ኢየሱስን አግኝተነዋል" አለው።
46ናትናኤልም፣ "ከናዝሬት በጎ ነገር
ሊወጣ ይችላልን?" አለ።
ፊልጶስም፣ "መጥተህ እይ" አለው።
47ኢየሱስም፣ ናትናኤል ወደ እርሱ
ሲመጣ አይቶ፣ "እነሆ፤ ተንኰል የሌለበት
እውነተኛ እስራኤላዊ" አለ።
48ናትናኤልም "እንዴት አወቅኸኝ?"
ሲል ጠየቀው።
ኢየሱስም፣ "ከበለስ ዛፍ ሥር ሳለህ፣ ገና
ፊልጶስ ሳይጠራህ አየሁህ" ሲል መለሰለት።
49ናትናኤልም መለሰ፤ "ረቢ፣ አንተ
የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤ አንተ የእስራኤል
ንጉሥ ነህ" አለ።
50ኢየሱስም፣ "የመንኸው ከበለስ ዛፍ
ሥር አየሁህ ስላልሁህ ነውን?[b] ገና ከዚህ
የሚበልጥ ነገር ታያለህ" አለው፤ 51ጨምሮም፣
"እውነት እላችኋለሁ፣ ሰማይ ተከፍቶ፣
የእግዚአብሔርም መላእክት በሰው ልጅ ላይ
ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ" አለው።

## ኢየሱስ ውሃን የወይን ጠጅ አደረገ

2 በሦስተኛው ቀን፣ በገሊላ አውራጃ፣ በቃና
ከተማ ሰርግ ነበር፤ የኢየሱስም እናት
በዚያ ነበረች፤ 2ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም
ወደ ሰርጉ ተጠርተው ነበር። 3የወይን ጠጅ
ባለቀ ጊዜም የኢየሱስ እናት፣ "የወይን ጠጅ

*[a] 1፥42 ኬፋ የሚለው የአራማይክ ቃልና ጴጥሮስ የሚለው የግሪኩ ቃል፣ የሁለቱም ትርጕም ዐለት ማለት ነው።*
*[b] 1፥50 ወይም ከበለስ ዛፍ ሥር አየሁህ ስላልሁህ አመንህ)*

**1፥33 በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቀው፤** "በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቀው" ኢየሱስ እንደ ሆነ ወንጌሎች ሁሉ አበክረው ይናገራሉ (ማቴ 3፥11፤ ማር 1፥8፤ ሉቃ 3፥16፤ ዮሐ 1፥33)። ይህ ጥምቀት የክርስቶስ ተከታዮች ምልክትና ጕልህ መለያ ነበር። የክርስቶስን የማዳን ሥራ በዓለም ዙሪያ ይዘው ይሄዱ ዘንድ (ከሐሥ 1፥8 ጋር ያነጻጽሩ) መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድባቸው ያስፈልግ ነበር። የኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ ተግባር እስከዘመኑ መጨረሻ ጸንቶ የሚቆይ ዐላማው ነው (የማቴ 3፥11 እና የሐሥ 2፥39ን ማብ ይመ)።
**1፥51 ሰማይ ተከፍቶ … ታያላችሁ፤** ኢየሱስ ራሱን የመሰለው የእግዚአብሔር መገለጥ ወደ ዓለም የሚሸጋገርበት መሰላል አድርጎ ነው (ከዘፍ 28፥12 ጋር ያነጻጽሩ፤ በሉቃ 5፥24 ላይ "የሰው ልጅ" ስሚለው ሐረግ የቀረበውን ማብ ይመ)።
**2፥3 የወይን ጠጅ፤** ወይን የሚለው ቃል በግሪኩ፣ «ኦይኖስ» ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፣ በአዲስ ኪዳን ተለዋዋጭ ትርጕም በመያዝ የፈላ ወይም ያልፈላ የወይን ጭማቂን ሊያመለክት ይችላል (በገጽ 1547 ላይ፤ እና በገጽ 1603 ላይ፤ «*የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1 እና -2*» በሚሉ ርእሶች የቀረቡትን የትኵረት ጽሑፎች ይመ)። የወይን ጠጅ ባሕርይ እንደ ግብዣው ዐይነትና እንደ ተጋባዡ ማኅበረሰባዊ ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል።
**2፥3 የወይን ጠጅ እኮ አለቀባቸው፤** በዚህ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ ከቀረበው ሐሳብ ጋር የሚቃረን አቋም ያላቸው አንዳንድ ሰዎች፣ በሰርጉ ላይ በመጀመሪያ የቀረበውና በኢየሱስ ታምር የተዘጋጀው የወይን ጠጅ ሁለቱም የሚያሰክሩና እድምተኛው በብዛት የጠጣቸው

እኮ አለቀባቸው" አለችው።
4ኢየሱስም፣ "አንቺ ሴት ሆይ፤ ምን
አድርግ ትይኛለሽ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም"
አላት።
5እናቱም በዚያ የነበሩትን አገልጋዮች፣
"የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ" አለቻቸው።
6በአይሁድ የመንጻት ሥርዐት መሠረት፣
ከሰባ አምስት እስከ አንድ መቶ ዐሥራ
አምስት ሊትር የሚይዙ ከድንጋይ የተሠሩ
ስድስት ጋኖች[a] በዚያ ነበሩ።
7ኢየሱስ አገልጋዮቹን፣ "ጋኖቹን ውሃ
ሙሏቸው" አላቸው፤ እነርሱም፣ ጋኖቹን
እስከ አፋቸው ሞሏቸው።
8እርሱም፣ "ከላዩ ቀድታችሁ ለድግሱ
ኀላፊ ስጡት" አላቸው።
እነርሱም እንዳዘዛቸው አደረጉ። 9የድግሱ
ኀላፊም ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠውን ውሃ
ቀመሰ፤ ሆኖም ከየት እንደ መጣ አላወቀም፤
ውሃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ
ነበር። እርሱም ሙሽራውን ለብቻው ጠርቶ፣
10"ሰው ሁሉ በመጀመሪያ የሚያቀርበው
ጥሩውን የወይን ጠጅ ነው፤ እንግዶቹም
ብዙ ከጠጡ በኋላ መናኛውን የወይን ጠጅ
ያቀርባል፤ አንተ ግን ጥሩውን የወይን
ጠጅ እስከ አሁን አቈይተሃል" አለው።

2፥4 ማቴ8፥29፤ ዮሐ19፥26፤ 26፥18
2፥5 ዘፍ41፥55
2፥6 ማር7፥3፡4፤ ዮሐ3፥25
2፥9 ዮሐ4፥46

[a] 2፥6 በግሪኩ *ሁለት ወይም ሦስት እንስራ*

እንደነበሩ ያምናሉ። ይህ መንደርደሪያ ሐሳብ ተቀባይነት ካገኘ የሚከተሉት ግንዛቤዎች ሊታወቁና ሊታሰብባቸው ይገባል፤ (1) በሰርጉ ላይ የታደሙት ተጋባዦች ሰክረው ሊሆን ይችላል፤ (2) የኢየሱስ እናት ማርያም የሚያሰክረው መጠጥ በማለቁ አዝና በስካር ናላቸው ለዞረው እድምተኞች ተጨማሪ የሚያሰክር የወይን ጠጅ እንዲዘጋጅላቸው ለመጠየቅ ወደ ኢየሱስ ቀርባለች ማለት ነው፤ (3) የእናቱን ፍላጎት ለማርካት ሲል እድምተኞቹ ጭራሽ ቀምብዘው ብሎው ለመስከር ከሚያስፈልጋቸው መጠን በላይ ከ48 እስከ 72 እንስራ የሚገመት የሚያሰክር ጠጅ (ቊ 6-9) ኢየሱስ እውን አድርጓል ማለት ነው። (4) ኢየሱስ «የታምራዊ ምልክቶቹ *መጀመሪያ*» የሆነውን ይህን የሚያሰክር መጠጥ የሰጣቸው ክብሩን ለመግለጥ (ቊ 11)፣ የእግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ልጅ መሆኑን ሰዎች ይቀበሉ ዘንድ ለማግባባት ፈልጎአል ማለት ነው።

መንደርደሪያ ሐሳቡ ካስከተላቸው ከፍ ብለው ከተመለከቱት ግንዛቤዎች ማፈግፈግ አይቻልም። ኢየሱስ የሚያሰክር የአልኮል መጠጥን አዘጋጅቶ እንዲጠጡ አቀረበ ብሎ መወንጀል የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐምን ስልት መተላለፍ ብቻ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ቃል ከተከተተው ከጠቅላላው የመልካም ምግባር ሥርዐት ጋር መጋጨት ነው። ከእግዚአብሔር ማንነት፥ ከክርስቶስ ጽድቅና ለሰዎችም ካለው ፍቅር እንዲሁም ከማርያም መልካም ባሕርይ አንጻር ሲታይ ከፍ ብሎ የተጠቀሰውና ቢቃና ዘገሊላ በሰርጉ ላይ ቀርቦ የነበረው የወይን ጠጅ የሚያሰክር ነበር የሚለው ግንዛቤ በእግዚአብሔር ላይ የስድብ ቃል እንደመሰንዘር ይቈጠራል። ይህንን የመሳሰሉ ግምታዊ ድምዳሜዎችንና እርስ በርሳቸው የሚጻረሩ አስተያየቶችን ያዘለ አተረጓጐም ተቀባይነትን ሊያገኝ አይገባም። ልብን የሚያሳርፈውና ብቸኛ መግለጫ ሊሆን የሚችለው ኢየሱስ ክብሩን ለመግለጽ የሰጣቸው የወይን ጠጅ የማያሰክረው ንጹሕ የወይን ፍሬ ጭማቂ ዐይነት እንደነበር የሚያስገነዝበው ነው። በድግሱ ኀላፊ ቀደም ብሎ የቀረበውም መናኛ የወይን ጠጅ የማያሰክር ሳይሆን አይቀርም። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ለተጨማሪ ማብራሪያ በገጽ 1603 ላይ፣ *«የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -2»* የሚለውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**2፥10 ጥሩውን የወይን ጠጅ፤** ልዩ ልዩ የጥንት ጸሐፊዎች እንዳመለከቱት፣ «ጥሩው» (ማለፊያው ወይም ምርጡ) የወይን ጠጅ ማንኛውም ሰው ያለ ሥጋት በነፃነትና ባለማቋረጥ ሊጠጣው የሚችለው እጅግ የሚጥመው ዐይነት ሲሆን፣ ይህም የወይን ጭማቂው እንዲፈላ ወይም እንዲከመጥጥ በማድረግ ጣፋጭነቱ እንዲወገድ ያልተደረገው ነው። «መናኛ» የወይን ጠጅ ማለት በብዙ ውሃ ተበርዞ ወይም በሌላ ምክንያት ጣዕሙን ያጣ የወይን ጠጅ ነው። የድግሱ ኀላፊ ለእድምተኞቹ በመጀመሪያ ያቀረበው ማለፊያ ነው ያለውን ቢሆንም፣ ኢየሱስ በኋላ ካቀረበው የወይን ጠጅ ጋር ሲነጻጸር ግን «መናኛ» ተብሏል። (1) ሮማዊው ጸሐፊ ኘሊኒ ይህንኑ ያረጋግጣል፤ ማለፊያ የሆነውና ያልፈላው የወይን ጠጅ «ሳፓ» ይባላል፤ «ሳፓ» የተባለው የወይን ጭማቂ የበለጠ ይጣፍጥ ዘንድ መጀመሪያ ከነበረው መጠን አንድ ሦስተኛው እስኪቀር ድረስ እሳት ላይ ይጣድ ነበር (ዕቭ. 13)። በሌላም ስፍራ ይኸው ጸሐፊ፣ «የወይን ጠጅ እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው የማስከር ኀይሉ በጠማቂው ፈጽሞ የተወገደ እንደሆነ ነው» ብሏል (ኘሊኒ፥ «ናቹራል ሂስትሪ» እዕቭ.23-24)። ኘሊኒ፣ ኘሉታርክና ሆሬስ በአንድነት ምርጡ የወይን ጠጅ «ጕዳት የማያደርሰውና ለስላሳው» ዐይነት እንደነበር አመልክተዋል። (2) የአይሁድ መምህራን ምስክርነት እንደሚያረጋግጠው አንዳንድ የአይሁድ መምህራን በእሳት ላይ ተጥዶ የቆየ የወይን ጠጅ ቢጠጣ የተሻለ እንደሚሆን ይመክራሉ። ሚሽና የተባለው መጽሐፍ የታወቁትን መምህር በመጥቀስ፣ «ረቢ ይሁዳ በእሳት ላይ መጣዱ የወይን ጠጁን ስለሚያሳምረው ለመወዝወዝ መባ እንዲቀርብ ፈቅደዋል» ይላል። (3) «ምርጥ» የሚለው ቃል እቻ ሆኖ የተተረጐመው የግሪኩ ቅጽል፣ «አጋቶስ» ሳይሆን፣ «እጅግ ጭምት ወይም ተገቢ የሆነ» የሚል ትርጕም ያለው «ካሎስ» የሚለው ቅጽል ነው።

**2፥10 ብዙ ከጠጡ በኋላ፤** «ብዙ ከጠጡ በኋላ» የሚለው ሐረግ የተገኘው ሁለት ትርጕም ካለው «ሜቱስኮ» ከሚለው የግሪክ ቃል ነው፤ (1) መስከር ወይም ስካራም መሆን፤ (2) መሞላት ወይም መርካት (ከስካር ጋር ባልተያያዘ መንገድ)። ከቀረቡት ትርጕሞች ዐውዱን መሠረት በማድረግ፣ «ሜቱስኮን» ልንረዳ የምንችለው በሁለተኛው መንገድ ነው። (1) ይህ ምንባብ በምንም ዓይነት ሁኔታ ቢተረጐምም እንኳ በሰርጉ ላይ የተጠጣው የወይን ጠጅ የሚያሰክር ነበር የሚለውን ግንዛቤ ለማጽናት ሊውል አይችልም። እዚህ ላይ የድግሱ ኀላፊ የሰጠው አስተያየት ምንም ዐይነት መጠጥ ቢቀርብ የሚደረገውን የሰርግ አከባበርን በተመለከተ አጠቃላይ ሥርዐት መናገሩ ነበር። (2) በምንም መንገድ ቢሆን ጌታ ኢየሱስ በስካራሞች ጉባኤ ተሳትፏል ወይም ለስካራቸው አስተዋፅኦ አድርጓል የሚል አስተሳሰብ ልናንጸባርቅ አይገባም (የቊ 3ን ማብራሪያ እንዲሁም በገጽ 1603 ላይ፣ *«የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -2»* የሚለውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

11ኢየሱስም ይህን የታምራዊ ምልክቶቹ
መጀመሪያ በገሊላ አውራጃ በቃና ከተማ
አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀ መዛሙር
ቱም በእርሱ አመኑ።

### ኢየሱስ ቤተ መቅደስን አጠራ

*2፥14-16 ተጓ ምብ — ማቴ 21፥12፡13፤ ማር 11፥15-17፤ ሉቃ 19፥45፡46*

12ከዚህ በኋላ ከእናቱ፣ ከወንድሞቹና
ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ቅፍርናሆም
ወረደ፤ በዚያም ጥቂት ቀን ተቀመጡ።
13የአይሁድ ፋሲካም እንደ ተቃረበ፣
ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። 14በቤተ
መቅደሱ አደባባይ ከብቶችን፣ በጎችንና
ርግቦችን የሚሸጡ እንዲሁም ተቀምጠው
የገንዘብ ምንዛሪ የሚያከናውኑ ሰዎች
አገኘ። 15የገመድ ጅራፍ አበጅቶ
በጎችንና ከብቶችን ሁሉ ከቤተ መቅደሱ
ግቢ አባረረ፤ የመንዛሪዎችን ገንዘብ
በትኖ፤ ጠረጴዛቻቸውንም ገለበጠ።
16ርግብ ሻጮችንም፣ "እነዚህን ከዚህ
አስወጧቸው፤ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት
አታድርጉት!" አላቸው።
17ደቀ መዛሙርቱም፣ "ለቤትህ ያለኝ
ቅናት ያቃጥለኛል" ተብሎ የተጻፈው ትዝ
አላቸው።
18አይሁድም፣ "ይህን ሁሉ ለማድረግ
ሥልጣን እንዳለህ የሚያረጋግጥ ምን
ታምራዊ ምልክት ታሳየናለህ?" አሉት።
19ኢየሱስም፣ "ይህን ቤተ መቅደስ
አፍርሱት፤ እኔም በሦስት ቀን መልሼ
አነሣዋለሁ" ብሎ መለሰላቸው።
20አይሁድም፣ "ይህን ቤተ መቅደስ
ለመሥራት አርባ ስድስት ዓመት ፈጅቶአል፤
ታዲያ አንተ እንዴት በሦስት ቀን መልሰህ
ታነሣዋለህ?" አሉት። 21ቤተ መቅደስ
ሲል ግን፣ ስለ ገዛ ሰውነቱ መናገሩ ነበር።
22ከሙታንም ከተነሣ በኋላ፤ ደቀ መዛሙርቱ
ምን እንደተናገረ አስታወሱ፤ መጻሕፍትንና
ኢየሱስ ያለውንም ቃል አመኑ።
23በፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም ሳለ፣ ብዙ
ሰዎች ያደረገውን ታምራት አይተው በስሙ
አመኑ፤‡ 24ኢየሱስ ግን ሰውን ሁሉ ስለሚ
ያውቅ፣ አይታመንባቸውም ነበር፤ 25በሰው
ውስጥ ያለውን ያውቅ ስለ ነበር፣ ማንም ስለ
ሰው እንዲመሰክርለት አላስፈለገውም።

2፥11 ቍ23፤ ዘፀ14፥31፤ ማቴ12፥38፤ ዮሐ1፥14፤ 3፥2፤ 4፥48፤ 6፥2፡14፡26፡30፤ 12፥37፤ 20፥30
2፥12 ማቴ4፥13፤ 12፡46
2፥13 ዘጸ16፥1-6፤ ሉቃ2፥41፤ ዮሐ11፥55
2፥14 ዘሌ1፥14፤ ዘጸ14፥25፡26
2፥16 ሉቃ2፥49
2፥17 መዝ69፥9
2፥18 ቍ11፤ ማቴ12፥38፤ ዮሐ1፥19
2፥19 ማቴ16፥21፤ 26፥61፤ 27፥40፤ ማር14፥58፤ 15፥29፤ ሐሥ6፥14
2፥21 1ቆሮ6፥19
2፥22 መዝ16፥10፤ ሉቃ24፥5-8፤ 24፥27፤ ዮሐ12፥16፤ 14፥26
2፥23 ቍ11፡13፤ ዮሐ3፥15
2፥25 ዘዳ31፥21፤ 1ነገ8፥39፤ ኢሳ11፥3፤ ማቴ9፥4፤ ዮሐ6፥61፡64፤ 13፥11
3፥1 ዮሐ7፥50፤ 19፥39፤ ሉቃ23፥13
3፥2 ቍ11፤ ሐሥ2፥22፤ 10፥38፤ ማቴ23፥7፤ ዮሐ2፥11፤ 10፥38፤ 14፥10፡11
3፥3 ማቴ3፥2፤ ዮሐ1፥13
3፥5 ሐሥ22፥16፤ ቲቶ3፥5
3፥6 ዮሐ1፥13፤ 1ቆሮ15፥50
3፥8 1ቆሮ2፥14-16
3፥9 ዮሐ6፥52፡60
3፥10 ሉቃ2፥46

### ኢየሱስ ኒቆዲሞስን አስተማረ

3 ከፈሪሳውያን ወገን፣ ከአይሁድ አለቆች
አንዱ የሆነ ኒቆዲሞስ የተባለ ሰው
ነበረ፤ 2በሌሊትም ወደ ኢየሱስ መጥቶ፣
"ረቢ፤ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ ሰው
በቀር አንተ የምታደርጋቸውን ታምራዊ
ምልክቶች ማንም ሊያደርግ ስለማይችል፣
ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣህ መምህር
እንደሆንህ እናውቃለን" አለው።
3ኢየሱስም መልሶ፣ "እውነት እልሃለሁ፤
ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ* በቀር
የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም"
አለው።
4ኒቆዲሞስም፣ "ሰው ከሸመገለ በኋላ
እንዴት ሊወለድ ይችላል? ዳግመኛ
እንዲወለድ ተመልሶ ወደ እናቱ ማሕፀንስ
ሊገባ ይችላልን?" አለው።
5ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤
"እውነት እልሃለሁ፤ ማንም ከውሃና
ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር
መንግሥት ሊገባ አይችልም፤ 6ከሥጋ
የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደም
መንፈስ ነው። 7'ዳግመኛ መወለድ አለባችሁ'
ስላልሁህ አትገረም፤ 8ነፋስ ወደሚወደው
ይነፍሳል፤ ድምፁንም ትሰማለህ፤
ነገር ግን ከየት እንደ መጣ፣ ወዴት
እንደሚሄድም አታውቅም፤ ከመንፈስም
የተወለደ ሁሉ እንደዚሁ ነው።"
9ኒቆዲሞስም፣ "ይህ እንዴት ሊሆን
ይችላል?" ሲል ጠየቀው።
10ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤
"አንተ የእስራኤል መምህር ሆነህ ሳለ
እነዚህን ነገሮች አታውቅምን? 11እውነት
እልሃለሁ፤ የምናውቀውን እንናገራለን፤
ያየነውንም እንመሰክራለን፤ እናንተ ግን
ምስክርነታችንን አትቀበሉም። 12ስለ
ምድራዊው ነገር ነግሬአችሁ ያላመናችሁ፣
ስለ ሰማያዊው ነገር ብነግራችሁ እንዴት
ታምናላችሁ? 13ከሰማይ ከወረደው ከሰው
ልጅ በቀር፣ ወደ ሰማይ የወጣ ማንም
የለም።† 14ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ

3፥11 ቍ32፤ ዮሐ1፥18፤ 7፥16፡17 3፥13 ቍ31፤ ምሳ 30፥4፤ ማቴ8፥20፤ ዮሐ6፥38፡42፤ ሐሥ2፥34፤ ኤፌ4፥8-10፤ ዕብ4፥14፤ 9፥24 3፥14 ዘኍ21፥8፡9፤ ዮሐ12፥32

‡2፥23 ወይም *በእርሱም አመኑ*
*3፥3 ወይም *ከላይ ካልተወለደ፤* ቍ 7 ይመ
†3፥13 ወይም *በሰማይ ካለው ሯ*

**2፥15 ከቤተ መቅደሱ ግቢ አባረረ፤** የሉቃ 19፥45ን ማብራሪያ ይመልከቱ።

**2፥19 ቤተ መቅደስ፤** በገጽ 641 ላይ፣ *«ቤተ መቅደሱ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**3፥3 ዳግመኛ ካልተወለደ፤** ዳግም ልደትን (ዳግመኛ መወለድን) በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ የሆነውን ሐሳብ በገጽ 1606 ላይ፣ *«ዳግም ልደት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**3፥5 ከውሃ … ካልተወለደ፤** ኢየሱስ ይህንን ሲናገር ምናልባት ሊያመለክት የፈለገው አዲስ ልደት በሚከናወንበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ስለሚፈጽመው የማንጻት ሥራ ነው፤ በቲቶ 3፥8 ላይ ጳውሎስ፣ «ዳግም ልደት በሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው» በማለት ይናገራል።

**3፥8 ነፋስ … መንፈስ፤** ነፋስ በዐይን ባይታይም እንኳ በሚያከናውነው ተግባርና በሚያሰማው ድምፅ እንደሚታወቅ ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስም ዳግመኛ በተወለዱት ሕይወት ውስጥ በሚፈጽመው ተግባርና በሚያስከትለው ውጤት ይገለጻል።

# የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -2

*ዮሐ 2፥11 "ኢየሱስም ይህን የታምራዊ ምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ አውራጃ በቃና ከተማ አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ።"*

ከዚህ ጽሑፍ ጋር በተያያዘ መልኩ በገጽ 1547 ላይ፣ "የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1" በሚል ርእስ የቀረበው የትኩረት ጽሑፍ መነበብ ይኖርበታል።

የወይን ጠጅ፣ ብርዝ ወይስ ደረቅ የወይን ጠጅ? በአይሁድና በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን በነበሩ ሌሎች ሕዝቦች፥ ስለ የወይን ጠጅ አጣጣልና አጠቃቀም ታሪክ የሚያመለክተን፣ (ሀ) አብዛሙኛውን ጊዜ ያልፈላ፣ (ለ) ባብዛኛው በውሃ የሚበረዝ እንደነበረ ነው። በገጽ 1547 ላይ፣ "የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1" የተሰኘው የመጀመሪያው ጽሑፍ የወይን ጠጅን ከነጣዕሙ ሳይፈላና በትኩሱ የሚዘጋጅበትን አንድ መንገድ ያትታል። ይኸኛው ጽሑፍ ደግሞ ወይንን ከውሃ ጋር መደባለቅን አስመልክቶ ሌሎች ሁለት መንገዶችን ያብራራል።

(1) አንደኛው መንገድ ወይኑን ለማድረቅ በወይራ ዘይት አርከፍክፎ በማርጠብ በእንስራ ውስጥ ማቆየት ነው (ዘ ዞንደርቫን ፒክቶሪያል ኢንሳይክሎፒዲያ ኦፍ ዘ ባይብል ቮ. 882፤ እንዲሁም ኮሉሜላ ኦን አግሪካልቸር 12.44.1-8 ይመ)። በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ የተቀመጠን ወይን፣ ውሃ ውስጥ በመንከር ወይም በማፍላት በማንኛውም ጊዜ ጣፋጭ የሆነ የወይን ጠጅ ማዘጋጀት ይቻላል። ፖሊቢየስ የተባለው የታሪክ ጸሐፊ ሮማውያን ሴቶች እንዲህ ዐይነቱን የወይን ጠጅ እንዲጠጡ እንደ ተፈቀደላቸው፣ የፈላውን የወይን ጠጅ ግን እንዳይጠጡ መከልከላቸውን ገልጿል (ፖሊቢየስ፣ ፍራግመንትስ፥ 6.4፥ ፕሊኒ፥ ናቹራል ሂስትሪ፥ 14.11.81 ይመ)።

(2) ሌላው መንገድ ደግሞ ወዲያው የተጨመቀ የወይን ጭማቂን የሚያጣብቅ የወይን ማር እስኪሆን ድረስ ማፍላት ነው፤ ይህ ዐይነቱ መንገድ የወይኑን ጭማቂ ጣፋጭነት እንደ ተጠበቀ አድርጎ አስካሪ ሊያደርገው የሚችለውን የስኳር ክምችት በማስወገድ ብዙ ጊዜ እንዲቀመጥ የሚያደርግ ነው (ኮሉሜላ 12:19.1-6 እና 20.1-8፥ ፕሊኒ 14.11.80 ይመ)። ይህ የላቆጠ የወይን ማር በትልቅ እንስራ ወይም በአቁማዳ ይቀመጣል፥ ከዚያም በተፈለገ ጊዜ ለዳቦ መብያ የሚቀባ ማር ይሆናል ወይም ተመልሶ በውሃ እየሟሟ በድጋሚ የወይን ጭማቂ ሆኖ ሊጠጣ ይችላል (ዘ ዞንደርቫን ፒክቶሪያል ኢንሳይክሎፒዲያ ኦፍ ዘ ባይብል፤ ቮ. 882—884)። ምናልባትም ስኳርን ለማግኘት ወይን በብዛት ሳይመረት አልቀረም፣ ምክንያቱም የወይኑን ጭማቂ በማፍላት "የወይን ማር" የተባለውን ማግኘት ይቻል ነበርና (ዘ ኢንተርናሽናል ስታንዳርድ ባይብል ኢንሳይክሎፒዲያ ቮ. 3050)። አብዛኛውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ማር ተብሎ የሚጠቀሰውም፣ ከንብ ማር ይልቅ በአይሁድ ዘንድ "ደባሽ" የሚባለው የወይን ማር ነው።

(3) ደግሞም ውሃ፣ በዘቢብ መልክ በደረቀው ወይንም ሆነ በወይኑ ጭማቂ እንዲሁም በደረቅ የወይን ጠጅ ውስጥ ሊጨመር ይችላል። የግሪክም ሆነ የሮማውያን ጸሐፊዎች በወይን ጠጅ ላይ የሚጨመርን ውሃ አስመልክቶ የተለያየ መጠን ጽፈዋል። ሆሜር (ኦዲሲይ ዐአ 208) በአንድ እጅ የወይን ጠጅ ላይ ሃያ እጅ ውሃ እንደሚጨመር ጠቅሷል። ፕሉታርክም በበኩሉ (ስምሲያክስ III ix) "ምንም እንኳ አብዛኛው እጅ ውሃ ቢሆንም ድብልቅ የወይን ጠጅ ብለን እንጠራዋለን" ብሏል። ፕሊኒም (14.6.54) በአንድ እጅ የወይን ጠጅ ላይ ስምንት እጅ ውሃ እንደሚጨመር ተናግሯል።

(4) በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የነበሩ ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ የአይሁድ ልማዶች የወይን ጠጅ ተበርዞ እንዲቀርብ አዘዋል፤ በተለይም ደረቅ የወይን ጠጅን ማቅረብ ፈጽሞ ያግዱ ነበር። በአንድ አይሁዳዊ ጸሐፊ የተዘጋጀውና ከ200 ዓ.ቅ.ክ አንሥቶ እስከ 200 ዓ.ም. ድረስ ያለውን የይሁዲነት ባህል የሚያብራራው፣ "ታልሙድ" የተሰኘው መጽሐፍ በበርካታ አጫጭር ጽሑፎቹ ስለ ወይን ጠጅ በውሃ መበረዝ ያወሳል (ለምሳሌ፣ ሻባት 77ሷ፥ ፔሳሒም 1086)። አንዳንድ የአይሁድ ረቢዎች (መምህራን) ደረቅ የወይን ጠጅ በሦስት እጅ ውሃ ካልተበረዘ በቀር የማይባረክና ጠጪውንም የሚያረክስ ነው ብለው አበክረው ያስጠነቅቁ ነበር። ሌሎች ደግሞ አንድ እጅ ደረቅ የወይን ጠጅ ከመቅረቡ በፊት በዐሥር እጅ ውሃ ሊበረዝ ይገባዋል ይሉ ነበር።

(5) በዮሐንስ ራእይ ላይ ደግሞ አንድ ትኩረታችንን የሚጠይቅ ክፍል አለ፤ በዚሁ ላይ መልአኩ ስለ "ቍጣው (የእግዚአብሔር) ጽዋ" ሲናገር፣ "ምንም ነገር ሳይቀላቀልበት" ይለዋል (ራእ 14፥10፤ የኤር 25፥15 ማብራሪያ ይመ)። እንዲህ የተጠቀሰበት ምክንያት አንባቢዎቹ

ብዙ ጊዜ ማንኛውም የወይን መጠጥ ሁሉ ውሃ የተጨመረበት ነው ብለው ስለሚገምቱ ነው (የሐ/ሥ 2፥3 ማብ ይመ)።

ባጭሩ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን በነበሩ አይሁድ ዘንድ የነበረው የወይን ጠጅ አጠቃቀም ልምድ በዚህ ዘመን ካለው የተለየ ነው። የዚያን ጊዜው የወይን ጠጅ፣ (ሀ) ወዲያው የተጨመቀ የወይን ጭማቂ፣ (ለ) ተጨምቆ የተቀመጠ የወይን ጭማቂ፣ (ሐ) ከደረቅ ወይን የሚዘጋጅ ጭማቂ፣ (መ) ውሃ የተጨመረበት የወይን ፈሳሽ እንዲሁም፣ (ሠ) ተቀምጦ የፈላ ሆኖ ያልፈላ አንድ በ20 እጅ በውሃ የተበረዘ ነበር። ወይኑ የፈላ ሆኖ ሳይበረዝ የቀረበ እንደ ሆነ እንደ አረማዊ የሚያስገምት፣ ሰውንም እንደሚያረክስ ተደርጎ የሚቈጠርና በረቢዎች ሊባረክ የማይችል ነበር። እንግዲህ ከእነዚህ እውነታዎች አንጻር በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የአይሁድን የወይን ጠጅ አጠቃቀም መሠረት በማድረግ፣ በዚህ ዘመን የሚጠጣውን የአልኮል መጠጥ ደግፎ መከራከር ፈጽሞ አይቻልም። ከዚህም በላይ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የነበሩ አማኞች ልዩ ልዩ ዐይነት የወይን ጠጅን በተመለከተ ከአይሁድ ይልቅ ጠንቃቆች ነበሩ (የሮሜ 14፥21፤ የ1ተሰ 5፥6፤ የ1ጢሞ 3፥3፤ የቲቶ 2፥2፤ ማብ ይመ)።

**የኢየሱስ ክብር በወይን ጠጅ አማካቃነት ተገለጠ፤** ዮሐንስ በዚህ በሁለተኛው ምዕራፍ ላይ ኢየሱስ በገሊላ ቃና ውሃን ወደ የወይን ጠጅ እንደለወጠ ጽፏል። ጥያቄው ግን "ምን ዐይነት የወይን ጠጅ ነበር?" የሚለው ነው። እንግዲህ ቀደም ብሎ እንደተመለከተው፣ የወይን ጠጅ አዘገጃጀት የፈላ ወይም ያልፈላ፣ የተበረዘ ወይም ያልተበረዘ ሊሆን ይችላል። መልሳችን ከምንባቡ ዐውደ ሐሳብና ከምግባር ምስስል አንጻር ሊወሰን ይገባዋል። ይህንን አስመልክቶ የዚህ ማጥኛ መጽሐፍ ቅዱስ አቋም በኢየሱስ የተለወጠው የወይን ጠጅ (አይኖስ) ንጹሕ ያልፈላ የወይን ጠጅ ነበር ማለት ነው። የሚቀጥሉት ጭብጦች በኢየሱስ ክርስቶስ የተለወጠው የወይን ጠጅ አስካሪ ላለመሆኑ ጠንካራ የማሳመኛ ሐሳቦች ናቸው፤

(1) የዚህ ታምር ተቀዳሚ ዐላማ የኢየሱስን ክብር መግለጥ ነው (ዮሐ 2፥11)፤ በዚህም እርሱ ሰዎችን ከኃጢአታቸው ለማዳን የተላከ የእግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ልጅ መሆኑን ሰዎች ዐውቀው የግል እምነት ያገኙ ዘንድ ነው (2፥11፤ ከማቴ 1፥21 ጋር ያነጻጽሩ)። ክርስቶስ አንድያ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መሆኑ መጠን መለኮትነቱን ለመግለጥ (ዮሐ 1፥14) መጠጥ ለጠገቡ ሰርገኛ ብዙ ጋን አስካሪ የወይን ጠጅ በታምር ሰጥቷል ማለትና (ሕዝቡ በጊዜው በብዙ መጠጥ እንደ ተስተናገደ 2፥10 ላይ ተመልክቶአል) ይህም ለመሲሐዊ ተልእኮው እጅግ አስፈላጊ ነው ብሎ ማሰብ ጥቂቶች በመለኮት ላይ በገሐድ የሚያሳዩትን ክብር ገፊ እንደ መቀበል ያህል ነው። እግዚአብሔር በመደበኛ የሥነ ፍጥረት ሕግ በየዓመቱ የሚያበቅለውን ወይን፣ ክርስቶስ ልዕለ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድ በቅጽበት ይህንን የወይን ጭማቂ ፈጠረ ብሎ ማመን በበለጠ የእግዚአብሔርን እና የክርስቶስን ክብር ገላጭ ይሆናል። (የዮሐ 2፥3ን ማብ ይመ)። ስለዚህ ይህ ታምር ክርስቶስ በፍጥረት ዓለሙ ላይ ሉዓላዊ መሆኑን ሲጠቁም፣ ኃጢአተኛ የሆኑትን የሰው ልጆች መንፈሳውያን የእግዚአብሔር ልጆች ሊያደርጋቸው የሚያስችል ኀይል እንዳለውም የሚያሳይ ምልክት ነው (ዮሐ 3፥1-15)። ከዚህም ታምር የተነሣ "... ከአባቱ ዘንድ የመጣውን የአንድያ ልጅን ክብር አየን" (ዮሐ 1፥14 ይመ ከ2፥11 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ክርስቶስ፣ "መልኩ ቀይ ሆኖ በብርጭቆ ሲያንጸባርቅ ሰተት ብሎ በሚወርድበትም ጊዜ ወደ ወይን ጠጅ ትክ ብለህ አትመልከት" (የምሳ 23፥31ን ማብ ይመ) የሚለውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዳልታዘዘ መቍጠሩ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሰው ለሰማይ አባቱ ፍጹም መታዘዙን ከሚገልጠው ሐሳብ ጋር የሚጋጭ ነው (ከ2ቆሮ 5፥21፤ ከዕብ 4፥15፤ ከ1ጴጥ 2፥22 ጋር ያነጻጽሩ)። በእርግጥ ክርስቶስ የመጣው ሕግን ለመፈጸም ነው (ማቴ 5፥17)፤ ይህም አስካሪ የወይን ጠጅን በሚመለከት፣ "ፌዘኛ"፣ ብርቱ መጠጥንም በሚመለከት፣ "ጠበኛ" እያለ የሚኰንነውን (የምሳ 20፥1ን ማብ ይመ) የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚደግፍ ሲሆን፣ በዕን 2፥15 "... ባልንጀሮቹን ለሚያጠጣ፣ እስኪሰክሩም ድረስ ወይን ለሚቀዳላቸው ወዮለት" ከሚለውና ከሚከተሉት ጥቅሶች ሐሳብ ጋር የሚስማማ ነው (ከዘሌ 10፥8-11፤ ከዘኍ 6፥1-5፤ ከዘዳ 21፥20፤ ከምሳ 31፥4-7፤ ከኢሳ 28፥7፤ ከአሞ 2፥8፡12፤ 4፥1፤ 6፥6፤ ከሮሜ 14፥13፡21 ያነጻጽሩ)።

(3) በተጨማሪም የሚከተሉትን የቅርብ ጊዜ የሕክምና መረጃዎች ልብ ማለቱ ይበጃል፤ (ሀ) ልከኛ የአልኮል መጠጥ እንኳ በመውለጃ የዕድሜ ዘመን ያሉ ሴቶችን የመውለድ ሥርዐት የሚያበላሽና ለውርጃ የሚዳርግ ነው፤ እንዲሁም ሕፃናት በማይድን አእምሮአዊና አካላዊ ጕዳት ይወለዱ ዘንድ መንስኤ እንደሚሆን እውቅ የሕክምና ባለሞያዎች ትክክለኛ ማስረጃዎችን አግኝተዋል። የዓለም ሥነ ጽንስ ጠበብቶች እንደሚያምኑት ገና በመጀመሪያዎቹ የጽንስ ቀናት ውስጥ (በ48 ሰዓት ጊዜ ውስጥ) ያሉ ሴቶች መጠነኛ የአልኮል መጠጥ እንኳ ቢጠጡ ከዕንቍላል ዕጢ ውስጥ በመውጣት ላይ ባለው ሐብለበራሂ (ክሮሞሶም) ላይ አደጋ የሚፈጥር

ሲሆን፣ በሚወለደውም ሕፃን አእምሮአዊና አካላዊ እድገት ላይ ጉዳት ያስከትላል። (ለ) በቅርቡ ለመጽነስ የተዘጋጀችውን ወጣቷን ሙሽሪት ጨምሮ ብዙ ሴቶች ባሉበት በዚህ ሰርግ ላይ ኢየሱስ ሰዎችን የሚያሰክር መጠጥ ይጠጡ ዘንድ አበረታቶአል ብሎ ማመን የተፋለሰ ሥነ መለኮታዊ አመለካከት ነው። ኢየሱስ አስካሪ መጠጥ ገና በሚወለዱ ሕፃናት ላይ ሊያመጣ የሚችለውን አስከፊ ጉዳት እንደማያውቅ አድርጎ መገመቱ የእርሱን መለኮትነት፣ ጥበቡን እንዲሁም ክፉ እና ደጉን የመለየት ችሎታውን እንደመጠራጠር ይቈጠራል። በአንጻሩ ደግሞ ኢየሱስ የአልኮል መጠጥ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት እንደሚያውቅ እያመነን ሰዎች ይጠጡት ዘንድ ግን ደግፎአል ብንል በጎነቱን፣ ርኅራኄውንና ፍቅሩን እንዳለመቀበል ይቈጠራል።

ይህንን ጉዳይ በሚመለከት፣ እንደ ባለ አእምሮም ሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሥነ መለኮታዊ አስተሳሰብ መሆን የሚገባው ትክክለኛ ድምዳሜ ኢየሱስ በሰርጉ ላይ ክብሩን ይገልጥ ዘንድ በታምር የሰጠው የወይን ጠጅ ከወይን ፍሬ የሚገኝ ንጹሕ፣ ጣፋጭና ያልፈላ ነበር የሚለው ይሆናል።

# ዳግም ልደት

*ዮሐ 3፥3 "ኢየሱስም መለሰ፣ 'እውነት እልሃለሁ፤ ማንም ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም' አለው።"*

በዮሐ 3፥1-8 ኢየሱስ በክርስትና እምነት ከመሠረታዊ አስተምህሮዎች አንዱ ስለሆነው የተናገረ ሲሆን፣ ይህም ዳግም ልደት (ቲቶ 3፥5) ወይም መንፈሳዊ ልደት የሚባለው ነው። ማንም ሰው ያለ ዳግም ልደት የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም፤ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘው የዘላለም ሕይወትና ድነት ነው። የሚከተሉት ነጥቦች ዳግም ልደትን በተመለከተ ሊተኰርባቸው የሚገባ እውነታዎች ናቸው፤

(1) ዳግም ልደት ሰው (ሮሜ 12፥12፤ ኤፌ 4፥23-24) በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ዳግም ሲፈጠር ወይም ሲለወጥ የሚፈጸም ነው (ዮሐ 3፥6፤ ቲቶ 3፥5፤ ይመ)። በዚህ መንገድ ከእግዚአብሔር የሆነ የዘላለም ሕይወት ሠርጾ በአማኙ ልብ ውስጥ የሚገባ ሲሆን (ዮሐ 3፥16፤ 2ጴጥ 1፥4፤ 1ዮሐ 5፥11) ያመነውም የእግዚአብሔር ልጅና (ዮሐ 1፥12፤ ሮሜ 8፥16-17፤ ገላ 3፥26) አዲስ ሰው (2ቆሮ 5፥17፤ ቈላ 3፥9-10) ይሆናል። አማኙ ዓለምን መምሰል ይተውና (ሮሜ 12፥2) "እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው (ኤፌ 4፥24) ይመስላል።

(2) ሰው ሁሉ ያለ ክርስቶስ በተፈጥሮው ኀጢአተኛ በመሆኑ፣ እግዚአብሔርን መታዘዝና ማስደሰት ስለማይችል ዳግም ልደት ያስፈልገዋል (መዝ 51፥5፤ ኤር 17፥9፤ ሮሜ 8፥7-8፤ 1ቆሮ 2፥14፤ ኤፌ 2፥3)።

(3) ዳግም ልደት ሰዎች ከኀጢአታቸው ንስሓ በመግባት ወደ እግዚአብሔር ሲመለሱና (ማቴ 3፥2) ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታና አዳኝ አድርገው ሲያምኑ (ዮሐ 1፥12 እና ማብ ይመ) እውን ይሆናል።

(4) ዳግም ልደት ከአሮጌው የኀጢአት ሕይወት ኢየሱስ ክርስቶስን ወደሚታዘዝ አዲስ ሕይወት መሸጋገርን ያካትታል (2ቆሮ 5፥17፤ ገላ 6፥15፤ ኤፌ 4፥23-24፤ ቈላ 3፥10)። በእውነት ዳግም የተወለዱት ከኀጢአት እስራት ነጻ የወጡ ሲሆን (ሮሜ 6፥14-23፤ የዮሐ 8፥36ን ማብ ይመ) እግዚአብሔርን ለመታዘዝና የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ለመከተል መንፈሳዊ መሻትና የልብ ፈቃድን ይቀበላሉ (ሮሜ 8፥13-14)። የጽድቅ ሕይወት ይኖራሉ (1ዮሐ 2፥29)፣ ሌሎችን አማኞች ይወዳሉ (1ዮሐ 4፥7)፣ ከኀጢአት ሕይወት ይርቃሉ (1ዮሐ 3፥9፤ 5፥18) ዓለምን መውደድ ይተዋሉ (1ዮሐ 2፥15-16)።

(5) ከእግዚአብሔር የተወለዱ አዘውትረው ኀጢአትን አይለማመዱም (1ዮሐ 3፥9 እና ማብ ይመ)። እግዚአብሔርን ለማስደሰትና ክፋትን ለመጥላት እውነተኛ መሻትና የተሳካ ጥረት ከሌላቸው ዳግም ልደታቸው የጸና አይሆንም (1ዮሐ 1፥5-7)። ዳግም ልደት ተፈጻሚ የሚሆነው ከክርስቶስ ጋር በመጽናት (ዮሐ 15፥4 እና ማብ ይመ) እና በመንፈስ ቅዱስ በመደገፍ (ሮሜ 8፥2-14) ለአማኞች ከሚሰጠው ከክርስቶስ ጸጋ የተነሣ ብቻ ነው (1ዮሐ 2፥3-11፡15-17፡24-29፤ 3፥6-24፤ 4፥7-8፡20፤ 5፥1)።

(6) በርኩሰት እየኖሩ ዓለማዊነትን የሚከተሉ፣ በከንፈራቸው የቱንም ያህል ቢመሰክሩም እንኳ፣ ዳግም ያልተወለዱ የሰይጣን ልጆች መሆናቸውን ያሳያሉ (1ዮሐ 3፥6-10)።

(7) አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ሕይወት በመቀበል ከመንፈስ እንደሚወለድ ሁሉ፥ በአንጻሩ የተቀበለውን ሕይወት ዓለማዊ በሆነ ምርጫና ጽድቅ በሌለው ሕይወት ተክቶ መንፈሳዊ ሞት በመሞት ሊያጠፋው ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ፤ "እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞታላችሁና፤ ክፉ የሆነውን የሥጋ ሥራ ብትገድሉ ግን በሕይወት ትኖራላችሁ" ብሎ (ሮሜ 8፥13) በማስረገጥ ይናገራል። ስለዚህም፣ ኀጢአትን በመፈጸምና መንፈስ ቅዱስን ላለመከተል እልከኛ መሆን በአማኙ ውስጥ ያለውን ከእግዚአብሔር የሆነውን ሕይወት አጨልሞ መንፈሳዊ ሞት የሚያስከትል ሲሆን፣ ከእግዚአብሔር መንግሥት እንዲቈረጥ ያደርጋል (ከማቴ 12፥31-32፤ ከ1ቆሮ 6፥9-10፤ ከገላ 5፥19-21፤ ከዕብ 6፥4-6፤ ከ1ዮሐ 5፥16 ጋር ያነጻጽሩ)።

(8) እግዚአብሔር ከአማኙ ጋር ያለው ግንኙነት መንፈሳዊ እንጂ ሥጋዊ ስላልሆነ አዲሱ ልደት ከተፈጥሮአዊ ልደት ጋር ሊተካከል አይችልም (ዮሐ 3፥6)። በአባትና ልጅ መካከል ያለው ሥጋዊ ትስስር የማይፋቅ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሊያደርግ የሚፈልገው የአባትና የልጅ ግንኙነት ግን በፈቃድ ላይ የተመሠረተና በምድር ላይ በሚኖረን የሙከራ ጊዜ

ሊቋረጥ የሚችል ነው (ሮሜ 8፥13 እና ማብ ይመ)። ይህ ግንኙነት በምድር ላይ በሚኖረን ቆይታ ጊዜ በክርስቶስ ባለን እምነት ማለትም ከቅንነት በሚመነጭ ታዛዥነታችንና የፍቅር ሕይወታችን የሚወሰን ግንኙነት ነው (ሮሜ 8፥12-14፤ 2ጢሞ 2፥12)።

ሰቀለ፣ የሰው ልጅም እንዲሁ ሊሰቀል
ይገባዋል፤ 15ይኸውም በእርሱ የሚያምን
ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ነው።
16"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም
ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ
እግዚአብሔር አንድ ያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ
ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና፤ 17እግዚአብሔር
ልጁን ወደ ዓለም የላከው በዓለም ለመፍረድ
ዮሐ 11፥25-26 ሳይሆን፣ ዓለምን በእርሱ ለማዳን ነው።
18በእርሱ የሚያምን ሁሉ አይፈረድበትም፤
በእርሱ የማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር
ልጅ ስም ስላላመነ፣ አሁኑኑ ተፈርዶበታል።
19ፍርዱም ይህ ነው፤ ብርሃን ወደ ዓለም
መጣ፤ ሰዎች ግን ሥራቸው ክፉ ስለ
ነበረ፣ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ፤
20ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላል፤
አድራጎቱም እንዳይገለጥበት ወደ ብርሃን
አይመጣም። 21በእውነት የሚመላለስ ግን
ሥራው በእግዚአብሔር የተሠራ መሆኑ በግልጽ
ይታይ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል።"ፐ

## መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ መሰከረ

22ከዚህ በኋላ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ
ወደ ይሁዳ አገር ሄዱ፤ እዚያም ከእነርሱ
ጋር ጥቂት ተቀመጠ፤ አጠመቀም።
23በዚህ ጊዜ ዮሐንስም በሳሌም አቅራቢያ
ሄኖን በተባለ ስፍራ ብዙ ውሃ ስለ ነበረ
ያጠምቅ ነበር፤ ሰዎችም ለመጠመቅ ይመጡ
ነበር። 24ይህም የሆነው ዮሐንስ ከመታሰሩ
በፊት ነበር። 25በአንዳንድ የዮሐንስ ደቀ
መዛሙርትና በአንድ አይሁዳዊ^ መካከል
ስለ መንጻት ሥርዐት ክርክር ተነሣ፤ 26ወደ
ዮሐንስም መጥተው፣ "ረቢ፤ በዮርዳኖስ
ማዶ ከአንተ ጋር የነበረው፣ ስለ እርሱም
የመሰከርህለት ሰው፣ እነሆ ያጠምቃል፤
ሰውም ሁሉ ወደ እርሱ እየሄደ ነው" አሉት።
27ዮሐንስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ከላይ
ካልተሰጠው በቀር ማንም አንዳች ሊቀበል
አይችልም። 28እኔ ክርስቶስ" አይደለሁም፤
ነገር ግን ከእርሱ በፊት ተልኬአለሁ'
እንዳልሁ እናንተ ራሳችሁ ትመሰክሩላችሁ፤
29ሙሽራይቱ የሙሽራው ናት፤ ድምፁን
ለመስማት በአጠገቡ የሚቆመው ሚዜ
ግን፣ የሙሽራውን ድምፅ ሲሰማ እጅግ
ደስ ይለዋል፤ ያ ደስታ የእኔ ነው፤ እርሱም
አሁን ተፈጽሞአል። 30እርሱ ሊልቅ፣ እኔ
ግን ላንስ ይገባል።
31"ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው፤
ከምድር የሆነው የምድር ነው፤ የምድሩንም
ይናገራል። ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ
ነው፤ 32ያየውንና የሰማውን ይመሰክራል፤
ነገር ግን ምስክርነቱን ማንም አይቀበልም፤
33ምስክርነቱንም የተቀበለ ሰው፣ እግዚአብሔር
እውነተኛ እንደ ሆነ አረጋገጠ። 34እግዚአብሔርሽ

3፥15 ቍ16፥36፤ ዘኍ15፥6፤ ዘኍ14፥11 ማቴ25፥46፤ 27፥42፤ ማር1፥15፤ ዮሐ1፥7፥12፤ 2፥23፤ 5፥24፤ 7፥38፤ 20፥29፤ 20፥31፤ ሐሥ13፥39፤ 16፥31፤ ሮሜ3፥22፤ 10፥9፥10፤ 1ዮሐ5፥1፥5፥10
3፥16 ቍ15፥36፤ ዘፍ22፥12፤ ኢሳ9፥6፤ ዮሐ1፥18፤ 6፥29፥40፤ 11፥25፥26፤ ሮሜ8፥32፤ 5፥8፤ ኤፌ2፥4፤ 1ዮሐ4፥9፥10
3፥17 ኢሳ53፥11፤ ማቴ1፥21፤ ሉቃ2፥11፤ 19፥10፤ ዮሐ1፥29፤ 6፥29፥57፤ 10፥36፤ 11፥42፤ 12፥47፤ 17፥8፥21፤ 20፥21፤ ሮሜ11፥14፤ 1ጢሞ1፥15፤ 2፥5፥6፤ 1ዮሐ2፥2፤ 3፥5
3፥18 ዮሐ1፥18፤ 5፥24፤ 1ዮሐ4፥9
3፥19 መዝ52፥3፤ ዮሐ1፥4፤ ዮሐ7፥7
3፥20 ኤፌ5፥11፥13፥22
3፥20 ዮሐ4፥2 3፥23 ማቴ3፥1 3፥24 ማቴ4፥12፤ 14፥33፥25 ዮሐ2፥6 3፥26 ማቴ23፥7፤ ዮሐ1፥7 3፥28 ዮሐ1፥20፥23 3፥29 ማቴ9፥15፤ ዮሐ16፥24፤ 17፥13፤ ፊል2፥2፤ 1ዮሐ1፥4፤ 2ዮሐ1፥12 3፥31 ቍ13፤ ዮሐ8፥23፤ 1ዮሐ4፥5 3፥32 ቍ11፤ ዮሐ8፥26፤ 15፥15 3፥34 ቍ17፤ ኢሳ42፥1፤ ማቴ12፥18፤ ሉቃ4፥18፤ ሐሥ10፥38

*3፥18 ወይም በእግዚአብሔር አንድ ያ ልጅ*
ፐ*3፥21* አንዳንድ ተርጓሚዎች ትምህርተ ጥቅሱን ከቍጥር 15 በኋላ ያደርጋሉ
^*3፥25* አንዳንድ ቅጆች አንዳንድ አይሁድ ይላሉ
"*3፥28 ወይም መሲሕ*
ሽ*3፥34* በግሪኩ እርሱ ይላል

**3፥16 እግዚአብሔር ... ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፤** ይህ ጥቅስ የእግዚአብሔርን የልብ ሐሳብና ዐላማውን ይገልጻል፡፡ (1) የእግዚአብሔር ፍቅር ሰዎችን ሁሉ ማለትም "ዓለምን" (ከ1ጢሞ 2፥4 ጋር ያነጻጽሩ) እስኪያካትት ድረስ እጅግ ሰፊ ነው፡፡

(2) በመስቀል ላይ የኀጢአት መሥዋዕት ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ልጁን አሳልፎ ሰጠ፡፡ የኀጢአት ስርየት ከእግዚአብሔር ልብ የሠረጸ ነው እንጂ በእርሱ ላይ የተጣለ ግዴታ አይደለም (ሮሜ 8፥32፤ 1ዮሐ 4፥10)፡፡

(3) ማመን (የግሪኩ ትርጉም፣ "ፒስቲኦ" ይለዋል) ሦስት ፈርጆች አሉት፡ (ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅና ጥፋት ውስጥ ለሚገኘው የሰው ልጅ ብቸኛ አዳኝ መሆኑን በሚገባ መረዳት፡ (ለ) ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ማድረግና ለእርሱም ለመታዘዝ ራስን ሙሉ በሙሉ መስጠት (ከዮሐ 15፥1-10 ጋር ያነጻጽሩ፤ 14፥21 እና ማብ፤ 15፥4 እና ማብ ይመ)፤ (ሐ) አማኙን ወደ ድኅነት ፍጻሜ ሊያደርስና በሰማይ ካለው እግዚአብሔር ጋር ኅብረት ያደርግ ዘንድ ለማብቃት ክርስቶስ ብርታት ያለውና ፈቃደኛ እንደ ሆነ በጽኑ ማመን (በገጽ 1746 ላይ፣ *"እምነትና ጸጋ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፡፡

(4) "እንዳይጠፋ" የሚለው ቃል በቍ 16 ላይ ከቀረበው ሐሳብ ውስጥ ብዙውን ጊዜ የሚዘነጋ ነው፡፡ ቃሉ የሚያመለክተው ሥጋዊ ሞትን ሳይሆን አስፈሪ የሆነውንና የማይቀረውን የዘላለም ቅጣት ነው (የማቴ 10፥28 እና ማብ ይመ)፡፡

(5) "የዘላለም ሕይወት" ዳግም በምንወለድበት ጊዜ እግዚአብሔር የሚያጐናጽፈን ስጦታ ነው (በገጽ 1606 ላይ፣ *"ዳግም ልደት"* የሚለውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፡፡ "ዘላለም" የሚለው ቃል ገደብ የሌለው ዘመንን ብቻ ሳይሆን ዐይነተኛ የሆነውን አኗኗርም ጭምር ያመለክታል፡ ይህም ዐይነተኛ ኑሮ ከኀጢአትና ከሰይጣን ኀይል ነጻ የሚያደርግና እግዚአብሔርን ማወቅ እንችል ዘንድ ምድራዊ ብቻ ከሆነው አኗኗር የሚያላቅቅ መለኮታዊ ዐይነት ሕይወት ነው (ከ8፥34-36 ጋር ያነጻጽሩ፤ 17፥3 እና ማብ ይመ)፡፡

**3፥19 ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ፤** የክፉ ሰዎች አንዱ መሠረታዊ መታወቂያቸው ጨለማን መውደዳቸው ነው፤ ይኸውም ደስታን የሚያገኙት ኀጢአትንና ርኵሰትን በመፈጸም ነው (ሮሜ 1፥18-32፤ ፊል 3፥19፤ 2ጢሞ 3፥2-5፤ 2ጴጥ 2፥12-15)፡፡ በሌላም በኩል፣ በእውነት ዳግመኛ የተወለዱ ሰዎች ጽድቅን ይወዳሉ፤ ክፉ ሥራ ደግሞ ይጠላሉ (ዕብ 1፥9 እና ማብ ይመ)፤ ብልሹ ሰዎች በሚፈጽሙት ርኵስ ተግባር ልባቸው ያዝናል (1ቆሮ 13፥6)፡፡ በዘመኑ ባለው ኅብረተሰብ ዘንድ በገሐድ በሚታየው የኃጢአት መግለጫ በሆነው ሥጋዊ ሥራ ደስ አይሰኙም (መዝ 97፥10፤ ምሳ 8፥13፤ ሮሜ 12፥9፤ 2ጴጥ 2፥8 እና ማብ፤ ራእ 2፥6 እና ማብ ይመ)፡፡

**3፥34 መንፈሱን ሳይሰፍር ስለሚሰጥ፤** ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ስለ መቀበሉ ማቴ 3፥16፤ ሉቃ 3፥22 እና ማብ ይመ፡ እንዲሁም በገጽ 1559 ላይ፡

መንፈሱን ሳይሰፍር ስለሚሰጥ፣ እግዚአብሔር
የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል። 35አብ
ወልድን ይወዳል፤ ሁሉንም ነገር በእጁ ሰጥ
ቶታል። 36በወልድ የሚያምን ሁሉ የዘላለም
ሕይወት አለው፤ በወልድ የማያምን ግን
የእግዚአብሔር ቍጣ በላዩ ይሆናል እንጂ
ሕይወትን አያይም።"[መ]

## ኢየሱስ ከአንዲት ሳምራዊት ጋር ተነጋገረ

4 ፈሪሳውያን ከዮሐንስ ይልቅ ኢየሱስ
ብዙ ደቀ መዛሙርትን እንዳፈራና
እንዳጠመቀ ሰሙ፤ 2ዳሩ ግን ያጠመቀው
ኢየሱስ ሳይሆን ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ።
3ጌታም ይህን እንዳወቀ ይሁዳን ለቆ ወደ
ገሊላ ተመልሶ ሄደ።
4በሰማርያም በኩል ማለፍ ነበረበት።
5ስለዚህ በሰማርያ፣ ያዕቆብ ለልጁ ለዮሴፍ
በሰጠው ቦታ አጠገብ ወደ ነበረች፣ ሲካር
ወደምትባል ከተማ መጣ። 6በዚያም የያዕቆብ
የውሃ ጕድጓድ ነበረ፤ ኢየሱስም ከጕዞው
የተነሣ ደክሞት ስለ ነበር በውሃው ጕድጓድ
አጠገብ ተቀመጠ፤ ጊዜውም ከቀኑ ስድስት
ሰዓት አካባቢ ነበር።
7አንዲት ሳምራዊት ሴት ውሃ ለመቅዳት
ስትመጣ ኢየሱስ፣ "እባክሽ የምጠጣው
ስጪኝ" አላት፤ 8ደቀ መዛሙርቱ ምግብ
ለመግዛት ወደ ከተማ ሄደው ነበር።
9ሳምራዊቷም፣ "አንተ አይሁዳዊ ሆነህ፣
እኔን ሳምራዊቷን እንዴት ውሃ አጠጪኝ
ትላለህ?" አለችው፤ ይህን ማለቷ አይሁድ
ከሳምራውያን ጋር ስለማይተባበሩ ነው።[ሠ]
10ኢየሱስም፣ "የእግዚአብሔርን ስጦታ
ብታውቂና ውሃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን
መሆኑን ብትረዺ ኖሮ፣ አንቺው በጠየቅሽው፣
እርሱም የሕይወትን ውሃ በሰጠሽ ነበር"
ሲል መለሰላት።
11ሴትዮዋም እንዲህ አለችው፤ "ጌታዬ፤
መቅጃ የለህም፤ ጕድጓዱም ጥልቅ ነው፤
ታዲያ ይህን የሕይወት ውሃ ከየት ታገኛ ለህ?
12ለመሆኑ አንተ፣ ይህን ጕድጓድ ከሰጠን፣
ከአባታችን ከያዕቆብ ትበልጣለህን? እርሱ
ራሱና ልጆቹ፣ እንስሳቱም ከዚሁ ጕድጓድ
ጠጥተዋል።"
13ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላት፤
"ከዚህ ውሃ የሚጠጣ እንደ ገና ይጠማል፤
14እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ግን ከቶ
አይጠማም፤ እኔ የምሰጠው ውሃ በውስጡ
የሚፈልቅ የዘላለም ሕይወት ውሃ ምንጭ
ይሆናል።"
15ሴትዮዋም፣ "ጌታዬ፤ እንዳልጠማና
ውሃ ለመቅዳት እንዳልመላለስ፣ እባክህ
ይህን ውሃ ስጠኝ" አለችው።
16እርሱም፣ "ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ
ወደዚህ ተመለሽ" አላት።
17ሴትዮዋም፣ "ባል የለኝም" ብላ
መለሰች።
ኢየሱስም፣ እንዲህ አላት፤ "ባል የለኝም
ማለትሽ ትክክል ነው፤ 18በርግጥ አምስት
ባሎች ነበሩሽ፤ አሁን ከአንቺ ጋር ያለውም
ባልሽ ስላልሆነ፣ የተናገርሽው እውነት
ነው።" 19ሴትዮዋም እንዲህ አለችው፤
"ጌታዬ፣ አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ፤
20አባቶቻችን በዚህ ተራራ ላይ ሰገዱ፤
እናንተ አይሁድ ግን ሰው መስገድ ያለበት

3፥35 ማቴ28፥18
3፥36 ቍ15፤ ዮሐ5፥24፤ 6፥47
4፥1 ዮሐ3፥22፡26
4፥3 ሉቃ7፥13፤ ዮሐ3፥22
4፥4 ማቴ10፥5
4፥5 ዘፍ33፥19፤ ኢያ24፥32
4፥7 ዘፍ24፥17፤ 1ነገ17፥10
4፥8 ቍ5፡39
4፥9 ማቴ10፥5
4፥10 ኢሳ44፥3፤ 55፥1፤ ኤር2፥13፤ 17፥13፤ ዘካ14፥8፤ ዮሐ7፥37፡38፤ ራእ7፥17፤ 21፥6፤ 22፥1፡17
4፥12 ቍ6
4፥14 ኢሳ12፥3፤ 58፥11፤ ማቴ25፥46፤ ዮሐ6፥35፤ 7፥38
4፥15 ዮሐ6፥34
4፥19 ማቴ21፥11
4፥20 ዘዳ11፥29፤ ኢያ8፥33፤ ሉቃ9፥53

*[መ]3፥36 አንዳንድ ተርጓሚዎች ትምሕርተ ጥቅሱን ከ30 በኋላ ያደርጋሉ።*
*[ሠ]4፥9 ወይም ሳምራውያን በተጠቀሙበት ሳሕን/ዕቃ አይጠቀሙም ነበር*

"ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ" የሚለውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**3፥36 የማያምን ግን፤** "የማያምን" ተብሎ የተተረጐመው በግሪኩ፥ "አፔይትዮ" ተብሎ ሲጠራ ትርጕሙም "አለመታዘዝ" ወይም፣ "ዝቅ ብሎ አለመገዛት" ማለት ሲሆን በጥቅሱ መጀመሪያ ካለው፣ "የሚያምን" (በግሪክ 'ፒስትዮ') ከሚለው ቃልም ጋር ተቃራኒ ሆኖ ቀርቦአል። በዮሐንስ ወንጌል አለማመን ማለት ልጁን አለመቀበል ወይም አለመታዘዝ ነው። እምነትና መታዘዝ ብዙውን ጊዜ በተወራራሽነት በቃሉ ውስጥ ቀርበዋል (ሮሜ 1፥8፣ ከሮሜ 16፥19 እና ከ1ተሰ 1፥8 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም ሮሜ 15፥18ን ይመ)። ወንጌል ነጻ ስጦታ ሆኖ ቀርቦልናል (ሮሜ 5፥15-16፤ 6፥23) ሆኖም አንድ ጊዜ ከተቀበልነው በኋላ እንደፈለግነው እንድንኖር አይፈቅድም። እግዚአብሔር ወደ ደነገገልን የድነት ጐዳና እንድንገባና ራሳችንንም ለእግዚአብሔር ጽድቅ እንድናስገዛ ይጠይቀናል (ሮሜ 10፥3፤ የሮሜ 1፥5 እን ማብ እንዲሁም በገጽ 1746 ላይ፣ "**እምነትና ጸጋ**" የሚለውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**4፥7 ሳምራዊት ሴት፤** አይሁድና ሳምራውያን ጠበኞች መሆናቸውን እያወቀ፣ ኢየሱስ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር መነጋገሩ ለሰማያዊው አባቱ ዐላማ ራሱን መስጠቱንና ይህችን ሴት ወደ ዘላለም ሕይወት ለማምጣት የነበረውን ልባዊ መሻት ያሳያል። ኢየሱስ ምግብና መጠጥ (ቍ 34) ከመሻት ይልቅ ዋና ፍላጎቱ በኀጢአታቸው የጠፉትን ሰዎች ማዳን ነበር (ሉቃ 15 ይመልከቱ፤ ከዮሳ 11፥30፤ ከዳን 12፥3 እና ከያዕ 5፥20 ጋር ያነጻጽሩ)። እኛም የኢየሱስን ምሳሌነት ልንከተል ይገባናል። በአካባቢያችን የሚኖሩ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ዝግጁ ናቸው፤ ስለሆነም እኛ ስለ መንፈሳዊ ፍላጎታቸውና ይህንን ፍላጎታቸውን ሊያሟላላቸው ስለሚችለው ስለ ኢየሱስ ልንነግራቸው ይገባል።

**4፥13-14 ከዚህ ውሃ የሚጠጣ ... የዘላለም ሕይወት፤** ኢየሱስ የሰጠው "ውሃ"፣ መንፈሳዊ ሕይወት ነው (ከኢሳ 12፥3 ጋር ያነጻጽሩ)። በዚህ የሕይወት ውሃ መረስረስ የሚፈልግ ውሃውን "መጠጣት" ይገባዋል (7፥37 ይመ)። መጠጣቱ የአንድ ወቅት ወይም የአንድ አፍታ ነገር ሳይሆን እየጨመረ የሚሄድና እየተደጋገመ የሚደረግ መሆን አለበት። ከሕይወት ውሃ መጠጣት፣ የሕይወት ውሃ ምንጭ ከሆነው ከራሱ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የማያሰልስ ኅብረት ማድረግን ይጠይቃል። ማንም ሰው ከምንጩ ጋር ያለውን ግንኙነት ካቋረጠ ይህንን የሕይወት ውሃ በመጠጣት ሊቀጥል አይችልም። ይህን እንዲህ ያሉ ሰዎች በጴጥሮስ አገላለጽ መሠረት "የደረቁ ምንጮች" (2ጴጥ 2፥17) ይሆናሉ።

በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ" አለችው።
21ኢየሱስም እንዲህ አላት፤ "አንቺ
ሴት፤ በዚህ ተራራም ሆነ በኢየሩሳሌም
ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ እንደሚመጣ
እመኚኝ። 22እናንተ ሳምራውያን
ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤ እኛ ግን
ድነት ከአይሁድ ስለሆነ ለምናውቀው
እንሰግዳለን። 23በእውነት የሚሰግዱ ለአብ
በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ
ይመጣል፤ አሁንም መጥቶአል፤ አብም
እንደዚህ በእውነት የሚሰግዱለትን
ይፈልጋል። 24እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤
የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት
ሊሰግዱለት ይገባል።"
25ሴትዮዋም፣ "ክርስቶስ የተባለ መሲሕ
እንደሚመጣ በውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ
ሁሉን ነገር ይነግረናል" አለችው።
26ኢየሱስም፣ "የማነጋግርሽ እኮ እኔ
እርሱ ነኝ" ሲል ገልጦ ነገራት።

### ደቀ መዛሙርቱ ተመልሰው መጡ

27በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ተመልሰው
መጡ፤ ከሴት ጋር ሲነጋገር በማግኘታቸው
ተደነቁ፤ ሆኖም ግን፤ "ምን ፈለግህ?"
ወይም፣ "ከእርሷ ጋር የምትነጋገረው
ለምንድን ነው?" ብሎ የጠየቀው ማንም
አልነበረም።
28ሴትዮዋም እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ
ተመለሰች፤ ለሕዝቡም፣ 29"ያደረግሁትን
ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፤ እርሱ ክርስቶስa
ዮሐ 15፥26-27 ይሆን እንዴ?" አለች፤ 30እነርሱም ከከተማ
ወጥተው እርሱ ወዳለበት አመሩ።
31በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ፣ "ረቢ፣
እህል ቅመስ እንጂ" አሉት።
32እርሱ ግን፣ "እናንተ የማታውቁት፣
የምበላው ምግብ አለኝ" አላቸው።
33ደቀ መዛሙርቱም፣ "ሰው ምግብ

4፥21 ሚል1፥11፤ ዮሐ5፥28፤ 16፥2፤ 1ጢሞ 2፥8
4፥22 2ነገ17፥28-41፤ ኢሳ2፥3፤ ሮሜ3፥1፡2፤ 9፥4፡5፤ 15፥8፡9
4፥23 ዮሐ5፥25፤ 16፥32፤ ፊል3፥3
4፥24 ፊል3፥3
4፥25 ማቴ1፥16፤ ዮሐ1፥41
4፥26 ዮሐ8፥24፤ 9፥35-37
4፥27 ቍ8
4፥29 ቍ17፡18፤ ማቴ12፥23፤ ዮሐ7፥26፡31
4፥31 ማቴ23፥7
4፥32 ኢዮ23፥12፤ ማቴ4፥4፤ ዮሐ6፥27
4፥34 ማቴ26፥39፤ ዮሐ19፥30
4፥35 ማቴ9፥37፤ ሉቃ10፥2
4፥36 ማቴ25፥46፤ ሮሜ1፥13
4፥37 ኢዮ31፥8፤ ሚክ6፥15
4፥39 ቍ5፡29
4፥42 ሉቃ2፥11
4፥43 ቍ40
4፥44 ማቴ13፥57፤ ሉቃ4፥24
4፥45 ዮሐ2፥23

እምጥቶለት ይሆን እንዴ?" ተባባሉ።
34ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "የእኔ
ምግብ የላከኝን ፈቃድ ማድረግና ሥራውን
መፈ ጸም ነው፤ 35እናንተ፣ 'ከአራት ወር
በኋላ መከር ይደርሳል' ትሉ የለምን?
እነሆ፣ አዝመራው ለመከር እንደ ደረሰ ቀና
ብላችሁ ማሳውን ተመልከቱ እላችኋለሁ።
36አጫጅ አሁንም ቢሆን እንኳ ደመወዙን
እየተቀበለ ነው፤ ለዘላለም ሕይወት ይሆን
ዘንድ አዝመራውን ይሰበስባል፤ ይህም
ዘሪውና አጫጁ በጋራ ደስ እንዲላቸው
ነው። 37ስለዚህ፣ 'አንዱ ይዘራል፤ ሌላውም
ያጭዳል' የተባለው ምሳሌ እውነት ነው።
38ያልደከማችሁበትን እንድታጭዱ
ላክኋችሁ፤ አድካሚውን ሥራ ሌሎች ሠሩ፤
እናንተም የድካማቸውን ፍሬ ሰበሰባችሁ።"

### ብዙ ሳምራውያን አመኑ

39ሴትዮዋ፣ "ያደረግሁትን ሁሉ ነገረኝ"
ብላ ስለ መሰከረች፣ ከዚያች ከተማ ብዙ
ሳምራ ውያን በእርሱ አመኑ። 40ስለዚህ፣
ሳምራውያኑ ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ
አብሮአቸው እንዲቈይ አጥብቀው ለመኑት፤
እዚያም ሁለት ቀን ቈየ። 41ከቃሉም የተነሣ
ሌሎች ብዙዎች አመኑ።
42ሴትዮዋንም፣ "ከእንግዲህ የምናምነው
አንቺ ስለ ነገርሽን ብቻ አይደለም፤ እኛ ራሳችን
ሰምተነዋል፤ ይህ ሰው በእውነት የዓለም
አዳኝ እንደሆነ እናውቃለን" አሏት።

### ኢየሱስ የሹሙን ልጅ ፈወሰ

43ከሁለቱ ቀናት በኋላም ወደ ገሊላ
ሄደ፤ 44ነቢይ በገዛ አገሩ እንደማይከበር
ኢየሱስ ራሱ ተናግሮ ነበርና። 45ገሊላ እንደ
ደረሰም የገሊላ ሰዎች በደስታ ተቀበሉት፤
ምክንያቱም፣ እነርሱም በፋሲካ በዓል

a4፥29 ወይም መሲሕ

---

**4፥23 የሚሰግዱ ... በመንፈስና በእውነት፤** እዚህ ላይ ኢየሱስ በርካታ ትምህርቶችን አስተምሮአል፤ (1) «በመንፈስ» የሚለው ቃል እውነተኛ አምልኮ የሚደረግበትን ደረጃ ያመለክታል:: አንድ ሰው በፍጹም ቅንነት ከመንፈስ ቅዱስ በሆነ ሕይወትና ትጋት ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብ ይገባል፤ (2) «እውነት» (በግሪኩ «አሌትያ») የእግዚአብሔር መለያ ባሕርይ ነው (መዝ 31፥5፤ ሮሜ 1፥25፤ 3፥7፤ 15፥8):: ይህም እውነት በክርስቶስ ትሥጉት የሆነ (14፥6፤ 2ቆሮ 11፥10፤ ኤፌ 4፥21)፣ ከመንፈስ ቅዱስ ማንነት ጋር የተያያዘና (14፥17፤ 15፥26፤ 16፥13) የወንጌል ትምህርት ዕንብርት ነው (8፥32፤ ገላ 2፥5፤ ኤፌ 1፥13):: ስለዚህ አምልኮ በወልድ በተገለጸውና ከመንፈስ ቅዱስ በተቀበልነው በእግዚአብሔር አብ እውነት መሠረት ሊከናወን ይገባል:: የእግዚአብሔርን ቃል እውነትና አስተምህሮ ገለል የሚያደርግ አምልኮን የሚያበረታቱ ሰዎች እንደ እውነቱ ከሆነው በማግለል ላይ የሚገኙት የእውነተኛ አምልኩን ብቸኛ መሠረት ነው (በገጽ 713 ላይ፣ «አምልኮተ እግዚአብሔር» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ.)::

**4፥24 እውነት፤** ኢየሱስ ክርስቶስ እውነት ስለሆነ (1፥14፤ 5፥31፤ 14፥6፤ ሉቃ 4፥25፤ 9፥27፤ 12፥44) ከእርሱ ጋር ኅብረትን መሥርቶ ለመኖር እውነትን መናገር ይጠይቃል (1ቆሮ 5፥8፤ ኤፌ 4፥25):: ከክርስቶስ ጋር ኅብረት አለኝ ድነትንም ተቀብያለሁ እያሉ እውነት እንደሚጠይቀው አለመኖርና አለመናገር ራስን ማታለል ነው (1ዮሐ 1፥6):: በውስጣቸው እውነት የሌላቸው ትክክለኛውን አቋማቸውን (8፥44፤ የሐሥ 5፥3) ማለትም ከእግዚአብሔር ጋር መሠረታዊ ቅራኔ እንዳላቸውና ከሰማዩ መንግሥት ውጪ መሆናቸውን ይገልጻሉ (ራእ 21፥8፡27፤ 22፥15፤ ከራእ 14፥5 ጋር ያነጻጽሩ.):: ሐሰተኛ ሰው «የሰይጣን ምኩራብ» (ራእ 3፥9) አባል ነው::

**4፥35 ቀና ብላችሁ ማሳውን ተመልከቱ፤** የማቴ 9፥37 ማብራሪያ ይመልከቱ::

**4፥36 ለዘላለም ሕይወት ይሆን ዘንድ አዝመራውን፤** በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው እንዲድኑ ሌሎችን ሰዎች የሚጋብዙ ዘላለማዊ ዋጋ ያለው ሥራ እየሠሩ ነው:: በእነርሱ ጸሎትና ምስክርነት ስለዳኑት ሰዎች አንድ ቀን በመንግሥተ ሰማይ ሐሤት ያደርጋሉ:: ይህ ሲሆን ታዲያ የእነርሱ አገልግሎት መሳካት የሌሎች ድካም ውጤት እንደሆነ ሊረዱ ይገባቸዋል (ቍ 38):: ዛሬ ለእግዚአብሔር የምናደርገው የተሳካ ነገር ሁሉ ክርስቶስ መሥዋዕት የከፈለበት ሥራና የሌሎችም ድካም ውጤት ነው::

ኢየሩሳሌም ስለ ነበሩና በዚያ ያደረገውን
ሁሉ ስላዩ ነው።
46ኢየሱስም ውሃውን የወይን ጠጅ
ወዳደረገበት፣ በገሊላ ወደምትገኘው ወደ
ቃና ከተማ ዳግመኛ መጣ፤ በቅፍርናሆምም
ልጁ የታመመበት አንድ የቤተ መንግሥት
ሹም ነበረ፤ 47ይህም ሰው ኢየሱስ ከይሁዳ
ወደ ገሊላ መምጣቱን በሰማ ጊዜ፣ ወደ
እርሱ ሄደና በሞት አፋፍ ላይ የነበረውን
ልጁን መጥቶ እንዲፈውስለት ለመነው።
48ኢየሱስም፣ "መቼውንም እናንተ
ምልክቶችንና ድንቅ ነገሮችን ካላያችሁ
አታምኑም" አለው።
49ሹሙም፣ "ጌታዬ፤ ልጄ ከመሞቱ በፊት
እባክህ ድረስልኝ" አለው።
50ኢየሱስም፣ "ልጅህ በሕይወት
ይኖራልና ሂድ" አለው።
ሰውየውም ኢየሱስ የተናገረውን ቃል
አምኖ ሄደ፤ 51በመንገድ ላይ እንዳለም፣
አገልጋዮቹ አግኝተውት ልጁ በሕይወት
መኖሩን ነገሩት። 52እርሱም ልጁ በስንት
ሰዓት እንደ ተሻለው ሲጠይቃቸው፣
"ትናንት የለቀቀው ትኩሳቱ በሰባት ሰዓት
ላይ ነው" አሉት።
53አባትየውም ሰዓቱ ኢየሱስ፣ "ልጅህ
በሕይወት ይኖራል" ያለበት ሰዓት መሆኑን
ተገነዘበ፤ እርሱና ቤተ ሰቡም ሁሉ አመኑ።
54ይህም፣ ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ
መጥቶ ያደረገው ሁለተኛው ታምራዊ
ምልክት ነው።

### በቤተ ሳይዳ የተደረገው ፈውስ

5 ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ነበረ፤
ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ።
2በኢየሩሳሌም፣ በበጎች በር አጠገብ፣
አምስት ባለ መጠለያ መመላለሻዎች
የነበሯት፣ በአራማይክ ቋንቋ ቤተ ሳይዳ*
የተባለች አንዲት መጠመቂያ አለች።
3በእነዚህም መመላለሻዎች ውስጥ ብዙ
አካለ ስንኩላን፣ ዐይነ ስውሮች፣ እንከኖችና
ሽባዎች ይተኙ ነበር። [የውሃውንም
መንቀሳቀስ እየተጠባበቁ፣ 4ዐልፎ ዐልፎ
የጌታ መልአክ ወርዶ ውሃውን በሚያ
ናውጥበት ጊዜ፣ ቀድሞ ወደ መጠመቂያዪቱ
የገባ ካደረበት ማንኛውም በሽታ ይፈወስ
ነበር።]† 5በዚያም ለሠላሳ ስምንት ዓመት
ሕመምተኛ ሆኖ የኖረ አንድ ሰው ነበር።
6ኢየሱስም ይህን ሰው ተኝቶ ባገኘው ጊዜ፣
ለብዙ ጊዜ በዚህ ሁኔታ እንደ ነበር ዐውቆ
"ልትድን ትፈልጋለህን?" አለው።
7ሕመምተኛውም መለሰ፣ "ጌታዬ፣ ውሃው
በሚናወጥበት ጊዜ ወደ መጠመቂያዪቱ
የሚያወርደኝ ሰው የለኝም፤ ለመግባትም
ስሞክር ሌላው ይቀድመኛል" አለው።
8ኢየሱስም፣ "ተነሥ! መተኛህን
ተሸክመህ ሂድ" አለው። 9ሰውየውም ወዲያው
ተፈወሰ፤ መተኛውንም ተሸክሞ ሄደ።
ይህም የሆነው በሰንበት ቀን ነበር።
10አይሁድም የተፈወሰውን ሰው፣ "ሰንበት
ስለ ሆነ መተኛህን እንድትሸከም ሕጉ
አይፈቅድልህም" አሉት።
11እርሱ ግን፣ "ያ የፈወሰኝ ሰው፣
'መተኛህን ተሸክመህ ሂድ' ብሎኛል" ሲል
መለሰላቸው።
12እነርሱም፣ "'መተኛህን ተሸክመህ
ሂድ' ያለህ እርሱ ማነው?" ብለው ጠየቁት።
13ኢየሱስ ፈቀቅ ብሎ ወደ ሕዝብ
መካከል ገብቶ ስለ ነበር፣ ሰውየው ማን
እንደፈወሰው አላወቀም።
14ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ያን ሰው በቤተ

4፥46 ዮሐ2፥1-11
4፥47 ቍ3፥54
4፥48 ዳን4፥2፡3፤ ዮሐ2፥11፤ ሐሥ2፥43፤ 14፥3፤ ሮሜ15፥19፤ 2ቆሮ12፥12፤ ዕብ2፥4
4፥53 ሐሥ11፥14
4፥54 ቍ48፤ ዮሐ2፥11
5፥2 ነህ3፥1፤ 12፥39፤ ዮሐ19፥13፤ 17፥20፤ 20፥16፤ ሐሥ21፥40፤ 22፥2፤ 26፥14
5፥8 ማቴ9፥5፡6
5፥9 ማቴ12፥1-14፤ ዮሐ9፥14
5፥10 ቍ16፤ ነህ 13፥15-22፤ ኤር17፥21፤ ማቴ12፥2
5፥14 ማር2፥5፤ ዮሐ8፥11

*5፥2 አንዳንድ ቅጆች ቤተ ዛታ ሌሎች ቅጆች ቤተ ሳይዳ ይላሉ
†5፥4 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ከቍ 3 የመጨረሻ ክፍል አንሥቶ እስከ ቍ 4 ድረስ ያለውን ክፍል አይጨምሩም

**4፥48 ምልክቶችንና ድንቅ ነገሮችን፤** ምልክቶችና ድንቆች በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሚፈጸሙ አስተማማኝ ተግባሮች ናቸው። ይሁን እንጂ, እምነታችን ማተኮር ያለበት በእነርሱ ላይ ሳይሆን ምልክቶችና ድንቆች ማንነቱን በሚመሰክሩለት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ሊሆን ይገባል (በገጽ 1443 ላይ፣ *"የእግዚአብሔር መንግሥት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ጌታችንና መድኃኒታችን በመሆኑ ልናምንበት ይገባል። ኢየሱስ ለሥጋችን ወይም በቁሳዊ መልክ ሊያደርግልን ስለሚችለው ነገር ብቻ ሳይሆን ስለ ፍቅሩ፣ ስለ ምሕረቱና የጽድቅ ባሕርይው ሊመለክና ከፍ ከፍ ሊደረግ ይገባዋል። ለሹሙ እንደሆነለት ሁሉ ምልክቶች፣ ድንቆችና ታምሮች ከጌታ ጋር ጥልቅ ወደሆነ መጣመርና ከፍተኛ ወደ ሆነ በእርሱ የመታመን ሁኔታ ሊመሩን ይገባል (ቍ 50-53)።

**5፥5 ለሠላሳ ስምንት ዓመት፤** ለሠላሳ ስምንት ዓመት የተሠቃየው ይህ ሰው በተደጋጋሚ እግዚአብሔርን በመተማመን ቢጠባበቅም ፈውስን ባለማግኘቱ ለረዥም ዘመን ተስፋ ሳይቈርጥ አልቀረም ይሁን እንጂ በመጨረሻ ፈውስ ማግኘቱ። ይህ ሰው ለረዥም ዓመት በመሠቃየቱ ኢየሱስ ራራለትና ፈወሰው። እግዚአብሔር በጉዳዮችን ጣልቃ የሚገባበት ጊዜ ፈጥኖ ሊመጣ ስለሚችል በፍጹም ተስፋ ልንቈርጥ አይገባንም።

**5፥9 ሰውዬውም ወዲያው ተፈወሰ፤** ኢየሱስ ብዙውን ጊዜ ሰዎችን ይፈውስ የነበረው በእምነት ወደ እርሱ በቀረቡበት ጊዜ ነበር። በዚህ ስፍራ ግን ኢየሱስ የሕመምተኛውን እምነት አልጠየቀም፤ ሰውዬው የተፈወሰው ኢየሱስ በተናገረው ቃል ብቻ ነበር። ዛሬም ቢሆን ሰዎች በኢየሱስ ማመናቸውን ባይገልጹም በእግዚአብሔር ፀጋ መሠረት ሊፈወሱ ይችላሉ። ለፈውስ የሚያበቃ እምነት የሚገለጽባቸው ሦስት መንገዶች እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል፤ (1) የሚፈወሰው ሰው እምነት (ማቴ 9፥27-29)፤ (2) በሕመም በሚሠቃየው ሰው ፊንታ የሚገለጥ የሌሎች ሰዎች እምነት (ማቴ 8፥5-10፤ ከማቴ 17፥15-20 እና ከያዕ 5፥14-16 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (3) ለፈውስ አገልግሎት የተቀባው ሰው እምነት (1ቆሮ 12፥9)።

**5፥14 ከእንግዲህ ግን ኃጢአትን አትሥራ፤** በስሙ ማመናቸውን የሚመሰክሩ ሰዎች ሁሉ ኃጢአት መሥራትን ያቆሙ ዘንድ ኢየሱስ አጥብቆ ይጠይቃል፤ በእርግጥ የዳኑትም ኃጢአት መሥራትን ያቆማሉ። ምንም

መቅደስ አግኝቶ፣ "እነሆ፣ ተፈውሰሃል፤
ከእንግዲህ ግን ኀጢአት አትሥራ፤
ያለዚያ ከዚህ የባሰ ይደርስብሃል" አለው።
ዮሐ 9፡1-12 15ሰውየውም የፈወሰው ኢየሱስ መሆኑን ሄዶ
ለአይሁድ ነገራቸው።

## ወልድ ሕይወትን ይሰጣል

16አይሁድም፣ በሰንበት ቀን እነዚህን
ድርጊቶች በመፈጸሙ፣ ኢየሱስን ያሳድዱት
ነበር። 17ኢየሱስም፣ "አባቴ እስካሁን
እየ ሠራ ነው፤ እኔም ደግሞ እሠራለሁ"
አላቸው። 18እንግዲህ አይሁድ፣ ኢየሱስ
ሰንበትን ስለሻረ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን
አባቱ በማድ ረግ፣ ራሱን ከእግዚአብሔር እኩል
በማድረጉ፣ ሊገድሉት አጥብቀው ይፈልጉት
ነበር።

19ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እውነት እላችኋለሁ፤ አብ ሲሠራ ያየውን
ብቻ እንጂ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ
አይችልም፤ አብ የሚያደርገውን ሁሉ
ወልድ ደግሞ ያደርጋልና፤ 20አብ ወልድን
ስለሚ ወድ የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል፤
ትደነ ቁም ዘንድ ከእነዚህም የሚበልጥ
ነገር ያሳየዋል። 21ምክንያቱም አብ
ሙታንን እንደ ሚያስነሣ፣ ሕይወትንም
እንደሚሰጥ፣ ወልድም ደግሞ ለሚፈቅደው
ሁሉ ሕይወትን ይሰጣል። 22አብ በማንም
ላይ አይፈርድም፤ ነገር ግን ፍርድን ሁሉ
ለወልድ አሳልፎ ሰጥቶታል፤ 23ይኸውም፣
ሁሉ አብን እንደሚያከብሩ ወል ድን
ያከብሩት ዘንድ ነው፤ ወልድን የማያከብር፣
የላከውን አብንም አያከብርም።

24"እውነት እላችኋለሁ፤ ቃሌን
የሚሰማ፣ በላከኝም የሚያምን የዘላለም
ሕይወት አለው፤ ከሞት ወደ ሕይወት
ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።
25እውነት እላችኋለሁ፤ ሙታን
የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት
ጊዜ ይመጣል፤ አሁንም መጥቶአል፤
የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ። 26አብ
በራሱ ሕይወት እንዳለው ሁሉ፣ ወልድም
በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና፤
27ወልድ የሰው ልጅ ስለሆነም እንዲፈርድ
ሥልጣን ሰጥቶታል።

28"በዚህ አትደነቁ፤ መቃብር ውስጥ ያሉ
ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ጊዜ ይመጣል፤
29መልካም የሠሩ ለሕይወት ትንሣኤ፣

5፥15 ዮሐ1፥19፤ 5፥17 ሉቃ2፥49፤ ዮሐ9፥4፤ 14፥10 5፥18 ማቴ12፥14፤ ዮሐ10፥30፡33፤ 19፥7 5፥19 ቁ30፤ ዮሐ14፥24 5፥20 ዮሐ3፥35፤ 14፥12 5፥21 ዮሐ11፥25 ሮሜ4፥17፤ 8፥11፤ 2ቆሮ1፥9፤ ዕብ11፥19 5፥22 ቁ27፤ ዘፍ18፥25፤ መሳ11፥27፤ ዮሐ9፥39፤ ሐሥ10፥42 5፥23 ሉቃ10፥16፤ 1ዮሐ2፥23 5፥24 ማቴ10፥40፤ 25፥46፤ ዮሐ3፥15፡17፤ 3፥18፤ 1ዮሐ3፥14 5፥25 ዮሐ4፥23፤ 8፥43፡47፤ 16፥32

5፥26 ዘጸ30፥20፤ ኢዮ10፥12፤ 33፥4፤ መዝ36፥9፤ ዮሐ1፥4 5፥27 ቁ22 5፥28 ዮሐ4፥21፤ 16፥2 5፥29 ማቴ25፥46

እንኳን ፍጹም ወይም አልፎ አልፎ በደል ከመፈጸም ነጻ ባይሆኑም እውነተኛ አማኞች ሕይወታቸውን ለክርስቶስ ያስገዛሉ። ከመንፈስ ቅዱስ ኀይል የተነሣም ኀጢአት የማንነታቸው መገለጫ ሆኖ አይቀጥልም (1ጴጥ 1፥5፡ 1ዮሐ 3፥6፡9)። ኢየሱስ ዳግመኛ ከተወለዱ ሰዎች ሕይወት የሚጠብቀው፣ አማኞች በየቀኑ በሐሳብ፣ በቃልና በተግባር ኀጢአት በማድረግ ይቀጥላሉ ብለው አበክረው ከሚናገሩት ሰዎች ትምህርት በፍጹም ይለያል።

**5፥16 ያሳድዱት ነበር፤** የሐንስ በወንጌሉ ኢየሱስ ታምራት ቢያደርግም እንኳ ወይም ከታአምራቱ የተነሣ የሃይማኖት መሪዎች በብርቱ ይቃወሙት እንደ ነበር እዚህ ላይ ማመልከት ጀመረ።

**5፥18-24 ራሱን ከእግዚአብሔር እኩል በማድረጉ፤** ኢየሱስ አምላክ መሆኑን የሚገልጽ ብዙ አስደናቂ ንግግር አድርጓል፤ ይኸውም እንደሚከተለው ነው፤ (1) ልዩ በሆነ መንገድ እግዚአብሔር አባቱ እንደሆነ፤ (2) ከእግዚአብሔር ጋር አንድነትና ኅብረት እንዳለው ሥልጣንም በጋራ እንደያዘ (ቍ 19-20)፤ (3) ሕይወትን ለመስጠትና ሙታንን ለማስነሣት ኀይል እንዳለው (ቍ 21)፤ (4) በሰዎች ሁሉ ላይ የመፍረድ ሥልጣን እንዳለው (ቍ 22)፤ (5) መለኮታዊ ክብር የተገባው መሆኑ፣ (ቍ 23)፤ እና (6) የዘላለም ሕይወትን ለመስጠት የሚችል መሆኑ (ቍ 24)።

**5፥24 የሚሰማ ... የሚያምን፤** የዘላለም ሕይወት የሚኖራቸውንና ወደ ፍርድ የማይመጡትን ኢየሱስ፣ «የሚሰማ ... የሚያምን» በማለት ገልጾአቸዋል። «የሚሰማ» የሚለው ግስና (በግሪኩ «አኩዎ» ከሚለው ግስ የተገኘ «አኩዎን» የሚል ነው)፤ «የሚያምን» የሚለው ግስ (በግሪኩ «ፒስትዩዎ» ከሚለው ግስ የተገኘ «ፒስትዩዎን» የሚል ነው) በቀጣይ ተግባር ላይ የሚያተኩሩ የአሁን ጊዜ አንቀጾች ናቸው። ስለሆነም «የሚሰማ» እና «የሚያምን» የሚሉት ቃላት የአንድ አፍታን ሳይሆን ቀጣይነት ያለውን ተግባር የሚያመለክቱ ናቸው። ዛሬ የያዝነው የዘላለም ሕይወት ጸንቶ ሊቆም የሚችለው በየዕለቱ በምናሳየው ሕያው እምነት እንጂ ቀደም ብሎ በተፈጸመ የአንድ አፍታ የእምነት ውሳኔ ብቻ እንዳልሆነ ክርስቶስ አረጋግጧል (1፥12 እና ማብ፤ 4፥14 እና ማብ ይመ)።

**5፥24 ወደ ፍርድ አይመጣም፤** «ፍርድ» የሚለው ቃል በግሪኩ «ክሪሲስ» ማለት ሲሆን ቃሉ የገባው ከዘላለም የሞት ፍርድ ጋር በተያያዘ መልኩ ነው። አማኞች ከዓለም ጋር ለፍርድ አይቀርቡም (1ቆሮ 11፥32)። ይህ ፍርድ አማኞች በምድር በኖሩበት ዘመን የተሰጣቸውን የእግዚአብሔር ጸጋ በታማኝነት መጠበቅ አለመጠበቅን በተመለከተ ከሚጠብቃቸው ተጠያቂነትና ፍርድ ጋር አንድ ዐይነት አይደለም (በገጽ 1822 ላይ፣ *«በአማኞች ላይ የሚሰጥ የተለየ ፍርድ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**5፥26 ወልድም በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታል፤** የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት በራሱ የዘላለም ሕይወት ምንጭ ነው፤ ይህም ሕይወት ከዘላለም በእርሱ ውስጥ ያለ ነው። ይሁን እንጂ አማኞች በራሳቸው የዘላለም ሕይወትን ይዞ የመኖር ኀይል ይኖራቸው ዘንድ ከእግዚአብሔር አልተሰጣቸውም። ሕይወት የሚኖረን ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ባደረግን መጠን ሲሆን፣ ይህም ሕያው በሆነ የእምነት ግንኙነት ክርስቶስ በእኛ ውስጥ ሲኖር ነው (15፥4፡6 እና ማብ፡ ገላ 2፥20 ይመ)።

**5፥29 መልካም የሠሩ፤** በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ምንጊዜም ፍርድ የሚሰጠው በተፈጸመው ድርጊት መሠረት ነው፤ ምክንያቱም የአንድ ሰው ተግባር የእምነቱና የውስጣዊ ስሜቱ መገለጫ በመሆኑ ነው። ይህ ማለት የምንዳንው በክርስቶስ ላይ ስላለን እምነት በቃል በምንሰጠው ምስክርነት መሠረት ብቻ ሳይሆን በኖርነው ዐይነት አኗኗር ይሆናል (ማቴ 12፥36-37፤ 16፥27፤ ሮሜ 2፥6-10፤ 14፥12፤ 1ቆሮ 3፥13-15፤ 2ቆሮ 5፥10፤ ኤፌ 6፥8፤ ቈላ 3፥25፤ ራእ 2፥23፤ 20፥12፤ 22፥12)።

**5፥29 ለሕይወት ትንሣኤ፤** አዲስ ኪዳን ሙታን ሁሉ በአንድ ጊዜ ሳይነጣጠሉ ስለሚነሡበት ትንሣኤ

ክፉ የሠሩ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ።
30እኔ ብቻዬን ከራሴ ምንም ማድረግ
አልችልም፤ የምፈርደው የምሰማውን
ብቻ ነው፤ የላከኝን እንጂ የራሴን ፈቃድ
ስለማልሻም ፍርዴ ትክክል ነው።

## ስለ ኢየሱስ የሚናገሩ ምስክርነቶች

31"እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር፣ ምስክርነቴ
ተቀባይነት አይኖረውም። 32ስለ እኔ
የሚመሰክር ሌላ አለ፤ እርሱ ስለ እኔ
የሚሰጠውም ምስክርነት እውነት እንደ ሆነ
ዐውቃለሁ።
33"ወደ ዮሐንስ ልካችሁ ነበር፤ እርሱም
ስለ እውነት መስክሮአል፤ 34እኔ የሰው
ምስክርነት የምቀበል አይደለሁም፤ ይህን
የምናገረው ግን እናንተ እንድትድኑ ነው።
35ዮሐንስ እየነደደ ብርሃን የሚሰጥ መብራት
ነበረ፤ እናንተም ለጥቂት ጊዜ በብርሃኑ ደስ
ሊላችሁ ወደዳችሁ።
36"እኔ ግን ከዮሐንስ ምስክርነት
የላቀ ምስክር አለኝ፤ እንድፈጽመው አብ
የሰጠኝ፣ እኔም የምሠራው ሥራ አብ እንደ
ላከኝ ይመሰክራል። 37የላከኝ አብ ራሱ ስለ
እኔ መስክሮአል፤ እናንተም ከቶ ድምፁን
አልሰማችሁም፤ መልኩንም አላያችሁም፤
38የላከውንም ስላላመናችሁ ቃሉ በእናንተ
አይኖርም። 39በእነርሱ የዘላለም ሕይወትን
የምታገኙ እየመሰላችሁ፣ መጻሕ ፍትን
ትመረምራላችሁ፤[ሀ] እነዚሁ መጻሕፍት ስለ
እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤ 40እናንተ ግን፣
ሕይወት እንዲኖራችሁ ወደ እኔ መምጣት
አትፈልጉም።
41"እኔ ከሰው ክብር አልቀበልም፤ 42ነገር
ግን እናንተን ዐውቃችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርም
ፍቅር በልባችሁ እንደሌለ ዐውቃለሁ።
43እኔ በአባቴ ስም መጥቼ
አልተቀበላችሁኝም፤ ሌላው በራሱ ስም
ቢመጣ ግን ትቀበሉታላችሁ። 44እናንተ
እርስ በርሳችሁ ክብር የምትሰጣጡ፣ ነገር
ግን ከአንዱ አምላክ[ለ] የሚመጣውን ክብር
የማትፈልጉ ከሆነ፣ እንዴት ልታምኑ
ትችላላችሁ?
45"ከሳሻችሁ ተስፋ የጣላችሁበት
ሙሴ እንጂ፣ እኔ በአብ ፊት የምከሳችሁ
አይምሰላችሁ፤ 46ሙሴን ብታምኑ ኖሮ፣
እኔን ባመናችሁ ነበር፤ ምክንያቱም እርሱ
የጻፈው ስለ እኔ ነው። 47እርሱ የጻፈውን
ካላመናችሁ፣ እኔ የምናገረውን እንዴት
ታምናላችሁ?"

## ኢየሱስ አምስት ሺህ ሕዝብ መገበ

*6፥1-13 ተጓ ምብ — ማቴ 14፥13-21፤ ማር 6፥32-44፤ ሉቃ 9፥10-17*

6 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ጥብርያዶስ
የተባለውን የገሊላ ባሕር ተሻግሮ ራቅ
ወዳለው የባሕሩ ዳርቻ ሄደ። 2ብዙ ሰዎችም
በሽተኞችን በመፈወስ ያደረጋቸውን

5፥30 ቍ19፤ ማቴ26፥39፤ ኢሳ28፥6፤ ዮሐ8፥16
5፥31 ዮሐ8፥14
5፥32 ቍ37፤ ዮሐ8፥18
5፥33 ዮሐ1፥7
5፥34 ሐሥ16፥30፡31፤ ኤፌ2፥8፤ ቲቶ3፥5፤ 1ዮሐ5፥9
5፥35 ዳን12፥3፤ 2ጴጥ1፥19
5፥36 ዮሐ3፥17፤ 14፥11፤ 15፥24፤ 1ዮሐ5፥9
5፥37 ዘዳ4፥12፤ ዮሐ1፥18፤ 8፥18፤ 1ጢሞ1፥17
5፥38 ኢሳ26፥10፤ ዮሐ3፥17፤ 1ዮሐ1፥10፤ 2፥14
5፥39 ማቴ25፥46፤ ሉቃ 24፥27፡44፤ ሮሜ2፥17፡18፤ ሐሥ13፥27
5፥40 ዮሐ6፥44
5፥41 ቍ44
5፥44 ሮሜ2፥29
5፥45 ዮሐ9፥28፤ ሮሜ2፥17
5፥46 ዘፍ3፥15፤ ሉቃ24፥27፡44፤ ሐሥ26፥22
5፥47 ሉቃ16፥29 16፡31 6፥2 ዮሐ2፥11

[ሀ]5፥39 ወይም መጻሕፍትን መርምሩ
[ለ]5፥44 አንዳንድ የጥንት ቅጆች

አያስተምርም፤ (1) ከኢየሱስ ትንሣኤ በኋላ ወዲያው ስለተፈጸመው የብዙ "ቅዱሳን ሰዎች" ትንሣኤ (ማቴ 27፥52-53)፣ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በሚነጥቅበት ጊዜ ስለሚሆነው ትንሣኤ (1ቆሮ 15፥51-52፤ በገጽ 1907 ላይ፣ "***ንጥቀት***" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፣ ስለ "*መጀመሪያው ትንሣኤ*" (የራእ 20፥6ን ማብ ይመ) እንዲሁም በራእ 20፥6 የተገለጸው "*የመጀመሪያው ትንሣኤ*" ከሆነ ከአንድ ሺህ ዓመታት በኋላ ስለሚሆነው ትንሣኤ ማለትም በራእይ 20፥4 ከተገለጸው ከክርስቶስ ሺህ ዓመት መንግሥት በኋላ፣ (2) "*የመጀመሪያው ትንሣኤ*" ከክርስቶስ ሺህ ዓመት መንግሥት (ራእ 20፥4-6) በፊት ያሉትን አማኞች ሁሉ የሚያካትት ሊሆን ይችላል። በዚህም ምክንያት በራእ 20፥4-6 የተጠቀሰው ትንሣኤ የመጀመሪያውን ትንሣኤ ሙሉ ያደርጋል።

**5፥29 ክፉ የሠሩ፤** መጋጣነት፣ ርኵሰት፣ ፍትወት፣ ክፉ ምኞትና የመሳሰሉት በአማኞች ሕይወት ስፍራ የላቸውም (ቈላ 3፥5 ይመ)። የክርስቶስንና የሐዋርያትን ትምህርት በመቃረን ከክርስቶስ ኅብረት ውጭ የሚኖር ሰው የዘላለም ሕይወት ሊኖረው ይችላል እያሉ የሚያስተምሩ እጅግ የከፋውን የሐሰት ትምህርት እያስተማሩ ነው። ይህ ዐይነቱ ትምህርት እነርሱንና ተከታዮቻቸው ወደ ተሳሳተ የዘላለም ዋስትና ትምህርት ይመራቸዋል (1ቆሮ 6፥9-10፤ ገላ 5፥19-21 ኤፌ 5፥5-6 ይመ)። "ክፉ የሠሩ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ" በማለት ኢየሱስ የተናገረው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

**5፥44 እርስ በርሳችሁ ክብር የምትሰጣጡ፤** እውነተኛ እምነት ያላቸው ሰዎች ከሌሎች ሰዎች በሚቀርብላቸው ውዳሴና ሙገሳ አይሸነገሉም። የሕይወታቸው ዐላማ አድርገው የሚይዙት እግዚአብሔር አብን ደስ ማሰኘት ነው። ከሌሎች ሰዎች ክብርን መቀበል አብዝተው የለመዱ አማኞች ራሳቸውን እንደ ጣዖት ያመልካሉ፤ በዚህም ምክንያት ራሳቸውን ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጭ ያደርጋሉ። ከእግዚአብሔር ሞገስ ይልቅ የሰዎችን ውዳሴ አስበልጦ መውደድ የክርስቶስን ወንጌል መካድና እውነተኛ እምነት እንዳይኖር ማድረግ ነው (ከሮሜ 2፥29 ጋር ያነጻጽሩ)።

**5፥47 እርሱ የጻፈውን ካላመናችሁ፤** ይህ ጥቅስ ኢየሱስ የብሉይ ኪዳንን አስፈላጊነት በማጽናት የተናገረውን ለመረዳት አስፈላጊ ነው። ኢየሱስ የአራት መጻሕፍትን ሙሴ እንደጻፋቸው በእርግጥ ያምናል። አይሁድም ሆኑ እኛ ዛሬ የሚያስፈልገን ትምህርት ቢኖር ይህ ነው፤ አንድ ሰው በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አፈዎትና እውነተኛነት የማያምን ከሆነ፣ በኢየሱስ ቃል ሥልጣንና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስለ እርሱ በሚመሰክሩት አያምንም ወይም ሊቀበሉ አይገባም ማለት ነው (በሐሥ 24፥14 ጳውሎስ ስለ ብሉይ ኪዳን የነበረውን አመለካከት የሚገልጸውን ማብራሪያ ይመልከቱ፤ በገጽ 1941 ላይ፣ "***መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑና ያለው ሥልጣን***" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**6፥2 *ታምራት*፤** (1) *ታምራት ምንድን ናቸው?* (ሀ) ከተፈጥሮ ሕግ በላይ በሆነ ኀይል (የግሪኩ ትርጉም "ዱናሚስ" ይለዋል፤ ሐሥ 8፥13 እና 19፥11ን ይመ) የሚከናወኑ ሥራዎች ናቸው፤ (ለ) የመለኮታዊ ሥልጣን (ሉቃ 23፥8፤ ሐሥ 4፥16፡30፡33) ምልክት ወይም

ታምራዊ ምልክቶች ስላዩ ተከተሉት።
[3]ከዚያም ኢየሱስ ወደ ተራራ ወጥቶ ከደቀ
መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ። [4]የአይሁድ
የፋሲካ በዓልም ተቃርቦ ነበር።
[5]ኢየሱስም ቀና ብሎ ሲመለከት ብዙ
ሕዝብ ወደ እርሱ ሲመጣ አየ፤ ፊልጶስንም፣
"እነዚህ ሰዎች እንዲበሉ እንጀራ ከየት እን
ግዛ?" አለው። [6]ይህን የጠየቀው ሊፈትነው
እንጂ ራሱ ሊያደርግ ያሰበውን ያውቅ
ነበር።
[7]ፊልጶስም፣"እያንዳንዱ ሰው ትንሽ ትንሽ
እንዲቃመስ ለማድረግ፣ የሁለት መቶ ዲናር[a]
እንጀራ እንኳ አይበቃም" ሲል መለሰ።
[8]ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፣ የስምዖን
ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስም፣ እንዲህ አለ፤
[9]"አምስት ትንንሽ የገብስ እንጀራና ሁለት
ትንንሽ ዓሣ የያዘ አንድ ልጅ እዚህ አለ፤ ይህ
ግን ለዚህ ሁሉ ሕዝብ እንዴት ይዳረሳል?"
[10]ኢየሱስም፣ "ሰዎቹ እንዲቀመጡ
አድርጉ" አለ። በዚያ ቦታ ብዙ ሣር ነበረ፤
አምስት ሺህ ያህል ወንዶችም ተቀመጡ።
[11]ኢየሱስ አምስቱን እንጀራ አንሥቶ
አመሰገነ፤ ለተቀመጡትም የሚፈልጉትን
ያህል ዐደለ፤ ዓሣውንም እንዲሁ።
[12]ሁሉም በልተው ከጠገቡ በኋላ፣ ደቀ
መዛሙርቱን፣ "ከተረፈው ቍርስራሽ
ምንም እንዳይባክን ሰብስቡ" አላቸው።
[13]እነርሱም፣ ከተበላው አምስት የገብስ
እንጀራ የተረፈውን ቍርስራሽ ሰብስበው
ዐሥራ ሁለት መሶብ ሞሉ።
[14]ሰዎቹም ኢየሱስ ያደረገውን ታምራዊ
ምልክት ካዩ በኋላ፣ "ወደ ዓለም የሚመጣው
ነቢይ በርግጥ ይህ ነው" አሉ። [15]ኢየሱስም ሰዎቹ
መጥተው በግድ ሊያነግሡት እንዳሰቡ ዐውቆ
እንደ ገና ብቻውን ወደ ተራራ ገለል አለ።

6፥3 ቍ15
6፥4 ዮሐ11፥55
6፥5 ዮሐ1፥43
6፥8 ዮሐ1፥40
6፥9 2ነገ4፥43
6፥11 ቍ23፤ ማቴ14፥19
6፥14 ዘዳ18፥15፡18፤ ማቴ11፥3፤ 21፥11፤ ዮሐ2፥11
6፥15 ማቴ14፥23፤ ማር6፥46፤ ዮሐ18፥36
6፥19 ኢዮ9፥8
6፥20 ማቴ14፥27
6፥22 ቍ2፡15-21
6፥23 ቍ1፡11

## ኢየሱስ በውሃ ላይ እየተራመደ ሄደ

*6፥16-21 ተጓ ምብ — ማቴ 14፥22-33፤ ማር 6፥47-51*

[16]በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ
ባሕር ወረዱ፤ [17]በጀልባውም ተሳፍረው
ወደ ቅፍርናሆም ለመሻገር ተነሡ። ጊዜው
መሽቶ ነበር፤ ኢየሱስም ወደ እነርሱ ገና
አልመጣም ነበር። [18]ኀይለኛ ነፋስ ይነፍስ
ስለነበር ባሕሩ ተናወጠ። [19]አምስት ወይም
ስድስት ኪሎ ሜትር[b] ያህል እንደ ቀዘፉ፣
ኢየሱስ በውሃ ላይ እየተራመደ ወደ ጀልባዋ
ሲመጣ አይተው ደነገጡ። [20]እርሱ ግን፣
"እኔ ነኝ፤ አትፍሩ" አላቸው። [21]እነርሱም
እንዲሳፈር ፈለጉ፤ ጀልባዋም ወዲያውኑ
ወደሚሄዱበት ዳርቻ ደረሰች።
[22]በማግሥቱ በባሕሩ ማዶ የቀሩት ሰዎች
በዚያ አንዲት ጀልባ ብቻ እንደ ነበረች
ተረዱ፤ ኢየሱስ እንዳልተሳፈረና ደቀ መዛ
ሙርቱ ብቻቸውን እንደ ሄዱም ዐወቁ።
[23]ከዚያም በኋላ፣ ሌሎች ጀልባዎች ከጥብርያዶስ፣ ሕዝቡ ጌታ የባረከውን እንጀራ
ወደ በላበት ስፍራ መጡ። [24]ሰዎቹም፣
ኢየሱስ ወይም ደቀ መዛሙርቱ በዚያ
አለመኖራቸውን እንዳወቁ፣ ኢየሱስን ፍለጋ
በጀልባዎቹ ወደ ቅፍርናሆም ሄዱ።

[a]6፥7 ወይም የስምንት ወር ደመወዝ
[b]6፥19 በግሪኩ ሃያ አምስት ወይም ሠላሳ ምዕራፍ ቀዘፉ ይላል

መታወቂያ (የግሪኩ ትርጉም "ሴሚዮን" ይለዋል) በመሆን ያገለግላሉ። የአዲስ ኪዳን እምነት ማዕከልና እጅግ ታላቅ የሆነው ታምር የክርስቶስ ትንሣኤ ነው (1ቆሮ 15)።

(2) ታምራት በእግዚአብሔር መንግሥት ቢያንስ ሦስት ዐላማዎችን ለማከናወን ያገለግላሉ፤ (ሀ) ኢየሱስ ያስተላልፍ ለነበረው እውነት ድጋፍ በመስጠትና ክርስቶስ አድርጎ እግዚአብሔር የሾመው ለመሆኑ ማረጋገጫ በመስጠት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመሰክራሉ (2፥23፤ 5፥1-21፤ 10፥25፤ 11፥42)፤ (ለ) የክርስቶስን ርኅራኄ የተሞላበት ፍቅር ይገልጻሉ (ማር 8፥2፤ ሉቃ 7፥12-15፤ የሐሥ 10፥38)፤ (ሐ) የድነት ዘመን መግባትን (ማቴ 11፥2)፣ የእግዚአብሔር መንግሥት መምጣትን (በገጽ 1443 ላይ፣ "*የእግዚአብሔር መንግሥት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) እንደዚሁም እግዚአብሔር የሰይጣንን ግዛት እያሸነፈ መሆኑን ያሳያሉ (በገጽ 1499 ላይ፣ "*በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) ታምራት በቤተ ክርስቲያን ዘመን ሁሉ እንደሚከናወኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ያረጋግጣሉ፤ (ሀ) ኢየሱስ እንዲሰብኩና ታምራትን እንዲያደርጉ ደቀመዛሙርቱን ልኳቸዋል (ማቴ 10፥7-8፤ ማር 3፥14-15፤ ሉቃ 9፥2 እና ማብ ይመ)፤ (ለ) ወንጌል ተሰብኮላቸው በእርሱ ያመኑ ሁሉ እርሱ የሠራውን ሥራና ከዚያም የበለጠ ሥራ እንኳ ሊሠሩ እንደሚችሉ ኢየሱስ ተናግሯል (14፥12፤ ማር 16፥15-20)፤ (ሐ) በአማኞች ሕይወት ውስጥ ታምራት ይከናወን እንደነበረ የሐዋርያት ሥራ ይናገራል (ሐሥ 3፥1…፤ 5፥12፤ 6፥8፤ 8፥6…፤ 9፥32…፤ 15፥12፤ 20፥7…)። የወንጌሉ ስብከት የሚረጋገጥባቸው ታምራት በሌሎች የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ "ምልክቶች" ተብለው ተጠርተዋል (ሐሥ 4፥29-30፤ 14፥3፤ ሮሜ 15፥18-19፤ 2ቆሮ 12፥12፤ ዕብ 2፥3-4)፤ (መ) መንፈስ ቅዱስ ይህ የአሁኑ ዘመን እስከሚያበቃ ድረስ፣ እነዚህን ምልክቶች ለቤተ ክርስቲያን ለመስጠት ፈቃዱ ነው (1ቆሮ 12፥8-12፡28፤ ያዕ 5፥14-15፤ በገጽ 1527 ላይ፣ "*አማኞች የሚከተሏቸው መንፈሳዊ ምልክቶች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(4) ምልክቶችና ድንቆች በሰይጣን ኀይል አማካይነት በሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችና ሰባኪዎች ይልቁንም በሐሰተኛው ክርስቶስና በሐሰተኛው ነቢይ እንደሚከናወኑ አዲስ ኪዳን ያስተምራል (በገጽ 1471 ላይ፣ "*ታላቁ መከራ*" እና በገጽ 1519 ላይ፣ "*የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች*" በሚሉ ርእሶች የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመ)።

6፥5፤ አምስት ሺህዎችን ስለ መመገብ በማቴ 14፥19 ያለውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

**6፥15 ኢየሱስ ብቻውን ወደ ተራራ ገለል አለ፤** ኢየሱስ ብቻውን የሄደው ለመጸለይ ነበር (የማቴ 14፥23 ማብ ይመ)።

**6፥20 አትፍሩ፤** ማቴ 14፥27 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

## ኢየሱስ የሕይወት እንጀራ

25በባሕሩ ማዶ ባገኙትም ጊዜ፣ "ረቢ፤
መቼ ወደዚህ መጣህ?" አሉት።
26ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እውነት እላችኋለሁ የምትፈልጉኝ እንጀራ
ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ እንጂ፣
ታምራዊ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም።
27ለሚጠፋ እንጀራ አትሥሩ፤ ነገር ግን
የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ለዘላለም ሕይወት
ለሚኖር ምግብ ሥሩ፤ ለዚህም እግዚአብሔር
አብ ማረጋገጫ ማኅተሙን በእርሱ ላይ
አትሞአልና።"
28እነርሱም፣ "ታዲያ የእግዚአብሔርን ሥራ
ለመሥራት ምን ማድረግ አለብን?" አሉት።
29ኢየሱስም፣ "እርሱ በላከው ታምኑ
ዘንድ፣ ይህ የእግዚአብሔር ሥራ ነው" ሲል
መለሰላቸው።
30ስለዚህ እንዲህ ብለው ጠየቁት፤
"አይተን እንድናምንህ ምን ታምራዊ
ምልክት ታደርጋለህ? ምንስ ትሠራለህ?
31'ይበሉ ዘንድ ከሰማይ እንጀራን ሰጣቸው'
ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ አባቶቻችን በምድረ
በዳ መና በሉ።"
32ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት
እላችኋለሁ፤ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ
ሙሴ አይደለም፤ እውነተኛውን እንጀራ
ከሰማይ የሚሰጣችሁ ግን አባቴ ነው፤
33የእግዚአብሔር እንጀራ እርሱ ከሰማይ
የሚወርድ፣ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ
ነውና።"
34እነርሱም፣ "ጌታ፣ እንግዲያውስ ይህን
እንጀራ ሁልጊዜ ስጠን" አሉት።
35ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "የሕይወት
እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ
አይራብም፤ በእኔም የሚያምን ፈጽሞ
አይጠማም። 36ነገር ግን እንደ ነገርኋችሁ፣
አይታችሁኝም እንኳ አታምኑም። 37አብ
የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፤ ወደ እኔ
የሚመጣውንም ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፤
38ከሰማይ የወረድሁት የራሴን ፈቃድ
ለማድረግ ሳይሆን፣ የላከኝን የእርሱን ፈቃድ
ለመፈጸም ነውና፤ 39የላከኝም ፈቃድ፣
ከሰጠኝ ሁሉ አንድ እንኳ ሳይጠፋብኝ
በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣ ነው። 40የአባቴ
ፈቃድ ወልድን አይቶ በእርሱ የሚያምን
ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ነው፤
እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።"
41አይሁድም፣ "ከሰማይ የወረደ እንጀራ
እኔ ነኝ" በማለቱ ያጕረመርሙበት ጀመር።
42ደግሞም፣ "ይህ አባቱንና እናቱን የምናው
ቃቸው፣ የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ አይደለምን?
ታዲያ አሁን እንዴት፣ 'ከሰማይ ወረድሁ
ይላል'" አሉ።
43ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"እርስ በርሳችሁ አታጕረምርሙ፤ 44የላከኝ
አብ ካልሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ መም
ጣት አይችልም፤ እኔም በመጨረሻው
ቀን አስነሣዋለሁ። 45በነቢያትም፣ 'ሁሉም
ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ' ተብሎ
ተጽፎአል፤ አብን የሚሰማና ከእርሱም
የሚማር ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል።
46ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሆነው በቀር አብን
ያየ ማንም የለም፤ አብን ያየው እርሱ ብቻ

6፥25 ማቴ23፥7
6፥26 ቍ24:30፤ ዮሐ2፥11
6፥27 ቍ54፤ ኢሳ55፥2፤ ማቴ8፥20፤ 25፥46፤ ሮሜ4፥11፤ 1ቆሮ9፥2፤ 2ቆሮ1፥22፤ ኤፌ1፥13፤ 4፥30፤ 2ጢሞ2፥19፤ ራእ7፥3
6፥29 ዮሐ3፥17፤ 1ዮሐ3፥23
6፥30 ማቴ12፥38፤ ዮሐ2፥11
6፥31 ዘፀ16፥4:15፤ ዘኍ11፥7-9፤ ነህ9፥15፤ መዝ78፥24፤ 105፥40
6፥33 ቍ50፤ ዮሐ3፥13:31
6፥34 ዮሐ4፥15
6፥35 ቍ48:51፤ ዘፀ3፥14፤ ዮሐ3፥15፤ 4፥14፤ 8፥12፤ 10፥7:11፤ 11፥25፤ 14፥6፤ 15፥1
6፥37 ቍ39፤ ዮሐ17፥2:6:9:24
6፥38 ማቴ26፥39፤ ዮሐ3፥13:31፤ 3፥17
6፥39 ቍ40:44:54፤ ኢሳ27፥3፤ ኤር23፥4፤ ዮሐ10፥28፤ 17፥12፤ 18፥9
6፥40 ማቴ25፥46፤ ዮሐ12፥45
6፥42 ቍ38:62፤ ሉቃ4፥22፤ ዮሐ7፥27:28
6፥44 ቍ65፤ ኤር31፥3፤ ዮሐ12፥32
6፥45 ኢሳ54፥13፤ ኤር31፥33:34፤ 1ቆሮ2፥13፤ 1ተሰ4፥9፤ ዕብ8፥10:11፤ 10፥16፤ 1ዮሐ2፥27
6፥46 ዮሐ1፥18፤ 5፥37፤ 7፥29

**6፥35 የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤** ይህ ዐረፍተ ነገር ክርስቶስ መንፈሳዊ ሕይወትን የሚያበለጽግ መሆኑን ሲገልጽ (ቍ 53 ይመ)፣ በዮሐንስ ወንጌል ከተጻፉት ሰባት የ«እኔ ነኝ» አባባሎች መካከል የመጀመሪያው ነው፤ እያንዳንዳቸውም በልዩ ልዩ መንገድ የኢየሱስን የግል አገልግሎት ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ አጕልተው ያሳያሉ። ሌሎች የ«እኔ ነኝ» አባባሎች «የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ» (8፥12)፣ «በሩ እኔ ነኝ» (10፥9)፣ «መልካም እረኛ እኔ ነኝ» (10፥11:14)፣ «ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ» (11፥25)፣ «መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ» (14፥6) ደግሞም «እውነተኛው የወይን ተክል እኔ ነኝ (15፥1-5) ናቸው።

**6፥37 ከቶ ወደ ውጭ አልጥለውም፤** በንስሓና በእምነት ወደ እርሱ የሚመጡትን ሁሉ እንደሚቀበል ኢየሱስ ተስፋ ሰጥቶአል፤ ወደ ኢየሱስ የመጡት እግዚአብሔር ለሰጣቸው ጸጋ ምላሽ በመስጠት የመጡ ናቸው (በገጽ 1746 ላይ፣ «እምነትና ጸጋ» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**6፥40 የአባቴ ፈቃድ፤** የእግዚአብሔር አብ ፈቃድ ከሰው ልጆች ኀላፊነት ጋር ያለውን ግንኙነት መረዳት አስፈላጊ ነው፤ (1) ማንኛውም አማኝ ከጸጋ ይርቅ ዘንድና (ከገላ 5፥4 ጋር ያነጻጽሩ) በዚህም ምክንያት ከእርሱ ይለይ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም፤ ደግሞም ማንኛውም ሰው ይጠፋ ዘንድ (2ጴጥ 3፥9) ወይም እውነቱን መረዳት ተስኖት ድኅነትን ሳያገኝ ይቀር ዘንድ (1ጢሞ 2፥4) የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም፤ (2) ይሁን እንጂ፣ በእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድና እግዚአብሔር ባወቀ በሚፈጸመው ክፉ ነገር መካከል ትልቅ ልዩነት አለ (በገጽ 1075 ላይ፣ «የእግዚአብሔር ፈቃድ» በሚል ርዕስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። የራሱ ፍጹም ፈቃድ ባይፈጸምም እንኳ የሰው ልጆችን ንስሐ የመግባትና የማመን ኀላፊነት አይነጥቅም (በሉቃ 19፥41 ላይ ስለ ኢየሩሳሌም ማልቀሱን በሚመለከት የቀረበውን ማብ ይመ.)፤ (3) አማኞች በመጨረሻው ቀን እንደሚነሡ የእግዚአብሔር ፍላጎት መሆኑ ለእርሱ ድምፅ ከመታዘዝና እርሱንም ከመከተል ካለባቸው ኀላፊነት ነጻ አያደርጋቸውም (10፥27፤ 14፥21)። ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት ምሽት ደቀ መዛሙርቱን፣ «በሰጠኸኝ ስም ከለልኋቸው፤ ጠበቅኋቸውም … ከአንዱ ከጥፋት ልጅ በቀር ከእነርሱ ማንም አልጠፋም» (17፥12) በማለት እንደጠበቃቸው ገልጾአል።

**6፥44 አብ ካልሳበው በቀር፤** እግዚአብሔር አብ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ይስባቸዋል፤ ኢየሱስ፣ «ሰውን ሁሉ ወደ ራሴ እስባለሁ» (12፥32) እንዳለ ሁሉ የእግዚአብሔርም የመሳብ ሥራ ሰዎችን ሁሉ ያጠቃልላል። ይህ የመሳብ ሥራ ግን እምቢ ሊባል የማይቻል አይደለም፤ ምክንያቱም ሳንቀበለው እንችላለንና (በማቴ 23፥37 ላይ ያለውን «እናንተ ግን አልፈቀዳችሁም» የሚለውን ይመ)።

ነው። 47እውነት እላችኋለሁ፤ የሚያምን
ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው። 48የሕይወት
እንጀራ እኔ ነኝ። 49አባ ቶቻችሁ በምድረ
በዳ መና በሉ፤ ይሁን እንጂ ሞቱ። 50ነገር
ግን ሰው እንዳይሞት ይበላው ዘንድ ከሰማይ
የሚወርድ እንጀራ ይህ ነው። 51ከሰማይ
የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ማንም
ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤
ይህም እንጀራ፣ ለዓለም ሕይወት እንዲሆን
የምሰጠው ሥጋዬ ነው።"
52አይሁድም፣ "እንዴት ዘንድ ይህ ሰው
ሥጋውን እንዴት ሊሰጠን ይችላል?"
እያሉ እርስ በርሳቸው እጥብቀው ይከራከሩ
ጀመር።
53ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እውነት
እላችኋለሁ፤ የሰውን ልጅ ሥጋውን
ካልበላችሁና ደሙንም ካልጠጣችሁ
በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። 54ሥጋዬን
የሚበላ፣ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም
ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን
አስነሣዋለሁ፤ 55ሥጋዬ እውነተኛ ምግብ፣
ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና፤ 56ሥጋዬን
የሚበላ፣ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤
እኔም በእርሱ እኖራ ለሁ። 57ሕያው አብ
እንደ ላከኝ፣ እኔም ከእርሱ የተነሣ በሕይወት
እንደምኖር፣ የሚበላኝም እንዲሁ ከእኔ
የተነሣ በሕይወት ይኖራል። 58ከሰማይ የወረደ
እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና በሉ፤
ሞቱም፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ግን ለዘላለም
ይኖራል።" 59ይህን የተናገረው በቅፍርናሆም፣
በምኩራብ እያስተማረ ሳለ ነበር።

**ብዙ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን መከተል ተዉ**

60ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ይህን
ሲሰሙ፣ "ይህ የሚያስጨንቅ ቃል ነው፤
ማንስ ሊቀበለው ይችላል?" አሉ።
61ደቀ መዛሙርቱም በዚህ ነገር
ማጕረምረማቸውን ኢየሱስ በግዛ
ራሱ ተረድቶ፣ እንዲህ አላቸው፤ "ይህ
ሰንቅፋት ይሆንባችኋልን? 62ታዲያ፣ የሰው
ልጅ ቀድሞ ወደ ነበረበት ሲወጣ ብታዩ
ምን ልትሉ ነው? 63መንፈስ ሕይወትን
ይሰጣል፤ ሥጋ ግን ምንም አይጠቅምም።
እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስም ሕይወትም
ነው፤ 64ይሁን እንጂ ከእናንተ የማያምኑ
አንዳንዶች አሉ።" ይህም፣ ኢየሱስ እነማን
እንደማያምኑና ማን አሳልፎ እንደሚሰጠው
ቀድሞውኑ ያውቅ ስለ ነበር ነው።
65ቀጥሎም፣ "ከአብ ካልተሰጠው
በቀር፣ ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም'
ያልኋችሁ ለዚህ ነው" አለ።
66ከዚህም በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ
ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ፤ ከዚያም ወዲያ
አልተከተሉትም።
67ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን፣ "እናንተም
ደግሞ መሄድ ትፈልጋላችሁ?" አላቸው።
68ስምዖን ጴጥሮስም እንዲህ ሲል
መለሰለት፤ "ጌታ ሆይ፤ ወደ ማን እንሄዳለን?
አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤ 69አንተ
እን ድያ የእግዚአብሔር ቅዱስ እንደ ሆንህ
አምነናል፤ ዐውቀናልም።"

6፥47 ማቴ25፥46
6፥48 ቍ35፡51
6፥49 ቍ31፡58
6፥50 ቍ33
6፥51 ቍ35፡41፡48፡58፤ ዕብ10፥10
6፥52 ዮሐ1፥19፤ 7፥43፤ 9፥16፤ 10፥19
6፥53 ማቴ8፥20፤ 26፥26፡28
6፥54 ቍ39
6፥56 ዮሐ15፥4-7፤ 1ዮሐ2፥24፤ 3፥24፤ 4፥15
6፥57 ዮሐ3፥17
6፥58 ቍ49-51፤ ዮሐ3፥36፤ 5፥24
6፥60 ቍ52፡66
6፥61 ማቴ13፥57
6፥62 ማቴ8፥20፤ ማር16፥19፤ ዮሐ3፥13፤ 17፥5
6፥63 2ቆሮ3፥6
6፥64 ማቴ10፥4፤ ዮሐ2፥25
6፥65 ቍ37፡44፤ ማቴ13፥11
6፥66 ቍ60
6፥67 ማቴ10፥2
6፥68 ቍ63፤ ማቴ16፥16
6፥69 ማር1፥24፤ 8፥29፤ ሉቃ9፥20

**6፥54 *ሥጋዬን የሚበላ፣ ደሜንም የሚጠጣ፤*** መንፈሳዊ ሕይወትን የምንቀበለው በክርስቶስ በማመንና በመስቀል ላይ የተፈጸመው ሞቱ ያስገኘልንን የቤዛነት በረከት በመካፈል ነው (ሮሜ 3፥24-25፤ 1ዮሐ 1፥7)። መንፈሳዊ ሕይወታችን የሚጠበቀው ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ሲኖረንና በቃሉ ጸንተን ስንቆም ነው። በቍ 53 ላይ ያለውን ሐሳብ፣ «እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስም ሕይወትም ነው» ከሚለው ከቍ 63 ጋር ያነጻጽሩ። በዚህም ዐይነት ከክርስቶስ የሆነውን የምንካፈለው በእርሱ ላይ ባለን እምነትና በጸሎት መንፈስ ቃሉን በመቀበል ስንጸና ነው።

(1) ኢየሱስ ሕያው ቃል ነው (1፥1-5)፤ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ የተጻፈ ቃል (2ጢሞ 3፥16፤ 2ጴጥ 1፥21)። እዚህ ላይ ኢየሱስ ራሱን «የሕይወት እንጀራ» (ቍ 35) ብሎ ሲጠራ በሌላ ስፍራ ደግሞ ይህንኑ እንጀራ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በማዛምድ፣ «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም» (ማቴ 4፥4) ይላል። ስለሆነም ሥጋውን የምንበላው በእርሱ (በክርስቶስ) በማመን ጸንተን ስንኖርና የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብለን ለቃሉ ስንታዘዝ ነው (ቍ 63)።

(2) ድኅነትን ያገኘነው በእግዚአብሔር ጸጋና ቃሉን በመጀመሪያ በሰማንበት ወቅት ዳግም ልደትን የሚሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ኀይል በሕይወታችን በፈጸመው ተግባር ነው (1፥12፤ ሐሥ 2፥41)። ያገኘነው ድኅነት የምንጸናውና ጸጋን በመቀበል መቀጠል የምንችለው፣ ከክርስቶስ ጋር ያለንን ኅብረት ስናጠናክር፣ የእግዚአብሔርን ቃል ያለማቋረጥ ስናነብና ስንታዘዝ እንዲሁም የቃሉን እውነት ወደ ልቦናችን በማስገባት ስንመገብ ነው (1ጢሞ 4፥13-16፤ ያዕ 1፥21)። ከክርስቶስ ጋር ያለውን ኅብረት ማቋረጥና ከቃሉ መለየት ወደ ሞት የሚያደርስ ስለሆነ አደገኛ ነው።

**6፥64 ኢየሱስ … ቀድሞውኑ ያውቅ ስለነበረ ነው፤** ይህ አባባል ይሁዳ ከመጀመሪያ እምነቱ መቼ መንሸራተት እንደ ጀመረና እርሱንም አሳልፎ ለመስጠት ምን ጊዜ እንዳቀደ ኢየሱስ ያውቅ እንደነበር ሊያመለክት ይችላል። ይሁዳ እንደ ሌሎቹ ዐሥራ አንድ ደቀ መዛሙርት ሁሉ ተመሳሳይ ምርጫ ነበረው። ክርስቶስ ለሌሎቹ ደቀመዛሙርት እንዳደረገው ሁሉ ለይሁዳም ከሰጠው ነጻነት አንጻር (2፥23-24፤ ማቴ 10፥1-15) ማየት እንደሚቻለው፣ ይሁዳ እማኝ ሲሆን፣ የኢየሱስ የቅርብና ዩታመኑ ወዳጅ ነበር (መዝ 41፥9፤ ዮሐ 13፥18)። የኋላ ኋላ ግን የራሱን መንገድ ተከትሎ ወደ ኋላ ተመለሰ (ሐሥ 1፥25) እንጂ ኢየሱስን እንዲከዳ ከመጀመሪያውኑ የሚያስገድድ ነገር አልገጠመውም። በሌላ አነጋገር የኢየሱስ መከዳት እውን እንደሚሆን ትንቢት ተነገረ እንጂ ማን እንደሚፈጽመው አልተነገረም። ክርስቶስን አሳልፎ የሚሰጠው ከዘላለም ዘመናት በፊት አስቀድሞ የተወሰነበት እከሌ የተባለ ሰው አልነበረም። የይሁዳ ወደ ጠላት ከድቶ መግባትና በውጤቱም የተከሠተው አሳዛኝ ሁኔታ ማንኛውም የክርስቶስ ተከታይ ከዓለም ጋር በመወዳጀትና ክርስቶስን ትቶ ወደ ነበረበት በመመለስ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠውን ማስጠንቀቂያ ተጋፍቶ እንዳይሄድ የሚያሳስብ ይሆናል (ዕብ 10፥29፤ 12፥25፤ ያዕ 4፥4)።

70ኢየሱስም መልሶ፣ "ዐሥራ
ሁለታችሁንም የመረጥኋችሁ እኔ
አይደለሁምን? ነገር ግን ከእናንተ አንዱ
ዲያብሎስ ነው" አላ ቸው። 71የአስቆሮቱ
የስምዖን ልጅ ይሁዳ፣ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ
ቢሆንም፣ ኋላ አሳልፎ ስለሚሰጠው ስለ
እርሱ መናገሩ ነበር።

## ኢየሱስ የዳስ በዓል ወደሚከበርበት ሄደ

7 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ፣ በዚያ የነበሩት
አይሁድ ሊገድሉት ስለ ፈለጉት፣ በይሁዳ
አውራጃ መዘዋወር ትቶ በገሊላ ተዘዋወረ።
2የአይሁድ የዳስ በዓል በተቃረበ ጊዜ ግን፣
3የኢየሱስ ወንድሞች እንዲህ አሉት፤ "ደቀ
መዛሙርትህም ደግሞ የምታደርገውን
ታምራት እንዲያዩ፣ ከዚህ ወደ ይሁዳ ሂድ፤
4ራሱን ሊገልጥ እየፈለገ በስውር የሚሠራ
ማንም የለምና። አንተም እነዚህን ነገሮች
የምታደርግ ከሆነ፣ ራስህን ለዓለም ግለጥ።"
5የገዛ ወንድሞቹ እንኳ አላመኑበትም ነበር።
6ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "ለእኔ
ትክክለኛው ጊዜ ገና አልደረሰም፤ ለእናንተ
ግን ማንኛውም ጊዜ ምቹ ነው። 7ዓለም እናንተን
ሊጠላ አይችልም፤ እኔ ግን፣ አድራጎቱ
ክፉ መሆኑን ስለምመሰክርበት ይጠላኛል።
8እናንተ ወደ በዓሉ ሂዱ፤ ለእኔ ትክክለኛው
ጊዜ ስላልደረሰ[ሠ] ወደ በዓሉ አልሄድም።"
9ይህን ብሎአቸው በገሊላ ቈየ።
10ይሁን እንጂ፣ ወንድሞቹ ወደ በዓሉ
ከሄዱ በኋላ፣ እርሱም በግልጥ ሳይሆን
በስውር ወደ በዓሉ ሄደ። 11በበዓሉም ላይ
አይሁድ፣ "ያ ሰው የት አለ?" እያሉ
ይፈልጉት ነበር።
12ስለ እርሱ በሕዝቡ መካከል ብዙ
ጕምጕምታ ነበር። አንዳንዶች፣ "ደግ ሰው
ነው" አሉ።
ሌሎች ግን፣ "የለም፤ ሕዝቡን የሚያስት
ነው" አሉ። 13ይሁን እንጂ አይሁድን
ከመፍራት የተነሣ ስለ እርሱ በግልጽ
የተናገረ ማንም አልነበረም።

6፥70 ዮሐ13፥27፤ 15፥16፡19፤ 17፥12
6፥71 ማቴ10፥4፤ 26፥14
7፥1 ቍ19፡25፤ ማቴ12፥14፤ ዮሐ1፥19
7፥2 ዘሌ23፥34፤ ዘዳ16፥16
7፥3 ማቴ12፥46
7፥5 መዝ69፥8፤ ማር3፥21
7፥6 ማቴ26፥18
7፥7 ዮሐ3፥19፡20፤ 15፥18፡19
7፥8 ቍ6፤ ማቴ26፥18
7፥11 ዮሐ11፥56
7፥12 ቍ40፡43
7፥13 ዮሐ9፥22፤ 12፥42፤ 19፥38፤ 20፥19
7፥14 ቍ28፤ ማቴ26፥55
7፥15 ማቴ13፥54፤ ዮሐ1፥19፤ ሐሥ26፥24
7፥16 ዮሐ14፥24
7፥17 መዝ25፥14
7፥18 ዮሐ5፥41፤ 8፥50፡54
7፥19 ቍ1፤ ዘዳ32፥46፤ ማቴ12፥14፤ ዮሐ1፥17
7፥20 ማር3፥22
7፥21 ቍ23፤ ዮሐ5፥2-9
7፥22 ዘፍ17፥10-14፤ ዘሌ12፥3
7፥24 1ሳሙ16፥7፤ ኢሳ11፥3፡4፤ ዮሐ8፥15፤ 2ቆሮ10፥7
7፥25 ቍ1፤ ማቴ12፥14
7፥26 ቍ48፤
7፥26 ዮሐ4፥29

## ኢየሱስ በበዓሉ ላይ ተገቃቶ አስተማረ

14በበዓሉም አጋማሽ ኢየሱስ ወደ
ቤተ መቅደስ ወጥቶ ያስተምር ጀመር።
15አይሁድም በመደነቅ፣ "ይህ ሰው ሳይማር
መጻሕፍትን እንዴት ሊያውቅ ቻለ?" አሉ።
16ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"የማስተምረው ትምህርት ከራሴ ሳይሆን፣
ከላከኝ የመጣ ነው። 17ማንም የእግዚአብሔርን
ፈቃድ ለማድረግ ቢፈልግ፣ የእኔ ትምህርት
ከእግዚአብሔር ወይም ከራሴ የመጣ መሆኑን
ለይቶ ያውቃል፤ 18ከራሱ የሚናገር፣ ያን
የሚያደርገው ለራሱ ክብርን ስለሚሻ
ነው፤ ስለላከው ክብር የሚሠራ ግን እርሱ
እውነተኛ ነው፤ ሐሰትም አይገኝበትም።
19ሙሴ ሕግን አልሰጣችሁምን? ነገር ግን
አንዳችሁም ሕጉን አልጠበቃችሁም። ለምን
ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ?"
20ሕዝቡም፣ "አንተ ጋኔን ያደረብህ!
ደግሞ አንተን ማን ሊገድል ይፈልጋል?"
አሉት።
21ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"አንድ ሥራ ብሠራ፣ ሁላችሁም
ተገረማችሁ። 22ግዝረት የመጣው ከአባቶች
እንጂ ከሙሴ አይደለም፤ ሆኖም ሙሴ
ግዝረትን ስለ ሰጣችሁ በሰንበት እንኳ ሕፃን
ትገርዛላችሁ። 23የሙሴ ሕግ እንዳይሻር
ሕፃን በሰንበት የሚገረዝ ከሆነ፣ የሰውን
ሁለንተና በሰንበት ስለ ፈወስሁ ለምን በእኔ
ላይ ትቈጣላችሁ? 24የሰውን ፊት በማየት
መፍረድ ትታችሁ ቅን ፍርድ ፍረዱ።"

## ኢየሱስ፣ እርሱ ክርስቶስ ስለ መሆኑ

25በዚህ ጊዜ በኢየሩሳሌም የነበሩ
አንዳንድ ሰዎች እንዲህ አሉ፤ "ሊገድሉት
የሚፈልጉት ሰው ይህ አይደለምን? 26ይኸው
እርሱ በአደባባይ ይናገራል፤ አንድም ቃል
አይናገሩትም፤ ክርስቶስ[ፀ] ነው ብለው ባለ

ሠ7፥8 አንዳንድ ቅጆች ገና ስላልደረሰ ይላሉ
ፀ7፥26 ወይም መሲሑ፤ እንዲሁም ቍ 27፡31፡41
እና 42 ይመ

7፥2 **የዳስ በዓል፤** የ"ዳስ በዓል" የሚከበረው የእስራኤላውያን ከምድረ ግብፅ ከወጡ በኋላ በእግዚአብሔር ጥበቃ በዳስ ወይም በድንኳን እየኖሩ (የዘሌ 23፥34-43 እና ማብ ዘካ 14፥16-19 ይመ) በምድረ በዳ ይንከራተቱ የነበሩበትን ወቅት ያደረጉትን ጕዞ ለማስታወስ ነው።

7፥7 **እኔን ... ይጠላኛል፤** ኢየሱስ ከእግዚአብሔር የተለዩ ሰዎች ሁሉ ጕስቋሎች፣ ኀጢአተኞችና በተፈጥሮ ራስ ወዳዶች መሆናቸውን ስለሚገልጥ፣ በዓለም ዘንድ የተጠላ ነበር (ከ2፥14-16፤ 3፥19-20፤ 5፥30-47 ጋር ያነጻጽሩ)። በአገልግሎት ዘመኑም ሁሉ የፍትሕ መጓደልን፣ ጭካኔንና ርኵሰትን አጥብቆ ያወግዝ ነበር። የሰው ልጅ ኀጢአተኛ እንደሆነ በማያሰልስ ሁኔታ የሚገልጸው ምስክርነት፣ በራሳቸው ጽድቅ ተነሣሥተው የወንጌልን እውነት በማለባበስ ኀጢአትን እንደሳቱ አይተው ከሚያልፉት አገልጋይ ተብየዎች አመለካከት ጋር የሚቃረን ነው፤ ይህም አድራጎታቸው ንስሓ እንዲገባና በጻድቅ መመሳለስ ተገቢ እንደ ሆነ ከሚያስገድደው ከነቢይነት ተልእኮ ጋር የተፋታ ነው።

7፥17 **ማንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ቢፈልግ፤** ወደ ድኅነት የሚያደርስ እውነተኛ እምነትና በተግባር የሚገለጽ የኢየሱስ ትምህርት፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በቅንነት የመፈጸም ፍላጎትን ይጠይቃሉ። ማመን ማለት ለመታዘዝ ቃል መግባት ነው (በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" የሚለውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

7፥18 **ለራሱ ክብርን ስለሚሻ ነው፤** ኢየሱስ የሃይማኖት ሰባኪያን ነን የሚሉ ሁሉ ከእግዚአብሔር መሆናቸውንና አለመሆናቸውን መለየት የሚያስችል ምንጊዜም ሊሠራበት የሚችል መመዘኛ ያቀርባል፤ የራሳቸውን ክብርና ጥቅም ማስጠበቅ ይፈልጋሉን? አገልጋዮችን በምትገመግሙበት ጊዜ ስብከታቸው እነርሱን ወይም ጌታ ኢየሱስን የሚያወድስ መሆን አለመሆኑን አስተውሉ።

ሥልጣኖቹም ተቀብለውት ይሆን? [27]ይህ
ሰው ግን ከየት እንደ ሆነ እኛ እናውቃለን፤
ክርስቶስ ሲመጣ እኮ ከየት እንደ ሆነ ማንም
አያውቅም።"
[28]ኢየሱስ በቤተ መቅደስ አደባባይ
ሲያስተምር ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲህ
አለ፤ "አዎን፣ እኔን ታውቁኛላችሁ፤ ከየት
እንደ ሆንሁም ታውቃላችሁ። እኔ እዚህ
ያለሁት በገዛ ራሴ አይደለም፤ ነገር ግን
የላከኝ እርሱ እውነተኛ ነው። እናንተ
አታውቁትም፤ [29]እኔ ግን ከእርሱ ዘንድ ስለ
ሆንሁ፣ እርሱም ስለ ላከኝ ዐውቀዋለሁ።"
[30]ስለዚህ ሊይዙት ፈለጉ፤ ነገር ግን ጊዜው
ገና ስላልደረሰ ማንም እጁን አላሳረፈበትም፤
[31]ሆኖም ከሕዝቡ ብዙዎች በእርሱ አምነው፣
"ታዲያ፣ ክርስቶስ ሲመጣ ይህ ሰው
ከሚሠራቸው ታምራዊ ምልክቶች የበለጠ
ያደርጋል?" አሉ። [32]ፈሪሳውያን፣ ሕዝቡ ስለ
እርሱ በጕምጕምታ የሚነጋገረውን ነገር
ሰሙ፤ የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያንም
እንዲይዙት የቤተ መቅደስ ጠባቂዎችን
ላኳቸው።
[33]ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ "ከእናንተ
ጋር የምቈየው ጥቂት ጊዜ ነው፤ ከዚያም
ወደ ላከኝ እሄዳለሁ፤ [34]ትፈልጉኛላችሁ፤
ግን አታገኙኝም፤ ወዳለሁበትም ልትመጡ
አትችሉም።"
[35]አይሁድም እርስ በርሳቸው እንዲህ
ተባባሉ፤ "ይህ ሰው፣ ልናገኘው የማንችለው
ወዴት ለመሄድ ቢያስብ ነው? በግሪኮች
መካከል ተበታትነው ወደሚኖሩት ወገኖቻችን
ሄዶ ግሪኮችን ሊያስተምር ፈልጎ ይሆን?
[36]'ትፈልጉኛላችሁ፤ ግን አታገኙኝም፤'
ደግሞም፣ 'እኔ ወዳለሁበት ልትመጡ
አትችሉም' ሲል ምን ማለቱ ይሆን?"
[37]የበዓሉ መጨረሻ በሆነው በታላቁ ቀን፣
ኢየሱስ ቆሞ ከፍ ባለ ድምፅ እንዲህ አለ፤
"ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና
ይጠጣ፤ [38]በእኔ የሚያምን፣ መጽሐፍ
እንዳለ[a] የሕይወት ውሃ ምንጭ ከውስጡ
ይፈልቃል።" [39]ይህን ያለው በእርሱ
የሚያምኑ ስለሚቀበሉት መንፈስ ነበር፤
ምክንያቱም ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ
አልተሰጠም ነበር።
[40]ከሕዝቡ አንዳንዶቹ ቃሉን ሰምተው፣
"ይህ ሰው በእርግጥ ነቢዩ ነው" አሉ።
[41]ሌሎችም፣ "እርሱ ክርስቶስ ነው"
አሉ።
ሌሎች ደግሞ እንዲህ አሉ፤ "ክርስቶስ
ከገሊላ እንዴት ሊመጣ ይችላል? [42]መጽሐፍ፣
ክርስቶስ ከዳዊት ዘር[b]፣ ዳዊትም ከኖረበት
ከቤተልሔም እንደሚመጣ ይናገር የለምን?"
[43]ስለዚህም በኢየሱስ ምክንያት በሕዝቡ
መካከል መለያየት ሆነ፤ [44]አንዳንዶቹም
ሊይዙት ፈለጉ፤ ነገር ግን ማንም እጁን
አላሳረፈበትም።

## የአይሁድ መሪዎች አለማመን

[45]በመጨረሻም የቤተ መቅደስ ጠባቂዎቹ፣
ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ፈሪሳውያን

7፥27 ማቴ13፥55፤ ሉቃ4፥22፤ ዮሐ6፥42
7፥28 ቍ14፤ ዮሐ8፥14፡26፡42
7፥29 ማቴ11፥17፤ ዮሐ3፥17
7፥30 ቍ32፡44፤ ማቴ26፥18፤ ዮሐ10፥39
7፥31 ዮሐ2፥11፤ 8፥30፤ 10፥42፤ 11፥45፤ 12፥11፡42
7፥33 ዮሐ12፥35፤ 13፥33፤ 16፥5፤ 10፡16፡17፡28
7፥34 ቍ36፤ ዮሐ8፥21፤ 13፥33
7፥35 ዮሐ12፥20፤ ሐሥ17፥4፤ 18፥4፤ ያዕ1፥1
7፥36 ቍ34
7፥37 ዘሌ23፥36፤ ኢሳ55፥1፤ ራእ22፥17
7፥38 ዮሐ3፥15፤ 4፥10፡14፤ ኢሳ58፥11
7፥39 ኢዩ2፥28፤ ዮሐ1፥33፤ 12፥23፤ 20፥22፤ ሐሥ2፥17፡33፤ 13፥31፡32
7፥40 ማቴ21፥11
7፥41 ቍ52፤ ዮሐ1፥46
7፥42 ማቴ1፥1፤ 2፥5፡6፤ ሉቃ2፥4፤ ሚክ5፥2
7፥43 ዮሐ6፥52፤ 9፥16፤ 10፥19 7፥44 ቍ30

[a]7፥37፡38 ወይም ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣ፤ [38]በእኔ የሚያምን ይጠጣ
[b]7፥42 ወይም ከዳዊት ቤተ ሰብ

7፥38 **መጽሐፍ እንዳለ፤** ኢየሱስ «መጻሕፍን» የጠቀሰው የአባቱ እውነተኛ ቃል ስለሆነና ከዚህም የተነሣ በሕይወቱና በትምህርቱ ላይ የመጨረሻ ሥልጣን ያለው ቃል በመሆኑ ነው:: የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ለክርስቲያኖች ፍጹም ሥልጣን ያለው ቃል ነው፤ ምክንያቱም የአኗኗራችንን መመዘኛ የመወሰን መብት ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ይህንን ሥልጣኑን በተግባር ሊያውል የመረጠው የእርሱ እውነት በቃሉ (በቅዱሳት መጻሕፍት) ውስጥ እንዲታወቅ በማድረግ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጥ እንደመሆኑ መጠን እግዚአብሔር ራሱ ለእኛ በቀጥታ ቢናገረን የሚኖረውን ያህል ሥልጣን አለው (በገጽ 1941 ላይ፣ *«መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑና ያለው ሥልጣን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

(1) የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያረፈባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ለአማኙ ሕይወት ዋና መመሪያ ናቸው:: የቤተ ክርስቲያን ወግ፣ ትንቢቶች፣ አዲስ መገለጥ የሚባሉት፣ አስተምህሮዎችና የሰው ሐሳቦች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ሊዳኙ ይገባል፤ መጽሐፍ ቅዱስ ወዳለው የሥልጣን ደረጃም ከፍ ከፍ ሊደረጉ ፈጽሞ አይገባም (ከማር 7፥13፤ ከቈላ 2፥8፤ ከ1ጴጥ 1፥18-19 ጋር ያነጻጽሩ)::

(2) ከእግዚአብሔርና እስትንፋሱ ካረፈበት ቃሉ ጋር በማስተካከል ወይም በማስበለጥ በሌላ ባለሥልጣን ማመን፣ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው እምነትና ከክርስቶስ ጌትነት ራስን ማራቅ ነው:: ማንኛውም ሰው፣ ድርጅት፣ ሃይማኖታዊ ማኅበር ወይም ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃል ከተሰጠው መገለጥ ጋር የሚተካከል ወይም የሚበልጥ ሥልጣን አለው ማለት ጣዖትን እንደ ማምለክ ነው:: ስለሆነም እምነታቸውን ለአዲስ ኪዳን ሥልጣን ለማስገዛት ፈቃደኞች ያልሆኑ ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ ከተመሠረተው ክርስትናና በክርስቶስ ከሚገኘው ድነት ራሳቸውን ያገለሉ ናቸው::

7፥38 **የሕይወት ውሃ ምንጭ፤** የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለአማኞች በተሰጣቸው ጊዜ በሚፍለቀለቅ የሕይወት ልምምድ ውስጥ ይገባሉ:: ከዚያም በኋላ ይህ «የሕይወት ውሃ» የኢየሱስ ክርስቶስን የፈውስ መልእክት ይዞ ወደ ሌሎች ሰዎች ይፈሳል (10፥10፤ 14፥12፤ 15፥5 በተጨማሪም መዝ 1፥3፤ 46፥4፤ ኢሳ 32፥15፤ 44፥3፤ 58፥11፤ ኤር 31፥12፤ ሕዝ 47፥1-12፤ ኢዮ 3፥18፤ ዘካ 14፥8 ይመ)::

7፥39 **ኢየሱስ ገና ስላልከበረ፤** ይህ ጥቅስ የሚናገረው በመስቀል ላይ ሊገለጽ ስላለው የኢየሱስ ክብር ነው (12፥23-24ን ይመ):: ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመውን ሥራ በማመን የኀጢአት ይቅርታን ካለገኙ በቀር መንፈስ ቅዱስ በሙላት አይሰጥም:: እዚህ ላይ «መንፈስ» ሲባል በአማኙ ሕይወት ውስጥ ዳግም ልደትን በማስገኘትና በመንፈስ ቅዱስ በማጥመቅ (ሐሥ 2፥4) የእግዚአብሔር መንፈስ የሚፈጽማቸውን ሥራዎች ሁሉ ለማለት ነው::

ተመልሰው ሄዱ፤ እነርሱም ጠባቂዎቹን፣
"ለምን አላመጣችሁትም?" አሏቸው።
[46]ጠባቂዎቹም፣ "እንደዚህ ሰው፣ ከቶ
ማንም ተናግሮ አያውቅም" ሲሉ መለሱ።
[47]ፈሪሳውያንም እንዲህ ሲሉ መለሱ፤
"እናንተም ተታላችኋል ማለት ነው?
[48]ለመሆኑ ከባለሥልጣኖችና ከፈሪሳውያን
በእርሱ ያመነ አለ? [49]ሕጉን የማያውቅ ይህ
ሕዝብ ግን የተረገመ ነው።"
[50]ከዚህ ቀደም ወደ ኢየሱስ ሄዶ የነበረ
ውና ከእነርሱ አንዱ የሆነው ኒቆዲሞስ
እን ዲህ አላቸው፤ [51]"ሕጋችን፣ አስቀድሞ
አንድን ሰው ሳይሰማና ምን እንዳደረገ
ሳይረዳ ይፈርድበታልን?"
[52]እነርሱም፣ "አንተም ደግሞ ከገሊላ
ነህን? ነቢይ[a] ከገሊላ እንደማይነሣ መርምር፤
ትደርስበታለህ" ብለው መለሱለት።
[53]ከዚህ በኋላ ሁሉም ወደየቤታቸው
ሄዱ።

7፥46 ማቴ7፥28
7፥47 ቍ12
7፥48 ዮሐ12፥42
7፥50 ዮሐ3፥1፤ 19፥39
7፥52 ቍ41
8፥1 ማቴ21፥1
8፥2 ቍ20፤ ማቴ26፥55
8፥5 ዘሌ20፥10፤ ዘዳ22፥22፤ ኢዮ31፥11
8፥6 ማቴ12፥10፤ 22፥15፥18

## በምንዝር የተያዘች ሴት

8 ኢየሱስ ግን ወደ ደብረ ዘይት ሄደ፡
፡ [2]በማለዳም በቤተ መቅደስ አደባባይ
እንደ ገና ታየ፤ ሕዝቡም በዙሪያው
ተሰበሰበ፤ ሊያስ ተምራቸውም ተቀመጠ፡
፡ [3]የኦሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን
በምንዝር የተያዘች ሴት አመጡ፤
በሕዝቡም ፊት አቁመዋት፣ [4]ኢየሱስን
እንዲህ አሉት፤ "መምህር ሆይ፣ ይህች ሴት
ስታመነዝር ተያዘች፤ [5]ሙሴም፣ እንደዚች
ያሉ ሴቶች በድንጋይ እንዲወገሩ በሕጉ
አዞናል፤ አንተስ ምን ትላለህ?" [6]ይህን
ጥያቄ ያቀረቡለት፣ እርሱን የሚከሱበት
ምክንያት ለማግኘት ሲፈትኑት ነው።
ኢየሱስ ግን ጎንበስ ብሎ በጣቱ በምድር
ላይ ይጽፍ ጀመር። [7]በጥያቄ ሲወተውቱት
ቀና ብሎ፣ "ከእናንተ ኀጢአት የሌለበት
እርሱ አስቀድሞ ድንጋይ ይወርውርባት"
አላቸው። [8]እንደ ገናም ጎንበስ ብሎ በም
ድር ላይ ጻፈ።
[9]ይህን እንደ ሰሙ፣ ከሽማግሌዎች ጀምሮ
አንድ በአንድ ወጡ፤ ሴትዮዋም እዚያው
ፊቱ እንደ ቆመች ኢየሱስ ብቻውን ቀረ።
[10]ኢየሱስም ቀና ብሎ፣ "አንቺ ሴት፣ ሰዎቹ
የት ሄዱ? የፈረደብሽ የለምን?" አላት።
[11]እርሷም፣ "ጌታ ሆይ፤ አንድም የለም"
አለች።
ኢየሱስም፣ "እኔም አልፈርድብሽም፤
በይ ሂጂ፤ ከእንግዲህ ግን ኀጢአት አትሥሪ"
አላት።*

## የኢየሱስ ምስክርነት እውነት መሆኑ

[12]ኢየሱስ እንደ ገና ለሰዎቹ፣ "እኔ የዓለም
ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝም የሕይወት
ብርሃን ይሆንለታል እንጂ ከቶ በጨለማ
አይመላለስም" አላቸው።
[13]ፈሪሳውያንም፣ "አንተ ስለራስህ
ስለምትመሰክር፣ ምስክርነትህ ተቀባይነት
የለውም" አሉት።
[14]ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤ "እኔ
ስለ ራሴ ብመሰክር ከየት እንደ መጣሁና
ወዴት እንደምሄድ ስለማውቅ ምስክርነቴ
እውነት ነው፤ እናንተ ግን ከየት እንደ መጣሁ

8፥7 ዘዳ17፥7፤ ሕዝ 16፥40፤ ሮሜ2፥1፥22
8፥11 ዮሐ3፥17፤ 5፥14
8፥12 ምሳ4፥18፤ ማቴ5፥14፤ ዮሐ1፥4፤ 6፥35

[a]7፡52 ሁለት የጥንት ቅጆች ነቢዩ ይላሉ
*ብዙ የጥንት ቅጆች ይህ ክፍል (7፥53—8፥11) የላቸውም፤ ወይም በሌላ ስፍራ ወይም በሌሎች ወንጌሎች ያስገቡታል።

8፥7 **ከእናንተ ኀጢአት የሌለበት፤** ይህ አነጋገር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኀጢአት ሲፈጸም እንዳናወግዝ ወይም ክርስቲያን ነን በሚሉት ዘንድ የሚታየውን የሥነ ምግባር ውድቀት በቸልታ እንድንመለከተው የሚያደርግ ሆኖ መታየት የለበትም። እንደዚህ ማድረግ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ስለሚታየው ኀጢአት መጽሐፍ ቅዱስ ያለውን አቋም ማዛባት ነው። (1) ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ለተገለጸው የእግዚአብሔር ጸጋ ምላሽ እንዳይሰጡ ከእርሷ ውጭ ሆነው የመስማት ዕድል ላላገኙትና በውስጧ ሆነው ኀጢአትን ለሚያደርጉ፣ ለክርስቶስም ለማይታዘዙ ያላት አመለካከት ሁለት የተለያዩ ሁኔታዎች ናቸው። (2) ቅዱሳት መጻሕፍት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገኙ ሰዎች የሚፈጸም ልዩ ልዩ ኀጢአት በብርቱ ሁኔታ ሊገሠጽና ሊጋለጥ እንጂ (ራእ 2፥20) ሊታለፍ እንደማይገባው ያስተምራሉ (ሉቃ 17፥3፤ 1ቆሮ 5፥1-13፤ 2ቆሮ 2፥6-8፤ ኤፌ 5፥11፤ 2ጢሞ 4፥2፤ ቲቶ 1፥13፤ 2፥15፤ ራእ 3፥19፤ እንዲሁም በማቴ 13፥30 ላይ ቤተ ክርስቲያን መውሰድ ስላለባት የሥነ ሥርዐት እርምጃ የቀረበውን ማብ ይመ)።

8፥11 **እኔም አልፈርድብሽም፤** ይህ የኢየሱስ ቃል ለሰው ልጆች ያለውን ቤዛዊ ዐላማ የሚያንጸባርቅ ነው (ዮሐ 3፥16)። ሴቲቱን ይቅርታ እንደማይገባት አድርጎ አላወገዛትም፤ ይልቁንም ወደ ንስሓ ይመራት ዘንድ በርኅራኄና በትዕግሥት አነጋገራት። በኀጢአት መኖሯን ብትተው፣ ማለትም ዘማዊ አኗኗሯን አቁማ ወደ ገዛ ባሏ ብትመለስ (ከሉቃ 7፥47 ጋር ያነጻጽሩ) ለእርሷ ድነት ተዘጋጅቶላታል። (1) ይሁን እንጂ ይህን አነጋገር መሠረት በማድረግ ኢየሱስ የዝሙትን ኀጢአትና ይህም ኀጢአት በወዋቂዎችም ሆነ በልጆች ላይ የሚያስከትለውን የልብ ስብራት አቅልሎ ይመለከተዋል ማለት እግዚአብሔርን እንደ ማቃለል ነው። (2) ኢየሱስ ለዚህች ሴት ያሳያት ድነትንና ከኀጢአት ከተሞላው ሕይወቷ የምትወጣበትን መንገድ ነው። በንስሓ ተመልሳ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት (ሮሜ 2፥1-10) እንጂ ብትል የእርሱ ፍርድ ይጠብቃት ነበር።

8፥12 **እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤** ኢየሱስ እውነተኛው ብርሃን ነው (1፥9)፤ ወደ እግዚአብሔርና ወደ ድነት የሚያመራውን ትክክለኛውን መንገድ ብሩህ በማድረግ ጨለማንና ሽንገላን ያስወግዳል። (1) ኢየሱስን የሚከተሉ ሁሉ ከኀጢአት ጨለማ፣ ከዓለምና ከሰይጣን ነጻ ወጥተዋል። በጨለማ ውስጥ የሚመላለሱ ሰዎች ግን እርሱን አይከተሉትም (ከ1ዮሐ 1፥6-7 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) «የሚከተለኝ» የሚለው እየተፈጸመ ያለ ቀጣይ ተግባርን የሚያመለክት የአሁን ጊዜያት ቃል ሲሆን፣ «በመከተሉ የሚቀጥል» የሚል ሐሳብንም ያዘለ ነው። ኢየሱስ የሚያውቀውና የሚቀበለው እምነቱ በደቀ መዝሙርነቱ የሚጸናውን ነው (የሚከተለውን ማብ ይመ)።

*ወይም ወደ*ት እንደምሄድ የም*ታውቁት
ነገር የለም። 15እናንተ እንደ ሰው አስተሳሰብ
ትፈርዳላችሁ፤ እኔ በማንም አልፈርድም፤
16ብፈርድም፣ ከላከኝ ከአብ ጋር እንጂ
ብቻዬን ስላልሆንሁ ፍርዴ ትክክል ነው።
17የሁለት ሰዎች ምስክርነት ተቀባይነት እን
ዳለው በሕጋችሁ ተጽፎአል። 18ስለ ራሴ
የምመሰክር አንዱ እኔ ነኝ፤ ሌላውም ምስ
ክሬ የላከኝ አብ ነው።"
19ከዚያም፣ "አባትህ የት ነው?" አሉት።
ኢየሱስም፣ "አባቴንም እኔንም አታውቁም፤
እኔን ብታውቁኝ ኖሮ፣ አባቴንም ባወቃችሁ
ነበር" ሲል መለሰላቸው። 20ኢየሱስ ይህን
የተናገረው በቤተ መቅደሱ ግቢ፣ በግምጃ
ቤት አጠገብ ሲያስተምር ነበር፤ ይሁን እንጂ
ጊዜው ገና ስላልደረሰ ማንም አልያዘውም።
21ኢየሱስም እንደ ገና፣ "እኔ
እሄዳለሁ፤ እናንተም ትፈልጉኛላችሁ፤
በኀጢአታችሁም ትሞታላችሁ፤ እኔ
ወደምሄድበት ግን ልትመጡ አትችሉም"
አላቸው።
22አይሁድም፣ " 'እኔ ወደምሄድበት
ልትመጡ አትችሉም' ያለው ራሱን ሊገድል
ይሆንን?" አሉ።
23እርሱ ግን እንዲህ አላቸው፤ "እናንተ
ከታች ናችሁ፤ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ
ዓለም ናችሁ፤ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም።
24በኀጢአታችሁ እንደምትሞቱ
ነግሬአችኋለሁ፤ እኔ እርሱ ነኝ[a] ስላችሁ
እኔ እርሱ እንደ ሆንሁ ካላመናችሁ፣
በኀጢአታችሁ ትሞታላችሁና።"
25እነርሱም፣ "ለመሆኑ፣ አንተ ማን ነህ?"
አሉት።
ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እስካሁን የነገርኋችሁ እኔ እርሱ ነኝ፤
26በእና ንተ ላይ ብዙ የምናገረውና ብዙ
የምፈርደው ነገር አለኝ፤ ዳሩ ግን የላከኝ
ታማኝ ነው፤ ከእርሱም የሰማሁትን ለዓለም
እናገራለሁ።"
27እነርሱም ስለ አብ እየነገራቸው እንደ
ነበር አላስተዋሉም። 28ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ
አለ፤ "የሰው ልጅን ከፍ ከፍ ባደረጋችሁ ሁት
ጊዜ፣ ያ ያልሁት እርሱ እኔ እንደ ሆን ሁና
አብ ያስተማረኝን እንደምናገር፣ በራሴም
ፈቃድ ምንም እንደማላደርግ ታውቃላችሁ፤
29የላከኝ እርሱ ከእኔ ጋር ነው፤ ምን ጊዜም
የሚያስደስተውን ስለማደርግ ብቻዬን
አልተወኝም።" 30ይህንም እንደ ተናገረ
ብዙዎች በእርሱ አመኑ።

## የአብርሃም ልጆች

31ኢየሱስም በእርሱ ያመኑትን አይሁድ
እንዲህ አላቸው፤ "በትምህርቴ ብትጸኑ
እናንተ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤
32እው ነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም ነጻ
ያወ ጣችኋል።"
33እነርሱም መልሰው፣ "እኛ የአብርሃም
ልጆች ነን[b]፤ ለማንም ባሪያዎች ሆነን
አናውቅም፤ ታዲያ፣ 'ነጻ ትወጣላችሁ'
እንዴት ትለናለህ?" አሉት።
34ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እውነት እላችኋለሁ፤ ኀጢአት የሚያደርግ
የኀጢአት ባሪያ ነው፤ 35ባሪያ ለዘለቄታ
በቤት ሰቡ ውስጥ አይኖርም፤ ልጅ ግን ምን
ጊዜም በቤት ይኖራል። 36እንግዲህ ወልድ

8፥15 ዮሐ3፥17፤ 7፥24
8፥16 ዮሐ5፥30
8፥17 ማቴ18፥16
8፥18 ዮሐ5፥37
8፥19 ዮሐ16፥3፤ 1ዮሐ2፥23
8፥20 ማቴ26፥18፡ 55፤ ማር12፥41
8፥21 ሕዝ3፥18፤ ዮሐ7፥34፤ 13፥33
8፥23 ዮሐ3፥31፤ 17፥14
8፥24 ዮሐ4፥26፤ 13፥19
8፥26 ዮሐ3፥32፤ 7፥28፤ 15፥15
8፥28 ዮሐ12፥32፤ 14፥24
8፥29 ቊ16፤ ኢሳ50፥5፤ ዮሐ4፥34፤ 5፥30፤ 6፥38፤ 16፥32
8፥30 ዮሐ7፥31
8፥31 ዮሐ15፥7፤ 2ዮሐ1፥9
8፥32 ቊ36፤ ሮሜ8፥2፤ 2ቆሮ 3፥17፤ ገላ5፥1፡13
8፥33 ቊ37፡39፤ ሉቃ3፥8
8፥34 ሮሜ6፥16
8፥35 ገላ4፥30
8፥36 ቊ32

[a]8፥24 ወይም ያ ያልሁት እርሱ እኔ ነኝ፡እንዲሁም ቊ 28 ይመ
[b]8፥33 በግሪኩ ዘር ይላል፤ ቊ 37 ይመ

**8፥31 በትምህርቴ ብትጸኑ፤** *ደቀ መዛሙርቱ ቀደም ብሎ በነበራቸው እምነት ወይም ልምምድ እንዲተማመኑ ኢየሱስ በፍጹም አላደፋፈራቸውም።* እንግዲህ ለድኅነት የተሰጠው ብቸኛ መተማመኛ «በትምህርቴ ብትጸኑ» የሚለው ነው። እውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ለክርስቶስ በመታዘዝ ጸንተው ይኖራሉ (15፥6 እና ማብ ይመ፣ ሉቃ 21፥19 ይመ)።

**8፥32 እውነትም ነጻ ያወጣችኋል፤** ከሰው ልጆች የዕውቀት ዐውድ አንጻር ሲታዩ ብዙ ነገሮች እውነት ናቸው፤ ሆኖም ሰዎችን ከኀጢአት፣ ከጥፋትና ከሰይጣን አገዛዝ ነጻ ሊያወጣ የሚችል አንድ እውነት ብቻ ነው፤ ይህም እውነት በእግዚአብሔር ቃል የሚገኝ የኢየሱስ ክርስቶስ የሆነው እውነት ነው። ስለ እውነት ልናስተውላቸው ከሚገቡ ነገሮች አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው፤ (1) ቅዱሳት መጻሕፍት በተለይም በክርስቶስና በሐዋርያት የተላለፉት መሠረታዊ መገለጦች ከኀጢአት፣ ከዓለምና ከሰይጣን አሠራር ነጻ ስለሚያወጣው እውነት ይመሰክራሉ (የኤፌ 2፥20 እና ማብ ይመ)። (2) የክርስቶስን ወንጌል ፍጹም ወይም የበለጠ ብቁ ለማድረግ ተጨማሪ መገለጥ አያስፈልግም፤ በራሱ ፍጹም ነውና። (3) ወደ ድኅነት የሚያደርስ እውነት የሚገለጠው «በመንፈሱ» (1ቆሮ 2፥10) በኩል ከእግዚአብሔር ብቻ እንጂ ከማንኛውም ሰው ወይም ከሰብአዊ ጥበብ አይመነጭም (1ቆሮ 2፥12-13)።

**8፥34 ኀጢአት የሚያደርግ፤** ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት የእርሱ ተከታዮች በሆኑት ላይ ሊሠለጥን የሚፈልገውን የኀጢአትን ኀይልና ብርታት ራሱ እንደሚሰብረው አዲስ ኪዳን (ቊ 31-32፡36) በግልጽ ያስተምራል። ኀጢአት ማድረግን የዕለት ተዕለት ልምምዳቸው አድርገው የያዙ ግለሰቦች ገና የኀጢአትና የክፉ ሥራ ባሪያዎች በመሆናቸው የሰይጣን ተገዥ ናቸው (ከ1ዮሐ 3፥6-10 ጋር ያነጻጽሩ)። የእውነተኛ አማኞች ከክርስቶስ ጋር በሞቱና በትንሣኤው በእምነት መተባበራቸው ከኀጢአት ባርነት ነጻ መውጣትን ያስገኝላቸዋል (ከሮሜ 6 ጋር ያነጻጽሩ፤ ቀጥሎ ያለውን ማብ ይመ)።

**8፥36 በእርግጥ ነጻ ትሆናላችሁ፤** ድኅነትን ያላገኙ ሰዎች የኀጢአት- የርኩሰትና የሰይጣን ባሪያዎች ናቸው (ቊ 34፤ ሮሜ 6፥17-20)። ኀጢአተኛ ተፈጥሮአቸው በሚያሳድርባቸው ምኞትና በሰይጣን መንገድ እየተመሩ ይኖራሉ (ኤፌ 2፥1-3)። (1) ድኅነትን ከክርስቶስ የተቀበሉና በውስጣቸው ከሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ጋር ያገኙ እውነተኛ አማኞች ከኀጢአትና ከርኩሰት ኀይል ነጻ ወጥተዋል (ሮሜ 6፥17-22፤ 8፥1-17)። ኀጢአት ለመሥራት በሚፈተኑበት ጊዜ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ እርምጃ ለመውሰድ ኀይል ይኖራቸዋል። ለእግዚአብሔርና ለጽድቅ ባሪያዎች ለመሆን የሚያግዳቸው ነገር አይኖርም (ሮሜ 6፥18፡22)።

(2) ከኀጢአት ባርነት ነጻ መውጣት፣ አማኞች ነን

ነጻ ካወጣችሁ፣ በእውነት ነጻ ትሆናላችሁ።
37የአብርሃም ልጆች መሆናችሁን
ዐውቃለሁ፤ ነገር ግን ቃሌን ስለማትቀበሉ
ልትገድሉኝ ቈርጣችሁ ተነሥታችኋል።
38እኔ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን እናገራለሁ፤
እናንተም ከአባታችሁ የሰማችሁትን
ታደርጋላችሁ።"[ሀ]
39እነርሱም፣ "አባታችንስ አብርሃም
ነው" ብለው መለሱለት።
ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "የአብርሃም
ልጆችስ ብትሆኑ[ለ]፣ አብርሃም የሠራውን
ትሠሩ ነበር። 40ከእግዚአብሔር ሰምቼ እውነ
ቱን የነገርኋችሁን እኔን ለመግደል ቈርጣ
ችሁ ተነሥታችኋል፤ አብርሃም ግን እንዲህ
አላደረገም። 41እናንተ የምታደርጉት አባታ
ችሁ የሚያደርገውን ነው።"
እነርሱም፣ "እኛስ በዝሙት የተወለድን
አይደለንም፤ አባታችንም አንዱ እግዚአብሔር
ብቻ ነው" ሲሉ መለሱለት።

## የዲያብሎስ ልጆች

42ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ "እግዚአብሔር
አባታችሁ ቢሆን ኖሮ፣ እኔ ከእግዚአብሔር
ወጥቼ መጥቻለሁና፣ በወደዳችሁኝ ነበር፤
እርሱ ላከኝ እንጂ በገዛ ራሴ አልመጣሁም።
43የምናገረውን ለምን አታስተውሉም?
ምክንያቱም ቃሌን መስማት ስለማ ትችሉ
ነው። 44እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ
ናችሁ፤ የአባታችሁንም ፍላጎት ለመፈ
ጸም ትሻላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ
ገዳይ ነበር፤ በእርሱ ዘንድ እውነት ስለሌለ
በእውነት አልጸናም፤ እርሱ ሐሰተኛ፣ የሐ
ሰትም አባት በመሆኑ ሐሰትን ሲናገር፣
የሚናገረው ከራሱ አፍልቆ ነው፤ 45እኔ
ግን እውነት ስለምናገር አታምኑኝም።
46ከእናንተ ስለ ኀጢአት በማስረጃ ሊከሰኝ
የሚችል አለን? እውነት የምናገር ከሆነ፣
ለምን አታ ምኑኝም? 47ከእግዚአብሔር የሆነ
እግዚአብሔር የሚለውን ይሰማል፤ እናንተ ግን
ከእግዚአብሔር ስላልሆናችሁ አትሰሙም።"

## ኢየሱስ ስለ ራሱ የተናገረው

48አይሁድም መልሰው፣ "አንተ ሳምራዊ
ነህ፤ ደግሞም ጋኔን አድሮብሃል ማለታችን
ትክክል አይደለምን?" አሉት።
49ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እኔስ አባቴን አከብረዋለሁ እንጂ ጋኔን
አላደረብኝም፤ እናንተ ግን ታዋርዱኛላችሁ።
50እኔ የራሴን ክብር አልፈልግም፤ የሚፈልግ
ግን አለ፤ ፈራጁም እርሱ ነው። 51እውነት
እላችኋለሁ፤ ማንም ቃሌን ቢጠብቅ፣ ሞትን
ፈጽሞ አያይም።"
52አይሁድም እንዲህ አሉት፤ "ጋኔን
እንዳለብህ አሁን ዐወቅን፤ አብርሃም ሞተ፤
ነቢያትም እንዲሁ፤ አንተ ግን ማንም ቃል
ህን ቢጠብቅ ሞትን ፈጽሞ እንደማይቀምስ
ትናገራለህ። 53አንተ ከአባታችን ከአብርሃም
ትበልጣለህን? እርሱ ሞተ፤ ነቢያቱም
እንዲሁ፤ ለመሆኑ አንተ ማን ነኝ ልትል
ነው?"
54ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤
"እኔ ራሴን ባከብር፣ ክብሬ ከንቱ ነው፤
የሚያከብረኝ ግን እናንተ አምላካችን
የምትሉት አባቴ ነው። 55እናንተ
ባታውቁትም እኔ ዐውቀዋለሁ፤ አላውቀውም
ብል፣ እኔም እንደ እናንተው ሐሰተኛ
እሆናለሁ። እኔ ግን ዐው ቀዋለሁ፤ ቃሉንም
እጠብቃለሁ። 56አባታ ችሁ አብርሃም ቀኔን

8፥37 ቍ39፡40
8፥38 ቍ41፡44፤ ዮሐ5፥19፡30፤ 14፥10፡24
8፥39 ቍ37፤ ሉቃ3፥8
8፥40 ቍ26፤ ማቴ12፥14
8፥41 ቍ38፡44፤ ኢሳ63፥16፤ 64፥8
8፥42 ዮሐ3፥17፤ 7፥28፤ 13፥3፤ 1ዮሐ5፥1
8፥44 ቍ38፡41፤ ዘፍ3፥4፤ 4፥9፤ 2ዜና 18፥21፤ መዝ5፥6፤ 12፥2፤ 1ዮሐ3፥8
8፥45 ዮሐ18፥37
8፥47 ዮሐ18፥37፤ 1ዮሐ4፥6
8፥48 ቍ52፤ ማቴ10፥5፤ ማር3፥22
8፥50 ቍ54፤ ዮሐ5፥41
8፥51 ዮሐ11፥26
8፥52 ቍ48፤ ማር3፥22
8፥53 ቍ39፤ ዮሐ4፥12
8፥54 ቍ50፤ ዮሐ16፥14፤ 17፥1፡5
8፥55 ቍ19፤ ዮሐ7፥28፡29፤ 15፥10
8፥56 ቍ37፡39፤ ዘፍ18፥18፤ ማቴ13፥17

*[ሀ] 8፥38 ወይም ስለዚህ ከአባታችሁ የሰማችሁትን አድርጉ*
*[ለ] 8፥39 አንዳንድ የጥንት ቅጆች የአብርሃም ልጆች ከሆናችሁ ይላሉ*

የሚሉ ሁሉ ዳግም ልደትና የሚቀድስ ጸጋ የሚሰጠው የዘላለም ሕይወት በውስጣቸው መኖሩን የሚፈትኑበት አንድ አስተማማኝ መመዘኛ ነው:: በክርስትና ሕይወት ውስጥ የርኩሰት ባሪያ የሆነ ሰው አንድም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መንፈሳዊ ዳግም ልደትን በፍጹም አላገኘም ወይም መንፈሳዊ ዳግም ልደትን ያገኘ ቢሆን እንኳ ለኀጢአት የተሸነፈና የኀጢአት ባርነትን ወደ ሚያስከትል መንፈሳዊ ሞት ሁኔታ ውስጥ ዳግመኛ የገባ ነው (ሮሜ 6፥16፡21፡23፤ 8፥12-13፤ 1ዮሐ 3፥15 እና ማብ ይመ)::

(3) ይሁን እንጂ እንዲህ ሲባል አማኞች ከኀጢአት ጋር ካለባቸው መንፈሳዊ ጦርነት ነጻ ናቸው ማለት አይደለም:: በሕይወታችን ዘመን ሁሉ ጥቃት ከሚሰነዝሩብን ከዓለም- ከኀጢአተኛ ተፈጥሮአችንና ከሰይጣን ጋር ያለማቋረጥ እንዋጋለን (ገላ 5፥17 እና ማብ፤ ኤፌ 6፥11፡12 እና ማብ ይመ):: ከፈተናና ከኀጢአት የመሳብ ኀይል ሙሉ በሙሉ ነጻ መሆን የሚቻለው በሥጋዊ ሞት ስንለይ ወይም በታማኝነት የምንጠባበቀው ክርስቶስ ዳግም በሚመለስበት ጊዜ ነው:: ክርስቶስ አሁን ለእኛ የሚሰጠን የመቀደስ ኀይል ያለውን ሕይወቱን ሲሆን በመንፈስ ቅዱስ የሚመሩ በዚህ ኀይል አማካይነት ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ከሚያመጣባቸው ፍላጎት ነጻ ይወጣሉ (ገላ 5፥16-24)፤ ደግሞም በእርሱ ፊት በቅድስናና ነቀፋ በሌለበት ሕይወት በፍቅር እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል (ኤፌ 1፥4)::

**8፥42 እግዚአብሔር አባታችሁ ቢሆን ኖሮ፤** እዚህ ላይ ኢየሱስ ስለ አንድ መሠረታዊ የድነት መርሕ ይናገራል:: በዚህም መሠረት አንድ አማኝ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ (ማለትም ከእግዚአብሔር ዳግም የተወለደ) መሆኑ የሚታወቀው ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባለው ፍቅር ነው:: ስለዚህ አንድ ሰው እውነተኛ እምነትና የመታዘዝ ዝንባሌ ሊያሳይ ይገባዋል:: ይህ ካልሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎ መናገር አግባብ የሌለው ይሆናል (ከቍ 31፤ ከ10፥2-5፡14፡27-28፤ ከ14፥15፡21 ጋር ያነጻጽሩ)::

**8፥44 እርሱ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት በመሆኑ፤** መዋሸት የሰይጣን ባሕርይ እንደሆነ በግልጽ ተመልክቷል፤ እርሱ የሐሰት ሁሉ ምንጭ ነው (ዘፍ 3፥1-6፤ ሐሥ 5፥3፤ 2ተሰ 2፥9-11፤ ራእ 12፥9):: መዋሸት እውነት ከሆነው ከእግዚአብሔር ሐሳብ (ራእ 19፥11) ጋር ፍጹም የሚቃረን ኀጢአት ነው:: ለውሸት ኀጢአት ግድየለሽነትን ማሳየት ግልጽ የሆነ የዓለማዊነት ምልክት ነው፤ ይህም አንድ ሰው ከመንፈስ ቅዱስ እንዳልተወለደና (3፥6) መንፈሳዊ አባቱ በሆነው በሰይጣን ተጽዕኖ ሥር እንደሆነ የሚያመለክት ነው (4፥24 እና ማብ፤ ራእ 22፥15 እና ማብ ይመ)::

ለማየት ተስፋ በማድረግ ተደሰተ፤ አየም፤ ሐሤትም አደረገ።"

57 አይሁድም፣ "ገና አምሳ ዓመት ያልሞላህ፣ አንተ አብርሃምን አይተሃል!" አሉት።

58 ኢየሱስም፣ "እውነት እላችኋለሁ፤ አብርሃም ከመወለዱ በፊት እኔ፣ እኔ ነኝ" አላቸው። 59 በዚህን ጊዜ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ ኢየሱስ ግን ተሰወረባቸው፤ ከቤተ መቅደስም ወጥቶ ሄደ።

## ኢየሱስ ዐይነ ስውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ፈወሰ

ሐሥ 3:1-10

9 በመንገድ ሲያልፍም ከተወለደ ጀምሮ ዐይነ ስውር የሆነ ሰው አየ። 2 ደቀ መዛሙርቱም፣ "ረቢ፤ ይህ ሰው ዐይነ ስውር ሆኖ እንዲወለድ ኀጢአት የሠራ ማን ነው? እርሱ ራሱ ወይስ ወላጆቹ?" ብለው ጠየቁት።

3 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "እርሱ ወይም ወላጆቹ ኀጢአት አልሠሩም፤ ይህ የሆነው ግን የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ ሕይወት እንዲገለጥ ነው። 4 ቀን ሳለ፣ የላከኝን ሥራ መሥራት አለብን፤ ማንም ሊሠራ የማይችልበት ሌሊት ይመጣል፤ 5 በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ።"

6 ይህን ካለ በኋላ፣ በምድር ላይ እንትፍ ብሎ በምራቁ ጭቃ አበጀ፤ የሰውየውንም ዐይን ቀባና፣ 7 "ሂድ፤ በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ" አለው፤ ሰሊሆም ማለት 'የተላከ' ማለት ነው። ሰውየውም ሄዶ ታጠበ፤ እያየም ተመልሶ መጣ።

8 ጎረቤቶቹና ከዚህ ቀደም ብሎ ሲለምን ያዩት ሰዎች፣ "ይህ ሰው ተቀምጦ ሲለምን የነበረው አይደለምን?" አሉ። 9 አንዳንዶቹም፣ "በርግጥ እርሱ ነው" አሉ።

ሌሎችም፣ "ይመስለዋል እንጂ እርሱ አይደለም" አሉ።

እርሱ ግን፣ "እኔው ነኝ" አለ።

10 እነርሱም፣ "ታዲያ ዐይኖችህ እንዴት ተከፈቱ?" ሲሉ ጠየቁት።

11 እርሱም፣ "ኢየሱስ የሚሉት ሰው ጭቃ አድርጎ ዐይኔን ቀባኝ፤ ወደ ሰሊሆም ሂድ እንድታጠብም ነገረኝ፤ ሄጄ ታጠብሁ፤ ማየትም ቻልሁ" ሲል መለሰ።

12 እነርሱም፣ "ታዲያ፣ ያ ሰው የት አለ?" አሉት።

እርሱም፣ "እኔ አላውቅም" አለ።

## ፈሪሳውያን ስውየው እንዴት እንደ ተፈወሰ ማጣራት ቀጠሉ

13 እነርሱም ዐይነ ስውር የነበረውን ሰው ወደ ፈሪሳውያን ወሰዱት። 14 ኢየሱስ ጭቃ የሠራበት፣ የሰውየውንም ዐይን የከፈተበት ቀን ሰንበት ነበር። 15 ስለዚህ ፈሪሳውያንም እንዴት ማየት እንደቻለ ጠየቁት። ሰውየውም፣ "እርሱ ዐይኔን ጭቃ ቀባኝ፤ እኔም ታጠብሁ፤ ይኸው አያለሁ" አላቸው።

16 ከፈሪሳውያንም አንዳንዶቹ፣ "ይህ ሰው ሰንበትን ስለማያከብር፣ ከእግዚአብሔር አይደለም" አሉ።

ሌሎች ግን፣ "ኀጢአተኛ፣ እንዲህ ያሉትን ታምራዊ ምልክቶች እንዴት ሊያደርግ ይችላል?" አሉ። በመካከላቸውም አለመስ ማማት ተፈጠረ።

17 ስለዚህ፣ ዐይነ ስውር ወደ ነበረው ሰው ተመልሰው፣ "ዐይንህን ስለ ከፈተው ሰው፣ እንግዲህ አንተ ምን ትላለህ?" አሉት።

ሰውየውም፣ "እርሱ ነቢይ ነው" አለ።

18 አይሁድ ወደ ወላጆቹ ልከው እስኪያስ ጠሯቸው ድረስ፣ ሰውየው ዐይነ ስውር እንደ ነበረና እንዳየ አላመኑም ነበር። 19 እነርሱም፣ "ዐይነ ስውር ሆኖ ተወለደ አል የምትሉት ልጃችሁ ይህ ነውን? ታዲያ አሁን እንዴት ሊያይ ቻለ?" አሏቸው።

20 ወላጆቹም እንዲህ ሲሉ መለሱ፤ "ልጃችን መሆኑንና ዐይነ ስውር ሆኖ መወለዱን እናውቃለን፤ 21 አሁን ግን እንዴት ማየት እንደቻለና ዐይኖቹን ማን እንደ ከፈተለት እኛ አናውቅም። ሙሉ ሰው ስለ ሆነ፣ ስለ ራሱ መናገር ይችላልና እርሱን ጠይቁት።" 22 ኢየሱስን፣ ክርስቶስ[a] ነው ብሎ የመሰከረ ሁሉ ከምኵራብ እንዲባረር አይሁድ አስቀድመው ወስነው ስለ ነበር፣ ወላጆቹ ይህን ያሉት አይሁድን ፈርተው ነው። 23 ስለዚህ ወላጆቹ፣ "ሙሉ ሰው ስለ ሆነ እርሱን ጠይቁት" አሉ።

24 ዐይነ ስውር የነበረውንም ሰው ዳግመኛ ጠርተው፣ "አንተ ሰው፤ እግዚአብሔርን አክብር[b]፤ ይህ ሰው ኀጢአተኛ መሆኑን እኛ እናውቃለን" አሉት።

25 እርሱም፣ "ኀጢአተኛ መሆኑን እኔ አላውቅም፤ ነገር ግን ዐይነ ስውር እንደ ነበርሁ፤ አሁን ግን እንደማይ ይህን አንድ ነገር ዐውቃለሁ" አለ።

26 እነርሱም፣ "ምን አደረገልህ? እንዴትስ ዐይንህን ከፈተ?" ብለው ጠየቁት።

27 እርሱም፣ "አስቀድሜ ነገርኋችሁ፤ አላዳመጣችሁኝም፤ ለምን እንደ ገና መስማት ፈለጋችሁ? እናንተም ደግሞ ደቀ

8:58 ዘፀ3:14፤ 6:3፤ ዮሐ1:2
8:59 ዘፀ17:4፤ ዘሌ24:16፤ 1ሳሙ 30:6፤ ዮሐ10:31፤ 11:8፤ 12:36
9:2 ቁ.34፤ ዘፀ20:5፤ ኢዮ21:19፤ ሕዝ18:20፤ ማቴ23:7፤ ሉቃ13:2፤ ሐሥ28:4
9:3 ዮሐ11:4
9:4 ዮሐ11:9፤ 12:35
9:5 ዮሐ1:4
9:6 ማር7:33፤ 8:23
9:7 ቁ.11፤ 2ነገ5:10፤ ኢሳ35:5፤ ሉቃ13:4፤ ዮሐ11:37
9:8 ሐሥ3:2:10
9:11 ቁ.7
9:14 ማቴ12:1-14፤ ዮሐ5:9
9:15 ቁ.10
9:16 ማቴ12:2፤ ዮሐ2:11፤ 6:52
9:17 ማቴ21:11
9:18 ዮሐ1:19
9:22 ቁ.34፤ ሉቃ6:22፤ ዮሐ7:13 12:42፤ 16:2
9:23 ቁ.21
9:24 ቁ.16፤ ኢያ7:19
9:27 ቁ.15

[a] 9:22 ወይም መሲሑ

[b] 9:24 እውነት ለመናገር የሚደረግ መሐላ ነው ኢያ (7:19 ይመ) አንዳንድ የጥንት ቅጆች ‹የእግዚአብሔር ልጅ› ይላሉ።

**9:3 የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ ... እንዲገለጥ፣** ማንኛውም ብርቱ ደዌ የአንድ ኀጢአት ውጤት ነው የሚለውን የደቀ መዛሙርቱን የተሳሳተ እምነት ኢየሱስ ዐረመ። አንዳንድ ጊዜ ብርቱ ኀጢአት ሕመምን ማስከተል ቢችልም (5:14) ይህ ሁልጊዜ አይሆንም። ሥቃይ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ይፈጽም ዘንድ፣ ማለትም የእግዚአብሔርን ምሕረት፣ ፍቅርና ኀይል ይገልጥ ዘንድ በአንድ ሰው ላይ እንዲደርስ እግዚአብሔር አልፎ አልፎ ይፈቅዳል። በዓለም ውስጥ ብዙውን ጊዜ ንጹሐን ሲሠቃዩ ክፉ ሰዎች ግን ይህ አይደርስባቸውም (ከመዝ 75:1-14 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 744 ላይ፣ *«የጻድቃን መከራ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

መዛሙርቱ ልትሆኑ ትሻላችሁ?" አለ።
28ከዚህ በኋላ ብእርሱ ላይ የስድብ ናዳ
በማውረድ እንዲህ አሉት፤ "የዚህ ሰው ደቀ
መዝሙር አንተ ነህ፤ እኛስ የሙሴ ደቀ
መዛሙርት ነን! 29እግዚአብሔር ሙሴን እንደ
ተናገረው እናውቃለን፤ ይህ ሰው ግን ከየት
እንደ መጣ እንኳ አናውቅም።"
30ሰውየውም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እናንተ ከየት እንደ መጣ አለማወቃችሁ
የሚያስደንቅ ነው፤ ይሁን እንጂ እርሱ
ዐይኖቼን ከፈተልኝ። 31እግዚአብሔር
የሚሰማው፣ የሚፈራውንና ፈቃዱን
የሚያደርገውን እንጂ፣ ኀጢአተኞችን
እንደማይሰማ እናውቃለን፤ 32ዐይነ ስውር
ሆኖ የተወለደን ሰው ዐይን የከፈተ አለ
ሲባል፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ማንም
ሰምቶ አያውቅም። 33ይህ ሰው ከእግዚአብሔር
ባይሆን ኖሮ ይህን ማድረግ ባልቻለ ነበር።"
34እነርሱም፣ "ሁለንተናህ በኀጢአት
ተነክሮ የተወለድህ፣ አንተ እኛን ለማስተማር
እንዴት ትደፍራለህ?" ሲሉ መለሱለት፤
አባረሩትም።

## መንፈሳዊ ዕውርነት

35ኢየሱስም ሰውየውን እንዳባረሩት
ሰማ፤ ባገኘውም ጊዜ፣ "በሰው ልጅ*
ታምናለህን?" አለው።
36ሰውየውም፣ "ጌታዬ፤ አምንበት ዘንድ
እርሱ ማን ነው?" ሲል ጠየቀው።
37ኢየሱስም፣ "አይተኸዋል፤ አሁንም
ከአንተ ጋር የሚነጋገረው እርሱ ነው"
አለው።
38ሰውየውም፣ "ጌታ ሆይ፤ አምናለሁ"
አለ፤ ሰገደለትም።
39ኢየሱስም፣ "ዕውሮች እንዲያዩ፣
የሚያዩም እንዲታወሩ፣ ለፍርድ ወደዚህ
ዓለም መጥቻለሁ" አለ።
40ከእርሱ ጋር ከነበሩት ፈሪሳውያን
እንዳንዶቹ ይህን ሰምተው፣ "ምን ማለትህ
ነው? ታዲያ እኛም ዕውሮች መሆናችን
ነው?" አሉት።
41ኢየሱስም፣ "ዕውሮችስ ብትሆኑ
ኀጢአት ባልሆነባችሁ ነበር፤ አሁን ግን
እናያለን ስለምትሉ፣ ኀጢአታችሁ እንዳለ
ይኖራል" አላቸው።

## እረኛና መንጋው

10 "እውነት እላችኋለሁ፤ ወደ በጎች
ጒረኖ በበሩ ሳይሆን፣ በሌላ በኩል
ዘሎ የሚገባ ሌባና ነጣቂ ነው፤ 2በበሩ
የሚገባ ግን እርሱ የበጎቹ እረኛ ነው፤ 3በር
ጠባቂው በሩን ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድም
ፁን ይሰማሉ። የራሱንም በጎች በየስማቸው
እየጠራ ያወጣቸዋል። 4የራሱ የሆኑትንም
ሁሉ ካወጣ በኋላ ፊት ፊታቸው ይሄዳል፤
በጎቹም ድምፁን ስለሚያውቁ ይከተሉታል።
5እንግዳ የሆነውን ግን ድምፁን ስለማያውቁ
ከእርሱ ይሸሻሉ እንጂ ፈጽሞ አይከተሉትም።
" 6ኢየሱስ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤ እነርሱ
ግን ምን እንደ ነገራቸው አላስተዋሉም።
7ስለዚህ ኢየሱስ ዳግም እንዲህ አላቸው፤
"እውነት እላችኋለሁ፤ የበጎች በር እኔ ነኝ።
8ከእኔ በፊት የመጡት ሁሉ ሌቦችና ቀማኞች
ነበሩ፤ በጎቹ ግን አልሰሟቸውም። 9በሩ እኔ
ነኝ፤ በእኔ በኩል የሚገባ ሁሉ ይድናል[ሀ]፤
ይገባል፤ ይወጣልም፤ መሰማሪያም ያገኛል።
10ሌባው ሊሰርቅ፣ ሊገድልና ሊያጠፋ ብቻ
ይመጣል፤ እኔ ግን ሕይወት እንዲኖራቸውና
እንዲትረፈረፍላቸው መጥቻለሁ።"
11"መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ መልካም

9፥28 ዮሐ5፥45
9፥29 ዮሐ8፥14
9፥31 ዘፍ18፥23-32፤ መዝ34፥15:16፤ 66፥18፤ 145፥19:20፤ ምሳ15፥29፤ ኢሳ1፥15፤ 59፥1:2፤ ዮሐ15፥7፤ 1ዮሐ5፥14-15፤ ያዕ5፥16-18
9፥33 ቁ16፤ ዮሐ3፥2
9፥34 ቁ2:22:35፤ ኢሳ66፥5
9፥35 ማቴ8፥20፤ ዮሐ3፥15
9፥36 ሮሜ10፥14
9፥37 ዮሐ4፥26
9፥38 ማቴ28፥9
9፥39 ማቴ13፥13፤ ሉቃ4፥18፤ ዮሐ3፥19፤ 5፥22፤ 12፥47
9፥40 ሮሜ2፥19
9፥41 ዮሐ15፥22:24
10፥1 ቁ8:10
10፥2 ቁ11:14፤ ማር6፥34
10፥3 ቁ4:5:14:16:27
10፥4 ቁ3
10፥6 ማር9፥32፤ ዮሐ16፥25
10፥7 ቁ9፤ ዮሐ6፥35
10፥8 ቁ1፤ ኤር23፥1:2፤ ሕዝ34፥2
10፥10 መዝ65፥11፤ ዮሐ1፥4፤ 3፥15:16፤ 5፥40፤ 20፥31፤ ሮሜ5፥17
10፥11 ቁ14:15:17:18፤ መዝ23፥1፤ ኢሳ40፥11፤ ሕዝ34፥11-16:23፤ ማቴ2፥6፤ ሉቃ12፥32 ዮሐ6፥35፤ 15፥13፤ ዕብ13፥20፤ 1ጴጥ2፥25፤ 5፥4፤ 1ዮሐ3፥16፤ ራእ7፥17

[ሀ] 10:9 ወይም በደኅና ይጠበቃል

**9፥34 አባረሩትም፤** ከተወለደ ጀምሮ ዕውር ለነበረው ሰው ከሆኑለት እጅግ ጥሩ ነገሮች አንዱ ከቀድሞ ወግ አጥባቂ ሃይማኖቱ እንዲገለል መገደዱ ነው። በምኩራብ እንዲቆይ ቢፈቀድለት ኖሮ ወደ ባሕላዊው የአይሁድ አኗኗር የመመለስና ከክርስቶስና ከወንጌል የመለየት አደጋ ሊገጥመው ይችል ነበር። ዛሬም ቢሆን ለዘብተኛ በሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ወይም የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በማያከብሩ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች የሚገኙ ሰዎች ይህን መሳይ ሁኔታ ሊገጥማቸው ይችላል። በዚያ ዐይነቱ ቤተ ክርስቲያን ወይም ሥርዐት የሚቆዩ ከሆነ ለእውነተኛው ክርስትና ያላቸውን ጥማት አጥተው ወደ ቀድሞ ሃይማኖታቸው ተመልሰው ሥርዐቱን ወደ መፈጸም ሊመጡ ይችላሉ። ክርስቶስ በሙላት ወደ እኛ ይቀርብ ዘንድ የእግዚአብሔር ካልሆነው ነገር መለየት እጅግ መልካም ነው (ቊ 35-38)።

**10፥1-30፤** ስለ መልካሙ እረኛ የቀረበው ምሳሌ፥ ኢየሱስን ከሐሰተኛ እረኞች ጋር በማነጻጸር እርሱ መልካም እረኛና የሕዝቡ መሪ እንደሆነ ይገልጻል። (ይህን ምዕራፍ በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ሐሰተኛ እረኞችን የሚያወግዙ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ሊነበቡ ይገባል፤ ኢሳ 56፥9-12፤ ኤር 23፥1-4፤ ሕዝ 34፤ ዘካ 11) ኢየሱስ ከቊ 7-18 ላይ ከቊ 1-5 የተነገረው ስለራሱ መሆኑን ይገልጻል።

**10፥9 በሩ እኔ ነኝ፤** በኢየሱስ በኩል የሚገቡ "ይድናሉ"፣ ማለትም የተትረፈረፈ ሕይወት ይኖራቸዋል (ቊ 10)፤ ከኀጢአት፣ ከበደለኛነት ስሜትና ከፍርድ ነጻ ለመውጣት የሚያስፈልገው ኀይል ሁሉ ይኖራቸዋል። ወደ ድነት የሚያስገባው በር ኢየሱስ ብቻ ነው፤ ሌላ ማንም የለም (ሐዋ 4፥12)።

**10፥11 መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤** በተስፋ የተጠበቀው መልካም እረኛ ክርስቶስ እርሱ ራሱ እንደሆነ ያውጃል (የመዝ 23፥1 እና ማብ፤ ኢሳ 40፥11 እና ሕዝ 34፥23 እና ማብ፤ 37፥24 ይመ)። (1) ይህ ዘይቤአዊ አገላለጽ ኢየሱስ ለሕዝቡ ያለውን ርኅራኄና ትጋት የተሞላውን ጥበቃ ያመለክታል። በሌላ አባባል፣ "መልካም እረኛ ለበጎቹ የሚጠነቀቅ፣ ንቁና አፍቃሪ እንደ ሆነ ሁሉ እኔም ለሚያምኑብኝ እንደዚያው ነኝ" ማለቱ ነው።

(2) የክርስቶስ መልካም እረኝነት መለያ ምልክት ስለበጎቹ ለመሞት መፍቀዱ ነው። ይህ አገላለጽ ክርስቶስ የተለየ እረኛ እንደ ሆነ በአጽንዖት ያመለክታል፤ በመስቀል ላይ መሞቱ በጎቹን ከሞት ያድናቸዋል (ኢሳ 53፥12፤ ማቴ 20፥28፤ ማር 10፥45)። በዚህ ስፍራ ላይ ክርስቶስ፣

እረኛ ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ
ይሰጣል፤ [12]ተቀጣሪው እረኛ ግን በጎቹ
የእርሱ ስላልሆኑ፣ ተኵላ ሲመጣ ጥሎአቸው
ይሸሻል፤ ተኵላውም በጎቹን ይነጥቃል፤
ይበትናቸዋልም። [13]የሚሸሸውም ተቀጣሪ
ስለ ሆነና ለበጎቹ ደንታ ስለሌለው ነው።
[14]"መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ በጎቼን
ዐውቃለሁ፤ እነርሱም ያውቁኛል፤ [15]ይህም
አብ እኔን እንደሚያውቀኝ እኔም አብን
እንደማውቀው ነው። ሕይወቴንም ስለ በጎቹ
አሳልፌ እሰጣ ለሁ። [16]ከዚህ ጕረኖ ያልሆኑ
ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱንም ማምጣት
አለብኝ። እነርሱም ድምፄን ይሰማሉ፤
አንድ መንጋም ይሆናሉ፤ እረኛውም አንድ።
[17]መልሼ ለማንሣት ሕይወቴን አሳልፌ
ስለምሰጥ አባቴ ይወደኛል። [18]ሕይወቴን
በራሴ ፈቃድ አሳ ልፌ እሰጣለሁ እንጂ ከእኔ
ማንም አይወስዳትም፤ አሳልፌ ለመስጠትም
ሆነ ለማንሣት ሥልጣን አለኝ፤ ይህን
ትእዛዝ የተቀበልሁትም ከአባቴ ነው።"
[19]ከዚህም ቃል የተነሣ በአይሁድ
መካከል እንደ ገና መለያየት ተፈጠረ።
[20]ብዙዎቹም፣ "ጋኔን ያደረበት እብድ ነው፤
ለምን ትሰሙታ§ችሁ?" አሉ።
[21]ሌሎች ግን፣ "ይህ ጋኔን ያደረበት ሰው
ንግግር አይደለም፤ ጋኔን የዐይነ ስውርን
ዐይን መክፈት ይችላልን?" አሉ።

## የአይሁድ አለማመን

[22]በኢየሩሳሌምም የቤተ መቅደስ
መታደስ በዓል[a] ሆነ፤ ጊዜውም ክረምት
ነበረ፤ [23]ኢየ ሱስም በቤተ መቅደስ ግቢ፣
በሰሎሞን መመ ላለሻ ይልፍ ነበር፤
[24]አይሁድም ከበውት፣ "እስከ መቼ ልባችንን
አንጠልጥለህ ታቈየናለህ? አንተ ክርስቶስ[b]
ከሆንህ በግልጽ ንገ ረን" አሉት።
[25]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"እኔ ነግሬአችሁ ነበር፤ እናንተ ግን
አታምኑም፤ በአባቴ ስም የማደርጋቸው
ታምራትም ስለ እኔ ይናገራሉ፤ [26]እናንተ
ግን በጎቼ ስላልሆና ችሁ አታምኑም፤ [27]በጎቼ
ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔ ዐውቃቸዋለሁ፤
እነርሱም ይከተሉኛል፤ [28]እኔ የዘላለም
ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ከቶ አይጠፉም፤
ከእጄም ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም የለም።
[29]እነርሱን የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል[c]፤
ከአባቴም እጅ ማንም ሊነጥቃቸው
አይችልም። [30]እኔና አብ አንድ ነን።"
[31]አይሁድ ሊወግሩት እንደ ገና ድንጋይ
አነሡ፤ [32]ኢየሱስ ግን፣ "ከአብ የሆኑ ብዙ
ታላላቅ ታምራትን አሳየኋችሁ፤ ታዲያ
ከእነ ዚህ ስለ የትኛው ትወግሩኛላችሁ?"
አላቸው።
[33]አይሁድም፣ "የምንወግርህ፣ ተራ ሰው
ሆነህሳለህ፣ ራስህንአምላክበማድረግ፣ የስድብ
ቃል ስለተናገርህ ነው እንጂ ከእነዚህ ስለ
የትኛውም አይደለም" ብለው መለሱለት።
[34]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤

10፥12 ዘካ11፥16፡17
10፥14 ቍ11፡27፡ ዘፀ33፥12
10፥15 ቍ11፡17፡18፤ ማቴ11፥27
10፥16 ኢሳ56፥8፤ ሕዝ34፥23፤ 37፥24፤ ዮሐ11፥52፤ 17፥20፡21፤ ሐሥ10፥34፡35፤ ኤፌ2፥11-19
10፥17 ቍ11፡15፡18
10፥18 ማቴ26፥53፤ ዮሐ15፥10፤ ፊል2፥8፤ ዕብ5፥8
10፥19 ዮሐ6፥52
10፥20 ማር3፥21፡22፤ 2ነገ9፥11፤ ኤር29፥26
10፥21 ዘፀ4፥11፤ ማቴ4፥24፤ ዮሐ9፥32፡33
10፥23 ሐሥ3፥11፤ 5፥12
10፥24 ዮሐ1፥19፤ 16፥25፡29፤ ሉቃ22፥67
10፥25 ዮሐ4፥26፤ 5፥36፤ 8፥58፤ 14፥11
10፥26 ዮሐ8፥47
10፥27 ቍ4፡14
10፥28 ኢሳ66፥22፤ ማቴ25፥46፤ ዮሐ6፥39
10፥29 ዮሐ14፥28፤ 17፥2፡6፡24
10፥30 ዘዳ6፥4፤ ዮሐ17፥21-23
10፥31 ዮሐ8፥59 ዮሐ5፥18
10፥34 መዝ82፥6፤ ዮሐ8፥17፤ 12፥34፤ 15፥25፤ ሮሜ3፥19፤ 1ቆሮ14፥21

[a] 10፥22 ኀኑካ ማለት ነው
[b] 10፥24 ወይም መሲሑ
[c] 10፥29 ብዙ የጥንት ቅጆች አባቴ የሰጠኝ ከሁሉ ይበልጣል ይላሉ

«መልካሙ እረኛ» ሲባል በዕብ 13፥20 ላይ «ታላቁ እረኛ» በ1ጴጥ 5፥4 ላይ ደግሞ «የእረኞች አለቃ» ተብሎአል።

(3) ኑሮውን ለማሸነፍ ወይም ክብርን ለማትረፍ የሚያገለግለው በቍ 12-13 ላይ የተጠቀሰው ቅጥረኛ ዐይነት እንደ ሆነ አስተውል። እውነተኛ መጋቢዎች በጎቻቸውን ይንከባከባሉ፣ ሐሰተኛ መጋቢዎች ግን ከሁሉም በፊት ለራሳቸውና ለሥልጣናቸው ያስባሉ።

**10፥14 በጎቼን ዐውቃለሁ፤** እግዚአብሔር ልጆቹን ማወቁና ለእነርሱም ያለው ፍቅር ለእነርሱ የሚያሳየውን መውደድ፣ ታማኝነትና የዘወትር መለኮታዊ እንክብካቤን ያካትታል። በእጆቹ መዳፍ ላይ ቀርጾናል (ኢሳ 49፥14-17 እና ማብ ይመ)። የእግዚአብሔር ዐይኖች ባለማቋረጥ በበጎነት ስለሚመለከቱን ከእግዚአብሔር ሐሳብ (ልብ) የወጣን አይደለንም (ከዘፀ 33፥17፥ እና ከኤር 1፥5 ጋር ያነጻጽሩ፤ ማቴ 10፥31 እና ሮሜ 8፥28 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 100 ላይ፣ *«መግቦተ እግዚአብሔር»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**10፥27 በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤** የክርስቶስ እውነተኛ በጎች የሆኑ ድምፁን ሰምተው ይታዘዛሉ፤ ይከተሉትማል። ከእረኛቸው ጋር የማያቋርጥ ኅብረት አላቸው። «ይሰማሉ» እና «ይከተሉኛል» የሚሉት ቃላት በአሁን ጊዜያት አንቀጽ የተነገሩ ሲሆኑ የማያሰልስ ወይም የዘወትር ድርጊትን የሚያመለክቱ ናቸው። እረኛው ለሚከተሉት ሁሉ የዘላለም ሕይወት ይሰጣል። ከእረኛው ርቀው የሚባዝኑና ድምፁን ለመስማት የማይፈልጉት በጎቹ አለመሆናቸውን ያረጋግጣሉ (15፥1-6)።

**10፥28 ከቶም አይጠፉም፤** ይህ የክርስቶስ በጎች ለሆኑት ሁሉ የተሰጠ የከበረ የተስፋ ቃል ነው። ከእግዚአብሔር ፍቅር ወይም ከህልዎቱ በፍጹም አይወገዱም፤ ምንም ዐይነት ኀይል ወይም ምድራዊ ሁኔታ ከእረኛቸው አይነጥቃቸውም (ከሮሜ 8፥35-39 ጋር ያነጻጽሩ)። መልካሙን እረኛ ለሚከተሉና ለማያዳምጡ እጅግ ደካማ በግ እንኳን በእርግጥ ጥበቃና ደህንነት አለ (ቀደም ያለውን ማብ ይመ)።

**10፥34 እናንተ አማልክት ናችሁ … ተብሎ አልተጻፈምን?** ይህ ኢየሱስ የተናገረው ቃል በምንም ዐይነት መንገድ አማኞች ራሳቸውን አማልክት አድርገው መቍጠር እንዳለባቸው አያስተምርም። እንዲያውም ራሳቸውን አማልክት አድርገው የሚቈጥሩ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆናሉ (ኤር 10፥11)። (1) «እናንተ አማልክት ናችሁ አልሁ» የሚለው አባባል የተነገረው ለክፉዎች ስለሚያደሉትና በልጆችም ላይ ጨካኞች ስለነበሩት ብልሹ የእስራኤል ገዥዎች ነበር (መዝ 82፥1-4)። አማልክት እንደነበሩ ያስቡ የነበሩት እነዚያ ገዥዎች ሕግ ፊት መቅረብና የሞት ፍርድ ይጠብቃቸው ነበር (መዝ 82፥7፤ ፀመዝ 82፥6 እና ማብ ይመ)። (2) ራስን አምላክ አድርጎ መቍጠርና ማወጅ ሐሰተኛው ክርስቶስ የሚፈጽመው ኀጢአት ነው (2ተሰ 2፥4፡11፤ በገጽ 1913 ላይ፣ *«የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

"በሕ ጋችሁ፣ 'እናንተ አማልክት ናችሁ
አልሁ' ተብሎ አልተጻፈምን? 35የእግዚአብሔር
ቃል የመጣላቸውን 'አማልክት' ካላቸውና
መጻሕፍም ሊሻር የማይቻል ከሆነ፣
36ታዲያ፣ 'የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ' ስላልሁ፣
አብ ለራሱ ለይቶ የቀደሰውንና ወደ ዓለም
የላከውን፣ ተሳድበሃል ብላችሁ ለምን
ትወነጅሉኛላችሁ? 37አባቴ የሚያደርገውን
ባላደርግ አትመኑኝ፤ 38የማደርገው ከሆነ
ግን እኔን ባታምኑኝ እንኳ፣ አብ በእኔ
እንዳለ እኔም በአብ እንዳለሁ ታውቁና
ታስተውሉ ዘንድ ታምራቱን እመኑ።"
39እንደገናም ሊይዙት ሞከሩ፤ እርሱ ግን
ከእጃቸው አመለጠ።
40ከዚያም ኢየሱስ፣ ቀደም ሲል ዮሐንስ
ያጠምቅበት ወደ ነበረበት፣ ወደ ዮርዳኖስ
ማዶ ተመለሰ፤ በዚያም ሰነበተ፤ 41ብዙ ሰዎ
ችም ወደ እርሱ መጡ። እነርሱም፣ "ዮሐንስ
አንድም ታምራዊ ምልክት አላደረገም፤
ነገር ግን ስለዚህ ሰው የተናገረው ሁሉ
እውነት ነበረ" አሉ። 42በዚያም ስፍራ
ብዙዎች በኢየሱስ አመኑ።

## የአልዓዛር መሞት

11 በማርያምና በእኅቷ በማርታ መንደር
በቢታንያ ይኖር የነበረው አልዓዛር
ታሞ ነበር።
2ይህች ወንድሟ አልዓዛር የታመመባት
ማርያም፣ በጌታ ላይ ሽቱ አፍስሳ
እግሩን በጠጕሯ ያበሰችው ነበረች።
3እኅትማማቾቹም፣ "ጌታ ሆይ፤ የምትወደው
ሰው ታሞአል" ብለው መልእክት ላኩበት።
4ኢየሱስ ይህን በሰማ ጊዜ፣ "ይህ ሕመም
የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ
ለእግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት የሚያደ
ርስ አይደለም" አለ። 5ኢየሱስም ማርታን፣
እኅቷንና አልዓዛርን ይወዳቸው ነበር።

10፥35 ዕብ4፥12፤ ማቴ5፥18
10፥33 ዘሌ24፥16፤ ማቴ26፥63-66፤
10፥36 ኤር1፥5፤ ዮሐ3፥17፤ 5፥17፡18፤ 6፥69
10፥37 ቍ25
10፥38 ዮሐ14፥10፤ 11፡20፤ 17፥21
10፥39 ሉቃ4፥30፤ ዮሐ7፥30፤ 8፥59
10፥40 ዮሐ1፥28
10፥41 ዮሐ1፥26፤ 27፡30፡34፤ 2፥11
10፥42 ዮሐ7፥31
11፥1 ማቴ21፥17፤ ሉቃ10፥38
11፥2 ማር14፥3፤ ሉቃ7፥38፤ ዮሐ12፥3
11፥3 ቍ5፡36
11፥4 ቍ40
11፥7 ዮሐ10፥40
11፥8 ማቴ23፥7፤ ዮሐ8፥59፤ 10፥31
11፥9 ዮሐ9፥4፤ 12፥35
11፥11 ቍ3፤ ማቴ9፥24
11፥13 ማቴ9፥24
11፥16 ማቴ10፥3፤ ዮሐ14፥5፤ 20፥24-28፤ 21፥2፤ ሐሥ1፥13
11፥17 ቍ6፡39
11፥18 ቍ1፤ ማቴ21፥17
11፥19 ቍ31፤ ኢዮ2፥11
11፥20 ሉቃ10፥38-42

6ሆኖም አልዓዛር መታመሙን በሰማ ጊዜ
በነበረበት ስፍራ ሁለት ቀን ቈየ።
7ከዚህም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን፣ "ወደ
ይሁዳ እንመለስ" አላቸው።
8እነርሱም፣ "መምህር ሆይ፤ ከጥቂት
ጊዜ በፊት አይሁድ በድንጋይ ሊወግሩህ
እየፈለጉህ ነበር፤ እንደ ገና ወደዚያ
ትሄዳለህን?" አሉት።
9ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ቀኑ
ዐሥራ ሁለት ሰዓት ብርሃን አይደለምን?
ከዚህ ዓለም ብርሃን የተነሣ ስለሚያይ በቀን
የሚመላለስ አይሰናከልም፤ 10የሚሰናከለው
ግን በሌሊት የሚመላለስ ነው፤ ብርሃን
የለውምና።"
11ይህን ከነገራቸው በኋላ፣ "ወዳጃችን
አልዓዛር ተኝቶአል፤ እኔም ከእንቅልፉ
ላስነሣው እሄዳለሁ" አላቸው።
12ደቀ መዛሙርቱም፣ "ጌታ ሆይ፤ ተኝቶ
ከሆነስ ይድናል" አሉት። 13ኢየሱስ ይህን
የነገራቸው ስለ ሞቱ ነበር፤ ደቀ መዛሙርቱ
ግን እንቅልፍ ስለ መተኛቱ የተናገረ
መሰላቸው።
14ስለዚህም በግልጽ እንዲህ አላቸው፤
"አልዓዛር ሞቶአል፤ 15ታምኑ ዘንድ፣ በዚያ
ባለ መኖሬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፤ አሁን
ግን ወደ እርሱ እንሂድ።"
16ከዚያም ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ
ለተቀሩት ደቀ መዛሙርት፣ "እኛም ሄደን
ከእርሱ ጋር እንሙት" አላቸው።

## ኢየሱስ የአልዓዛርን እኅቶች ማጽናናቱ

17ኢየሱስ ሲደርስ አልዓዛር ከተቀበረ
አራት ቀን ሆኖት ነበር። 18ቢታንያ
ከኢየሩሳሌም አሥራ አምስት ምዕራፍ[a]
ያህል ትርቅ ነበር። 19ብዙዎች አይሁድም
ማርታንና ማርያምን ስለ ወንድማቸው ሞት
ሊያጽናኗቸው መጥተው ነበር፤ 20ማርታ

[a] 11፥18 ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ነው

**11፥4 ይህ ሕመም ... ለእግዚአብሔር ክብር ነው፤** በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የሚከሠተው ሕመም የመጨረሻ ውጤቱ ከቶ የዘላለም ሞት አይሆንም፡፡ ሞት የኋላ ኋላ በትንሣኤ ይሸነፋልና (ቍ 25-26)፡፡ ማጠቃለያው እውነት፣ በክርስቶስ የሚያምኑ "ከቶውንም አለመሞታቸው" ነው (ቍ 26፤ በገጽ 765 ላይ፣ "ሞት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፡፡

**11፥5 ኢየሱስም ማርታን፣ እኅትዋንና አልዓዛርን ይወዳቸው ነበር፤** በዚህ ስፍራ ራሱን ለኢየሱስ በእውነትና በሙሉ ልብ የሰጠ (ቍ 2)፣ ከእርሱም ጋር የጠበቀ ኅብረት የነበረው (ሉቃ 10፥38-42) እንዲሁም ኢየሱስ በልዩ ፍቅር የወደደው (ቍ 3-5) ቤተሰብ ቀርቦአል፡፡ ይሁን እንጂ ቤተሰቡ ሐዘን፣ በሽታና የሞት አደጋ አጋጥሞታል፡፡ ዛሬም ይህን የመሰለ ችግር ታማኝ በሆኑና በተመረጡ የእግዚአብሔር ልጆች ላይ ሊደርስ የሚችልና መድረሱም የማይቀር ነገር ነው (በገጽ 744 ላይ፣ "የጻድቃን መከራ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፡፡ ቤተ ክርስቲያን እንደ ማርያም በፍቅር ራሳቸውን ለጌታ አሳልፈው በመስጠት የሚጸኑ፣ እንደ ማርታ መልካም ሥራ በመሥራት ታማኞች የሆኑና እንደ አልዓዛር መከራን የሚቀበሉና የሚሞቱ ምእመናን አሏት፡፡ እንዲህ ዐይነት ቤተሰብ፣ "ጌታ ሆይ፤ እስከ መቼ ነው? ለዘላለም ትረሳኛለህን?" እያለ ይጮኽ ይሆናል (መዝ 13፥1 ይመ፤ ከማቴ 27፥46፤ ራእ 6፥10 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ መዘግየቱ ከፍቅር፣ ከምሕረት ወይም ከርኅራኄ ጕድለት ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብር (ቍ 4) እና ለእርሱ መንግሥት እንዲሁም በችግር ለተሠቃዩት ሁሉ ዘላለማዊ በጎነት ለማስገኘት መሆኑን ኢየሱስ ተናግሮአል (ቍ15፡23-26፤ 40፥44)፡፡

**11፥6 በነበረበት ስፍራ ሁለት ቀን ቈየ፤** የዚያን ቤተሰብና የደቀ መዛሙርቱን እምነት ለማጠንከር፥ የበለጠም መልካም ነገር ለማድረግ ይወደው ወደ ነበረው ቤተሰብ ከመሄድ ዘገየ፡፡ በመጀመሪያ ኢየሱስ ለቤተሰቡ ሥቃይ ግድ የሌለው ይመስል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ቤተሰቡን ይወድ እንደነበረና ሐዘናቸውንም እንደተካፈለ (ቍ 3፡5፡35) ዮሐንስ በመደጋገም አበክሮ ያቀርባል፡፡ የኢየሱስ የጊዜ ዕቅድና ፈቃዱ ከእነርሱ ፍላጎት የተለየ ነበር፡፡ ፈተና በሚያጋጥመን ወቅት የእግዚአብሔር የጊዜ ዕቅድና ፈቃዱ እኛ ከምንፈልገው ሊለይ ይችላል፤ እግዚአብሔር የሚመልስልን እንደ ራሱ ጥበብና ፍቅር መጠን ነውና፡፡

የኢየሱስን መምጣት ሰምታ ልትቀበለው
ወጣች፤ ማርያም ግን በቤት ቀርታ ነበር።
[21]ማርታም ኢየሱስን እንዲህ አለችው፤
"ጌታ ሆይ፤ አንተ በዚህ ብትሆን ኖሮ፣
ወንድሜ ባልሞተ ነበር። [22]አሁንም
ቢሆን የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር
እንደሚሰጥህ ዐውቃለሁ።"
[23]ኢየሱስም፣ "ወንድምሽ ይነሣል"
አላት።
[24]ማርታም፣ "በመጨረሻው ቀን፣
በትንሣኤ እንደሚነሣ ዐውቃለሁ" አለችው።
✝ [25]ኢየሱስም እንዲህ አላት፤ "ትንሣኤና
ሕይወት እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚያምን ቢሞት
እንኳ በሕይወት ይኖራል፤ [26]በእኔ የሚኖር፣
ዮሐ የሚያምንብኝም ከቶ አይሞትም፤ ይህን
20፥31 ታምኛለሽን?"
[27]እርሷም፣ "አዎን ጌታ ሆይ፤ አንተ ወደ
ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ⁺ የእግዚአብሔር
ልጅ መሆንህን አምናለሁ" አለችው።
[28]ይህን ካለች በኋላ፣ ተመልሳ እኅቷን
ማርያምን ለብቻዋ ጠርታ፣ "መምህሩ
መጥቷል፤ ይፈልግሻልም" አለቻት።
[29]ማርያምም ይህን እንደ ሰማች፣ ፈጥና
ተነሥታ ወደ እርሱ ሄደች። [30]በዚህ ጊዜ
ኢየሱስ፣ ማርታ እርሱን በተቀበለችበት
ቦታ ነበር እንጂ፣ ገና ወደ መንደር አልገባም
ነበር። [31]ማርያምን ሲያጽናኑ በቤት ውስጥ
የነበሩ አይሁድም፣ ብድግ ብላ መውጣቷን
ሲያዩ፣ ወደ መቃብሩ ሄዳ የምታለቅስ
መስሎአቸው ተከተሏት።
[32]ማርያምም ኢየሱስ ወደ ነበረበት ቦታ
ደርሳ እንዳየችው፣ እግሩ ላይ ተደፍታ፣
"ጌታ ሆይ፤ አንተ እዚህ ብትሆን ኖሮ፣
ወንድሜ ባልሞተ ነበር" አለችው።

11፥21 ቍ32፡37
11፥22 ቍ41፡42
11፥24 ዳን12፥2፤ ዮሐ5፥28፡29፤ 6፥39፡40፤ ሐሥ24፥15
11፥25 ዮሐ1፥4፤ 3፥15፤ 6፥35
11፥26 ማቴ25፥46፤ ዮሐ3፥15
11፥27 ማቴ4፥3፤ ሉቃ2፥11፤ ዮሐ6፥14
11፥28 ማቴ26፥18፤ ዮሐ13፥13
11፥30 ቍ20
11፥31 ቍ19
11፥32 ቍ21
11፥33 ቍ38፤ ዮሐ12፥27
11፥35 ሉቃ19፥41
11፥36 ቍ3
11፥37 ቍ21፡32፤ ዮሐ9፥6፡7
11፥38 ቍ33፤ ማቴ27፥60፤ ሉቃ24፥2፤ ዮሐ20፥1
11፥39 ቍ17
11፥40 ቍ4፡23-25
11፥41 ማቴ11፥25፤ ዮሐ17፥1
11፥42 ዮሐ3፥17፤ 12፥30
11፥43 ሉቃ7፥14

[33]ኢየሱስም እርሷ ስታለቅስ፣
ተከትለዋትም የመጡት አይሁድም
ሲያለቅሱ ባየ ጊዜ መንፈሱ በኀዘን ታውኮ፣
[34]"የት ነው ያኖራችሁት?" ሲል ጠየቀ።
እነርሱም፣ "ጌታ ሆይ፤ መጥተህ እይ"
አሉት።
[35]ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ።
[36]አይሁድም፣ "እንዴት ይወደው እንደ
ነበር እዩት" አሉ።
[37]ከእነርሱ አንዳንዶቹ ግን፣ "የዐይነ
ስውሩን ዐይን የከፈተ፣ ይህም ሰው እንዳይሞት
ማድረግ አይችልም ነበር?" አሉ።

## ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ማስነሣቱ

[38]ኢየሱስ ልቡ ዳግመኛ በኀዘን ተነክቶ
ወደ መቃብሩ መጣ፤ መቃብሩም በድንጋይ
የተገጠመ ዋሻ ነበር፤ [39]እርሱም፣ "ድንጋዩን
አንሡት" አለ።
የሟቹም እኅት ማርታ፣ "ጌታ ሆይ፤
አሁንማ አራት ቀን ስለ ቈየ ይሸታል"
አለችው።
[40]ኢየሱስም፣ "ብታምኚስ የእግዚአብሔርን
ክብር ታያለሽ ብዬ አልነገርሁሽም?"
አላት።
[41]ስለዚህ ድንጋዩን አነሡ። ኢየሱስም ወደ
ላይ ተመልክቶ እንዲህ አለ፤ "አባት ሆይ፤
ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ፤ [42]ሁልጊዜም
እንደምትሰማኝ ዐውቃለሁ፤ ይህን መናገሬ
ግን በዚህ የቆሙ ሰዎች አንተ እንደ ላክኸኝ
ያምኑ ዘንድ ነው።"
[43]ኢየሱስ ይህን ካለ በኋላ በታላቅ
ድምፅ፣ "አልዓዛር፣ ና ውጣ!" ብሎ ተጣራ።

⁺11፥27 ወይም መሲሕ

---


**11፥25-26 ትንሣኤ ... እኔ ነኝ፤** በኢየሱስ ለሚያምን ሰው ሥጋዊ ሞት አሳዛኝ ፍጻሜ አይሆንም፤ ይልቁንም ለተትረፈረፈ ሕይወትና ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖረን ኅብረት መግቢያ በር ነው። በቍ 25 «ይኖራል» የሚለው ቃል የሚያመለክተው ትንሣኤን ሲሆን፣ በቍ 26 «ከቶ አይሞትም» የሚለው ደግሞ አካላዊ ትንሣኤ ያገኙ ክርስቲያኖች ወደፊት ከቶ አይሞቱም የሚል ትርጕም አለው። የማይሞትና የማይበሰብስ (1ቆሮ 15፥42፡54) ማለትም ሊሞት እና ሊፈርስ የማይችል አዲስ አካል ይኖራቸዋል (ከሮሜ 8፥10፤ ከ2ቆሮ 4፥16 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1810 ላይ፣ *«አካላዊ ትንሣኤ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**11፥33 መንፈሱ በሐዘን ታውኮ፤** በዓለም ውስጥ ካለው ክፋት ሁሉ የተነሣ የተከሠተውን ሰቆቃና ሥቃይ ኢየሱስ በተመለከተ ጊዜ ልቡና ስሜቱ እንዴት እንደነበር ይህ ሐረግ ይገልጻል። (1) «በሐዘን ታውኮ» (በግሪኩ «ኢምብሪማኦማይ») የሚለው ሐረግ ቍጣ የተቀላቀለበትን ጥልቅ ስሜት የሚያሳይ ነው። ኀጢአት፣ ሰይጣንና ሞት ካስከተሉት ጕስቍልና የተነሣ ኢየሱስ አዝኖና ተቈጥቶ ነበር። ኢየሱስ ለሰው ዘር ድኅነት በሚጋደልበት ጊዜ ነፍሱ በኀጢአትና በክፋት ላይ በቍጣ ተሞልታ ነበር (11፥35 እና ማብ፤ ማቴ 23፥13 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም ማቴ 21፥12-13፤ ማር 11፥15-17፤ ሉቃ 19፥45-46፤ ዮሐ 2፥14-16 ይመ)።

(2) በሕይወታችን የእግዚአብሔር ሥራ እንደ ተከናወነ ከሚያመለክቱት እርግጠኛ ምልክቶች አንዱ ኀጢአት በዓለም ላይ እያስከተለ ያለው ጕስቍልና፣ ሐዘንና ሥቃይ መጠኑ ምን ያህል መሆኑን ማገናዘብ መጀመራችን ነው (ከዘፍ 3፥16-19 ከሮሜ 5፥12 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህንን በምናደርግበት ጊዜ ለሚሠቃዩት የሚኖረን ርኅራኄና በኀጢአት ላይ ያለን ጥላቻ በልባችን ውስጥ ከፍ እያለ ይመጣል። በምንም ዐይነት መንገድ በኀጢአት ደስ ልንሰኝ አንችልም (ሮሜ 1፥32 እና ማብ፤ 2ተሰ 2፥12 እና ማብ፤ ዕብ 1፥9 እና ማብ ይመ)።

**11፥35 ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ፤** ይህ ሐረግ እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ የቱን ያህል እንደሚገደው ያመለክታል። «እንባውን አፈሰሰ» (ግሪኩ «ዳክሩኦ») የሚለው ሐረግ፣ ኢየሱስ በትድሚያ ተንሰቅስቆ እንዳለቀሰና በኋላም በጸጥታ እንዳነባ ያመለክታል። ይህ ሐዘን ለደረሰባቸው ሁሉ መጽናናትን የሚሰጥ ነው። ክርስቶስ ለአልዓዛር ዘመዶች የነበረውን ዐይነት የኀዘኔታ ስሜት ለእናንተም አለው። ለአንተም ያለው ፍቅር ይህን ያህል ነው። ይህ ጥቅስ የሚገኘው ስለ ኢየሱስ መለኮትነት ከማንኛውም መጽሐፍ ይልቅ አበክሮ በሚናገረው መጽሐፍ ውስጥ መሆኑን አስተውል። እንባውን ያፈሰ የነበረው አምላክም ሰውም የሆነው መለኮት ኢየሱስ ነው። እግዚአብሔር ልብን የሚነካና ርኅራኄ የተሞላው ጥልቅ ፍቅር ለአንተና ለሌሎችም አለው (ሉቃ 19፥41)።

## ኢየሱስ በይሁዳና በሰማርያ




© 1989 The Zondervan Corporation

[44]የሞተውም ሰው እጅና እግሩ በቀጭን ስስ
ጨርቅ እንደ ተጠቀለለ፣ ፊቱም በሻሽ እንደ
ተጠመጠመ ወጣ።
ኢየሱስም "መግነዙን ፍቱለትና ይሂድ"
አላቸው።

## ኢየሱስን ለመግደል የተደረገ ሤራ

[45]ስለዚህ ወደ ማርያም ከመጡት፣
ኢየሱስ ያደረገውን ካዩት አይሁድ ብዙዎች
በእርሱ አመኑ። [46]አንዳንዶቹ ግን ሄደው
ኢየሱስ ያደረገውን ለፈሪሳውያን ተናገሩ፤
[47]ከዚያም የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን
የአይሁድን ሸንጎ ስብሰባ ጠሩ።
እነርሱም እንዲህ አሉ፤ "ይህ ሰው
ብዙ ታምራዊ ምልክቶችን እያደረገ ስለ
ሆነ ምን ብና ደርግ ይሻላል? [48]እንዲሁ
ብንተወው ሰው ሁሉ በእርሱ ያምናል፤
ሮማውያንም መጥተው ሥፍራችንንና*
ሕዝባችንን ይወስዱብናል።"
[49]ከመካከላቸውም አንዱ፣ በዚያ ዓመት
ሊቀ ካህናት የነበረው ቀያፋ እንዲህ ሲል
ተናገረ፤ "እናንተ እኮ ምንም አታውቁም!
[50]ሕዝቡ ሁሉ ከሚጠፋ ስለ ሕዝቡ አንድ ሰው
ቢሞት የሚሻል መሆኑን አታስተውሉም።"
[51]ይህን ያለው ከራሱ አልነበረም፤ ነገር ግን
በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት እንደ መሆኑ፣
ኢየሱስ ለአይሁድ ሕዝብ እንደሚሞት
ትንቢት መናገሩ ነበር፤ [52]ለዚያም ሕዝብ
ብቻ ሳይሆን፣ የተበተኑትን የእግዚአብሔርን
ልጆች በአንድነት ለመሰብሰብ ነው። [53]ከዚያን
ቀን ጀምሮ፣ ሊገድሉት አሤሩ።
[54]ስለዚህ ኢየሱስ ከዚያ ወዲያ በአይሁድ
መካከል በይፋ አልተመላለሰም፤ ነገር ግን
በምድረ በዳ አጠገብ ወደምትገኝ ኤፍሬም
ወደ ተባለች መንደር ገለል አለ፤ በዚያም
ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሰነበተ።
[55]የአይሁድ ፋሲካ እንደ ተቃረበም፣
በዓሉ ከመድረሱ በፊት የመንጻት ሥርዐት
ለማ ድረግ ብዙዎች ከአገር ቤት ወደ
ኢየሩሳሌም ወጡ። [56]ኢየሱስንም ይፈልጉት
ነበር፤ በቤተ መቅደስም ቆመው፣ "ምን
ይመስላችኋል? ለበዓሉ አይመጣ ይሆን?"
ተባባሉ። [57]የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን
ግን ኢየሱስን ይይዙት ዘንድ የት እንዳለ
የሚያውቅ ሰው እንዲጠቍም ትእዛዝ
ሰጥተው ነበር።

11፥44 ዮሐ19፥40፤ 20፥7
11፥45 ቍ19፤ ዘፀ14፥31፤ ዮሐ2፥23፤ 7፥31
11፥47 ቍ57፤ ማቴ5፥22፤ 26፥3፤ ዮሐ2፥11
11፥49 ቍ51፤ ማቴ26፥3፤ ዮሐ18፥13፥14
11፥50 ዮሐ18፥14
11፥52 ኢሳ49፥6፤ ዮሐ10፥16
11፥53 ማቴ12፥14
11፥54 ዮሐ7፥1
11፥55 ዘፀ12፥13፥23፥27፤ 2ዜና30፥17፥18፤ ማቴ26፥1፥2፤ ማር14፥1፤ ዮሐ13፥1
11፥56 ዮሐ7፥11
12፥1 ማቴ21፥17፤ ዮሐ11፥55
12፥2 ሉቃ10፥38-42
12፥3 ማር14፥3፤ ዮሐ11፥2
12፥4 ማቴ10፥4
12፥6 ዮሐ13፥29
12፥7 ዮሐ19፥40
12፥8 ዘዳ15፥11
12፥9 ዮሐ11፥43፥44
12፥11 ቍ17፥18፤ ዮሐ11፥45፤ 7፥31
12፥13 ዘሌ23፥40፤ መዝ118፥25፥26፤ ዮሐ1፥49

## ኢየሱስ በቢታንያ ሽቱ መቀባቱ

*12፥1-8 ተጓ ምባ — ማቴ 26፥6-13፤*
*ማር 14፥3-9፤ ሉቃ 7፥37-39*

**12** የፋሲካ በዓል ስድስት ቀን ሲቀረው
ኢየሱስ፣ ከሞት ያስነሣው አልዓ
ዛር ወደሚኖርበት፣ ወደ ቢታንያ መጣ።
[2]በዚያም ለኢየሱስ ቢባል ራት ተዘጋጀ።
ማርታ ስታገለግል፣ አልዓዛር ከእርሱ ጋር
በማእድ ከተቀመጡት አንዱ ነበር። [3]ማር
ያምም ዋጋው ውድ የሆነ፣ ግማሽ ሊትር†
ንጹሕ የናርዶስ ሽቱ አምጥታ በኢየሱስ
እግር ላይ አፈሰሰች፤ እግሩንም በጠጕሯ
አበሰች፤ ቤቱንም የሽቱው መዓዛ ሞላው።
[4]ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ፣ ኋላ አሳልፎ
የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ ግን በመቃወም
እንዲህ አለ፤ [5]"ይህ ሽቱ በሦስት መቶ
ዲናር ተሽጦ ገንዘቡ ለድኾች ለምን
አልተ ሰጠም?" [6]ይህን የተናገረው የገንዘብ
ከረጢት ያዥ በመሆኑ፣ ከሚቀመጠው
ለራሱ የሚጠቀም ሌባ ስለ ነበር እንጂ
ለድኾች ተቈርቍሮ አልነበረም።
[7]ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ "ይህ ሽቱ
ለቀብሬ ቀን የታሰበ ስለሆነ እንድታቈየው
ተዋት፤ [8]ድኾች ምንጊዜም ከእናንተ ጋር
ናቸው፤ እኔን ግን ሁል ጊዜ አታገኙኝም።"
[9]በዚህ ጊዜ ብዙ አይሁድ ኢየሱስ በዚያ
መኖሩን ዐውቀው መጡ፤ የመጡትም
ኢየሱስን ብለው ብቻ ሳይሆን፣ እርሱ
ከሙታን ያስነሣውን አልዓዛርንም ለማየት
ነበር። [10]ስለዚህ የካህናት አለቆች አልዓዛርን
ጭምር ለመግደል ተማከሩ፤ [11]ይህም በእርሱ
ምክንያት ብዙ አይሁድ ወደ ኢየሱስ እየሄዱ
ያምኑበት ስለ ነበር ነው።

## ኢየሱስ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ

*12፥12-15 ተጓ ምባ — ማቴ 21፥4-9፤*
*ማር 11፥7-10፤ ሉቃ 19፥35-38*

[12]በማግሥቱም ለበዓሉ የመጣው ብዙ
ሕዝብ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም እየመጣ
መሆኑን ሰሙ፤ [13]የዘንባባም ዝንጣፊ ይዘው
ሊቀበሉት ወጡ፤ ድምፃቸውንም ከፍ አድር
ገው እንዲህ አሉ፤

*11፥48 ወይም መቅደሳችንን
†12፥3 በግሪኩ ሊትራ ይላል
‡12፥13 በዕብራይስጡ ሕድን ማለት ሲሆን የምስጋና ድምፅ ነው

**11፥44 የሞተውም ሰው ... ወጣ፤** የአልዓዛር ከሞት የመነሣት ታምር ኢየሱስ ትንሣኤና ሕይወት እንደሆነ የሚያሳይ ምልክት ነው:: ይህ ታምር እግዚአብሔር ለሞቱት አማኞች በሙሉ ምን እንደሚያደርግ ይገልጻል፤ አማኞችም ከሙታን ይነሣሉና (14፥3፤ 1ተሰ 4፥13-18):: ይህም የአይሁድ መሪዎች ኢየሱስ ሊሞት ይገባዋል ብለው እንዲወስኑ ያደረጋቸው የመጨረሻው ጉዳይ ነበር (ቍ 45-53)::

**12፥3 ማርያምም ... በኢየሱስ እግር ላይ አፈሰሰች፤** ሽቶው በጣም ውድ ስለነበር- ማርያም ኢየሱስን መቀባቷ የታላቅ መሥዋዕትና የቀልቅ ፍቅር መግለጫ ነበር:: ለኢየሱስ ያላትን ፍቅር መግለጽ የምትችልበት ዕድል ፈጥኖ እንደሚያከትም ዐውቃ ስለነበር፣ ያገኘችውን አጋጣሚ ተጠቀመችበት:: እምነቷና ለጌታ የነበራት መሰጠት እግዚአብሔር ከአማኞች ለሚፈልገው መሰጠት ታላቅ ምሳሌ ነበር:: በዚህ ምክንያት እርሷ ከፍቅር የተነሣ ያደረገችው፣ ወንጌል በተሰበከበት ስፍራ ሁሉ እንደሚነገር ኢየሱስ ተናገረ (ማቴ 26፥13 እና ማብ ይመ)::

**12፥12-19፤** ወደ ኢየሩሳሌም በክብር ስለመግባቱ ማር 11፥9 እና ማብራሪያውን፤ ሉቃ 19፥28 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

"ሆሣዕና!"
"በጌታ ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው!"
"የእስራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው!"
14ኢየሱስም የአህያ ውርንጫላ አግኝቶ
ተቀመጠበት፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤
15"የጽዮን ልጅ ሆይ፤ አትፍሪ፤
እነሆ፤ ንጉሥሽ በአህያ ግልገል ተቀምጦ
ይመጣል።"
16ደቀ መዛሙርቱ ይህን ሁሉ በመጀመሪያ
አላስተዋሉም፤ ስለ እርሱ የተጻፉትንና
ለእርሱም የተደረጉትን ልብ ያሉት ኢየሱስ
ከከበረ በኋላ ነበር።
17አልዓዛርን ከመቃብር ጠርቶ ከሙታን
ባስነሣበት ጊዜ፣ ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች
መነሣቱን ይመሰክሩ ነበር። 18ብዙ ሰዎችም
ይህን ታምራዊ ምልክት ማድረጉን ስለ ሰሙ
ሊቀበሉት ወጡ። 19ስለዚህም ፈሪሳውያን
እርስ በርሳቸው፣ "እንግዲህ ምን ማድረግ
ይቻላል? እያችሁ ዓለሙ ሁሉ ግልብጥ
ብሎ ተከትሎታል" ተባባሉ።

## ኢየሱስ ስለ ሞቱ አስቀድሞ ተናገረ

20ለአምልኮ ወደ በዓሉ ከወጡት መካከል
የግሪክ ሰዎችም ነበሩ። 21እነርሱም በገሊላ
ከምትገኘው ከቤተ ሳይዳ ወደ ሆነው ሰው፣
ወደ ፊልጶስ መጥተው፣ "ጌታው፤ እባክህን፣
ኢየሱስን ለማየት እንፈልጋለን" አሉት።
22ፊልጶስም፤ ለእንድርያስ ሊነግረው ሄደ፤
እንድርያስና ፊልጶስም ለኢየሱስ ነገሩት።
23ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
"የሰው ልጅ የሚከብርበት ሰዓቱ
ደርሶአል፤ 24እውነት እላችኋለሁ፤ የስንዴ
ቅንጣት መሬት ላይ ወድቃ ካልሞተች
ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ
ፍሬ ታፈራለች። 25ሕይወቱን የሚወድ
ያጣታል፤ በዚህ ዓለም ሕይወቱን የሚጠላ
ግን ለዘላለም ሕይወት ይጠ ብቃታል።
26የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተ ለኝ፤ እኔም
ባለሁበት አገልጋዬም በዚያ ይሆናል፤
የሚያገለግለኝንም አባቴ ያከብረዋል።
27"አሁንስ ነፍሴ ተጨንቀች፤ ምን
ልበል? አባት ሆይ፤ ከዚች ሰዓት ታድነኝ?
የለም፤ ይህን የመጣሁት ለዚህች ሰዓት
ነውና። 28አባት ሆይ፤ ስምህን አክብረው።"
ከዚያም፣ "አክብሬዋለሁ፤ ደግሞም አከብ
ረዋለሁ" የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ።
29በዚያ የነበሩት፣ ድምፁን የሰሙት
አያሌ ሰዎች፣ "ነጐድጓድ ነው" አሉ፤
ሌሎች ደግሞ፣ "መልአክ ተናገረው" አሉ።
30ኢየሱስም እንዲህ አለ፤ "ይህ ድምፅ
የመጣው ስለ እኔ ሳይሆን ስለ እናንተ
ነው፤ 31ይህ ዓለም የሚፈረድበት ጊዜ አሁን
ነው፤ የዚህም ዓለም ገዥ አሁን ወደ ውጭ
ይጣላል። 32እኔ ግን ከምድር ከፍ ከፍ ባልሁ
ጊዜ ሰውን ሁሉ ወደ ራሴ እስባለሁ።"
33ይህን የተናገረው በምን ዐይነት ሞት
እንደሚሞት ለማመልከት ነበር።
34ሕዝቡም፣ "እኛስ ክርስቶስ[y] ለዘላለም
እንደሚኖር ከሕግ ሰምተናል፤ ታዲያ፣ 'የሰው
ልጅ ከፍ ከፍ ማለት አለበት' እንዴት ትላለህ?
ይህስ 'የሰው ልጅ' ማን ነው?" አሉት።
35ኢየሱስም እንዲህ ሲል ተናገራቸው፤
"ከእንግዲህ ለጥቂት ጊዜ ብርሃን አለላችሁ፤
ጨለማ ሳይመጣባችሁ፣ ብርሃን ሳለላችሁ
ተመላለሱ፤ በጨለማ የሚመላለስ ወዴት
እንደሚሄድ አያውቅም። 36የብርሃን ልጆች
እንድትሆኑ ብርሃን ሳለላችሁ በዚህ ብርሃን
እመኑ።" ኢየሱስ ይህን ተናግሮ እንደ ጨረሰ
ተለያቸው፤ ተሰወረባቸውም።

12፥15 ዘካ9፥9
12፥16 ቍ23፤ ማር9፥32፤ ዮሐ2፥22፤ 7፥39
12፥17 ዮሐ11፥42
12፥18 ቍ11፤ ሉቃ19፥37
12፥19 ዮሐ11፥47፡48
12፥20 ዮሐ7፥35፤ ሐሥ11፥20
12፥21 ማቴ11፥21
12፥23 ማቴ26፥18፤ ዮሐ13፥32፤ 17፥1
12፥24 1ቆሮ15፥36
12፥25 ማቴ10፥39፤ 25፥46፤ ማር8፥35፤ ሉቃ14፥26፤ 17፥33
12፥26 ዮሐ14፥3፤ 17፥24፤ 2ቆሮ5፥8፤ ፊል1፥23፤ 1ተሰ4፥17
12፥27 ቍ23፤ ማቴ11፥25፤ 26፥38፡39፤ ዮሐ11፥33፡38፤ 13፥21
12፥28 ማቴ3፥17
12፥30 ዘፀ19፥9፤ ዮሐ11፥42
12፥31 ዮሐ14፥30፤ 16፥11፤ 2ቆሮ4፥4፤ ኤፌ2፥2፤ 1ዮሐ4፥4፤ 5፥19
12፥32 ቍ34፤ ኢሳ11፥10፤ ዮሐ3፥14፤ 6፥44፤ 8፥28
12፥33 ዮሐ18፥32፤ 21፥19
12፥34 መዝ110፥4፤

12፥34 ኢሳ9፥7፤ ሕዝ37፥25፤ ዳን7፥14፤ ማቴ8፥20፤ ዮሐ3፥14፤ 10፥34 12፥35 ቍ46፤ ኤፌ5፥8፤ 1ዮሐ1፥6፤ 2፥11 12፥36 ቍ46፤ ሉቃ16፥8፤ ዮሐ8፥59

[y]12፥34 ወይም መሲሕ

**12፥23 የሰው ልጅ የሚከብርበት፤** ኢየሱስ ስለ ሞቱ የተናገረው እንደ አሳዛኝ ሁኔታ ሳይሆን ወደ ክብር እንደ መሄድ አድርጎ ነው፡፡ ወደ ፍሬያማነት የሚመራው መንገድ በመከራና በሞት ውስጥ በማለፍ እንደሆነ ለደቀ መዛሙርቱ ይነግራቸው ነበር (ቍ 24)፡፡

**12፥25 በዚህ ዓለም ሕይወቱን የሚጠላ፤** የራስን ሕይወት መጥላት ከዚህ ዓለም ነገር ይልቅ ለሰማያዊው የበለጠ ዋጋ የመስጠትን አዝማሚያ ያመለክታል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚከተሉ ለዓለማዊ ተድላ፣ ፍልስፍና፣ ስኬታማነት፣ ፋይዳ፣ ግቦች ወይም አሠራሮች ትኩረት አይሰጡም፡፡ እንዲህ ያሉ ሰዎች በዓለም ላይ ውድ የሚሆንባቸው ለጌታ ሲሉ የማይተውት ምንም ነገር ስለሌለ፣ «የዘላለምን ሕይወት» ያተርፋሉ (ማቴ 16፥24-25፤ ማር 8፥34-35)፡፡

**12፥26 የሚያገለግለኝ ቢኖር፤** አንድ ሰው በኢየሱስ ሲያምን እርሱን ለመከተል፣ ትምህርቱን ለመጠበቅና እርሱ ባለበት ለመሆን የግል ውሳኔ ማድረግ ይገባዋል፡፡ ኢየሱስን መከተል ራስን መካድና የራሱን መስቀል መሸከምን ያካትታል (በማር 8፥34 ላይ የራስን መስቀል መሸከም ምን ማለት እንደ ሆነ የሚያሳየውን ማብ ይመ)፡፡

**12፥31 የዚህ ዓለም ገዥ አሁን ወደ ውጭ ይጣላል፤** የሰይጣንና የእርሱ የሆነው ሁሉ መሸነፍ የጀመረው በክርስቶስ መስቀልና በትንሣኤው በኩል ነው፡፡ የሰይጣን የመጨረሻ ሽንፈት የሚሆነው ወደሚነደው የድኝ ባሕር በሚጣልበት ጊዜ ነው (ራእ 20፥10)፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ሰይጣን የዚህ ዓለም ገዥ ወይም አለቃ እንደ መሆኑ መጠን በትጋት እየሠራ ነው (14፥30፤ 16፥11፤ 2ቆሮ 4፥4፤ ከኤፌ 2፥2 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ ሰይጣን በዚህ ዓለም ላይ ኀይልና ሥልጣን አለው፤ የዓለም የሆኑትን ነገሮች ክርስቶስንና ቤተ ክርስቲያንን ለመዋጋት ይጠቀምባቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ነው፣ «ከዓለም ጋር ወዳጅ መሆን የእግዚአብሔር ጠላት መሆን እንደሆነ» የተባለው (ያዕ 4፥4 በተጨማሪ 1ዮሐ 2፥15-16 ይመ)፡፡

**12፥32 ሰውን ሁሉ ወደ ራሴ እስባለሁ፤** የእግዚአብሔር ጸጋ ለሁሉም ነው፤ ማለትም ለአንዳንዶች የሚሰጥና ለሌሎች የሚከለከል አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ ኀጢአትን ከመውደዳቸው የተነሣ በውሳኔያቸውና በተግባራቸው የእግዚአብሔርን ጸጋ ያቃልላሉ (ማቴ 23፥37ን ይመ)፡፡

### አይሁድ ባለማመን መጽናታቸው

37ኢየሱስ እነዚህን ታምራዊ ምልክቶች
ሁሉ በፊታቸው ቢያደርግም እንኳ፣
አሁንም አላመኑበትም፤ 38ይኸውም ነቢዩ
ኢሳይያስ፣
"ጌታ ሆይ፤ ምስክርነታችንን ማን
አመነ?
የጌታ ክንድስ ለማን ተገለጠ?" ያለው
ቃል እንዲፈጸም ነው።
39ስለዚህ ማመን አልቻሉም፤ ይህም
ኢሳይያስ በሌላ ቦታ እንዲህ ሲል እንደ
ተናገረው ነው፤

40"ዐይናቸውን አሳውሯል፤
ልባቸውንም አደንድኖአል፤
ስለዚህ በዐይናቸው አያዩም፤
በልባቸውም አያስተውሉም፤
እንዳልፈውሳቸውም አይመለሱም።"
41ኢሳይያስ ይህን ያለው የኢየሱስን ክብር
ስላየ ነው፤ ስለ እርሱም ተናገረ። 42ይህም
ቢሆን፣ ከአለቆች መካከል እንኳ ሳይቀር
ብዙዎች በእርሱ አመኑ፤ ይሁን እንጂ
ፈሪሳውያን ከምኵራብ እንዳያስወጧቸው
ስለ ፈሩ ማመናቸውን አይገልጡም ነበር።
43ይህም የሆነው በእግዚአብሔር ከመመስገን
ይልቅ በሰው መመስገንን ስለ ወደዱ ነው።
44ከዚያም ኢየሱስ ድምፁን ከፍ አድርጎ
እንዲህ አለ፤ "ማንም በእኔ ቢያምን በእኔ
ብቻ ሳይሆን በላከኝም ማመኑ ነው፤ 45እኔ
ንም የሚያይ የላከኝን ያያል። 46በእኔ
የሚያምን በጨለማ እንዳይኖር ብርሃን ሆኜ
ወደ ዓለም መጥቻለሁ።
47"ቃሌን ሰምቶ በማይፈጽመው ላይ
የምፈርደው እኔ አይደለሁም፤ ዓለምን ላድን
እንጂ በዓለም ላይ ልፈርድ አልመጣሁምና።
48በማይቀበለኝና ቃሌን በሚያቃልል ላይ
የሚፈርድበት አለ፤ የተናገርሁት ቃል
ራሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል፤
ምክንያቱም 49እኔ ከራሴ አልተናገርሁም፤
ነገር ግን የላከኝ አብ ምን እንደምናገርና
እንዴት እንደምናገር አዘዘኝ። 50የእርሱ
ትእዛዝ ወደ ዘላለም ሕይወት እንደሚያደርስ
ዐውቃለሁ፤ ስለዚህም የምለው ሁሉ አብ
እንድናገረው የነገረኝን ብቻ ነው።

### ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠቡ

13 ጊዜው ልክ ከፋሲካ በዓል በፊት ነበረ፤
ኢየሱስም ይህን ዓለም ትቶ ወደ አብ
የሚሄድበት ጊዜ እንደ ደረሰ ዐወቀ። በዓለም
የነበሩትን፣ የራሱ የሆኑትን ወደዳ ቸው፤
በፍጹም ፍቅሩም ወደዳቸው።[A]
2እራትም ቀርቦ ሳለ፣ ኢየሱስን አሳልፎ
እንዲሰጥ ዲያብሎስ የስምዖንን ልጅ የአስ
ቆሮቱን ይሁዳ ልብ አነሣሥቶ ነበር።
3ኢየሱስም፣ አብ ሁሉን ነገር በሥልጣኑ
ሥር እንዳደረገለት፣ ከእግዚአብሔር እንደ
ተላከና ወደ እግዚአብሔርም እንደሚመለስ
ዐውቆ፣ 4ከእራት ተነሣ፤ መጐናጸፊያውን
አስቀመጠ፤ ወገቡንም በፎጣ ታጠቀ።
5ከዚያም በመታጠቢያው ውሃ ጨምሮ የደቀ
መዛሙርቱን እግር እያጠበ በታጠቀው ፎጣ
ያብስ ጀመር።
6ወደ ስምዖን ጴጥሮስም መጣ፤
ጴጥሮስም፣ "ጌታ ሆይ፤ አንተ እግሬን
ታጥባለህ?" አለው።
7ኢየሱስም መልሶ፣ "የማደርገውን አሁን
አታውቅም፤ በኋላ ግን ታስተውለዋለህ"
አለው።

[A]13፥1 ወይም እስከ መጨረሻው

12፥37 ዮሐ2፥11
12፥38 ኢሳ53፥1፤ ሮሜ10፥16
12፥40 ኢሳ6፥10፤ ማቴ13፥13፡15
12፥41 ኢሳ6፥1-4፤ ሉቃ24፥27
12፥42 ቊ11፤ ዮሐ7፥13፡48፤ 9፥22
12፥43 1ሳሙ15፥30፤ ሮሜ2፥29
12፥44 ማቴ10፥40፤ ዮሐ5፥24
12፥45 ዮሐ14፥9
12፥46 ዮሐ1፥4
12፥47 ዮሐ3፥17
12፥48 ዮሐ5፥45
12፥49 ዮሐ14፥31
12፥50 ማቴ25፥46፤ ዮሐ14፥24
13፥1 ማቴ26፥18፤ ዮሐ11፥55፤ 16፥28
13፥2 ማቴ10፥4
13፥3 ማቴ28፥18፤ ዮሐ8፥42፤ 16፥27፡28፡30፤ 17፥8
13፥4 ማቴ20፥28
13፥5 ሉቃ7፥44
13፥7 ቊ12

**12፥39 ማመን አልቻሉም፤** ሰዎቹ ኢየሱስን ስላልተቀበሉት እግዚአብሔር ልባቸውን አደነደነ ከዚህም የተነሣ ሊያምኑ አልቻሉም። ወንጌል ለማዳመጥ፣ ንስሐ ለመግባትና ለማመን የማይፈቅደውን ሰው ጎጂ ሁኔታ ሳያስከትልበት አይቀርም። ሐዋርያው ጳውሎስ ባለማመናቸው ምክንያት የእስራኤል ሕዝብ እንደተቈረጡ ተናግሯል (ሮሜ 11፥20፤ ይመ፤ ከመዝ 95፥8 እና ዕብ 3፥8 ጋር ያነጻጽሩ)። ይሁን እንጂ ይህ የልብ ድንዳኔ በዚያ አገር በሚገኝ በእያንዳንዱ ሰው ላይ ስዘለቄታው የጸና አልነበረም። ማንኛውም የመነ ሰው የዘላለም ሕይወትን ይቀበላል (ቊ 44-50)። በእርግጥም ከበዓለ ሃምሳ በኋላ ብዙ እስራኤላውያን አምነዋል (ሐሥ 2፥41)።

**12፥43 በሰው መመስገንን ስለወደዱ፤** ብዙ ሰዎች የሌሎችን ሰዎች ሙገሳ ስለሚወዱ ላመኑበት ነገር ባለመቆም ከሕሊናቸው ተቃራኒ የሆነ ተግባርን ይፈጽማሉ። ከብዙኃኑ ጋር በመመሳሰል (ከዳን 11፥32-34 ጋር ያነጻጽሩ) የኀይለኞችን ወይም የሕዝቡን ሙገሳ ለመፈለግ ዝግጁ ናቸው። ሰዎችን ከመፍራት ወጥመድና ከንቱ ውዳሴ ከማግኘት ምኞት ድል የመቀዳጀት ምስጢር ምንድነው? እምነታችን ነው (1ዮሐ 5፥4)፤ ይህም እግዚአብሔር፣ ክርስቶስ፣ መንግሥት ሰማያት፣ ገሃነመ እሳት፣ ፍርድና ዘላለማዊነት የማይሸሩ እውነታዎች እንደሆኑ የሚቀበል እምነት ነው (ሮሜ 1፥20፤ ኤፌ 3፥16-19፤ ዕብ 11)። ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የሰውን ክብር አስበልጠው እየፈሩ ክርስቶስን እከተላለሁ ማለት የለየለት ግብዝነት ነው።

**12፥50 የዘላለም ሕይወት፤** 17፥3 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**13፥5 የደቀ መዛሙርቱን እግር እያጠበ፤** ይህ አስደናቂ የእግር ማጠብ ክንውን የተከሄደው ኢየሱስ ከመሞቱ በፊት በምድር ላይ ባሳለፈው የመጨረሻው ሌሊት ነበር። ኢየሱስም ይህን ያደረገው፦ (1) ምን ያህል እንደሚወዳቸው ለደቀ መዛሙርቱ ለማሳየት፤ (2) በመስቀል ላይ ራሱን አሳልፎ እንደሚሰጥ አስቀድሞ ለማመልከትና (3) ደቀ መዛሙርቱ የተጠሩበትን እርስ በርሳቸው በትህትና እንዲያገለግሉ የሚያስተምረውን እውነት ለመግለጽ ነበር። ትልቅ የመሆን ፍላጎት ያለማቋረጥ ደቀ መዛሙርቱን ይፈታተናቸው ነበር (ማቴ 18፥1-4፤ 20፥20-27፤ ማር 9፥33-37፤ ሉቃ 9፥46-48)። ከሁሉ ቀዳሚ ለመሆን ማለትም ከሌሎች ክርስቲያኖች ከፍ ብሎና ተከብሮ ለመታየት መፈለጋቸው ከጌታ ከኢየሱስ መንፈስ ጋር ተጻራሪ መሆኑን እንዲመለከቱ ክርስቶስ ፈልጎ ነበር (ሉቃ 22፥24-30 እና ማብ ይመ፤ ዮሐ 13፥12-17፤ 1ጴጥ 5፥5)።

8 ጴጥሮስም፣ "የለም፤ እግሬን ከቶ አታጥ
ብም" አለው።
ኢየሱስም፣ "ካላጠብሁህማ ከእኔ ጋር
ዕድል ፈንታ የለህም" አለው።
9 ስምዖን ጴጥሮስም፣ "ጌታ ሆይ፤
እንግዲያውስ እግሬን ብቻ ሳይሆን እጄንም
ራሴንም እጠበኝ" አለው።
10 ኢየሱስም፣ "ገላውን የታጠበ ሰው
የሚያስፈልገው እግሩን ብቻ መታጠብ ነው፤
የቀረው አካሉ ግን ንጹሕ ነው። ሁላችሁም
ባትሆኑ፣ እናንተ ንጹሓን ናችሁ" አለው።
11 "ሁላችሁም ንጹሓን አይደላችሁም"
ያለው አሳልፎ የሚሰጠው ማን እንደ ሆነ
ያውቅ ስለ ነበር ነው።
12 እግራቸውን አጥቦ ካበቃ በኋላም፣
ልብሱን ለብሶ ተመልሶ በቦታው ተቀመጠ፤
እንዲህም አላቸው፤ "ያደረግሁላችሁን
ታስተውላላችሁን? 13 እናንተ፣ 'መምህርና፣
ጌታ' ትሉኛላችሁ፤ ትክክል ነው፤
እንደምትሉኝ እንዲሁ ነኝና። 14 እንግዲህ
እኔ ጌታችሁና መምህራችሁ ሆኜ ሳለሁ
እግራችሁን ካጠብሁ፣ እናንተም እንደዚሁ
እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ልትተጣጠቡ
ይገባችኋል። 15 እኔ እንዳደረግሁላችሁ
እናንተም እንደዚሁ እን ድታደርጉ ምሳሌ
ትቼላችኋለሁ። 16 እውነት እላችኋለሁ፤
አገልጋይ ከጌታው፣ መልእክተኛም ከላከው
አይበልጥም። 17 እንግዲህ እነዚህን ነገሮች
በውቃችሁ ብትፈጽሙ ትባረካላችሁ።

## አልፎ እንደሚሰጥ ኢየሱስ መናገሩ

18 "ስለ ሁላችሁ መናገሬ አይደለም፤
የመረጥኋቸውን ዐውቃለሁ፤ ነገር ግን፣
'እንጀራዬን አብሮኝ የቈረሰ ተረከዙን
አነሣብኝ' የሚለው የመጽሐፍ ቃል
እንዲፈጸም ነው።
19 "ሲፈጸም እኔ እንደ ሆንሁ ታምኑ
ዘንድ፣ ይህ ከመሆኑ በፊት አሁን
ነገርኋችሁ። 20 እውነት እላችኋለሁ፤ እኔ
የላክሁትን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔን
የተቀበለም የላከኝን ይቀበላል።"
21 ይህን ካለ በኋላም ኢየሱስ በመንፈሱ
ታውኮ፣ "እውነት እላችኋለሁ፤ ከእናንተ
አንዱ እኔን አሳልፎ ይሰጣል" ሲል በግልጽ
ተናገረ።

13፥10 ቍ18፤ ዮሐ15፥3
13፥11 ማቴ10፥4
13፥13 ማቴ26፥18፤ 28፥18፤ ሉቃ1፥43፤ 2፥11፤ ዮሐ11፥28፤ 6፥46፤ 11፥13 ሐሥ10፥36፤ ሮሜ10፥9፡12፤ 14፥9፤ 1ቆሮ12፥3፤ ፊል2፥11፤ ቈላ2፥6
13፥14 1ጴጥ5፥5
13፥15 ማቴ11፥29፤ 1ጢሞ4፥12
13፥16 ማቴ10፥24፤ ሉቃ6፥40፤ ዮሐ15፥20
13፥17 ማቴ7፥24፡25፤ ሉቃ11፥28፤ ያዕ1፥25
13፥18 ቍ10፤ መዝ41፥9፤ ማቴ1፥22፤ 26፥23፤ ዮሐ6፥70፤ 15፥16፡19
13፥19 ዮሐ4፥26፤ 8፥24፤ 14፥29፤ 16፥4
13፥20 ማቴ10፥40
13፥21 ማቴ26፥21፤ ዮሐ12፥27
13፥23 ዮሐ19፥26፤ 20፥2፤ 21፥7፡20
13፥25 ማቴ26፥22፤ ዮሐ21፥20
13፥26 ማቴ10፥4
13፥27 ሉቃ22፥3
13፥29 ቍ1፤ ዮሐ12፥5፡6
13፥30 ሉቃ22፥53
13፥31 ማቴ8፥20፤ ዮሐ7፥39፤ 12፥23፤ 14፥13፤ 17፥4፤ 1ጴጥ4፥11

22 ደቀ መዛሙርቱም ማንን ማለቱ እንደ
ሆነ ግራ ተጋብተው እርስ በርሳቸው ተያዩ።
23 ከእነርሱ አንዱ፣ ኢየሱስ ይወደው የነበረ
ደቀ መዝሙር ወደ ኢየሱስ ደረት ተጠግቶ
ተቀምጦ ነበር። 24 ስምዖን ጴጥሮስም ይህን
ደቀ መዝሙር በምልክት ጠቅሶ "ማንን
ማለቱ እንደ ሆነ ጠይቀው" አለው።
25 እርሱም ወደ ኢየሱስ ደረት ደገፍ
ብሎ፣ "ጌታ ሆይ፤ ማን ይሆን?" ብሎ
ጠየቀው።
26 ኢየሱስም፣ "ይህን ቍራሽ እንጀራ
ከወጭቱ አጥቅሼ የምሰጠው እርሱ ነው"
አለው፤ ከዚያም ቍራሹን እንጀራ አጥቅሶ
ለስምዖን ልጅ ለአስቆሮቱ ይሁዳ ሰጠው።
27 ይሁዳም ቍራሹን እንጀራ እንደ ተቀበለ
ወዲያው ሰይጣን ገባበት።
ኢየሱስም፣ "የምታደርገውን ቶሎ
አድርግ" አለው፤ 28 ይሁን እንጂ ኢየሱስ
ለምን እንዲህ እንዳለው ማንም አላወቀም
ነበረ። 29 ይሁዳ ገንዘብ ያዥ ስለ ነበር፣
አንዳንዶቹ ለበዓሉ የሚያስፈልግ ነገር
እንዲገዛ ወይም ለድኾች እንዲሰጥ ኢየሱስ
የተናገረው መስ ላቸው። 30 ይሁዳም ያን
ቍራሽ እንጀራ እንደ ተቀበለ ወጥቶ ሄደ፤
ሌሊትም ነበረ።

## ጴጥሮስ እንደሚክደው ኢየሱስ መናገሩ

*13፥37-38 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥33-35፤ ማር 14፥29-31፤ ሉቃ 22፥33-34*

31 ይሁዳ ከወጣ በኋላ፣ ኢየሱስ እንዲህ
አለ፤ "አሁን የሰው ልጅ ከበረ፤ በእርሱም
እግዚአብሔር ከበረ። 32 እንግዲህ እግዚአብ
ሔር በእርሱ ከከበረ[h]፣ እግዚአብሔር ልጁን
በራሱ ዘንድ ያከብረዋል፤ ወዲያውም
ያከብረዋል።
33 "ልጆቼ ሆይ፤ ከእናንተ ጋር
የምቈየው ለጥቂት ጊዜ ነው፤ እናንተም
ትፈልጉኛላችሁ፤ ለአይሁድ፣ 'እኔ
ወደምሄድበት ልትመጡ አትችሉም'
እንዳልኋቸው፣ አሁንም ለእናንተ ይህንኑ
እላችኋለሁ።

13፥32 ዮሐ17፥1 13፥33 ዮሐ7፥33፡34

*[h] 13፥32 አያሌ የጥንት ቅጆች እግዚአብሔር በእርሱ ከከበረ የሚለው ሐረግ የላቸውም*

13፥8 **ካላጠብሁህማ**፤ ይህ ቃል ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለሚያከናውነው መንፈሳዊ እጥበት ያመለክታል። ከዚህ እጥበት ውጪ ማንም የክርስቶስ ሊሆን አይችልም (1ዮሐ 1፥7)።
13፥14 **እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ልትተጣጠቡ**፤ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በትሕትና እርስ በርሳቸው እግራቸውን በፍቅር የታጠቡት በዚህ ጊዜ ክርስቶስ ያሳያቸውን ምሳሌነት ቃል በቃል ተከትለው በመታዘዝ ነበር። ለምሳሌ ያህል፣ የተወሰኑ መበለቶችን የሚያሟሉ እስከሆኑ ድረስ ባልቴቶች በቤተ ክርስቲያን እንክብካቤ ሊያገኙ እንደሚገባቸው ጳውሎስ በ1ጢሞ 5፥10 ላይ ተናግሮአል። ከእነዚያ መመዘኛዎችም አንዱ የቅዱሳንን እግር ማጠብ ነበር።
13፥22 **ማንን ማለቱ እንደ ሆነ ግራ ተጋብተው**፤ እዚህ ላይ የይሁዳን አጭበርባሪነት ደቀ መዛሙርት እንዳልነቁበት መገንዘብ አስፈላጊ ነው። ግብዝነቱ እንዳይታወቅበት በሚገባ ሸፍኖት ነበር። ዛሬም ቢሆን በቤተ ክርስቲያን ውጭ ውጩን ጻድቃን መስለው የሚታዩ በውስጣቸው ግን ምንም እውነተኛ እምነትና ለክርስቶስ የተሰጠ ሕይወት የሌላቸው ይኖራሉ (በገጽ 1519 ላይ፣ *"የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት መጽሐፍ ይመ)።
13፥26 **ቍራሽ እንጀራ**፤ ኢየሱስ ቍራሽ እንጀራ ለይሁዳ መስጠቱ ከንስሓ ይመለስ ዘንድ የመጨረሻ የፍቅር ጥሪ ማድረጉ ሳይሆን አይቀርም። ይሁን እንጂ ይሁዳ ሐሳቡን ለመቀየር አልፈቀደም፤ ስለዚህ ሰይጣን ተቈጣጠረው (ቍ 27፤ ሉቃ 22፥3 እና ማብ ይመ)።

34 "አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ፤
ይኸውም እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ
ነው፤ እንግዲህ እኔ እንደ ወደድኋችሁ
እናንተም እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። 35 እርስ
በርሳችሁ ብትዋደዱ፣ ሰዎች ሁሉ የእኔ ደቀ
መዛሙርት እንደ ሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ።"
36 ስምዖን ጴጥሮስ፣ "ጌታ ሆይ፤
የምትሄደው ወዴት ነው?" አለው።
ኢየሱስም፣ "ወደምሄድበት አሁን
ልትከተለኝ አትችልም፤ ኋላ ግን
ትከተለኛለህ" ሲል መለሰለት።
37 ጴጥሮስም፣ "ጌታ ሆይ፤ አሁን
ልከተልህ የማልችለው ለምንድን ነው?
ስለ አንተ ሕይወቴንም ቢሆን አሳልፌ
እሰጣለሁ" አለው።
38 ኢየሱስም፣ እንዲህ ሲል መለሰ፤
"ሕይወትህን በርግጥ ለእኔ አሳልፈህ
ትሰጣለህን? እውነት እልሃለሁ፤ ዶሮ
ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ።"

13፥34
ዘሌ.19፥18፤
ዮሐ15፥12፤
ኤፌ5፥2፤
1ተሰ4፥9፤
1ጴጥ1፥22፤
1ዮሐ2፥7-11፤
3፥11፤ 4፥10፡11
13፥35
1ዮሐ3፥14፤ 4፥20
13፥36 ቁ.33፤
ዮሐ14፥2፤ 16፥5፤
21፥18፡19፤
2ጴጥ1፥14
13፥38 ዮሐ18፥27
14፥1 ቁ.27፤
መዝ4፥5፤
ዮሐ3፥15
14፥2
ዮሐ13፥33፡36፤
16፥5
14፥3 ሐዋ18፡28፤
ማቴ16፥27፤

## ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አበረታታ

14 "ልባችሁ አይጨነቅ፤ በእግዚአብሔር
እመኑ[*]፤ በእኔም ደግሞ እመኑ።
2 በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ ይህ ባይሆ
ንማ ኖሮ እነግራችሁ ነበር፤ የምሄደውም
ስፍራ ላዘጋጅላችሁ ነው። 3 ሄጄም ስፍራ
ካዘጋጀሁላችሁ በኋላ፣ እኔ ባለሁበት
እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ
ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመጣለሁ። 4 እኔ
ወደምሄድበትም ስፍራ የሚያደርሰውን
መንገድ ታውቃላችሁ።"

## ወደ አብ የሚያደርሰው መንገድ

5 ቶማስም፣ "ጌታ ሆይ፤ ወዴት
እንደምትሄድ አናውቅም፤ ታዲያ፣ መንገዱን
እንዴት ማወቅ እንችላለን?" አለው።

14፥3 ዮሐ12፥26 14፥5 ዮሐ11፥16

*14፥1 *ወይም እናንተ በእግዚአብሔር ታምናላችሁ*

**13፥34 እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ፤** አንድ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያኑን አባላት ወይም ተመሳሳይ የሥነ መለኮት አቋም ያላቸውን ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን፣ እውነተኛ ክርስቲያኖችን ሁሉ ላቅ ባለና ልዩ በሆነ ሁኔታ ይወድ ዘንድ ታዟል። (1) ለኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸውን ፍቅርና ለቅዱስ ቃሉም የሚያሳዩትን ታዛዥነት በመመርመር፣ አማኞች እውነተኛ ክርስቲያኖችን ክርስቲያን ካልሆኑት ሊለዩ ይገባቸዋል (5፥24፤ 8፥31፤ 10፥27፤ ማቴ 7፥21፤ ገላ 1፥9 እና ማብ ይመ)።

(2) በኢየሱስ ክርስቶስ ሕያውነት ያለው በተገለጠውና ስሕተት አልባ ለሆነው ቃል፣ በቅንነት በተረዳው መጠን ታማኝ ሆኖ የሚኖር እንዲሁም በዘመናችን ተንሰራፍቶና ገኖ ያለውን ክፋውን መንፈስ ጸንቶ በመቃወም የሚቆም ማንኛውም ሰው እኅቴ ወይም ወንድሜ ነው፡ ከዚህም የተነሣ የተለየ ፍቅርና እንክብካቤ ላደርግለት ይገባል።

(3) የቤተ ክርስቲያናችን አባላት ያልሆኑትን ጨምሮ እውነተኛ ክርስቲያኖችን ሁሉ መውደድ ስንል ተለይተን የምንታወቅበትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነታችንን ወይም የአስተምህሮ ልዩነቶቻችንን ማቻቻል ወይም ማስተናገድ አለብን ማለት አይደለም፤ ይህም ሲባል አንድ ቤተ ክርስቲያን በተቋምነቱ ከሌላው ቤተ ክርስቲያን ጋር ተደባልቆ አንድ ይሁን ማለታችን አይደለም።

(4) ከሰዎች ጋር ተስማምቶ ለመኖር ሲባል፣ በክርስቲያኖች ዘንድ ሊታይ የሚገባው የእግዚአብሔር ቅድስና ሊጓደል ዝም ማለት አይገባም። በቃሉ በተገለጸው መሠረት ለእግዚአብሔርና ለፈቃዱ የሚኖረን ፍቅር ለሌሎች ሰዎች የሚኖረንን ፍቅር ሊቈጣጠርና ሊመራው ይገባል። ለእግዚአብሔር የሚኖረን ፍቅር ምን ጊዜም ሊቀድም ይገባል (የሚከተለውን ማብ እንዲሁም ማቴ 22፥37፡39 እና ማብ ይመ)።

**13፥35 የእኔ ደቀ መዛሙርት እንደሆናችሁ በዚህ ያውቃሉ፤** ፍቅር በግሪኩ፣ «አጋፔ» የተባለው የክርስቶስ ተከታዮች ልዩ መታወቂያ ሊሆን ይገባል (1ዮሐ 3፥23፤ 4፥7-21)። በመሠረቱ ይህ ዐይነቱ ፍቅር ሌሎች በጎ ነገር እንዲሆንላቸው ራሱን አሳልፎ የሚያሰጥና መሥዋዕትነትንም ያዘለ ፍቅር ነው (1ዮሐ 4፥9-10)። ከዚህም የተነሣ በአማኞች ሁሉ መካከል የሚኖረው የእርስ በርስ ግንኙነት በክርስቶስ የሆኑት ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ፍጹም በጎ ነገር እንዲሆንላቸው በሚመኝና ራስን እስከ መሠዋት በሚፈልግ ሐቀኛ መንገድ ሊገለጽ ይገባዋል። ክርስቲያኖች በመከራ ጊዜ አንዳቸው ለሌላው ወዳጆች ሊሆኑ፣ አንዳቸው የሌላውን ስሜት ወይም መልካም ዝና ለመጠበቅ ሊጠነቀቁና አንዳቸው የሌላውን በጎነት ለማሳደግ ሲሉ ራሳቸውን ሊክዱ ይገባል (ከ1ቆሮ 13፤ ከገላ 6፥2፤ ከ1ተሰ 4፥9፤ ከ2ተሰ 1፥3፤ ከ1ጴጥ 1፥22፤ ከ2ጴጥ 1፥7፤ ከ1ዮሐ 3፥23 ጋር ያነጻጽሩ)።

**14፥2 በአባቴ ቤት፤** ኢየሱስ ስፍራ ያዘጋጅልን ዘንድ ወደዚያ መሄድ ስላለበት (ማቴ 6፥9 ይመ፤ ከመዝ 33፥13-14 እና ከኢሳ 63፥15 ጋር ያነጻጽሩ) ይህ ሐረግ በግልጽ የሚናገረው ስለ መንግሥተ ሰማያት ነው። «በዚህ ቋሚ ከተማ የለንም» (ዕብ 13፥14) ሲል በምድር የሚኖሩ «የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ» (ኤፌ 2፥19) የሆኑት ከዚህ ሲሄዱ ብዙ መኖሪያ ያለው ቤት ከእግዚአብሔር ዘንድ ይጠብቃቸዋል ማለት ነው።

**14፥3 ዳግመኛ እመጣለሁ፤** (1) ክርስቶስ በእርግጥ ወደ ሰማይ እንደሄደ ሁሉ ከአባቱ ዘንድ ወደዚህ እንዲሁ ይመለሳል፤ ከእርሱም ጋር ይሆኑ ዘንድ ተከታዮቹን ለእነርሱ ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ ወደ ሰማይ ይወስዳቸዋል (ከዚህ ቀደም ያለውን ማብ ይመ፤ ከ17፥24 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ በመጀመሪያው የአዲስ ኪዳን ዘመን ለነበሩ ክርስቲያኖች ተስፋ ሲሆን፣ በአሁኑ ዘመን ለሚገኙ አማኞችም ሁሉ ተስፋቸው ይህ ነው። የጌታ መመለስ ማጠቃለያ ዓላማ አማኞች ከእርሱ ጋር ለዘላለም ይኖሩ ዘንድ ነው (በገጽ 1810 ላይ፣ «*አካላዊ ትንሣኤ*» እና በገጽ 1907 ላይ፣ «*ንጥቀት*» በሚሉ ርእሶች የቀረቡትን የትኵረት ጽሑፎች ይመ)።

(2) «እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ ልወስዳችሁ» የሚለው ሐረግ ሕያው የሆኑ አማኞች ሁሉ፣ «ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ በዚህም መሠረት ለዘላለም ከጌታ ጋር እንሆናለን» (1ተሰ 4፥17) የሚለው እውነታ ስለሚፈጸምበት ስለ ንጥቀት ይናገራል።

(3) ክርስቶስ ታማኞቹ ወደሆኑት መምጣቱ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እንዲያመልጡ ያስችላቸዋል (ሉቃ 21፥36 እና ማብ፤ 1ተሰ 1፥10 እና ማብ፤ 5፥9፤ ራእ 3፥10 እና ማብ ይመ)።

(4) ይህ ክብር የሞላበትና ዘላለማዊ የሆነ ኅብረት ከኢየሱስ ጋር ለዘላለም ለመኖር ለሚፈልጉ ተከታዮች ሁሉ የሚያጽናና አስተምህሮ ነው። (1ተሰ 4፥17-18)።

[6]ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "መንገዱ
እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤
በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ
የለም። [7]እኔን ብታውቁኝ ኖሮ አባቴንም
ባወቃችሁት ነበር።ª ከአሁን ጀምሮ ግን
ታውቁታላችሁ፤ አይታችሁታልም።"
[8]ፊልጶስም፣ "ጌታ ሆይ፤ አብን አሳየንና
ይበቃናል" አለው።
[9]ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "አንተ
ፊልጶስ! ይህን ያህል ጊዜ ከእናንተ ጋር ስኖር
አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤
እንዴትስ 'አብን አሳየን' ትላለህ? [10]እኔ
በአብ እንዳለሁ፣ አብም በእኔ እንዳለ አታ
ምንምን? የምነግራችሁ ቃል ከራሴ አይደ
ለም፤ ነገር ግን ሥራውን የሚሠራው በእኔ
የሚኖረው አብ ነው። [11]እኔ በአብ እንዳለሁ
አብም በእኔ እንዳለ ስነግራችሁ እመኑኝ፤
ሊያው ቢቀር ስለ ድንቅ ሥራዎቹ እንኳ
እመኑ። [12]እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚ
ያምን እኔ የማደርገውን ሥራ ይሠራል፤
እን ዲያውም እኔ ወደ አብ ስለምሄድ፣
ከእነዚህ ም የሚበልጥ ያደርጋል። [13]አብ
በወልድ እንዲከብር፣ በስሜ የምትለምኑትን
ሁሉ አደርገዋለሁ፤ [14]ማንኛውንም ነገር
በስሜ ብትለምኑኝ፣ እኔ አደርገዋለሁ።

ሐሥ 3፥16

## ስለ መንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ተስፋ

[15]"ብትወዱኝ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ።
[16]እኔ አብን እለምናለሁ፤ እርሱም ከእናንተ
ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣ
ችኋል፤
[17]እርሱም የእውነት መንፈስ ነው፤ ዓለም
ስለማያየውና ስለማያውቀው ሊቀበለው አይ
ችልም። እናንተ ግን፣ አብሮአችሁ ስለሚ

14፥6 ዮሐ1፥4:14፤ 6፥35፤ 10፥9፤ ሐሥ4፥12፤ ኤፌ2፥18፤ ዕብ10፥20 14፥7 ዮሐ1፥18፤ 1ዮሐ2፥23 14፥8 ዮሐ1፥43 14፥9 ኢሳ9፥6፤ ዮሐ1፥14፤ 12፥45፤ 2ቆሮ4፥4፤ ፊል2፥6፤ ቈላ1፥15፤ ዕብ1፥3 14፥10 ቍ11:20:24፤ ዮሐ10፥38፤ 17፥21 14፥11 ዮሐ5፥36፤ 10፥38 14፥12 ማቴ21፥21፤ ሉቃ10፥17 14፥13 ማቴ7፥7 14፥15 ቍ21:23፤ መዝ103፥18፤ ዮሐ15፥10፤ 1ዮሐ2፥3-5፤ 3፥22:24፤ 5፥3፤ 2ዮሐ1፥6፤ ራእ12፥17፤ 14፥12 14፥16 ቍ26፤ ዮሐ15፥26፤ 16፥7 14፥17 ዮሐ15፥26፤ 16፥13፤ 1ቆሮ2፥14፤ 1ዮሐ4፥6፤ 5፥6

ª14፥7 አንዳንድ የጥንት ቅጆች በርግጥ እኔን ብታውቁ አባቴንም ታውቃላችሁ ይላሉ

**14፥12 ከእነዚህም የሚበልጥ፤** የኢየሱስ ፍላጎት እርሱ ያደረገውን ተከታዮቹ ያደርጉ ዘንድ ነው። (1) "የሚበልጥ" የሚለው ቃል ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣትንና ታምራት ማድረግን ያጠቃልላል። ይህ በሐዋርያት ሥራ ትረካዎች (ሐሥ 2፥41:43፤ 4፥33፤ 5፥12) እንዲሁም ኢየሱስ በማር 16፥17-18 ባስተላለፈው ቃል ተገልጿል (በገጽ 1527 ላይ፣ *"አማኞች የሚከተሏቸው መንፈሳዊ ምልክቶች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። (2) ደቀ መዛሙርቱ የበለጡ ነገሮችን የሚያደርጉት ምክንያት ኢየሱስ ወደ አባቱ ሄዶ የመንፈስ ቅዱስን ኀይል በመላኩና (ቍ 16፤ 16፥7፤ ሐሥ 1፥8፤ 2፥4 ይመ) በስሙ ለተጸለየው ጸሎት መልስ መስጠቱ ነው (ቍ 14)። የደቀ መዛሙርት አገልግሎት የበለጠ የሚሆነው በመጠንና በስፋት ነው።

**14፥13 በስሜ የምትለምኑትን፤** በኢየሱስ ስም መጸለይ቎ ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ያካትታል፤ (1) ከእርሱ ማንነት፣ ባሕርይና ፈቃድ ጋር የሚጣጣም ጸሎት መጸለይ፤ (2) በእርሱና በሥልጣኑ በማመን እንዲሁ አብንና ወልድን ለማክበር በመፈለግ (ሐሥ 3፥16) መጸለይ። ስለሆነም፣ በኢየሱስ ስም መጸለይ ማለት ኢየሱስ ራሱ ቢጸልይ የሚጸልየው ጸሎት ዐይነትና መልስ የሚያስገኝ ጸሎት ማለት ነው። በተቀደሰ እምነትና እንደ እርሱ ፈቃድ ወደ አብ ወይም ወደ ኢየሱስ የሚደረግ ጸሎት ገደብ የሌለበትና ታምር የሚሠራ ነው (ማቴ 17፥20 እና ማብ፤ እንዲሁም በገጽ 528 ላይ፣ *"መልስ የሚያስገኝ ጸሎት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**14፥16 እኔ አብን እለምናለሁ፤** ለእርሱ እውነተኛ የጠበቀ ፍቅር ላላቸውና ቃሉንም በመጠበቅ ለሚተጉ ብቻ ኢየሱስ አጽናኙን እንዲልክላቸው አብን ይለምንላቸዋል። ኢየሱስ ቍ 15 ("ብትወዱኝ") ሲል፣ ቀጣይነት ባለው የአሁን አንቀጽ በመናገር እርሱን መውደድና ለእርሱ መታዘዝ ዘላቂነት ያለው አቋም መሆን እንደሚገባው አበክሮ አመልክቷል።

**14፥16 አጽናኝ፤** ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን፣ "ሌላው አጽናኝ" ብሎ ይጠራዋል። አጽናኝ የሚለው ቃል በግሪኩ "ፓራክሊቶስ" የሚል ሲሆን፣ የቃል በቃል ትርጓሜውም "ለመርዳት ከአንድ ሰው ጎን የሚቆም" ማለት ነው። ይህ ቃል አያሌ ትርጕም የያዘ ነው፤ ይኸውም አጽናኝ፣ አበረታች፣ አረጋጊ፣ ረዳት፣ አማካሪ፣ ጠበቃ፣ አማላጅ፣ ወገንና ወዳጅ ማለት ነው። "ሌላ" የሚለው የግሪኩ አቻው፣ "የዚያው ዐይነት ሆኖ ሌላ" የሆነው "አሎን" የሚለው የግሪክ ቃል ነው እንጂ ትርጓሜው "የዚያው ዐይነት ያልሆነ ሌላ" የሆነው የግሪክ ቃል "ሔቴሮስ" አይደለም። በሌላ አንጻር መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ ራሱ በምድር ሳለ የጀመረውን ያንኑ ሥራ ይቀጥላል ማለት ነው።

(1) መንፈስ ቅዱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የሚሆነው እንዲረዳቸውና እንዲያጠነክራቸው (ከማቴ 14፥30-31 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ሕይወታቸው የሚመራበትን እውነተኛ መንገድ እንዲያሳያቸው (ቍ 26)፤ በመከራ ጊዜ እንዲያጽናናቸው (ቍ 18)፣ በጸሎታቸውም ወቅት እንዲማልድላቸው (ሮሜ 8፥26-27 ይመ፤ ከሮሜ 8፥34 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ለእነርሱም መልካም የሆነው እንዲፈጸምላቸው የሚያማልድ ወዳጅ እንዲሆንና (ቍ 17) በእነርሱም ውስጥ ለዘላለም እንዲኖር ነው።

(2) "ፓራክሊቶስ" የሚለው የግሪኩ ቃል በ1ዮሐ 2፥1 ጌታ ኢየሱስን አስመልክቶ ተጠቅሶአል። ስለሆነም ኢየሱስ በሰማይ የእኛ ረዳትና አማላጅ ሲሆን (ከዕብ 7፥25 ጋር ያነጻጽሩ)፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በምድር በእኛ ውስጥ የሚኖር ረዳታችንና አማላጃችን ነው (ሮሜ 8፥9:26፤ 1ቆሮ 3፥16፤ 6፥19፤ 2ቆሮ 6፥16፤ 2ጢሞ 1፥14)።

**14፥17 የእውነት መንፈስ፤** መንፈስ ቅዱስ እውነት የሆነው የኢየሱስ መንፈስ ስለሆነ፣ "የእውነት መንፈስ" ተብሎ ይጠራል (15፥26፤ 16፥13 ይመ፤ ከ1ዮሐ 4፥6፤ 5፥6 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህም በመሆኑ ለእውነት ይመሰክራል (18፥37)፣ እውነቱን ብሩህ ያደርጋል፣ እውነት ያልሆነውን ያጋልጣል (16፥8)፣ ደግሞም አማኙን ወደ እውነት ሁሉ ይመራዋል (16፥13)። መንፈሳዊ ሳልሆነ አንድነት፣ ፍቅር ወይም ለሌላ ማንኛውም ምክንያት እውነትን የሚረግጡ በውስጣችን ይኖራል የሚሉትን የእውነትን መንፈስ ይክዳሉ። እውነትን የተወች ቤተ ክርስቲያን ጌታዋንም ትታለች ማለት ነው። ለእምነታቸው ግድየለሽ ለሆኑትና ለእውነት ያላቸው መስጠት ከፊል ለሆነ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ አጽናኝ አይሆንላቸውም። እርሱ የሚመጣው ጌታን በመንፈስና በእውነት ወደሚያመልኩት ብቻ ነው (4፥24)።

**14፥17 አብሮአችሁ ስለሚኖርና በውስጣችሁ**

ኖርና በውስጣችሁ ስለሚሆን° ታውቁታላ
ችሁ። [18]ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች
አልተዋችሁም፤ ወደ እናንተ እመጣለሁ።
[19]ከጥ ቂት ጊዜ በኋላ፣ ዓለም ከቶ አያየኝም፤
እና ንተ ግን ታዩኛላችሁ። እኔ ሕያው ስለ
ሆንሁ እናንተም ሕያዋን ትሆናላችሁ። [20]እኔ
በአባቴ እንዳለሁ፣ እናንተም በእኔ እንዳላ
ችሁ፣ እኔም ደግሞ በእናንተ እንዳለሁ በዚያ
ቀን ትረዳላችሁ። [21]የሚወደኝ ትእዛዜን ተቀ
ብሎ የሚጠብቅ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ
ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ፤ ራሴንም
እገ ልጥለታለሁ።"

[22]ከዚያም የአስቆሮቱ ያልሆነው ይሁዳ፣
"ጌታ ሆይ፣ ታዲያ፣ ለዓለም ሳይሆን
ራስህን ለእኛ የምትገልጠው እንዴት
ነው?" አለው።

[23]ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "የሚወደኝ
ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደ
ዋል፤ ወደ እርሱ እንመጣለን፤ ከእርሱም
ጋር እንኖራለን። [24]የማይወደኝ ቃሌን አይ
ሐሥ 10፥34-35 ጠብቅም። ይህ የምትሰሙት ቃል የላከኝ
የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም።

[25]"አሁን ከእናንተ ጋር እያለሁ ይህን
ሁሉ ነግሬአችኋለሁ፤ [26]አብ በስሜ የሚልከው
አጽናኝ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስ
ተምራችኋል፤ እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳ

14፥18 ቍ3:28፤ 1ነገ6፥13፤ ማቴ16፥27
14፥19 ዮሐ6፥57፤ 7፥33:34፤ 16፥16
14፥20 ቍ10:11፤ ዮሐ10፥38፤ 16፥23:26፤ 17፥21፤ ሮሜ8፥10
14፥21 ቍ15፤ ዘጸ7፥13፤ ዮሐ16፥27፤ 1ዮሐ2፥5
14፥22 ሉቃ6፥16፤ ሐሥ1፥13፤ 10፥41
14፥23 ቍ15፤ ሮሜ8፥10
14፥24 ቍ10፤ ዘዳ18፥18፤ ዮሐ5፥19፤ 7፥16፤ 8፥28፤ 12፥49:50
14፥26 ቍ16፤ ሐሥ2፥33፤ ዮሐ2፥22፤ 15፥26፤ 16፥7:13፤ 1ዮሐ2፥20:27

14፥27 ቍ1፤ ዘኍ6፥26፤ መዝ85፥8፤ ሚል2፥6፤ ሉቃ2፥14፤ 24፥36፤

ስባችኋል። [27]ሰላምን እተውላችኋለሁ፤ ሰላ
ሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም
እንደሚሰጣችሁ አይደለም። ልባችሁ አይ
ጨነቅ፤ አይፍራም።

[28]"'እሄዳለሁ፤ ተመልሼም ወደ እናንተ
እመጣለሁ' ማለቴን ሰምታችኋል፤ ብትወዱ
ኝስ አብ ከእኔ ስለሚበልጥ ወደ አብ በመ
ሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር፤ [29]የተናገርሁት ሲፈ
ጸም እንድታምኑ፣ ከመሆኑ በፊት አሁን ነግ
ሬአችኋለሁ። [30]የዚህ ዓለም ገዥ ስለሚመጣ
ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር ብዙ አልናገ
ርም። እርሱም በእኔ ላይ ሥልጣን የለውም፤
[31]ነገር ግን እኔ አብን እንደምወድ፣ አባቴ
ያዘዘኝንም እንደማደርግ ዓለም እንዲያውቅ
ነው። "ተነሡ፤ ከዚህ እንሂድ።"

## የወይን ግንድና ቅርንጫፎቹ

15 "እውነተኛው የወይን ተክል እኔ
ነኝ፤ አትክልተኛውም አባቴ ነው።

14፥27 ዮሐ16፥33፤ ፊል4፥7፤ ቈላ3፥15 14፥28 ቍ2-4:18፤ ማቴ16፥27፤ ዮሐ5፥18፤ 10፥29 14፥29 ዮሐ13፥19፤ 16፥4 14፥30 ዮሐ12፥31 14፥31 ዮሐ10፥18፤ 12፥49 15፥1 መዝ80፥8-11፤ ኢሳ5፥1-7፤ ዮሐ6፥35

°14፥17 *አንዳንድ የጥንት ቅጆች በውስጣችሁ ስላለ* ይላሉ

**ስለሚሆን፤** *መንፈስ ቅዱስ ከደቀ መዛሙርት ጋር ይኖራል፤ ወደፊት ደግሞ በእነርሱ ውስጥ እንደሚሆን ክርስቶስ ተስፋ ሰጣቸው። በአማኞች ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንደሚኖር የተሰጠው ተስፋ የተፈጸመው ከትንሣኤ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርት ላይ ከወረደ በኋላ ነው (ሐሥ 2)።*

**14፥18 ወደ እናንተ እመጣለሁ፤** *ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ትእዛዙን ለሚያከብሩ አማኞች ራሱን ይገልጻል፤ መንፈስ ቅዱስም ኢየሱስን በሚወዱት ዘንድ (ቍ 21) የክርስቶስ ህልዎት በእነርሱ ውስጥና ከእነርሱም ጋር እንደ ሆነ ያስገነዝባል። መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስን ቅርብነትና የፍቅሩን እውነተኝነት፣ በረከቱንና ርዳታውን እንድናውቅ ያደርገናል፤ ይህም ከመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚ ተግባሮች አንዱ ነው። እንግዲህ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ክርስቶስ ወደ እኛ መምጣቱ በፍቅር፣ በአምልኮና ራሳችንን በመስጠት ምላሽ እንድንሰጥ ሊያነሣሣን ይገባል።*

**14፥21 ትእዛዜን ተቀብሎ፤** *የዘላለም ሕይወት ላላቸው የክርስቶስን ሕግ መታዘዝ ግዴታቸው ነው (3፥36፤ 14፥21:23፤ 15፥8-10:13-14፤ ሉቃ 6፥46-49፤ ያዕ 1፥22፤ 2ጴጥ 1፥5-11፤ 1ዮሐ 2፥3-6)። (1) ለክርስቶስ ያለን ታዛዥነት ፍጹም ሊሆን ባይችልም መታዘዛችን በቅን ልብ ሊሆን ይገባል። ይህ መታዘዛችን ለእርሱ ካለን ፍቅር (ቍ 15:21:23-24፤ ማቴ 7፥21 እና ማብ ይመ) የሚመነጭ ሲሆን፣ ለድነት የሚያበቃው እምነት ዋና ገጽታ ነው። ለክርስቶስ ፍቅር ሳይኖረን ትእዛዞቹን ለመፈጸም መሞከር በሕግ መታሰር ይሆናል። (2) ክርስቶስ እርሱን ለሚወድና ትእዛዙንም ያለማዛነፍ ለመታዘዝ ጥረት ለሚያደርግ ልዩ ፍቅሩን፣ ጸጋውንና ጥልቅ ህልዎቱን በሕይወቱ እውን እንደሚያደርግለት (ከቍ 23 ጋር ያነጻጽሩ) ቃል ኪዳን ገብቶአል።*

**14፥23 ከእርሱም ጋር እንኖራለን፤** *ኢየሱስን በእውነት የሚወዱና ለቃሉም የሚታዘዙ የእግዚአብሔር አብንና የወልድን ህልዎትና ፍቅር ይለማመዳሉ። አብና ወልድ ወደ አማኙ የሚመጡት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው (ቍ 18 እና ማብ ይመ)። የእግዚአብሔር ፍቅር እኛ ለኢየሱስ ባለን ፍቅርና ለቃሉ በምናሳየው ታማኝነት ላይ የተደገፈ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል።*

**14፥24 የማይወደኝ፤** *ለክርስቶስ ትምህርት የማይታዘዙ ለእርሱ እውነተኛ ፍቅር የላቸውም፤ ለክርስቶስ እውነተኛ ፍቅር ከሌለ ደግሞ ወደ ድነት የሚያደርስ እምነት የለም ማለት ነው (1ዮሐ 2፥3-4)። ሰዎች ለክርስቶስ ያላቸውን ፍቅር ትተው በምግባረ ብልሹነት፣ የእግዚአብሔርን ስም በማቃለል፣ በጭካኔ፣ በነፍስ ግድያና በስካር ወ.ዘ.ተ እየኖሩ ሳለ ድነታቸውን እንደ ያዙ ይቈያሉ ማለት እነዚህን ቃሎች ኢየሱስ ስለ ፍቅር፣ ስለ መታዘዝ፣ መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ስለማደሩ የሰጠውን ቃል እንደ መቃረን ይቈጠራል።*

**14፥26 መንፈስ ቅዱስ፤** *በዚህ ስፍራ አጽናኝ የተባለው፣ «መንፈስ ቅዱስ» እንደ ሆነ ተገልጾአል። ለአዲስ ኪዳን ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስን በሚመለከት እጅግ አስፈላጊው ነገር ኀይሉን (ሐሥ 1፥8) ብቻ ሳይሆን «ቅዱስ» መሆኑንም መረዳት ነው። ዋናው ነገር የእርሱ ቅዱስ ባሕርይ በአማኞች ሕይወት ሠርጾ ባሕርያቸውን ቅዱስ ማድረጉ ነው (ከሮሜ 1፥4፤ ከገላ 5፥22-26 ጋር ያነጻጽሩ)።*

**15፥1 እውነተኛው የወይን ተክል እኔ ነኝ፤** *በዚህ ምሳሌ ወይም ተምሳሌት ኢየሱስ ራሱን እንደ «እውነተኛ የወይን ተክል» የእርሱ ደቀ መዛሙርት የሆኑትን ደግሞ «ቅርንጫፎች» አድርጎ ይገልጻል። የሕይወታቸው ምንጭ ከሆነው ከእርሱ ጋር ተጣብቀው ሲቆዩ ፍሬ ያፈራሉ። ቅርንጫፎቹ ፍሬ ያፈሩ ዘንድ (ቍ 2፥8) የሚንከባከባቸው አትክልተኛ እግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር ሁላችንም ፍሬ እንድናፈራ ይጠብቅብናል (ቀጥሎ ያለውን ማብ ይመ)።*

[2]እርሱም በእኔ ያለውን፣ የማያፈራውን ቅር
ንጫፍ ሁሉ ቈርጦ ይጥለዋል፤ ፍሬ የሚያ
ፈራውን ቅርንጫፍ ሁሉ ግን የበለጠ እንዲ
ያፈራ ይገርዘዋል።ª [3]ከነገርኋችሁ ቃል
የተነሣ እናንተ አሁን ንጹሓን ናችሁ። [4]በእኔ
ኑሩ፤ እኔም በእናንተ እኖራለሁ። ቅርንጫፍ
በወይኑ ግንድ ካልሆነ በቀር ብቻውን ፍሬ
ሊያፈራ አይችል ልም፤ እናንተም በእኔ
ካልኖራችሁ ፍሬ ልታፈሩ አትችሉም።
[5]"እኔ የወይን ተክል ነኝ፤ እናንተም
ቅርንጫፎች ናችሁ።ማንም በእኔ ቢኖር እኔም
በእርሱ ብኖር፣ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል፤ ያለ
እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና። [6]በእኔ
የማይኖር ተጥሎ እንደሚደርቅ ቅርንጫፍ
ነው፤ እንዲህ ያሉት ቅርንጫፎች ተለ
ቅመው ወደ እሳት ይጣላሉ፤ ይቃጠላሉም።
[7]በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ
ቢኖሩ፣ የምትፈልጉትን ማንኛውንም
ነገር ለምኑ፤ ይሰጣችኋልም። [8]ብዙ ፍሬ
በማፍራት ደቀ መዛሙርቴ መሆናችሁን
ብትገልጡ፣ በዚህ አባቴ ይከብራል። ሐሥ 13:52
[9]"አብ እንደ ወደደኝ ሁሉ እኔም

15፥2 ቍ6፤ መዝ92፥14፤ ማቴ3፥8፡10፤ 7፥20፤ ገላ5፥22፤ ኤፌ5፥9፤ ፊል1፥11
15፥3 ዮሐ13፥10፤ 17፥17፤ ኤፌ5፥26
15፥4 ዮሐ6፥56
15፥5 ቍ16
15፥6 ቍ2፤ ሕዝ15፥4፤ ማቴ3፥10
15፥7 ቍ4፤ ማቴ7፥7፤ ዮሐ6፥56 15፥8 ማቴ9፥8፤ ዮሐ8፥31
15፥9 ዮሐ17፥23፡24፡26

*ª15፥2 ይገርዘዋል የሚለው የግሪኩ ቃል ያጠራዋል የሚል ትርጉም አለው።*

**15፥2 ቅርንጫፍ ሁሉ፤** ኢየሱስ ስለ ሁለት ዐይነት ቅርንጫፎች ማለትም ፍሬ ስለሚያፈሩትና ፍሬ ስለማያፈሩት ቅርንጫፎች ይናገራል፤ (1) ፍሬ ማፍራት ያቆሙት ቅርንጫፎች፣ በክርስቶስ ላይ ከጸና እምነትና ለእርሱ ከሚኖር ፍቅር ሊገኝ የሚችለው ሕይወት በውስጣቸው የሌላቸው ናቸው። አብ እንደነዚህ ዐይነቶቹን "ቅርንጫፎች" ይቈርጣቸዋል፤ ይህም ከክርስቶስ ጋር ካላቸው ሕያው ኅብረት ይነጥላቸዋል (ከማቴ 3፥10 ጋር ያነጻጽሩ) ማለት ነው። በክርስቶስ ጽንቶ መኖር ሲተው የዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል፤ ከፊቱም አውጥቶ ይጥላቸዋል (ቍ 6)። (2) ፍሬ የሚያፈሩት ቅርንጫፎች በክርስቶስ ላይ ካላቸው የጸና እምነትና ለእርሱ ካላቸው ፍቅር የተነሣ በውስጣቸው ሕይወት ያላቸው ናቸው (በገጽ 1853 ላይ፣ *"የኀጢአተኛ ተፈጥሮ ሥራዎችና የመንፈስ ፍሬ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። አብ እነዚህን ቅርንጫፎች አብዝተው ያፈሩ ዘንድ ይገርዛቸዋል። ይህም ክርስቶስ ወደ እነርሱ የሚፈሰውን የሚያረክሰውን የሕይወት ምንጭ የሚያስተጓጉለውን ወይም የሚገታውን ማንኛውንም ነገር ከሕይወታቸው ያስወግድላቸዋል ማለት ነው። ፍሬውም በሕይወትና በምስክርነት (ማቴ 3፥8፤ 7፥20፤ ሮሜ 6፥22፤ ኤፌ 5፥9፤ ፊል 1፥11 ይመ) እግዚአብሔርን የሚያስከብረው ዐይነተኛ የክርስቲያን ባሕርይ ነው።

**15፥4 በእኔ ኑሩ፤** አንድ ሰው በክርስቶስ ካመነና ይቅር ከተባለ በኋላ የዘላለምን ሕይወት ያገኛል፤ በክርስቶስ ለመጽናትም የሚያስፈልገውን ኀይል ይቀበላል። ይህ ኀይል ከተሰጠው፣ አማኙ በቀጣይነት ድኅነቱንና የማንጸባርቅን በክርስቶስ የመጽናትን ኀላፊነት ሊቀበል ይገባዋል። "ሜኖ" የሚለው የግሪኩ ቃል መቆየት፣ መቀጠል፣ መጽናት ወይም መኖር ማለት ነው። ቅርንጫፉ በሕይወት የሚቆየው የወይን ተክሉ ሕይወት በውስጡ እስከተላለፈ ብቻ እንደ ሆነ ሁሉ አማኞችም እንደዚሁ በክርስቶስ በመጽናት ብቻ በውስጣቸው ከሚተላለፈው የክርስቶስ ሕይወት የተነሣ የክርስቶስ ሕይወት ይኖራቸዋል። በክርስቶስ የምንጸናባቸው መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፤ (1) የእግዚአብሔርን ቃል ዘወትር በልባችንና በአእምሮአችን ማሳደር እንዲሁም የተግባራችን መሪ እንዲሆን ማድረግ (ቍ 7)፤ (2) ከእርሱ ዘንድ በረከትን ለማግኘት (ቍ 7) ከክርስቶስ ጋር የሚያቋርጥ ኅብረት የማድረግን ልምድ ጠብቆ መኖር፤ (3) ትእዛዛቱን መጠበቅ፦ በፍቅሩ መጽናት (ቍ 10) እንዲሁም እርስ በርስ መዋደድ (ቍ 12፡17)፤ (4) ሕይወታችንን በቃሉ ማንጻት፣ ከኀጢአት ሁሉ መራቅ፣ ለመንፈስ ቅዱስ ምሪት ራስን አሳልፎ መስጠት (ቍ 3፤ 17፥17፤ ሮሜ 8፥14፤ ገላ 5፥16-25፤ ኤፌ 5፥26፤ 1ጴጥ 1፥22)።

**15፥6 ተጥሎ እንደሚደርቅ ቅርንጫፍ፤** ስለ ወይን ተክሉና ስለ ቅርንጫፎቹ በተነገረው ምሳሌ "አንድ ጊዜ ከወይን ተክሉ ጋር ከተጣበቅህ ምን ጊዜም እዚያው ትሆናለህ" የሚለውን አንድምታ ክርስቶስ እንደማይቀበለው በማያወላውል ሁኔታ ግልጽ ያደርጋል። ይልቁንም ኢየሱስ በዚህ ምሳሌ ለደቀ መዛሙርቱ ጠንከር ያለ ሆኖም በፍቅር የተሞላ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአቸዋል። ይኸውም እውነተኛ ክርስቲያኖች እምነታቸውን ቢተዉ፣ በኢየሱስ ላይ ጀርባቸውን ቢያዞሩና በክርስቶስ መጽናት ባይችሉ የኋላ ኋላ በገሃነም ዘላለማዊ እሳት ውስጥ መጣል እንደሚያጋጥማቸው በማስገንዘብ ነው።

(1) በክርስቶስና በአማኙ መካከል ያለው ድኅነትን የሚያስገኘው ግንኙነት የሚገነዘበትን መሠረታዊ መርሕ በዚህ ስፍራ እናገኛለን። ይህም ግንኙነት እኛ ቀደም ሲል ባደረግነው የድኅነት ውሳኔና ባለፈው በኖርነው መልካም የክርስትና ሕይወት ላይ ብቻ የተመሠረተ አይደለም፤ ይልቁንም ክርስቶስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ በመኖር መለኮታዊ ሕይወቱን ባካፈለው መጠን እያሳየ የሚጎለብት ግንኙነት ነው። (17፥3 እና ማብ ይመ፤ ቈላ 3፥4፤ 1ዮሐ 5፥11-13)።

(2) በዚህ ምሳሌ ሦስት መሠረታዊ እውነቶችን ያዘለ ትምህርት ተሰጥቶአል፤ (ሀ) የደቀ መዛሙርቱ ኀላፊነት በክርስቶስ ላይ መጽናት ነበር (ቍ 4 እና ማብ ይመ)። ይህም ሕይወታችን ሲለወጥ እግዚአብሔር ከሁሉ ቀዳሚ አድርጎ ለሰጠን መለኮታዊ ሕይወትና ኀይል የምንሰጠው ምላሽ ነው፤ (ለ) በክርስቶስ መጽናት የሚያስገኘው ውጤት ክርስቶስ ለዘለቄታው በአማኝ ውስጥ መኖሩ (ቍ 4)፣ የደቀ መዝሙሩ ፍሬያማነት (ቍ 5)፣ ውጤት ያለው ጸሎት መጸለይ መቻልና (ቍ 7) በሐሤት በተሞላ ሕይወት መኖር ነው (ቍ 11)፤ (ሐ) በክርስቶስ ያለመጽናት ውጤቶች ፍሬ ቢስነት (ቍ 4-5)፣ ከክርስቶስ መወገድና ጥፋት (ቍ 2፡6) ናቸው።

**15፥7 የምትፈልጉትን ማንኛውንም ነገር ለምኑ፤** የጸሎት መልስ የማግኘት ምስጢሩ በክርስቶስ መጽናት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በማሰላሰልና በማጥናት ወደ ክርስቶስ ተጠግተን በኖርን መጠን ጸሎታችንም ከክርስቶስ ማንነትና ከቃሉ ጋር የበለጠ እየተስማማና ውጤታማም እየሆነ ይመጣል (14፥13 እና ማብ፤ 15፥4 እና ማብ፤ መዝ 66፥18 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 528 ላይ፣ *"መልስ የሚያስገኝ ጸሎት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

**15፥9 በፍቅሬ ኑሩ፤** አማኙ በክርስቶስ ፍቅር ውስጥ ሊኖር ይገባዋል። ይህም የሚሆነው ትእዛዙን በመፈጸም (ቍ 10) እንደ ሆነ ኢየሱስ አሁንም ይገልጻል።

ወደድኳችሁ፤ በፍቅሬ ኑሩ። 10እኔ የአባቴን
ትእዛዝ ጠብቄ በፍቅሩ እንደምኖር፣
እናንተም ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ
ትኖራላችሁ። 11ደስታዬ በእናንተ
እንዲሆንና ደስታችሁም ሙሉ እንዲሆን
ይህን ነግሬአችኋለሁ። 12ትእዛዜ ይህች
ናት፤ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እናንተም
እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። 13ስለ ወዳጆቹ
ሕይወቱን አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ
ፍቅር ማንም የለውም፤ 14የማዛችሁን
ብትፈጽሙ ወዳጆቼ ናችሁ። 15ከእንግዲህ
አገልጋዮች አልላችሁም፤ አገልጋይ ጌታው
የሚሠራውን አያውቅምና፤ ነገር ግን
ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ስለ ገለጽሁላችሁ
ወዳጆች ብያችኋለሁ። 16እኔ መረጥኋችሁ
እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤
እንድትሄዱና ፍሬ እንድታፈሩ
ፍሬያችሁም እንዲኖር ሾምኋችሁ።
ስለዚህም አብ በስሜ የምትለምኑትን
ሁሉ ይሰጣችኋል። 17እርስ በርሳችሁ
እንድትዋደዱ፣ ትእዛዜ ይህቺ ናት።

## ዓለም ደቀ መዛሙርትን መጥላቱ

18"ዓለም ቢጠላችሁ፣ ከእናንተ በፊት
እኔን እንደ ጠላኝ ዕወቁ። 19ከዓለም ብትሆኑ
ኖሮ፣ ዓለም የራሱ እንደ ሆኑት አድርጎ
በወደዳችሁ ነበር፤ ከዓለም ለይቼ ስለ
መረጥኋችሁ የዓለም አይደላችሁም፤ ዓለም
የሚጠላችሁም ስለዚሁ ነው። 20'አገልጋይ
ከጌታው አይበልጥም' ብዬ የነገርኋችሁን
ቃል አስታውሱ። እኔን አሳደውኝ ከሆነ፣
ዮሐ እናንተንም ያሳድዱአችኋል፤ ቃሌን ጠብቀው
16፡33 ከሆነም ቃላችሁን ይጠብቃሉ። 21የላከኝን
ስለማያውቁ፣ በስሜ ምክንያት ይህን
ያደርጉባችኋል። 22መጥቼ ባልነግራቸው
ኖሮ ኀጢአት ባልሆነባቸው ነበር፤ አሁን
ግን ለኀጢአታቸው የሚሰጡት ምክንያት
የላቸውም። 23እኔን የሚጠላ፣ አባቴንም
ይጠላል። 24ሌላ ሰው ያላደረገውን
በመካከላቸው ባላደርግ ኖሮ፣ ኀጢአት
ባልሆነባቸው ነበር፤ አሁን ግን እነዚህን
ታምራት አይተዋል፤ ሆኖም እኔንም
አባቴንም ጠልተዋል። 25ይህም፣ 'ያለ
ምክንያት ጠሉኝ' ተብሎ በሕጋቸው
የተጻፈው ቃል እንዲፈጸም ነው።
26"እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ፣ ከአብ
የሚወጣው አጽናኝ የእውነት መንፈስ
በመጣ ጊዜ፣ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል።
27እናንተም ደግሞ፣ ከመጀመሪያው ከእኔ
ጋር ስለ ነበራችሁ፣ ትመሰክራላችሁ።

16 "ይህን ሁሉ የነገርኋችሁ
እንዳትሰናከሉ ነው። 2ከምኵራብ
ያስወጧችኋል፤ እንዲያውም
የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንዳገለገለ
የሚቈጥርበት ጊዜ ይመጣል። 3ይህን
ሁሉ የሚያደርጉባችሁ፣ አብን ወይም
እኔን ስላላወቁ ነው። 4አስቀድሜ ይህን
የነገርኋችሁ ጊዜው ሲደርስ እንድታስታውሱ
ነው፤ ከእናንተ ጋር ስለ ነበርሁ፣ ይህን
ከመጀመሪያው አልነገርኋችሁም።

## የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

5"እንግዲህ ወደ ላከኝ እሄዳለሁ፤
ይሁን እንጂ ከእናንተ፣ 'የምትሄደው የት
ነው?' ብሎ የሚጠይቀኝ የለም። 6ይህን
በመናገሬም ልባ ችሁ በሐዘን ተሞልቶአል፤

15፥10 ዮሐ14፡15
15፥11 ዮሐ3፡29
15፥12 ቍ17፤ ዮሐ13፥34
15፥13 ዘፍ44፥33፤ ዮሐ10፡11፤ ሮሜ5፡7፡8
15፥14 ኢዮ16፥20፤ ምሳ18፥24፤ ማቴ12፥50፤ ሉቃ12፡4
15፥15 ዮሐ8፥26
15፥16 ቍ5፡19፤ ማቴ7፥7፤ ዮሐ13፥18
15፥17 ቍ12
15፥18 ኢሳ66፥5፤ ዮሐ7፡7፤ 1ዮሐ3፥13
15፥19 ቍ16፤ ዮሐ17፥14
15፥20 ዮሐ13፥16፤ 2ጢሞ3፥12
15፥21 ኢሳ66፥5፤ ማቴ5፡10፡11፤ 10፥22፤ ሉቃ6፥22፤ ዮሐ16፡3፤ ሐሥ5፥41፤ 1ጴጥ4፥14፤ ራእ2፡3
15፥22 ሕዝ2፥5፤ 3፥7፤ ዮሐ9፥41፤ ሮሜ1፥20፤ 2፥1
15፥24 ዮሐ5፥36፤ 9፥41
15፥25 መዝ35፥19፤ 69፡4፤ 109፡3፤ ዮሐ10፥34
15፥26 ዮሐ14፡16 ፡17፡26፤ 16፥7፤ 1ዮሐ5፡7
15፥27 ሉቃ1፥2፤ 24፥48፤ ዮሐ21፥24፤ 1ዮሐ1፥2፤ 4፥14
16፥1 ማቴ11፥6፤ ዮሐ15፥18-27
16፥2 ዮሐ9፥22፤ 12፥42፤ ኢሳ66፥5፤ ሐሥ26፥9፡10፤ ራእ6፡9
16፥3 ዮሐ15፥21፤ 17፥25፤ 1ዮሐ3፥1
16፥4 ዮሐ15፥27፤ 13፥19፤ 14፥29
16፥5 ቍ10፡17፡28፤ ዮሐ7፥33፤ 13፥36፤ 14፥5
16፥6 ቍ22

**15፥16 እንድትሄዱና ፍሬ እንድታፈሩ፤** ክርስቲያኖች ሁሉ፣ «ከዓለም የተመረጡት» (ቍ 19) «ፍሬ እንዲያፈሩ» ነው (ቍ 2፡4-5፡8)። ይህ ፍሬ ማፍራት የሚያመለክተው (1) በገላትያ 5፥22-23 ላይ የመንፈስ ፍሬዎች በመባል ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ ገርነት፣ ራስን መግዛት የመሳሰሉት መንፈሳዊ ጸጋዎችንና (ከኤፌ 5፥9፤ ቈላ 1፥6፤ ከዕብ 12፡11፤ ከያዕ 3፥18 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (2) ሌሎች ሰዎችን ወደ ክርስቶስ በማምጣት የሚከናወነውን ሥራ ነው (4፥36፤ 12፥24)።

**15፥20 እናንተንም ያሳድዷችኋል፤** የክርስቶስ ተከታዮች በዚህ ዓለም በሚኖሩበት ጊዜ ስለ ስሙ ይጠላሉ፤ ይሰደዳሉ፤ ደግሞም ይገፋሉ። በታሪክ ዘመናት ሁሉ ዓለም የክርስቶስና የሕዝቡ ዋና ተቃዋሚ ነች። (1) እውነተኛ አማኞች፣ ሐሰተኛ የሃይማኖት ድርጅቶችንና እውነተኛ ያልሆኑ ቤተ ክርስቲያኖችን ጨምሮ ዓለም ምንጊዜም የእግዚአብሔርና የእርሱም መንግሥት መርሖችን የምትቃወም እንደ ሆነች ሊረዱ ይገባቸዋል። ስለሆነም፣ ዓለም የታማኝ ክርስቲያኖች ጠላትና አሳዳጅ በመሆን እስከ መጨረሻው ትጸናለች (ያዕ 4፥4፤ ማቴ 5፥10 እና ማብ ይመ)። (2) አማኞች በዓለም እጅ መከራን የሚቀበሉት ከዓለም ጋር መሠረታዊ ልዩነት ስላላቸው ነው፤ አማኞች፣ «ከዓለም ወጥተዋል» (ቍ 19) «ከዓለምም አይደሉም»። ታማኝ የሆኑት ክርስቲያኖች ከፍተኛ ግምት የሚሰጡት ጉዳይ ቀምነገራቸው፣ መመዘኛቸውና መመሪያቸው ብልሹ ከሆነው የኅብረተሰባቸው የዐመፅ አሠራር ጋር ይቃረናል። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ካልሆነው የዓለም መመዘኛ ጋር መስማማትን አይፈቅዱም፤ ይልቁንም ልባቸውን በምድር ባለው ላይ ሳይሆን በሰማይ ባለው ላይ አድርገዋል (ቈላ 3፥2)።

**16፥2 ከምኵራብ ያስወጡአችኋል፤** ኢየሱስ እዚህ ላይ የተናገረው ከማያምኑ ሰዎች ስለሚሰነዘረው ስደት ሳይሆን ከሃይማኖት መሪዎችና ከጉባኤዎች ስለሚደርሰው ተቃውሞና ጠላትነት ነበር። ቀደም ሲል ዓለም አማኞችን እንደምትጠላ ሲጠቀስ (15፥18-19)፣ እነዚህን የሃይማኖት ሰዎችንም ያጠቃልላል። (1) የኢየሱስን ትምህርትና ለሐዋርያት የሰጠውን ራእይ አጥብቀው የማይዙ ወይም ከተበላሸው ኅብረተሰብ አሠራር በመለየት መጽናት የማይፈልጉ አማኞች ወይም አብያተ ክርስቲያናት ነን የሚሉ ሁሉ ከዓለም ናቸው (ከ1ዮሐ 4፥5-6 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) እነዚህ አማኝ ተብዬዎች መስፈርታቸው ከእውነተኛው የአዲስ ኪዳን ወንጌል ፍጹም የተለየ በመሆኑ እውነተኛ የክርስቶስ ተከታዮችን ሲያሳድዱ ወይም ሲገድሉ እግዚአብሔርን እንዳገለገሉ ይቈጥሩታል።

7ነገር ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፤ መሄዴ
ይበጃችኋል። እኔ ካልሄድሁ አጽናኙ ወደ
እናንተ አይመጣም፤ ከሄድሁ ግን እርሱን
ወደ እናንተ እልከዋለሁ፤ 8በሚመጣበትም
ጊዜ ዓለምን ስለ ኀጢአት*፣ ስለ ጽድቅና
ስለ ፍርድ ይወቅሳል። 9ስለ ኀጢአት
ሲባል፣ ሰዎች በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ 10ስለ
ጽድቅ፣ ወደ አብ ስለምሄድና ከእንግዲህ
ስለማታዩኝ ነው፤ 11ስለ ፍርድም፣ የዚህ
ዓለም ገዥ ስለ ተፈረደበት ነው።
12"ብዙ የምነግራችሁ ነበረኝ፤ አሁን
ግን ልትሸከሙት አትችሉም። 13የእውነት
መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ
ይመራችኋል። እርሱ ከራሱ አይናገርም፤
የሚሰማውን ብቻ ይናገራል፤ እንዲሁም
ወደ ፊት ስለሚሆነው ይነግራችኋል፤ 14የእኔ

16፥7 ዮሐ7፥39፤ 14፥16፡26፤ 15፥26
16፥9 ዮሐ15፥22
16፥10 ቁ5፤ ሐሥ3፥14፤ 7፥52፤ ሮሜ1፥17፤ 3፥21፡22፤ 1ጴጥ3፥18
16፥11 ዮሐ12፥31
16፥12 ማር4፥33፤ 1ቆሮ3፥2 16፥13 መዝ25፥5፤ ዮሐ14፥17፡26

*16፥8 ወይም የዓለምን ኀጢአት ይገልጣል

**16፥7 ከሄድሁ ግን እርሱን ወደ እናንተ እልካለሁ፤** በበዓለ ኀምሳ ቀን የሚፈሰው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት እውን የሚሆነው ክርስቶስ ከሄደ በኋላ ብቻ ነው (ከሐሥ 2፥33 ጋር ያነጻጽሩ)፡ በበዓለ ኀምሳ ዕለት የተከሠተው ፍሰት የመንፈስ ቅዱስን ዘመን መግባት አበሠረ።

**16፥8 ዓለምን ... ይወቅሳል፤** መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ኀምሳ ዕለት ሲመጣ (ሐሥ 2፥4፡ ቀደም ያለውን ማብ ይመ) በወንጌል ዕወጃ ውስጥ ሀብይ ተግባሩ ሰዎችን ስለ ኀጢአ ታቸው መውቀስ ነው። መውቀስ የሚለው ቃል (በግሪኩ "ኤሌንኮ") ሲሆን፣ ትርጕሙም ማጋለጥ፣ ስሕተትን ማስረዳትና ማሳመን ማለት ነው።

(1) የመንፈስ ቅዱስ የመውቀስ አገልግሎት በሦስት አቅጣጫ ይከናወናል፤ (ሀ) ኀጢአትን ማጋለጥ፡ በደለኛነታችን እንዲሰማንና ይቅርታንም ማግኘት እንደሚያስፈልገን ማስተዋልን በውስጣችን ይቀሰቅስ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ኀጢአትንና አለማመንን ያጋልጣል። በደለኛው በተሳሳተ መንገዱ የሚጸና ከሆነ፣ ሊከተል ስለሚችለው አስፈሪ ውጤት የመንፈስ ቅዱስ ወቀሳ በግልጽ ያስገነዝበዋል። ከኀጢአት ወቀሳ በኋላ ምርጫው ውሳኔ ላይ መድረስ ነው። አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ ዐይነቱ ሁኔታ ወደ እውነተኛ ንስሐና ኢየሱስን ጌታና መድኀኒት አድርጎ ለመከተል ወደ መወሰን ያመራል (ሐሥ 2፥37-38)። (ለ) ስለ ጽድቅ ማሳመን፤ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ ጻድቅ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ከሙታን ተለይቶ የተነሣ፣ ለተቀበለው መከራ ደግሞ ብድራትን ተቀብሎ አሁን የሁሉም ጌታ ሆኖ በዙፋን ላይ ያለ መሆኑን ለሰዎች ያስገነዝባል። እግዚአብሔር በክርስቶስ የገለጠውን የጽድቁን ልክ እንዲረዱ ያደርጋቸዋል፣ ኀጢአት ምን እንደ ሆነ ያሳያቸዋል፤ ዓለምንም እንዲያሸንፉ ኀይል ይሰጣቸዋል (ሐሥ 3፥12-16፤ 7፥51-60፤ 17፥31፤ 1ጴጥ 3፥18)። (ሐ) ስለ ፍርድ፡ በመስቀል ላይ ሰይጣን ድል እንደተነሣ (12፥31፤ 16፥11)፣ እግዚአብሔር በአሁኑ ዓለም ላይ ፍርድን እንደሚተላለፈ (ሮሜ 1፥18-32) ደግሞም ሰው ሁሉ ወደፊት ሊደርስበት ስላለው ፍርድ መንፈስ ቅዱስ በአጽንዖት ያሳውቃል (ማቴ 16፥27፤ የሐዋ 17፥31፤ 24፥25፤ ሮሜ 14፥10፤ 1ቆሮ 6፥2፤ 2ቆሮ 5፥10፤ ይሁ 1፥14)።

(2) ሰዎችን ስለ ኀጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ በመውቀስ የእግዚአብሔር መንፈስ የሚሠራው ሥራ በመንፈስ ቅዱስ በተጠመቁና በእርግጥ በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ አማኞች ሁሉ ውስጥ ይገለጻል። ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ (ሉቃ 4፥1) ዓለም፡ "አድራጎቱ ክፉ መሆኑን" በመመስከር (7፥7፤ 15፥18 ይመ) ሰዎች ንስሐ ይገቡ ዘንድ ጥሪ አቅርቦላቸዋል (ማቴ 4፥17)። መጥምቁ ዮሐንስ ከመወለዱ ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት (የሉቃ 1፥15 ማብ ይመ) የአይሁድን ሕዝብ ኀጢአት አጋለጠ፡ መንገዳቸውንም እንዲለውጡ አዘዛቸው (ማቴ 11፥7 እና ማብ ይመ፤ ሉቃ 3፥1-20)። ጴጥሮስ፣ "በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ" (ሐሥ 2፥4) ሦስት ሺህ ሰዎች ስለ ኀጢአት እንዲወቀሱ አደረገ፤ ንስሐ እንዲገቡና የኀጢአትንም ይቅርታ እንዲቀበሉ ጥሪ አደረገላቸው (ሐሥ 2፥37-41)።

(3) እንግዲህ ማንኛውም ሰባኪ ወይም ቤተ ክርስቲያን ኀጢአትን በይፋ የማያጋልጥ፣ ወደ ንስሐና ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽድቅ ሰዎችን የማይጠራ ከሆነ፣ በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ አይደለም። በአንድ ጉባኤ መካከል የእግዚአብሔር ሕልውና መኖሩ የሚረጋገጠው የማያምኑ ሰዎች ኀጢአት በመጋለጡ (ማለትም፣ በልቦናቸው የተሰወረው ምስጢር ይፋ በመሆኑ) ይህንንም ተከትሎ ስለ ኀጢአት በመወቀሳቸውና ድኅነትን በመቀበላቸው መሆኑን 1ቆሮ 14፥24-25 በግልጽ ይናገራል።

**16፥13 ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤** የመንፈስ ቅዱስ የመውቀስ ሥራ የሚያተኩረው ባልዳኑት ላይ ብቻ ሳይሆን (ቁ 7-8) ያስተምራቸው፣ ያስተካክላቸውና ወደ እውነት ይመራቸው ዘንድ በአማኞችና በቤተ ክርስቲያንም ላይ ጭምር ነው (ማቴ 18፥15፤ 1ጢሞ 5፥20፤ ራእ 3፥19)።

(1) መንፈስ ቅዱስ ስለ ኀጢአት፡ የክርስቶስን ጽድቅና በክፉው ላይ ፍርድ ስለ መወሰኑ ለአማኞች የሚናገረው (ሀ) ክርስቶስን እንዲመስሉና ከእርሱ የጽድቅ መመዘኛ ጋር የሚመጥን ጽድቅ ይኖራቸው ዘንድ (ከ2ቆሮ 3፥18 ጋር ያነጻጽሩ)፣ (ለ) ወደ እውነት ሁሉ ይመራቸው ዘንድና (ሐ) ክርስቶስን ያከብሩት ዘንድ ነው (ቁ 14)። ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ የሚሠራው የክርስቶስን ቅዱስ ሕይወት በሕይወታቸው ለመሳል ነው።

(2) በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ አማኞች የመንፈስ ቅዱስን አመራርና ስለ ኀጢአት የመውቀስ ሥራውን የሚቃወሙ ከሆነና "ክፉ የሆነውን የሥጋ ሥራ በመንፈስ የሚገድሉ" (ሮሜ 8፥13) ከሆነ ወደ ፍርድ ይገባሉ። እውነትን የሚቀበሉና በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ብቻ እነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው (ሮሜ 8፥14)፤ እንዲህም በመሆናቸው በመንፈስ ቅዱስ ሙላት መቀጠል ይቻላቸዋል (የኤፌ 5፥18 ማብ ይመ)። ኀጢአት በአማኙ ውስጥ ያለውን ሕይወትና የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ያሳጣል (ሮሜ 6፥23፤ 8፥13፤ ገላ 5፥17 ይመ፤ ከኤፌ 5፥18 እና 1ተሰ 5፥19 ጋር ያነጻጽሩ)።

**16፥14 የእኔ ከሆነው ወስዶ፤** መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ ከሆነው ወስዶ ለአማኙ ይገልጽለታል። መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ ጋር ካለን የእምነት ግንኙነት የተነሣ የእኛ የሆኑትን በሙሉ፣ ማለትም የክርስቶስን ሕልውና፣ ፍቅር፡ ይቅርታ፣ ቤዛነት፡ ቅድስና፣ ኀይል፣ መንፈሳዊ ስጦታዎችና ፈውስ ወስዶ በዘወትር ሕይወታችን እንዲገለጡ ያደርጋቸዋል። ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ፍቅሩን፣ ጸጋውንና በግል ከእርሱ ጋር እንድንኖረን የሚፈልገውን ኅብረት ይገልጽ ዘንድ ወደ እኛ ይመለሳል (ከ14፥16-23 ጋር ያነጻጽሩ)። መንፈስ ቅዱስ በእምነት፣

ከሆነው ወስዶ እንድ ታውቁ በማድረግ
ያከብረኛል። 15የአብ የሆነ ነው ሁሉ የእኔ
ነው፤ እንግዲህ፣ 'የእኔ ከሆነው ወስዶ
እንድታውቁ ያደርጋል' ያልኋችሁ ለዚሁ
ነው።
16"ከጥቂት ጊዜ በኋላ አታዩኝም፤ ይሁን
እንጂ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ ታዩኛላ
ችሁ።"

### የደቀ መዛሙርት ሐዘን ወደ ደስታ መለወጥ

17ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንዶቹ፣ "'ከጥ
ቂት ጊዜ በኋላ አታዩኝም፤ ይሁን እንጂ ከጥ
ቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ ታዩኛላችሁ' እንዲ
ሁም፣ 'ወደ አብ ስለምሄድ' ሲል ምን ማለቱ
ነው?" ተባባሉ፤ 18"'ጥቂት ጊዜ' ማለቱስ
ምን ይሆን? የሚለውም ነገር አልገባንም"
እያሉ ይጠያየቁ ነበር።
19ኢየሱስም ሊጠይቁት እንደ ፈለጉ
ባወቀ ጊዜ እንዲህ አላቸው፤ "እኔ፣ 'ከጥቂት
ጊዜ በኋላ አታዩኝም፤ ይሁን እንጂ ከጥቂት
ጊዜ በኋላ ደግሞ ታዩኛላችሁ' ስላልኋችሁ፣
ምን ማለቴ እንደ ሆነ እርስ በርሳችሁ
ትጠያየቃላችሁ? 20እውነት እላችኋለሁ፤
እናንተ ታለቅሳላችሁ፤ ታዝናላችሁም፤
ዓለም ግን ሐሤት ያደርጋል፤ ይሁን እንጂ
ሐዘናችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል። 21ሴት ቀኗ
ደርሶ ስትወልድ ትጨነቃለች፤ ከተገላገለች
በኋላ ግን፣ ሰው ወደ ዓለም ስለ መጣ
ጭንቋን ትረሳለች፤ 22ለእናንተም እንደዚሁ
አሁን የሐዘን ጊዜ ነው፤ ሆኖም እንደገና
ስለማያችሁ ደስ ይላችኋል፤ ደስታችሁንም
የሚወስድባችሁ የለም። 23በዚያ ቀን ከእኔ
ምንም አትለምኑም፤ እውነት እላችኋለሁ፤
አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ
ይሰጣችኋል። 24እስከ አሁን በስሜ ምንም
አልለመናችሁም፤ ለምኑ ትቀበላላችሁ፤
ደስታችሁም ሙሉ ይሆናል።
25"እስከ አሁን የነገርኋችሁ በምሳሌ
ቢሆንም እንኳ፣ ከእንግዲህ ግን ስለ አብ
በምሳሌ ሳይሆን በግልጽ የምናገርበት ጊዜ
ይመጣል። 26በዚያ ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፤
ይህም በእናንተ ፈንታ አብን እለምናለሁ
ማለቴ አይደለም፤ 27ስለ ወደዳችሁኝና
ከእግዚአብሔርም እንደ ወጣሁ ስላመናችሁ
አብ ራሱ ይወዳችኋል። 28ከአብ ወጥቼ ወደ
ዓለም መጥቻለሁ፤ አሁን ግን ዓለምን ትቼ
ወደ አብ እሄዳለሁ።"
29ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አሉ፤
"አሁንም እኮ ያለ ምሳሌ በግልጽ እየተናገርህ
ነው። 30አሁን ሁሉን ነገር እንደምታውቅና
ማንም ሊጠይቅህ እንደማያስፈልግ
ተረድተናል፤ ይህም ከእግዚአብሔር እንደ
ወጣህ እንድናምን አድርጎናል።"
31ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፤
"አሁንስ አመናችሁ ማለት ነው?ᵃ 32እነሆ፤
ሁላችሁም በየፊናችሁ የምትበታተኑበት
ጊዜ ይመጣል፤ ያም ጊዜ አሁን ነው።
እኔንም ብቻዬን ትተዉኛላችሁ፤ ይሁን
እንጂ አባቴ ከእኔ ጋር ስለሆነ ብቻዬን
አይደለሁም።
33"በእኔ ሰላም እንዲኖራችሁ፣ ይህን
ነግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ
አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ
ዓለምን አሸንፌዋለሁ።"

### ኢየሱስ ስለ ራሱ መጸለዩ

17 ኢየሱስ ይህን ከተናገረ በኋላ ወደ
ሰማይ ቀና ብሎ እንዲህ ሲል ጸለየ፤
"አባት ሆይ፤ ጊዜው ደርሶአል፤ ልጅህ
ያከበርህ ዘንድ ልጅህን አክብረው፤ 2ለእርሱ
ለተቀበላቸው ሁሉ የዘላለምን ሕይወት
እንዲሰጥ በሰው ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥተኸ
ዋልና። 3እውነተኛ አምላክ የሆንኸውን አን

16፥15 ዮሐ17፥10
16፥16 ቁ22፤ ዮሐ7፥33፤ 14፥18-24
16፥17 ቁ5፡16
16፥20 ማር16፥10፤ ሉቃ23፥27፤ ዮሐ20፥20
16፥21 ኢሳ13፥8፤ 21፥3፤ 26፥17፤ ሚክ4፥9፤ 1ተሰ5፥3
16፥22 ቁ6፡16፡20፤ ኤር31፥12
16፥23 ቁ26፤ ማቴ7፥7፤ ዮሐ14፥20
16፥24 ማቴ7፥7፤ ዮሐ3፥29
16፥25 ቁ2፡29፤ መዝ78፥2፤ ሐዝ 29፥49፤ ማቴ13፥34፤ ማር4፥33፡34፤ ዮሐ10፥6
16፥26 ቁ23፡24
16፥27 ቁ30፤ ዮሐ13፥3፤ 14፥21፡23
16፥28 ቁ5፡10፡17፤ ዮሐ13፥3
16፥29 ቁ25
16፥30 ቁ27፤ 1ነገ17፥24፤ ዮሐ13፥3
16፥32 ቁ2፡25፤ ማቴ26፥31፡56፤ ዮሐ8፥16፡29
16፥33 ዮሐ14፥27፤ 15፥18-21፤ ሮሜ8፥37፤ 1ዮሐ4፥4፤ 5፥4፤ ራእ2፥7፤ 11፡17፡26፤ 3፥5፡12፡21፤

16፥33 ራእ21፥7 17፥1 ማቴ26፥18፤ ዮሐ11፥41፤ 12፥23፤ 13፥31፡32 17፥2 ቁ6፡9፡24፤ ዳን7፥14፤ ማቴ25፥46፤ 28፥18፤ ዮሐ6፥37፡39 17፥3 ቁ8፡18፤ 21፡23፡25፤ ዮሐ3፥17፤ ፊል3፥8

ᵃ16፥31 ወይም በስተ መጨረሻው አመናችሁ

በፍቅር፣ በመታዘዝ፣ ኅብረትን በማድረግ፣ በአምልኮና በምስጋና ልባችንን ወደ እርሱ አቅርበ በሕይወታችን ያለውን የኢየሱስን ህልዎት በጥልቀት እንድንረዳ አስፈላጊውን ሁሉ በመፈጸም በውስጣችን ይሠራል (በገጽ 1559 ላይ፣ "ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**16፥27 አብ ራሱ ይወዳችኋል፤** አብ ሰዎችን ሁሉ ይወዳል (3፥16)። ይህም ሆኖ ሳለ፣ በኢየሱስ አማካይነት ከእርሱ ጋር ለታረቁት፣ ለሚወዱትና በዚህ ዓለም የሚደርስባቸውን መከራ እየተቋቋሙ (ቁ 33) ለእርሱ ታማኝ ሆነው ለሚጸኑት የተለየ ቤተሰባዊ ፍቅር እንዳለው ደግሞ እውነት ነው። ለኢየሱስ ያለን ፍቅር የአብን ፍቅር ወደ እኛ ያመጣልናል፤ ፍቅር ፍቅርን ይስባልና።

**17፥1፤** ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የጸለየው የመጨረሻው ጸሎት በዚያን ጊዜም ይሁን በአሁኑ ጊዜ ጌታችን ለተከታዮቹ የቱን ያህል ፍቅር እንዳለው ይገልጻል። በተጨማሪም መጋቢዎች ሁሉ ለመንጎቻቸው፣ ክርስቲያን ወላጆችም ለልጆቻቸው እንዴት መጸለይ እንደሚገባቸው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የቀረበ ምሳሌ ነው። በነቢፈነታችን ሥር ለሚገኙ ስንጸልይ ከፍተኛ ትኩረት ማድረግ የሚገባን (1) ኢየሱስ ክርስቶስንና ቃሉን በሚገባ እንዲያውቁ (ቁ 2-3፡17፡19፤ ቁ 3 እና ማብ ይመ)፤ (2) ከዓለም፣ ከውድቀት፣ ከሰይጣንና ከስሕተት ትምህርት እግዚአብሔር እንዲጠብቃቸው (ቁ 6፡11፡14-17)፤ (3) በክርስቶስ የሚገኘውን ደስታ በሙሉ እንዲለማመዱ (ቁ 13)፤ (4) በሐሳብ፣ በተግባርና በባሕርይ እንዲቀደሱ (ቁ 17 እና ማብ ይመ)፤ (5) በኢየሱስና በአብ መካከል በተገለጸው ምሳሌ መሠረት በዐላማና በኅብረት አንድ እንዲሆኑ (ቁ 11፡21-22፤ ቁ 21 እና ማብ ይመ)፤ (6) ሌሎችን ወደ ክርስቶስ እንዲመሩ (ቁ 21፡23)፤ (7) በእምነት እንዲጸኑና በመጨረሻም በመንግሥተ ሰማያት ከክርስቶስ ጋር እንዲሆኑ (ቁ 24)፤ እንዲሁም (8) በእግዚአብሔር ፍቅርና ህልዎት ውስጥ ዘወትር እንዲኖሩ ነው (ቁ 26)።

**17፥3 የዘላለም ሕይወት፤** የዘላለም ሕይወት ማብቂያ ከሌለው ኑሮ የላቀ ነው፤ ይህ ሕይወት አማኞች እንደመሆናችን በክርስቶስ የሚገኘውን የእግዚአብሔር ዐይነተኛ ሕይወት ተሳታፊ በምንሆንበት ጊዜ የምንቀበለው

ተንና የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን
ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።
[4]እኔ የሰጠኸኝን ሥራ በመፈጸም በምድር
አከበርሁህ። [5]እንግዲህ አባት ሆይ፤ ዓለም
ሳይፈ ጠር ከአንተ ጋር በነበረኝ ክብር
በአንተ ዘንድ አክብረኝ።

## ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ጸለየ

[6]"ለእነዚህ ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች
ስምህን ገልጬላቸዋለሁ። የአንተ ነበሩ ለእኔ
ሰጠኸኝ፤ እነርሱም ቃልህን ጠብቀዋል።
[7]የሰጠኸኝ ሁሉ ከአንተ እንደ ሆነ አሁን
ዐውቀዋል፤ [8]ምክንያቱም የሰጠኸኝን ቃል
ሰጥቻቸው ተቀብለዋል፤ እኔም ከአንተ
እንደወጣሁ በርግጥ ዐውቀዋል፤ አንተ
እንደላክኸኝም አምነዋል፤ [9]እነርሱ የአንተ
ስለሆኑ እጸልይላቸዋለሁ፤ ለሰጠኸኝና
የአንተ ለሆኑት እንጂ ለዓለም አልጸልይም።
[10]የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው፤ የአንተ
የሆነውም ሁሉ የእኔ ነው፤ በእነርሱም
ከብሬአለሁ። [11]ከእንግዲህ እኔ በዓለም
አልቈይም፤ እነርሱ ግን በዓለም ውስጥ
ናቸው፤ እኔም ወደ አንተ መምጣቴ ነው።
ቅዱስ አባት ሆይ፤ እኛ አንድ እንደ ሆንን፣
እነርሱም አንድ እንዲሆኑ በሰጠኸኝ በስምህ
ጠብቃ ቸው። [12]እኔ ከእነርሱ ጋር ሳለሁ፣
በሰጠኸኝ ስም ከለልኋቸው፤ ጠበቅኋቸውም፤
የመጽሐፍ ቃል እንዲፈጸም ከአንዱ ከጥፋት
ልጅ በቀር ከእነርሱ ማንም አልጠፋም።
[13]"አሁን ወደ አንተ መምጣቴ ነው፤
ነገር ግን ደስታዬ በእነርሱ ዘንድ የተሟላ
እንዲ ሆን፣ አሁን በዓለም እያለሁ ይህን
እናገራለሁ።
[14]ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ፤ እኔ ከዓለም
እንዳይደለሁ፣ እነርሱም ከዓለም
ባለመሆናቸው ዓለም ጠልቶአቸዋል።
[15]የምለምንህም ከክ ፉው እንድትጠብቃቸው
እንጂ፣ ከዓለም እንድታወጣቸው አይደለም።
[16]እኔ ከዓለም እንዳልሆንሁ ሁሉ፣ እነርሱም
ከዓለም አይደሉም። [17]ቃልህ እውነት ነው፤
በእውነትህ ቀድሳቸው[a]። [18]አንተ ወደ
ዓለም እንደ ላክኸኝ እኔም ወደ ዓለም ዮሐ 18፥36-
ላኬአቸዋለሁ። [19]እነርሱ በእውነት የተቀደሱ 37
እንዲሆኑ፣ ራሴን ስለ እነርሱ ቀድሻለሁ።

## ኢየሱስ ለአማኞች ሁሉ ጸለየ

[20]"የእነርሱን ትምህርት ተቀብለው በእኔ
ለሚያምኑ ጭምር እንጂ ለእነዚህ ብቻ
አልጸልይም፤ [21]ይህም፣ አባት ሆይ፤ አንተ

17፥4 ዮሐ13፥31፤ 19፥30
17፥5 ቍ1፤ ዮሐ1፥2፤ ፊል2፥6
17፥6 ቍ2፡26፤ ዮሐ1፥18
17፥8 ቍ3፡14፡ 18፡21፡23፡25፡26፤ ዮሐ3፥17፤ 13፥3፤ 14፥24
17፥9 ቍ2፤ ሉቃ22፥32
17፥10 ዮሐ16፥15
17፥11 ቍ13፡21-23 መዝ133፥1፤ ዮሐ7፥33፤ 10፥30፤ 13፥1
17፥12 ማቴ1፥22፤ ዮሐ6፥39፡70
17፥13 ቍ11፤ ዮሐ3፥29
17፥14 ቍ16፤ ዮሐ8፥23፤ 15፥19
17፥15 ማቴ5፥37
17፥16 ቍ14
17፥17 ዮሐ15፥3፤ 2ሳሙ 7፥28፤ 1ነገ 17፥24
17፥18 ቍ3፡8፡21፡23፡25፤ ዮሐ3፥17፤ 20፥21
17፥19 ቍ17
17፥21 ቍ3፡8፡11፡18፡ 23፡25፤ ኤር32፥39፤ ዮሐ3፥17፤ 10፥38

[a]17፥17 በግሪኩ *ሀጊያዞ* የሚለው ቅዱስ ለሆነ ተግባር መለየት ወይም መቀደስ ማለት ነው፤ ቍ 19 ይመ

---

የተለየ የሕይወት ጣዕም ነው፡፡ ይህ ዐይነቱ ሕይወት ሁልጊዜ እያደገ በሚሄድ ዕውቀት ከአብ፣ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት በማድረግ እግዚአብሔርን እንድናውቅ ያስችለናል፡፡ በአዲስ ኪዳን የዘላለም ሕይወት በሚከተሉት ሁኔታዎች ተገልጾአል፤

(1) አሁን ከዚሁ የሚጀምር ሕይወት (5፥24፤ 10፥27-28)፡፡ በአሁኑ ጊዜ የዘላለምን ሕይወት አለኝታ ለማድረግ ሕያው እምነትን ይጠይቃል፡፡ የዘላለም ሕይወት የሚገኘውና የሚጠበቀውም ቀድሞ በተደረገ የንስሓና የእምነት እርምጃ ብቻ ሳይሆን (5፥24 እና ማብ ይመ)፤ በአሁኑ ወቅት ከክርስቶስ ጋር የምናደርገውን አንድነትንና ኅብረትንም የሚያካትት ነው (1ዮሐ 5፥12)፡፡ ከእርሱ ውጭ የዘላለም ሕይወት የለም (10፥27…፤ 11፥25…፤ 1ዮሐ 5፥11-13)፡፡

(2) የወደፊት ተስፋ፤ የዘላለም ሕይወት ክርስቶስ ለታማኞቹ ዳግም ከመምጣቱ ጋር የተያያዘ እና (14፥3 እና ማብ ይመ፤ ከማር 10፥30፤ ከ2ጢሞ 1፥1፡10፤ ከቲቶ 1፥2፤ 3፥7 ጋር ያነጻጽሩ) እንደ መንፈስ ፈቃድ ከመኖርም ጋር የተሳሰረ ነው (ሮሜ 8፥12-17፤ ገላ 6፥8)፡፡

**17፥6 እነርሱም ቃልህን ጠብቀዋል፤** ክርስቶስ በዚህ ስፍራ ለጥበቃ፣ ለሐሤት፣ ለቅድስና፤ ለፍቅርና ለአንድነት ክርስቶስ የጸለየው ጸሎት የሚመለከተው ለተለዩ ሰዎች ማለትም ለእግዚአብሔር ለሆኑት፣ በክርስቶስ ላመኑት (ቍ 8)፤ ከዓለም ለተለዩት (ቍ 14-16) እንዲሁም ለክርስቶስ ቃል ለሚታዘዙና ትምህርቱን ለተቀበሉ (ቍ 6፡8) ብቻ ነው፡፡

**17፥17 በእውነትህ ቀድሳቸው፤** "መቀደስ" ማለት ቅዱስ ማድረግ፣ መለየት ወይም ለይቶ ማስቀመጥ ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ ከስቅለቱ በፊት በነበረው ምሽት፣ ደቀ መዛሙርቱ እግዚአብሔርን ያመልኩና ያገለግሉ ዘንድ ቅዱሳን እንዲሆኑ፣ ከዓለምና ከኀጢአት እንዲለዩ ጸለየ፡፡ ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ፣ ለእርሱ እንዲሆኑና እርሱንም እንዲመስሉ መለየት ይገባቸዋል፡፡ ይህ ቅድስና ሰዎች በእውነት መንፈስ ለተገለጸላቸው እውነት ራሳቸውን ሲሰጡ የሚከናወን ነው (ከ14፥17 እና 16፥13 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡ ይህም እውነት ሕያው የእግዚአብሔር ቃልና (1፥1ን ይመ) በተጻፈው ቃል ውስጥ ያለው መገለጥ ነው (በገጽ 2000 ላይ፤ "*መቀደስ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፡፡

**17፥19 ራሴን … ቀድሻለሁ፤** የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ማለትም በመስቀል ላይ ለመሞት ራሱን በመለየት ኢየሱስ ራሱን ቀደሰ፡፡ ኢየሱስ ተከታዮቹ ከዓለም ተላቀው ለእግዚአብሔር ይለዩ ዘንድ በመስቀል ላይ መከራን ተቀበለ (ዕብ 13፥12 ይመ)፡፡

**17፥21 ሁሉም አንድ እንዲሆኑ፤** ኢየሱስ በጸሎቱ እውን እንዲሆን የፈለገው አንድነት ድርጅታዊ አንድነት ሳይሆን፣ መንፈሳዊ አንድነት ነው፤ ይህም ለክርስቶስ በመኖር (ቍ 23)፣ የአብን ፍቅርና የክርስቶስን ኅብረት በማወቅና በመለማመድ (ቍ 26)፣ ከዓለም በመለየት ላይ (ቍ 14-16)፣ በእውነት በመቀደስ ላይ (ቍ 17፡19)፣ የቃሉን እውነት ቃል በመቀበልና በማመን (ቍ 6፡8፡17)፣ ለቃሉ በመታዘዝ (ቍ 21፡23) እንዲሁም የጠፉት ወደ ድኅነት እንዲመጡ በመፈለግ (ቍ 21፡23) የተመሠረተ አንድነት ነበር፡፡ ከእነዚህ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች አንዱም እንኳ ቢጎደል ኢየሱስ የጸለየበት እውነተኛ አንድነት ሊኖር አይችልም፡፡

(1) ኢየሱስ የጸለየው ተከታዮቹ ወደ ኅብረት እንዲመጡ ሳይሆን፣ እነርሱ ራሳቸው አንድ እንዲሆኑ ነው፡፡ አንድነቱ ቀጣይነት ያለው ስለመሆኑ ቃሉ ያመለክታል፡፡ ይህም የማያቋርጥ አንድነት የኢየሱስ ተከታዮች ከአብና ከወልድ ጋር ባላቸው የጋራ ግንኙነት እንዲሁም ለዓለም፣ ለቃሉና ወደ ጠፉት ለመድረስ ባለው ተመሳሳይ አመለካከት ላይ የተመሠረተ ነው

በእኔ፣ እኔም በአንተ እንዳለሁ ሁሉም አንድ
እንዲ ሆኑ፣ እንዲሁም አንተ እኔን እንደ
ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፣ እነርሱም በእኛ
እንዲሆኑ ነው። 22እኛ አንድ እንደ ሆንን
እነርሱም አንድ እንዲሆኑ፣ የሰጠኸኝን
ክብር ሰጥቻቸዋለሁ። 23ይህም እኔ በእነርሱ፣
አንተም በእኔ መሆንህ ነው። አንተ
እንደ ላክኸኝና እኔን በወደድኸኝ መጠን
እነርሱንም እንደ ወደድሃቸው ዓለም ያውቅ
ዘንድ፣ አንድነታቸው ፍጹም ይሁን።

24"አባት ሆይ፤ እነዚህ የሰጠኸኝ፣ እኔ
ባለ ሁበት እንዲሆኑ ዓለም ሳይፈጠር ስለ
ወደድ ኸኝ የሰጠኸኝንም ክብሬን እንዲያዩ
እፈ ልጋለሁ።

25"ጻድቅ አባት ሆይ፤ ዓለም ባያውቅህም፣
እኔ ዐውቅሃለሁ፤ እነዚህም አንተ እንደ ላክ
ኸኝ ያውቃሉ። 26ለእኔ ያለህ ፍቅር በእነ
ርሱ እንዲሆን፣ እኔም በእነርሱ እንድሆን፣
አንተን እንዲያውቁ[ᶻ] አድርጌአለሁ፤ እንዲ
ያውቁህም አደርጋለሁ።

## ኢየሱስ በተቃዋሚዎቹ መያዙ

*18፥3-11 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥47-56፤ ማር 14፥43-50፤ ሉቃ 22፥47-53*

18 ኢየሱስ ይህን ካለ በኋላ ከደቀ
መዛሙርቱ ጋር ሆኖ የቄድሮንን
ሸለቆ ተሻገረ፤ ማዶ ወደ ነበረውም የአትክ
ልት ስፍራ ገቡ።

2በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ
ጋር በዚያ ስለሚገናኝ፣ አሳልፎ የሰጠው
ይሁዳ ቦታውን ያውቅ ነበር። 3ይሁዳም
ወታ ደሮችን እንዲሁም ከካህናት አለቆችና
ከፈ ሪሳውያን የተላኩ ሎሌዎችን እየመራ
ወደ አትክልቱ ስፍራ መጣ፤ እነርሱም ችቦ፣
ፋኖስና የጦር መሣሪያ ይዘው ነበር።

4ኢየሱስም የሚደርስበትን ሁሉ ዐውቆ
ወጣና፣ "የምትፈልጉት ማንን ነው?"
አላቸው።

5እነርሱም፣ "የናዝሬቱን ኢየሱስን"
አሉት።

ኢየሱስም፣ "እርሱ እኔ ነኝ" አላቸው።
አሳ ልፎ የሰጠውም ይሁዳ ከእነርሱ ጋር ቆሞ
ነበር። 6ኢየሱስም፣ "እርሱ እኔ ነኝ" ባለ ጊዜ
ወደ ኋላ አፈግፍገው መሬት ላይ ወደቁ።

7እንደ ገናም፣ "የምትፈልጉት ማንን
ነው?" ሲል ጠየቃቸው።

እነርሱም፣ "የናዝሬቱን ኢየሱስን"
አሉት።

8ኢየሱስም መልሶ፣ "'እርሱ እኔ ነኝ'
ብዬ ነግሬአችኋለሁ እኮ፤ እኔን የምትፈልጉ ከሆነ፣
እነ ዚህ፣ ይሂዱ ተዉአቸው" አለ፤ 9ይህ
የሆነው፣ "ከሰጠኸኝ ከእነዚህ አንድም
አልጠፋብ ኝም" ብሎ የተናገረው ቃል
እንዲፈጸም ነው።

10ሰይፍ ይዞ የነበረው ስምዖን ጴጥሮስም፣
ሰይፉን መዞ የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ቀኝ
ጆሮ ቈረጠ፤ የአገልጋዩም ስም ማልኮስ
ይባል ነበር።

11ኢየሱስም ጴጥሮስን፣ "ሰይፍህን ወደ
ሰገባው መልስ! አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠ
ጣውምን?" አለው።

## ኢየሱስ በሊቀ ካህናቱ በሐና ፊት ቀረበ

*18፥12፡13 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥57*

12ወታደሮቹም ከአዛዣቸውና ከአይሁድ
ሎሌዎች ጋር በመሆን ኢየሱስን ያዙት፤
አሰሩትም፣ 13በመጀመሪያ፣ የቀያፋ አማት
ወደ ነበረው ወደ ሐና አመጡት፤ ቀያፋም
የዓመቱ ሊቀ ካህናት ነበር። 14ቀያፋም፣
'ለሕዝቡ ሲባል አንድ ሰው ቢሞት ይሻላል'
ብሎ አይሁድን የመከረ ነበር።

## የጴጥሮስ ክሕደት

*18፥16-18 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥69፡70፤ ማር 14፥66-68፤ ሉቃ 22፥55-57*

15ስምዖን ጴጥሮስና አንድ ሌላ ደቀ
መዝሙር ኢየሱስን ተከተሉት። ይህም ደቀ
መዝሙር በሊቀ ካህናቱ ይታወቅ ስለ ነበር፣
ከኢየሱስ ጋር ወደ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ገባ፤
16ጴጥሮስ ግን ከበሩ ውጭ ቀረ። በሊቀ
ካህናቱ የታወቀው ሌላው ደቀ መዝሙርም
ተመለሰና በር ጠባቂዋን አነጋግሮ ጴጥሮስን
ይዞት ገባ።

17በር ጠባቂዋም ጴጥሮስን፣ "አንተ ከዚህ
ሰው ደቀ መዛሙርት አንዱ አይደለህምን?"
አለችው።

17፥22 ዮሐ1፥14፤ 14፥20፤ 17፥23 ቆላ3፥8፡21፡18፡25፤ ዮሐ3፥17፤ 16፥27፤ 17፥24 ቆላ2፥5፤ ማቴ25፥34፤ ዮሐ1፥2፡14፤ 12፥26 17፥25 ቆላ3፥8፡18፡21፡23፤ ዮሐ3፥17፤ 15፥21፤ 16፥3፡27 17፥26 ቆላ6፤ ዮሐ15፥9 18፥1 ቆላ26፤ 2ሳሙ15፥23፤ ማቴ21፥1፤ 26፥36 18፥2 ሉቃ21፥37፤ 22፥39 18፥3 ቆላ12፤ ሐሥ1፥16 18፥4 ቆላ7፤ ዮሐ6፥64፤ 13፥1፡11 18፥5 ማር1፥24 18፥7 ቆላ4 18፥9 ዮሐ6፥39 18፥11 ማቴ20፥22 18፥12 ቆላ3 18፥13 ቆላ24፤ ማቴ26፥3 18፥14 ዮሐ11፥49-51 18፥15 ማቴ26፥3፡58፤ ማር14፥54፤ ሉቃ 22፥54 18፥17 ቆላ25

[ᶻ]17፥26 በግሪኩ *ስምህን እንዲያውቁ ይላል*

(ከ1ዮሐ 1፥7 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ስብሰባዎችን፣ ኮንፍራንሶችን ወይም ትልልቅ ድርጅቶችን በማዘጋጀት ሰው ሠራሽ አንድነትን ለመፍጠር መሞከር ኢየሱስ የጸለየበትን ያንን አንድነት መጻረር ነው። በኢየሱስ ሐሳብ የነበረው አንድነት ላይ ላዩን ከተቀባባ፣ «የአንድነት ስብሰባ» ፍጹም የተለየ ነው። ይህም አንድነት ለክርስቶስ፣ ለቃሉና ለቅድስና ሙሉ በሙሉ በተሰጡት ዘንድ የሚገኝ የልብ፣ የዓላማ፣ የአስተሳሰብና የፈቃድ መንፈሳዊ አንድነት ነው (ኤፌ 4፥3 እና ማብ ይመ)።

**17፥22 የሰጠኸኝን ክብር፤** የክርስቶስ ክብር ራሱን ዝቅ በማድረግ የሰጠው አገልግሎትና የሰው ልጆችን ለመዋጀት ሲል በመስቀል ላይ መሞቱ ነው። እንደዚሁም የአማኙ፣ «ክብር» ትሕትና በተሞላበት አገልግሎትና መስቀልን በመሸከም ጐዳና መጓዝ ነው (ከሉቃ 9፥23 እና ከማብራሪያው ጋር ያነጻጽሩ)። ትሕትና፣ ራስን መካድና ስለ ክርስቶስ መከራን ለመቀበል መፍቀድ እውነተኛ የአማኞች አንድነት መኖሩን የሚያረጋግጥ ሲሆን፣ ወደ እውነተኛ ክብርም ይመራል (በገጽ 1205 ላይ፣ «*የእግዚአብሔር ክብር*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**18፥11 ጽዋ፤** በማቴ 26፥39 የክርስቶስን የመከራ ጽዋ በሚመለከት የቀረበውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

**18፥12 ኢየሱስን ያዙት፤** በማቴ 26፥57 ከክርስቶስ መያዝ እስከ ስቅለቱ የተፈጸሙትን ሁኔታዎች ቅደም ተከተል በሚመለከት የቀረበውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

**18፥15-27፤** እነዚህ ጥቅሶች ጴጥሮስ በተከታታይ ጌታን የካደበትን ሁኔታዎች ያሳያሉ፤ በማር 14፥50፡ 14፥71፣

እርሱም፣ "አይደለሁም" አለ።
[18]ብርድ ስለ ነበር አገልጋዮቹና ሎሌዎቹ
ባያያዙት የከሰል ፍም ዙሪያ ለመሞቅ
ቆመው ሳሉ፣ ጴጥሮስም ከእነርሱ ጋር ቆሞ
እሳት ይሞቅ ነበር።

## ኢየሱስ በሊቀ ካህናቱ ፊት መቅረቡ

*18፥19-24 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥59-68፤ ማር 14፥55-65፤ ሉቃ 22፥63-71*

[19]በዚያን ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ኢየሱስን ስለ
ደቀ መዛሙርቱና ስለ ትምህርቱ ጠየቀው።
[20]ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፤
"እኔ ለዓለም በግልጽ ተናግሬአለሁ፤
አይሁድ በሙሉ በሚሰበሰቡበት ምኵራብ፣ በቤተ
መቅደስም ሁል ጊዜ አስተምሬአለሁ፤
በስውር የተናገርሁት የለም። [21]ለምን እኔን
ትጠይቀኛለህ? የሰሙኝን ጠይቃቸው፤
እነሆ፤ የተናገርሁትን እነርሱ ያውቃሉ።"
[22]ኢየሱስ ይህን በተናገረ ጊዜ፣ አጠገቡ
ቆመው ከነበሩት ሎሌዎች አንዱ፣ "ለሊቀ
ካህናቱ የምትመልሰው እንዲህ ነውን?"
ብሎ በጥፊ መታው።
[23]ኢየሱስም፣ "ክፉ ተናግሬ ከሆን ክፉ
መናገሬን መስክር፤ እውነት ከተናገርሁ
ግን ለምን ትመታኛለህ?" አለው። [24]ሐናም
ኢየሱስ ታስሮ እንዳለ ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ
ቀያፋ ላከው።[t]

## የጴጥሮስ ሁለተኛና ሦስተኛ ክህደት

*18፥25-27 ተጓ ምብ — ማቴ 26፥71-75፤ ማር 14፥69-72፤ ሉቃ 22፥58-62*

[25]ስምዖን ጴጥሮስም ቆሞ እሳት ሲሞቅ፣
"አንተ ከእርሱ ደቀ መዛሙርት አንዱ
አይደለህምን?" አሉት።
እርሱም፣ "አይደለሁም" ሲል ካደ።
[26]ከሊቀ ካህናቱ አገልጋዮች አንዱ፣
ጴጥሮስ ጆሮውን የቈረጠው ሰው ዘመድ፣
"በአትክልቱ ስፍራ አንተን ከእርሱ ጋር
አላየሁህም?" ሲል ጠየቀው። [27]ጴጥሮስም
እንደ ገና ካደ፤ ወዲያውም ዶሮ ጮኸ።

## ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት

*18፥29-40 ተጓ ምብ — ማቴ 27፥11—18፥20-23፤ ማር 15፥2-15፤ ሉቃ 23፥2፡3፡18-25*

[28]አይሁድም ኢየሱስን ከቀያፋ ወደ ሮማ
ዊው ገዥ ግቢ ይዘውት ሄዱ፤ ጊዜውም
ማለዳ ነበር። አይሁድም ፋሲካን መብላት
እንዲችሉ፣ ላለመርከስ ወደ ገዥው ግቢ
አልገቡም። [29]ስለዚህ ጲላጦስ ወደ እነርሱ
ወጥቶ፣ "በዚህ ሰው ላይ የምታቀርቡት ክስ
ምንድን ነው?" ብሎ ጠየቃቸው።
[30]እነርሱም፣ "ይህ ሰው ወንጀለኛ ባይሆን
ኖሮ፣ አንተ ፊት ባላቀረብነውም ነበር"
ብለው መለሱለት።
[31]ጲላጦስም፣ "እናንተ ራሳችሁ ወስዳችሁ
በሕጋችሁ መሠረት ፍረዱበት" አላቸው።
አይሁድም፣ "እኛማ በማንም ላይ
የሞት ፍርድ ለመፍረድ መብት የለንም"
አሉት። [32]ይህ የሆነው በምን ዐይነት ሞት
እንደሚሞት ለማመልከት ሲል ኢየሱስ
የተናገረው ቃል እንዲፈጸም ነው።
[33]ጲላጦስም ወደ ግቢው ተመልሶ
ኢየሱስን አስጠራና፣ "አንተ የአይሁድ
ንጉሥ ነህን?" ብሎ ጠየቀው።
[34]ኢየሱስም፣ "ይህ ሐሳብ የራስህ ነው?
ወይስ ሌሎች ስለ እኔ የነገሩህ?" ሲል
መለሰለት።
[35]ጲላጦስም መልሶ፣ "እኔ አይሁዳዊ
ነኝን? ወደ እኔ የላኩህ የራስህ ወገኖችና
የካህናት አለቆች ናቸው፤ ለመሆኑ ምን
አድርገህ ነው?" አለው።
[36]ኢየሱስም፣ "የእኔ መንግሥት ከዚህ
ዓለም አይደለም፤ ቢሆንማ ኖሮ አይሁድ

18፥18 ማር14፥54፡67፤ ዮሐ21፥9
18፥20 ማቴ4፥23፤ 26፥55፤ ዮሐ7፥26
18፥22 ቍ3፤ ማቴ16፥21፤ ዮሐ19፥3
18፥23 ማቴ5፥39፤ ሐሥ23፥2-5
18፥24 ቍ13፤ ማቴ26፥3
18፥25 ቍ17፡18
18፥26 ቍ1፡10
18፥27 ዮሐ13፥38
18፥28 ቍ33፤ ማቴ27፥2፤ ዮሐ11፥55፤ 19፥9
18፥32 ማቴ20፥19፤ 26፥2፤ ዮሐ3፥14፤ 8፥28፤ 12፥32፡33
18፥33 ቍ28፡29፤ ማቴ2፥2፤ ሉቃ23፥3፤ ዮሐ19፥9
18፥36 ማቴ3፥2፤ 26፥53፤ ሉቃ17፥21፤ ዮሐ6፥15

*[t]18፥24 ወይም ሐናም ወደ ቀያፋ እንደታሰረ ላከው*

በሉቃ 22፥62 ላይ የቀረቡትን ማብራሪያዎች ይመልከቱ።

18፥28-40፤ እነዚህ ጥቅሶች ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት እንደቆመ ያሳያሉ፤ ማቴ 27፥2 እና ማብራሪያውን፣ ሉቃ 23፥1 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**18፥36 የእኔ መንግሥት ከዚህ ዓለም አይደለም፤** የክርስቶስን መንግሥት ምንነትና ቤዛዊ ዐላማን በሚመለከት ሦስት ነጥቦች ሊሰተዋሉ ይገባል፤

(1) የኢየሱስ መንግሥት፣ "ከዚህ ዓለም" አይደለም፤ ምንጩ ከዚህ ዓለም አይደለም፤ የዓለምን ሥርዐት አይከተልም፤ ኢየሱስ ሃይማኖትንና ፖለቲካን ያጣመረ መለኮታዊ መንግሥትን ሊመሠርት ወይም የዓለም ገዥ ለመሆን አልመጣም። በምድር ላይ የፖለቲካን መንግሥት ለመመሥረት ቢመጣ ኖሮ አገልጋይ መላእክቱ ይዋጉለት እንደነበር ኢየሱስ ተናግሮአል። የመንግሥቱ ባሕርይ ይህ ስላልሆነ በምድር ላይ የክርስቶስን ዐላማ ለማራመድ ወደ ጦርነት ወይም ወደ ዐመፅ አሠራር አይዘኑም (ከማቴ 26፥51-52 ጋር ያነጻጽሩ)። የእግዚአብሔርን መንግሥት ያቋቋሙ ዘንድ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከማኅበራዊ ቅስቀሳ ቡድኖች ወይም ከማንኛውም ምድራዊ ድርጅት ጋር አይተባበሩም። መስቀሉን በትምክህት ኅብረተሰብን የመጨቆኛ መሣሪያ አድርገው ለመጠቀም አይፈቅዱም። የኢየሱስ ተከታዮች ለመንፈሳዊ ተጋድሎ የሚጠቀሙት ሥጋዊ የጦር ዕቃዎችን ሳይሆን (2ቆሮ 10፥4) መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎችን ብቻ ነው (ኤፌ 6፥10-18)። ይህንን ስንል ግን ቅንነት ለሰፈነበት መንግሥት፣ እግዚአብሔር ለሚሻው ፍትሕ፣ ለሰላም ወይም ለሕገ ወጥነት መወገድ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ግድየለሽ ናቸው ማለት አይደለም። ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር አኳያ መንግሥት ስላለበት ግብረገባዊ ኀላፊነት፣ "ትንቢታዊ መልእክት" የሚያሙጡ ሊሆኑ ይገባል።

(2) የኢየሱስ መንግሥት ግን የክርስቶስ መንግሥት ነው፤ ይኸውም የእግዚአብሔር መንግሥት፣ በተቀበሉትና ለእውነት ቃሉ በሚታዘዙ (ቍ 37) ሰዎች አኗኗር ሁሉ ኢየሱስ ያለውን አገዛዝ፣ ጌትነት፣ ኀይልና መንፈሳዊ አሠራር የሚያጠቃልል የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት፣ "ጽድቅ፣ ሰላምና ሐሤት ነው" (ሮሜ 14፥17)። የሰይጣንን መንፈሳዊ ኀይሎች በመንፈሳዊ የጦር ዕቃዎች ይቋቋማል (ማቴ 12፥28፤ ሉቃ 11፥20፤ ሐሥ 26፥18፤ ኤፌ 6፥12)። ቤተ ክርስቲያን መፈጸም ያለባት የክርስቶስ አገልጋይ

እንዳይዙኝ ሎሌዎቼ በተከላከሉልኝ ነበር፤
አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለም"
አለው።
37ጲላጦስም፣ "ታዲያ፣ ንጉሥ ነህ ማለት
ነዋ!" አለው።
ኢየሱስም፣ "እኔ ንጉሥ እንደ ሆንሁ
መናገርህ ትክክል ነው፤ የተወለድሁት፣
ወደዚህም ዓለም የመጣሁት ስለ እውነት
ሮሜ 12፥1-2 ለመመስከር ነው፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ
ይሰማኛል" አለው።
38ጲላጦስም፣ "እውነት ምንድንነው?"
አለው፤ ይህን ከተናገረ በኋላም እንደ ገና
ወደ አይሁድ ወጥቶ እንዲህ አላቸው፤ "እኔ
የሚያስከስስ በደል አላገኘሁበትም፤ 39ነገር
ግን በፋሲካ አንድ እስረኛ እንድፈታላችሁ
ልማድ አላችሁ፤ ስለዚህ፣ 'የአይሁድን
ንጉሥ' እንድፈታላችሁ ትፈልጋላችሁን?"
40እነርሱም እንደ ገና በመጮኽ፣ "የለም፤
እርሱን አይደለም! በርባንን ፍታልን!"
አሉ። በርባን ግን ወንበዴ ነበረ።

### ኢየሱስ እንዲሰቀል ተፈረደበት

*19፥1-16 ተጓ ምብ — ማቴ 27፥27-31፤
ማር 15፥16-20*

19 ጲላጦስም ኢየሱስን ወስዶ አስገረ
ፈው። 2ወታደሮችም የእሾህ አክ
ሊል ጐንጕነው በራሱ ላይ አደረጉ፤ ሐም
ራዊ ልብስም አለበሱት፤ 3እየተመላለሱም፣
"የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፤ ሰላም ለአንተ
ይሁን" እያሉ በጥፊ ይመቱት ነበር።
4ጲላጦስም እንደ ገና ወደ ውጭ ወጥቶ፣
"እንግዲህ ወደ እናንተ ያወጣሁት ለክስ
የሚያደርስ ወንጀል እንዳላገኘሁበት እንድ
ታውቁ ነው" አላቸው። 5ኢየሱስ የእሾህ
አክሊል ደፍቶ ሐምራዊ ልብስም ለብሶ
ወጣ፤ ጲላጦስም፣ "እነሆ፤ ሰውየው!"
አላቸው።
6የካህናት አለቆችና ሎሌዎቻቸውም
ባዩት ጊዜ፣ "ስቀለው! ስቀለው!" እያሉ
ጮኹ። ጲላጦስ ግን፣ "እናንተ ወስዳችሁ
ስቀሉት፤ በእኔ በኩል ለክስ የሚያደርስ
ወንጀል አላገኘሁበትም" አላቸው።
7አይሁድም፣ "እኛ ሕግ አለን፤ ራሱን
የእግዚአብሔር ልጅ ስላደረገ በሕጋችን
መሠረት መሞት አለበት" አሉ።
8ጲላጦስ ይህን ሲሰማ የባሰውን ፈራ፤
9ወደ ግቢው ተመልሶ ኢየሱስን፣ "ከየት ነው
የመጣኸው?" በማለት ጠየቀው፤ ኢየሱስ
ግን ምንም አልመለሰለትም። 10ጲላጦስም፣
"አታናግረኝምን? ልፈታህ ወይም ልሰቅልህ
ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅም?" አለው።
11ኢየሱስም፣ "ከላይ ባይሰጥህ ኖሮ
በእኔ ላይ ሥልጣን ባልኖረህ ነበር፤ ስለዚህ
ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ሰው የባሰ ኀጢአት
አለበት" አለው።
12ከዚያ በኋላ ጲላጦስ ኢየሱስን ሊፈታው
ፈለገ፤ አይሁድ ግን፣ "ይህን ሰው ብትፈታው
የቄሣር ወዳጅ አይደለህም፤ ራሱን ንጉሥ
የሚያደርግ የቄሣር ተቃዋሚ ነው" በማለት
ጮኹታቸውን ቀጠሉ።
13ጲላጦስም ይህን ሲሰማ ኢየሱስን ወደ
ውጭ አወጣው፤ 'የድንጋይ ንጣፍ' በተባለ፣
በአራማይክ ቋንቋ 'ገበታ' ብለው በሚጠሩት
ስፍራ፣ በፍርድ ወንበር ላይ ተቀመጠ።
14ቀኑ የፋሲካ በዓል መዘጋጃ፣ ጊዜውም
ከቀኑ ስድስት ሰዓት ያህል ነበር።

18፥37 ዮሐ3፥32፤ 8፥47፤ 1ዮሐ4፥6
18፥38 ሉቃ23፥4
18፥40 ሐሥ3፥14
19፥1 ዘዳ25፥3፤ ኢሳ50፥6፤ 53፥5፤ ማቴ27፥26
19፥3 ማቴ27፥29፤ ዮሐ18፥22
19፥4 ቍ6፤ ሉቃ 23፥4፤ ዮሐ18፥38
19፥5 ቍ2
19፥6 ቍ4፤ ሉቃ 23፥4፤ ሐሥ3፥13
19፥7 ዘሌ24፥16፤ ማቴ26፥63-66፤ ዮሐ5፥18፤ 10፥33
19፥9 ማር14፥61፤ ዮሐ18፥33
19፥11 ዮሐ18፥28-30፤ ሐሥ3፥13፤ ሮሜ13፥1
19፥12 ሉቃ23፥2
19፥13 ማቴ27፥19፤ ዮሐ5፥2
19፥14 ቍ19:21 ማቴ27፥62፤ ማር15፥25

---

የሚፈጽመውን እንጂ የዚህ ዓለም ገዥ የሚያደርገውን አይደለም። ብርታትዋም የክርስቶስ መስቀል እንጂ የዚህ ዓለም ኀይል አይደለም፤ ከዓለም የሚሰነዘርባት ሥቃይና ጥላቻ ከብርዋ ነው (2ቆሮ 3፥7-18)። የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ኀይል ያገኘችው የዓለምን ኀይል በመካድ ብቻ ነበር ይኸው እውነት በዛሬው ዘመንም ላለችው ቤተ ክርስቲያን በፊቷ የሚገጥማት ጉዳይ ነው፤ በእግዚአብሔር ውስጥ ራሷን የምታገኘውም በዚህ ዓለም ያላትን ሕይወት ስታጣ ብቻ ነው (ማቴ 16፥25 ይመ) እንዲሁም (በገጽ 1443 ላይ፣ *"የእግዚአብሔር መንግሥት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ.)።

(3) ወደፊት የክርስቶስ መንግሥት አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ነው። ይህም ተፈጻሚ የሚሆነው በመንግሥታት ላይ ሊፈርድ፣ ሐሰተኛውን ክርስቶስ ሊያጠፋ፣ በምድር ላይ ሺህ ዓመት ሊነግሥና ሰይጣንን ወደ እሳት ባሕር በመጣል ወደ ፍጻሜው ሊያመጣው ወደ ምድር ከመጣ በኋላ ነው (ራእ 19፥11-20፥15)።

**18፥37 ስለ እውነት ለመመስከር ነው፤** የኢየሱስ ዐይነተኛ ተልዕኮ ለእውነት መመስከርና ሰዎችን ወደ እውነት መምራት ነው፤ ይህም አሁን በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎ የሚገኝ በሥጋ የተገለጠ የአብና የወንጌሉ እውነት ምስክር ነው። በዛሬው ዘመን አንዳንድ አገልጋዮች እውነትንና ጤናማ ትምህርትን ከአጉል ትምህርት ጋር አስማምተው፣ ግልጽ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል ትርጓሜ በመጋረድና መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እምነት በመጣል አንድነትን ማጠናከራቸው እንዴት የሚያስገርም ነገር ነው? እንዲህ ዐይነቶቹ አገልጋዮች በበጎውና በክፉው፣ በእውነትና በሐሰት መካከል ለመለየት ባለመፍቀድ የስሕተትን ትምህርት በማቀፍ ይስታሉ። ፍቅርንና ሰፊ አመለካከትን ምክንያት በማድረግ ክርስቶስ የመጣበትን ዐላማ ይቃወማሉ። አብያተ ክርስቲያናት እውነትን ፈጽሞ ችላ ማለት የለባቸውም፤ ጌታ የመጣው ስለ እውነት ለመመስከር ነውና (ከ17፥8፡17፤ ከ2ተሰ 2፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

**19፥1 አስገረፈው፤** የሮማውያን አገራረፍ ስልት እንዴት እንደ ነበረ በተመለከት ዝርዝሩን ማቴ 27፥26 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**19፥4 ለክስ የሚያደርስ ወንጀል እንዳላገኘሁበት፤** ሉቃ 23፥14 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**19፥11 ከላይ ባይሰጥህ ኖሮ ... ሥልጣን፤** ባለ ሥልጣን በሥልጣን ላይ የሚሆነው እግዚአብሔር ሲፈቅድ ብቻ እንደ ሆነ ኢየሱስ ተናገረ (ከዳን 4፥34-35 እና ከሮሜ 13፥1 ጋር ያነጻጽሩ)። የጲላጦስ ኀጢአት በፖለቲካዊ ጥቅም ተገፋፍቶ ለሕዝቡ ጥያቄ መንበርከኩ ሲሆን፣ የእስራኤላውያን ኀጢአት ደግሞ መሲሐቸውን ባለመቀበላቸው እጅግ የከፋ ነበር።

ጲላጦስም አይሁድን፣ "እነሆ፤
ንጉሣችሁ" አላቸው።
15እነርሱ ግን፣ "አስወግደው! አስወግደው!
ስቀለው!" እያሉ ጮኹ።
ጲላጦስም፣ "ንጉሣችሁን ልስቀለውን?"
አለ።
የካህናት አለቆችም፣ "ከቄሣር በቀር ሌላ
ንጉሥ የለንም" ብለው መለሱለት።
16በመጨረሻም ጲላጦስ እንዲሰቅሉት
አሳ ልፎ ሰጣቸው።

## በ ስቅለት

*19፥17-24 ተጓ ምብ — ማቴ 27፥33-44፤ ማር 15፥22-32፤ ሉቃ 23፥33-43*

ወታደሮቹም ኢየሱስን ይዘው ወሰዱት፤
17እርሱም የራሱን መስቀል ተሸክሞ
በአራማይክ 'ጎልጎታ' ተብሎ ወደሚጠራው
'የራስ ቅል' ወደ ተባለው ቦታ ወጣ።
18በዚያም ሰቀሉት፤ ከእርሱም ጋር ሁለት
ሰዎችን፣ አንዱን በዚህ በኩል፣ ሌላውን
በዚያ በኩል፣ ኢየሱ ስንም በመካከል
አድርገው ሰቀሉ።
19ጲላጦስም ጽሑፍ ጽፎ በመስቀሉ ላይ
እንዲለጠፍ አደረገ፤ ጽሑፉም፣ 'የናዝሬቱ ኢየ
ሱስ፣ የአይሁድ ንጉሥ' የሚል ነበር። 20ኢየ
ሱስ የተሰቀለበት ቦታ ከከተማው አጠገብ ስለ
ነበር ብዙዎቹ አይሁድ ጽሑፉን አነበቡት፤
ጽሑፉም፣ በአራማይክና በላቲን፣ በግሪክም
ነበር። 21የአይሁድ የካህናት አለቆች
ጲላጦስን በመቃወም፣ "እርሱ፣ 'የአይሁድ
ንጉሥ ነኝ' እንዳለ ጻፍ እንጂ 'የአይሁድ
ንጉሥ' ብለህ አትጻፍ" አሉት።
22ጲላጦስም፣ "በቃ፤ የጻፍሁትን
ጽፌአለሁ" ብሎ መለሰ።
23ወታደሮቹ ኢየሱስን ከሰቀሉ በኋላ፣
እጀ ጠባቡ ሲቀር፣ ልብሱን ወስደው
ለእያንዳንዱ አንድ አንድ እንዲደረስ
ለአራት ተከፋፈሉት፤ እጀ ጠባቡም ከላይ

19፥16 ማቴ27፥26፤ ማር15፥15፤ ሉቃ23፥25
19፥17 ዘፍ22፥6፤ ሉቃ14፥27፤ 23፥33፥26፤ ዮሐ5፥2
19፥18 ሉቃ23፥32
19፥19 ቍ14፥21፤ ማር1፥24
19፥20 ዕብ13፥12
19፥21 ቍ14
19፥24 ቍ28፥36፥37፤ መዝ22፥18፤ ማቴ1፥22
19፥25 ማቴ12፥46፤ 27፥55፥56፤ ሉቃ8፥2፤ ዮሐ20፥1፥18
19፥26 ማቴ12፥46፤ ዮሐ13፥23
19፥28 ቍ24፥30፥36፥37፤ ማቴ1፥22፤ ዮሐ13፥1
19፥29 መዝ69፥21
19፥30 ሉቃ12፥50፤ ዮሐ4፥34፤ 17፥4
19፥31 ቍ14፥42፤ ዘዳ21፥23፤ ኢሱ8፥29፤ 10፥26፥27

እስከ ታች አንድ ወጥ ሆኖ ያለ ስፌት
የተሠራ ነበር።
24ስለዚህ፣ "ዕጣ ተጣጥለን ለሚደርሰው
ይድረስ እንጂ አንቅደደው" ተባባሉ። ይህም
የሆነው፣

"ልብሴን ተከፋፈሉት፤
በእጀ ጠባቤም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ"

የሚለው የመጽሐፍ ቃል እንዲፈጸም ነው።

ወታደሮቹ ያደረጉትም ይህንኑ ነው።
25በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱና
የእናቱ እኅት፣ እንዲሁም የቀልዮጳ
ሚስት ማርያምና መግደላዊት ማርያም
ቆመው ነበር። 26በዚያም ኢየሱስ እናቱንና
የሚወደውም ደቀ መዝሙር አጠገቧ
ቆሞ ሲያያቸው እናቱን፣ "አንቺ ሴት
ሆይ፤ ልጅሽ ይኸው" አላት፤ 27ደቀ
መዝሙሩንም፣ "እናትህ ይህችው" አለው።
ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይህ ደቀ መዝሙር
ወደ ቤቱ ወሰዳት።

## የኢየሱስ መሞት

*19፥29-30 ተጓ ምብ — ማቴ 27፥48-50፤ ማር 15፥36-37፤ ሉቃ 23፥36*

28ከዚያም ኢየሱስ ሁሉ ነገር እንደ
ተፈጸመ ዐውቆ፤ የመጽሐፍ ቃል
እንዲፈጸም፣ "ተጠማሁ" አለ። 29በዚያም
የሆመጠጠ ወይን የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ
ነበር፤ እነርሱም ሰፍነግ በወይን ጠጅ
ነክረው፣ በሂሶጵ ዘንግ ወደ አፉ አቀረቡለት፤
30ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፣
"ተፈጸመ" አለ፤ ራሱን አዘንብሎ፣
መንፈሱን አሳልፎ ሰጠ።
31ዕለቱ ለሰንበት መዘጋጃ ቀን ነበር።
አይሁድ፣ የተሰቀሉት ሰዎች ሬሳ በሰንበት
ቀን በመስቀል ላይ እንዳይውል ስለ ፈለጉና
ያም የተለየ ሰንበት ስለ ነበር፣ የተሰቀሉት
ሰዎች ጭናቸው ተሰብሮ በድናቸው እንዲ

**19፥14 ከቀኑ ስድስት ሰዓት፤** በኢየሱስ ላይ የተደረገው ምርመራ የተጠናቀቀው፣ «ከቀኑ ስድስት ሰዓት ያህል» እንደነበር ዮሐንስ ተናግሮአል። ማርቆስ ግን ኢየሱስ የተሰቀለው «በሦስት ሰዓት» ነበር' ብሏል (ማር 15፥25)። ዮሐንስ የሮማውያንን፣ ማርቆስ ደግሞ የፓለስቲናን የሰዓት አቈጣጠር ስልት መጠቀሙን መረዳት አስፈላጊ ነው። የሮማውያን ቀን የሚጀምረው በእኩለ ሌሊት ሲሆን የፓለስቲናውያን ደግሞ ጀምበር ስትወጣ ነበር።

**19፥16 እንዲሰቅሉት አሳልፎ ሰጣቸው፤** ሉቃ 23፥25 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**19፥17 የራሱን መስቀል ተሸክሞ፤** ማቴ 27፥31 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**19፥18 በዚያም ሰቀሉት፤** ስቅለቱን በሚመለከት ለተሰጠው አስተያየት ማቴ 27፥55 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**19፥26 አንቺ ሴት ሆይ ልጅሽ ይኸው፤** ኢየሱስ በሞት ጣር ውስጥ በነበረበት ጊዜ እንኳ ስለ እናቱ ደህንነት ይገደው ነበር። «የሚወደውንም ደቀ መዝሙር» (ዮሐንስን ሳይሆን አይቀርም) እንዲንከባከባት ኀላፊነት ሰጠው። እስከ ዕለተ ሞታችን ድረስ የቤተሰባችንን አባላት መርዳት ግዴታችን ነው። በዚህ ላይ ትኩረት የተሰጠው ወላጆቻቸውን መርዳት ያለባቸው ልጆች ያላቸውን ኀላፊነት በሚመለከት ነው።

**19፥29 የኮመጠጠ የወይን ጠጅ፤** ኮምጣጣ ወይን ጠጅ ለሚለው የግሪኩ ቃል «ኦክሶስ» ሲሆን፣ ይህም መራራ ወይም ኮምጣጤ ማለት ነው። ቪኒጋር (ኮምጣጤ) የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል «ቪን» (ወይን) እና «ኤግር» (ኮምጣጣ) ከሚሉት የፈረንሳይኛ ቃላት የተገኘ ሲሆን፥ ይህም ኮምጣጣ ወይን ማለት ነው። ኮምጣጤ ወይም መራራ ወይን የሚሠራው በአቼቶ (አሴቲክ አሲድ) ተብላልቶ አልኮል ወደ ኮምጣጤነት ሲለወጥ ነው። ክርስቶስ ኮምጣጤውን መቅመሱ በመዝ 69፥21 ላይ «ለጥማቴም ሆምጣጤ ሰጡኝ» የሚለው ትንቢት ፍጻሜ ነበር።

**19፥30 ተፈጸመ፤** በኀጢአት ለወደቀው የሰው ዘር ቤዛ ለመሆን ኢየሱስ የተወቃየው ሥቃይ አበቃ፣ የእርሱም የቤዛነት ሥራ ተፈጸመ። የኀጢአታችንን ቅጣት እርሱ ተሸከመ፣ ለሰዎችም ሁሉ የድኅነትን መንገድ ከፈተ (ማቴ 27፥50 እና ማብ፤ ሉቃ 23፥46 እና ማብ ይመ)።

ወርዶ ጲላጦስን ለመኑት። 32ስለዚህም ወታ
ደሮቹ መጥተው ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሎ
የነበረውን የመጀመሪያውን ሰው ጭን ሰበሩ፤
ደግሞም የሌላውን ጭን ሰበሩ። 33ወደ ኢየ
ሱስ በመጡ ጊዜ ግን ሞቶ ስላገኙት ጭኖ
ቹን አልሰበሩም፤ 34ነገር ግን ከወታደሮቹ
አንዱ የኢየሱስን ጐን በጦር ወጋው፤ ወዲ
ያውም ደምና ውሃ ፈሰሰ። 35ይህን ያየው
ሰው ምስክርነቱን ሰጥቶአል፤ ምስክርነቱም
እውነት ነው፤ እውነትን እንደሚናገርም ያው
ቃል፤ እናንተም እንድታምኑ ይመሰክራል።
36ይህም የሆነው፣ መጽሐፍ፣ "ከአጥንቱ
አንድ ድም አይሰበርም" ያለው እንዲፈጸም፣
37ሌላውም መጽሐፍ፣ "የወጉትም ያዩታል"
ስለሚል ነው።

## የኢየሱስ መቀበር

*19፥38-42 ተጓ ምብ — ማቴ 27፥57-61፤ ማር 15፥42-47፤ ሉቃ 23፥50-56*

38ከዚህ በኋላ የአርማትያሱ ዮሴፍ
የኢየሱስን በድን ለመውሰድ ጲላጦስን
ለመነው፤ ዮሴፍም አይሁድን ስለ ፈራ
በስውር የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበር።
እርሱም ጲላጦስን ካስፈቀደ በኋላ መጥቶ
በድኑን ወሰደ። 39ከዚህ ቀደም በሌሊት ወደ
ኢየሱስ መጥቶ የነበረው ኒቆዲሞስ አንድ
መቶ ሊትርa ያህል የሚመዝን የከርቤና
የእሬት ቅልቅል ይዞ መጣ። 40እነርሱም
የኢየሱስን በድን ወስደው እንደ አይሁድ
አገናነዝ ልማድ ከሽቱ ጋር ከተልባ እግር
በተሠራ ጨርቅ ከፈኑት። 41ኢየሱስ
በተሰቀለበት ቦታም የአትክልትስፍራ ነበር፤
በአትክልቱም ስፍራ ማንም ያልተቀበረበት
አዲስ መቃብር ነበር። 42ዕለቱ ለአይሁድ
የሰንበት መዘጋጃ ቀን ስለ ነበርና መቃብሩም
ቅርብ ስለ ሆነ ኢየሱስን በዚያ ቀበሩት።

## ኢየሱስ ከሞት ተነሣ

*20፥1-8 ተጓ ምብ — ማቴ 28፥1-8፤ ማር 16፥1-8፤ ሉቃ 24፥1-10*

20 በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን፣ በማለዳ
ገና ጨለማ ሳለ፣ መግደላዊት
ማርያም ወደ መቃብሩ ሄደች፤ ድንጋዩም
ከመቃ ብሩ መግቢያ ተንከባሎ አየች።
2ስለዚህም ወደ ስምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ
ይወደው ወደ ነበረው ሌላው ደቀ መዝሙር
እየሮጠች መጥታ፣ "ጌታን ከመቃብር
አውጥተው ወስደውታል፤ የት እንዳኖሩትም
አናውቅም" አለቻቸው።
3"ከዚያም ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር
ወጥተው ወደ መቃብሩ ሄዱ። 4ሁለቱም
ይሮጡ ነበር፤ ሌላው ደቀ መዝሙርም
ጴጥሮስን ቀድሞት ከመቃብሩ ደረሰ።
5ጐንበስ ብሎ ሲመለከት ከተልባ እግር
የተሠራውን ከፈን በዚያው እንዳለ አየ፤
ወደ መቃብሩ ግን አልገባም። 6ይከተለው
የነበረው ስምዖን ጴጥ ሮስ ደረሰና ወደ
መቃብሩ ገባ፤ እርሱም ከተ ልባ እግር
የተሠራውን ከፈን አየ፤ 7እንዲሁም
በኢየሱስ ራስ ላይ ተጠምጥሞ የነበረውን
ጨርቅ አየ፤ ይህም ጨርቅ ከከፈኑ ተለይቶ
እንደ ተጠቀለለ ነበር። 8ከዚያም አስቀድሞ
ከመቃብሩ የደረሰው ሌላው ደቀ መዝሙር
ወደ ውስጥ ገባ፤ አይቶም አመነ፤ 9ይኸውም
ኢየሱስ ከሙታን መነሣት እንዳለበት ገና
ከመጽሐፍ ስላልተረዱ ነበር።

## ኢየሱስ ለመግደላዊት ማርያም ታየ

10ከዚያም በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ተመ
ልሰው ወደየቤታቸው ሄዱ፤ 11ማርያም
ግን ከመቃብሩ ውጭ ቆማ ታለቅስ ነበር፤
እያ ለቀሰችም መቃብሩን ለማየት ጐንበስ
አለች። 12የኢየሱስ ሥጋ በነበረበት ቦታ፣
ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት መላእክት አንዱ
በራሱጌ ሌላው በግርጌ ተቀምጠው አየች።
13እነርሱም፣ "አንቺ ሴት፤ ለምን
ታለቅሻለሽ?" ብለው ጠየቋት።
እርሷም፣ "ጌታዬን ወስደውታል፤ የት
እንዳኖሩትም አላውቅም" አለች። 14ይህን
ብላ ዘወር ስትል ኢየሱስ በዚያው ቆሞ
አየች፤ ኢየሱስ መሆኑን ግን አላወቀችም።
15እርሱም፣ "አንቺ ሴት፤ ለምን
ታለቅሻለሽ? ማንንስ ትፈልጊአለሽ?"
አላት።
እርሷም የአትክልቱ ቦታ ጠባቂ
መስሎአት፣ "ጌታዬ፤ አንተ ወስደኸው
ከሆነ፣ እባክህ እንድወስደው፣ የት
እንዳኖርኸው ንገረኝ" አለችው።
16ኢየሱስም፣ "ማርያም" አላት።
እርሷም፣ ወደ እርሱ ዞር ብላ

a19፥39 መሳሳ አራት ኪሎ ግራም ያህል ነው

19፥32 ቊ18
19፥34 ዘካ12፥10፤ 1ዮሐ5፥6:8፤ ራእ1፥7
19፥35 ሉቃ24፥48፤ ዮሐ15፥27፤ 21፥24
19፥36 ቊ24፥28፥37፤ ዘፀ12፥46፤ ዘኍ 9፥12፤ መዝ34፥20፤ ማቴ1፥22
19፥37 ዘካ12፥10፤ ራእ1፥7
19፥38 ዮሐ7፥13
19፥39 ዮሐ3፥1፤ 7፥50
19፥40 ማቴ26፥12፤ ሉቃ24፥12፤ ዮሐ11፥44፤ 20፥5፥7
19፥42 ቊ14፥31፥20፥41
20፥1 ቊ18፤ ሉቃ 8፥2፤ ማቴ27፥60:66፤ ዮሐ19፥25
20፥2 ቊ13 ዮሐ13፥23፤
20፥3 ሉቃ24፥12
20፥5 ቊ11፤ ዮሐ19፥40
20፥7 ዮሐ11፥44
20፥8 ቊ4
20፥9 ሉቃ24፥26፥46፤ ሐሥ2፥24፤ ማቴ22፥29፤ ዮሐ2፥20
20፥11 ቊ5
20፥12 ማቴ28፥2:3፤ ማር16፥5፤ ሉቃ24፥4፤ ሐሥ1፥10፤ 5፥19፤ 10፥30
20፥13 ቊ2፥15
20፥14 ማር16፥9፤ ሉቃ24፥16፤ ዮሐ21፥4
20፥15 ቊ13
20፥16 ማቴ23፥7፤ ዮሐ5፥2

---

**19፥41 አዲስ መቃብር፤** መቃብሩ ከዐለት ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሠራ ነበር (ማር 15፥46)፤ ወደ ውስጡ ለመግባት እስከሚቻል ድረስ ትልቅ እንደ ሆነ ቢገመትም ለመግባት ማጎንበስ ያስፈልግ ነበር (20፥11)። ዮሴፍ የኢየሱስን አስከሬን በመቃብር ውስጥ ካስቀመጠ በኋላ በመቃብሩ ደጃፍ ትልቅ ድንጋይ አንከባሎ ዘጋው (ማቴ 27፥60)።

**20፥9 ከሙታን መነሣት እንዳለበት፤** የኢየሱስን ትንሣኤ አስፈላጊነት በተመለከተ ማቴ 28፥6 እና ማብራሪያውን፤ የክርስቶስን ትንሣኤ ማረጋገጫ በተመለከተ ደግሞ ሉቃ 24፥6 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ ።

**20፥16-18፤** እነዚህ ጥቅሶች ኢየሱስ ራሱን ለማርያም እንደ ገለጸ ያሳያሉ። ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ራሱን የገለጸው ለማርያም ነበር። በወንጌሎችም ውስጥ ጎላ ብላ የምትታይ ግለሰብ አልነበረችም፤ ሆኖም ከደቀመዛሙርቱ መካከል የቅርብ ከነበሩት ለአንዱ ሳይገለጥ ለእርሷ በመጀመሪያ ተገለጠላት። በዘመናት ሁሉ፤ ኢየሱስ ሕልውናውንና ፍቅሩን በተለይ በመንፈስ ድኾች ለሆኑት (ማቴ 5፥3) ይገልጣል። እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጥላቸው ሰዎች በሐዘን ውስጥ እንደነበረችው እንደ ማርያም ለጌታቸው ያላቸውን ፍቅር አጥብቀው የሚይዙ ማንነታቸው ያልታወቀ ሰዎች ናቸው።

በአራማይክ ቋንቋ፣ "ረቡኒ" አለችው፤
ትርጒሙም "መምህር ሆይ" ማለት ነው።
[17]ኢየሱስም፣ "ገና ወደ አብ ስላላረግሁ፣
አትንኪኝ፤ ይልቁንስ ወደ ወንድሞቼ ሂደሽ፣
'ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፣ ወደ አምላ
ኬና ወደ አምላካችሁ ዐርጋለሁ' ብሎአል
ብለሽ ንገሪአቸው" አላት።
[18]መግደላዊት ማርያምም፣ ወደ ደቀ
መዛሙርቱ መጥታ፣ "ጌታን እኮ አየሁት!"
አለች፤ እርሱ ያላትንም ነገረቻቸው።

## ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ታየ

[19]በዚያን ዕለት፣ በሳምንቱ መጀመሪያ
ቀን በምሽት፣ ደቀ መዛሙርቱ አይሁድን
በመፍራት በሮቹን ቈልፈው ተሰብስበው ሳለ፣
ኢየሱስ መጣና በመካከላቸው ቆሞ፣ "ሰላም
ለእናንተ ይሁን" አላቸው። [20]ይህንም ብሎ
እጆቹንና ጐኑን አሳያቸው፤ ደቀ መዛሙርትም
ጌታን ባዩት ጊዜ እጅግ ደስ አላቸው።
[21]ኢየሱስም እንደ ገና፣ "ሰላም ለእናንተ
ይሁን፤ አብ እኔን እንደ ላከኝ፣ እኔም
እናንተን እልካችኋለሁ" አላቸው። [22]ይህን ካለ
በኋላም፣ እፍ አለባቸውና እንዲህ አላቸው፤
"መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤ [23]የሰዎችን
ኀጢአት ይቅር ብትሉ፣ ኀጢአታቸው
ይቅር ይባልላቸዋል፤ ኀጢአታቸውን ይቅር
ባትሉ ግን፣ ይቅር አይባልላቸውም።"

20፥17 ማቴ28፥10፤ ዮሐ7፥33
20፥18 ቍ1፤ ሉቃ24፥10፡22፡23
20፥19 ቍ21፡26፤ ሉቃ24፥36-39፤ ዮሐ7፥13፤ 14፥27
20፥20 ሉቃ24፥39፡40፤ ዮሐ16፥20፡22፤ 19፥34
20፥21 ቍ19፤ ማቴ28፥19፤ ዮሐ3፥17፤ 17፥18
20፥22 ዮሐ7፥39፤ ሐሥ2፥38፤ 8፥15-17፤ 19፥2፤ ገላ 3፥2
20፥23 ማቴ16፥19፤ 18፥18
20፥24 ዮሐ11፥16
20፥25 ቍ20፤ ማር16፥11
20፥26 ቍ21፤ ዮሐ14፥27
20፥27 ቍ25፤ ሉቃ24፥40
20፥29 ዮሐ3፥15፤ 1ጴጥ1፥8
20፥30 ዮሐ2፥11፤ 21፥25
20፥31 ማቴ4፥3፤ 25፥46፤
20፥31 ዮሐ3፥15፤ 19፥35

## ኢየሱስ ለቶማስ ታየ

[24]በዚህ ጊዜ ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ
የሆነው፣ ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ፣
ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር
አልነበረም። [25]ሌሎች ደቀ መዛሙርትም፣
"ጌታን አየነው እኮ!" አሉት።
እርሱ ግን፣ "በምስማር የተቸነከሩትን
የእጆቹን ምልክቶች ካላየሁ፣ ምስማሮቹ
በነበሩበት ቦታ ጣቴን ካላደረግሁ፣ በጐኑም
እጄን ካላስገባሁ አላምንም" አለ።
[26]ከስምንት ቀን በኋላም፣ ደቀ መዛሙርቱ
በቤት ውስጥ ነበሩ፤ ቶማስም ከእነርሱ ጋር
ነበር፤ በሮቹ ተቈልፈው ነበር፤ ኢየሱስ
ግን መጥቶ በመካከላቸው ቆመና፣ "ሰላም
ለእናንተ ይሁን" አላቸው። [27]ከዚያም
ቶማስን፣ "ጣትህን ወደዚህ አምጣ፤
እጆቼንም ተመልከት፤ እጅህን ዘርጋና በጐኔ
አስገባ፤ አትጠራጠር፤ እመን" አለው።
[28]ቶማስም፣ "ጌታዬ፤ አምላኬም!"
አለው።
[29]ኢየሱስም፣ "አንተ ስላየኸኝ አምነሃል፤
ሳያዩ የሚያምኑ ግን ብፁዓን ናቸው" አለው።
[30]ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፉ
ሌሎች አያሌ ታምራዊ ምልክቶችን በደቀ
መዛሙርቱ ፊት አደርጓል፤ [31]ነገር ግን
ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔርም †
ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ* ዘንድ፣ አምናችሁም

*20፥31 አንዳንድ ቅጆች በማመን እንድትድኑ ይላሉ

20፥17 **አትንኪኝ፤** የዚህ ጥቅስ ትርጒም "እኔን የሙጥኝ ብለሽ በመያዝ አትቅሪ፤ እኔ ገና ወደ አባቴ አልሄድኩም፤ እኔን እንደ ገና የማየቱ ዕድል አለሽ" የሚል ሳይሆን አይቀርም። ይህ እስከሚሆን ግን እርስዋ ልታከናውነው የሚገባትን ተግባር ሰጥቷታል።

20፥22 **መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤** ከሐሥ 2 ጋር ያነጻጽሩ።

20፥23 **የሰዎችን ኀጢአት ይቅር ብትሉ፤** ማቴ 16፥19 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

20፥28 **ጌታዬ አምላኬም፤** ቅዱሳት መጻሕፍት ኢየሱስ አምላክ እንደሆነ በግልጽ ይናገራሉ። አምላክነቱን ማመን የክርስትና እምነት መሠረት ነው፤ ለድነታችንም እጅግ አስፈላጊ ነው። ክርስቶስ መለኮት ባይሆን ኖሮ የዓለምን ኀጢአት ማስተስረይ ባልቻለም ነበር። የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት በሚከተሉት ሁኔታዎች ተገልጾአል፤

(1) በቅዱሳት መጻሕፍት መለኮታዊ ስሞች ተሰጥተውታል፤ (ሀ) አምላክ (20፥28፤ ኢሳ 9፥6፤ ሮሜ 9፥5፤ ቲቶ 2፥13፤ ዕብ 1፥8)፤ (ለ) የእግዚአብሔር ልጅ (5፥25፤ ማቴ 16፥16-17፤ 8፥29፤ 27፥40፡43፤ ማር 14፥61-62፤ ሉቃ 22፥70)፤ (ሐ) የመጀመሪያውና የመጨረሻው (ራእ 1፥17፤ 2፥8፤ 22፥13)፤ (መ) አልፋና ኦሜጋ (ራእ 1፥8፤ 22፥13)፤ (ሠ) ፊተኛውና ኋለኛው (ራእ 22፥13)፤ (ረ) ቅዱሱ (ሆሴ 11፥9፤ ሐሥ 3፥14)፤ (ሰ) ጌታ (ሉቃ 2፥11፤ ሐሥ 4፥33፤ 9፥17፤ 16፥31)፤ (ሸ) የሁሉም ጌታና የክብር ጌታ (መዝ 4፥8-10፤ ሐሥ 10፥36፤ 1ቆሮ 2፥8)።

(2) ክርስቶስ መለኮታዊ አምልኮ ቀርቦለታል (5፥23፤ 13፥13፤ 20፥28፤ ማቴ 14፥33፤ ሉቃ 5፥8)፤ ሰዎችም ወደ እርሱ ጸልየዋል (ሐሥ 7፥59፤ 1ቆሮ 1፥2፤ 2ቆሮ 12፥8-9)።

(3) ክርስቶስ መለኮታዊ ተግባሮችን እንዲያከናውን ኀላፊነት ተሰጥቶታል፤ (ሀ) የዓለም ፈጣሪ (1፥3፤ ቈላ 1፥16፤ ዕብ 1፥8፡10፤ ራእ 3፥14)፤ (ለ) ሁሉንም ነገር ደግፎ የያዘ (ቈላ 1፥17፤ ዕብ 1፥3)፤ (ሐ) ኀጢአትን ይቅር የሚል (ማር 2፥5፡10፤ ሉቃ 7፥48-50)፤ (መ) የትንሣኤን ሕይወት የሚሰጥ (5፥28-29፤ 6፥39-44)፤ (ሠ) በሰው ሁሉ የሚፈርድ (5፥21-23፤ ማቴ 25፥31-46፤ ሐሥ 17፥31፤ 2ጢሞ 4፥1)፤ (ረ) ድነትን የሚሰጥ (5፥24-26፤ 6፥47፤ 10፥28፤ 17፥2) ነው።

(4) በብሉይ ኪዳን ስለ ጌታ የሚናገሩ ክፍሎች ክርስቶስን የሚያመለክቱ መሆናቸውን አዲስ ኪዳን ይገልጻል፤ መዝ 23፥1ን ከዮሐ 10፥11 ጋር፤ መዝ 102፥24-27ን ከዕብ 1፥10-12 ጋር፤ ኢሳ 8፥13-14ን ከ1ጴጥ 2፥7-8 ጋር፤ ኤር 17፥10ን ከራእ 2፥23 ጋር፤ ሕዝ 34፥11-12ን ከሉቃ 19፥10 ጋር ያነጻጽሩ።

(5) የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከእግዚአብሔር አብ ስም ጋር አብሮ ተጠቅሷል (14፥1-23፤ ማቴ 28፥19፤ ሮሜ 1፥7፤ 2ቆሮ 13፥14፤ ቈላ 2፥2፤ 1ተሰ 3፥11፤ ያዕ 1፥1፤ ራእ 5፥13፤ 7፥10)።

(6) ክርስቶስ ያለ ኀጢአት መሆኑና ፍጹም ቅዱስ መሆኑ ለመለኮትነቱ ምስክር ነው (ሉቃ 1፥35፤ 2ቆሮ 5፥21፤ ዕብ 4፥15)።

(7) ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በትንሣኤው ተረጋግጧል (ሮሜ 1፥4)።

እነዚህ የክርስቶስን መለኮትነት የሚያረጋግጡ መረጃዎች አማኞች ወደ እግዚአብሔር አብ በሚቀርቡበት ፍጹም ተመሳሳይ ሁኔታ ወደ ክርስቶስም መቅረብ እንዳለባቸው ያመለክታሉ። አማኞች ክርስቶስን ሊያምኑት፣ ሊያመልኩት፣ ወደ እርሱ ሊጸልዩ፣ ሊያገለግሉትና ሊወዱት ይገባቸዋል (1፥1 እና ማብ፣ ሥላሴን በሚመለከት ማር 1፥11 እና ማብ ይመ)።

# የደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን መቀበል

*ዮሐ 20፥22 "ይህን ካለ በኋላም፣ እፍ አለባቸውና እንዲህ አላቸው፡ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤ ..."*

ከትንሣኤ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የነበራቸው ልምምድ በበዓለ ኀምሳ ቀን ከተቀበሉት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ልምምድ የተለየ ነው (ሐሥ 1፥5፤ 2፥4)። በዮሐንስ 20፥22 ላይ ደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን ስለ መቀበላቸው መጠቀሱ በክርስቶስ ትንሣኤ የሚገኘው የአዲሱ ሕይወት ማረጋገጫና የአዲስ ልደት ልምምድ ማስረጃ ነው።

(1) ኢየሱስ ከመከራውና ከስቅለቱ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ ባስተላለፈው የመጨረሻ ንግግር መንፈስ ቅዱስን ስለ መቀበል እንዲህ የሚል ተስፋ ሰጥቶ ነበር፡ " ... እናንተ ግን፣ አብሮአችሁ ስለሚኖርና በውስጣችሁ ስለሚሆን ታውቃላችሁ" (ዮሐ 14፥17)። ኢየሱስ አሁን የፈጸመው ይህን ተስፋ ነበር።

(2) በዮሐ 20፥22 ላይ የተጠቀሰው "እፍ አለባቸው" (በግሪኩ "ኢምፉሳኦ") የሚለው ሐረግ በሰብዓ ሊቃናት ትርጉም በዘፍ 2፥7 ላይ "በአፍንጫው (በአዳም) የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ሆነ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው። በሕዝቅኤል 37፥9 "በእነዚህ በተገደሉት ላይ እፍ በልባቸው" የሚለው ሐረግም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። ዮሐንስ "እፍ አለባቸው" የሚለውን ግሥ መጠቀሙ የሚያሳየው ኢየሱስ መንፈሱን ሲሰጥ በሰው ውስጥ መንፈስ ሕይወትን እንደሚዘራና እንደሚያድስ ለማመልከት ነው። እግዚአብሔር በአካላዊ/ ፍጥረታዊ ሰው እፍ ሲልበት ሕይወት እንደዘራበት ሁሉ ክርስቶስም በደቀ መዛሙርቱ ላይ እፍ ሲልባቸው መንፈሳዊ ሕይወትን እንደዘራባቸው ያመለክታል (በገጽ 1606 ላይ፣ "ዳግም ልደት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ኢየሱስ ከትንሣኤው የተነሣ "ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ" ሆነ (1ቆሮ 15፥45)።

(3) "መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ" የሚለው ሐረግ መንፈስ ቅዱስ በዚህ ታሪካዊ ወቅት በደቀ መዛሙርቱ ሕይወት ማደር መጀመሩን ያሳያል። "መቀበል" የሚለው ግሥ በግሪኩ ቋንቋ "ላቤቴ" ሲሆን፣ "ላምባኖ" ከሚለው ቃል የተወሰደ ነው፤ ትርጉሙም አንድን የተፈጸመ ድርጊት ያመለክታል። ደቀ መዛሙርቱ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የተቀበሉት ይህ የሕይወት ልምምድ ከኢየሱስ የአገልግሎት ሥልጣንና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ኀይል ከመቀበላቸው በፊት የተከናወነ ነው (ዮሐ 20፥23፤ ሐሥ 2፥4)።

(4) ደቀ መዛሙርቱ ከዚህ የመንፈስ ቅዱስ ልምምድ በፊት እውነተኛ አማኞችና የኢየሱስ ተከታዮች መሆናቸው የተረጋገጠ ነው። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን የመቀበላቸው ሁኔታ ከቀድሞው ኪዳን በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ወደተገኘው አዲስ ኪዳን መግባታቸውን የሚያረጋግጥ የሽግግር ልምምድ ነው። ይህም ደቀ መዛሙርትና ቤተ ክርስቲያን በበዓለ ኀምሳ ቀን ኀይልን ከመቀበላቸው በፊት በክርስቶስ የሚገኘውን አዲስ ሕይወት ለመቀበላቸው ማስረጃ ነው (ማቴ 26፥28፤ ሉቃ 22፥20፤ 1ቆሮ 11፥25፤ ኤፌ 2፥15-16፤ ዕብ 9፥15-17 እንዲሁም በገጽ 1606 ላይ፡ "ዳግም ልደት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ ቁ 47)።

(5) ይህ ምንባብ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ሕዝብ ሕይወት ውስጥ ያለውን ሥራ ይገልጻል። ይህን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሁለት አቅጣጫ ማየት ይቻላል። (ሀ) ደቀ መዛሙርቱ ከበዓለ ኀምሳ ቀን በፊት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ነበር፤ ይኸውም በውስጣቸው ስለሚኖር ከበዓለ ኀምሳ ቀን በፊት ዳግም ተወልደዋል ማለት ነው። (ለ) በሐሥ 2፥4 ላይ የተጠቀሰው የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ከዳግም ልደት በኋላ የሚመጣ ልምምድ ነው። በደቀ መዛሙርቱ ሕይወት የተፈጸመው የመንፈስ ቅዱስ ልምምድ ዳግም ልደትን ተከትሎ የሚመጣና መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው ያደረገው ልዩ ሥራ ነው።

(6) በደቀ መዛሙርቱ ሕይወት የተፈጸሙት እነዚህ ሁለት የተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች በሁሉም ክርስቲያኖች ሕይወት የሚፈጸሙ መደበኛ ልምምዶች ናቸው። ይህም ማለት አማኞች በክርስቶስ ዳግም ልደትን ሲቀበሉ መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ማደር ይጀምራል። ከዚህም በኋላ እነዚህ ዳግም የተወለዱ አማኞች የክርስቶስ ምስክር ለመሆን የሚያስችላቸውን ኀይል ይቀበሉ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን ማግኘት አለባቸው (ሐሥ 1፥5፡8፤ 2፥4፤ 2፥39)።

(7) ኢየሱስ እፍ ብሎባቸው ደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ በዮሐ 20፥22 ላይ የተጠቀሰው ሐሳብ በበዓለ ኀምሳ ቀን ሊመጣ ላለው መንፈስ ቅዱስ ትንቢታዊ መግለጫ ብቻ ነው ብሎ መተርጐም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም:: በግሪኩ "ተቀበሉ" የሚለው ግሥ የሚያመለክተው ድርጊቱ በዚያው ቅጽበትና ስፍራ መከናወኑን ነው:: የሆነውና ዮሐንስም የመዘገበው ታሪካዊ እውነታ በጊዜና በስፍራ ሊጠቀስ የሚችል ተግባርና ልምምድ ነው::

ሐሥ 4፥12 በስሙ ሕይወት እንዲኖራችሁ ይህ
ተጽፎአል።

## ደቀ መዛሙርቱ ዓሣ በታምር መያዛቸው

21 ከዚያም በኋላ ኢየሱስ በጥብርያዶስ
ባሕር* እንደ ገና ለደቀ መዛሙርቱ
ታየ፤ በዚህም ሁኔታ ተገለጠ፤ 2ስምዖን
ጴጥሮስ፣ ዲዲሞስ የተባለው ቶማስ፣ የቃና
ዘገሊላው ናትናኤል፣ የዘብዴዎስ ልጆችና
ከደቀ መዛሙርቱ ሌሎች ሁለት አንድ
ላይ ነበሩ፤ 3ስምዖን ጴጥሮስም፣ "ዓሣ
ላጠምድ መሄዴ ነው" አላቸው፤ እነርሱም፣
"እኛም ከአንተ ጋር እንሄዳለን" አሉት፡
፡ ወጥተውም ወደ ጀልባዋ ገቡ፤ በዚያ
ሌሊት ግን ምንም አላጠመዱም።
4ሲነጋም፣ ኢየሱስ በባሕሩ ዳርቻ ቆመ፤
ደቀ መዛሙርቱ ግን ኢየሱስ መሆኑን
አላወቁም ነበር።
5እርሱም፣ "ልጆች፣ ዓሣ አላችሁ?"
አላቸው።
እነርሱም፣ "የለንም" አሉት።
6እርሱም፣ "መረባችሁን ከጀልባው
በስተቀኝ ጣሉ፤ ዓሣ ታገኛላችሁ" አላቸው።
እነርሱም በጣሉ ጊዜ ከዓሣው ብዛት የተነሣ
መረቡን መጐተት አቃታቸው።
7ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ
መዝሙርም፣ ጴጥሮስን፣ "ጌታ እኮ
ነው!" አለው። ስምዖን ጴጥሮስም፣ 'ጌታ
እኮ ነው!' የሚለውን ቃል በሰማ ጊዜ፣
አውልቆት የነበረውን መደረቢያ ልብስ
ታጠቀና ዘሎ ወደ ባሕሩ ገባ። 8ሌሎች ደቀ
መዛሙርት ግን ከባሕሩ ዳርቻ የራቁት
ሁለት መቶ ክንድ ያህል* ብቻ ስለ ነበር፣
ዓሣ የሞላበትን መረብ እየሳቡ በጀልባዋ

21፥1 ቍ14፡ ዮሐ6፥1፡ 20፥19:26
21፥2 ማቴ4፥21፤ ዮሐ1፥45፤ 2፥1፤ 11፥16
21፥3 ሉቃ5፥5
21፥4 ሉቃ24፥16፤ ዮሐ20፥14
21፥6 ሉቃ5፥4-7
21፥7 ዮሐ13፥23
21፥9 ቍ10:13፡ ዮሐ18፥18
21፥13 ቍ9
21፥14 ዮሐ20፥19:26
21፥15 ማቴ6፥33:35፡ ሉቃ12፥32፤ ዮሐ13፥37
21፥16 2ሳሙ5፥2፤ ሕዝ34፥2፤ ማቴ2፥6፤ ዮሐ10፥11፡ ሐሥ20፥28፤ 1ጴጥ5፥2:3

መጡ። 9ወደ ምድርም በደረሱ ጊዜ፣ ዓሣ
በላዩ የነበረበት የከሰል ፍምና እንጀራ
አዩ።
10ኢየሱስም፣ "አሁን ካጠመዳችሁት
ዓሣ አስቲ አምጡ" አላቸው።
11ስለዚህ ስምዖን ጴጥሮስ ወደ ጀልባዋ
ወጥቶ መረቡን ወደ ምድር ጐተተው፤
መረቡንም መቶ አምሳ ሦስት ትልልቅ ዓሣ
ሞል ተውት ነበር፤ ይህን ያህል ቢይዝም
መረቡ አልተቀደደም። 12ኢየሱስም "ኑ፤
ቍርስ ብሉ" አላቸው። ጌታ እንደ ሆነ
ዐውቀው ስለ ነበር፣ ከደቀ መዛሙርቱ፣
"አንተ ማን ነህ?" ብሎ ለመጠየቅ የደፈረ
አልነበረም። 13ኢየሱስም መጥቶ እንጀራውን
አንሥቶ ሰጣቸው፤
ዓሣውንም ሰጣቸው። 14እንግዲህ ኢየሱስ
ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ
ሲታይ ይህ ሦስተኛ ጊዜ ነው።

## ኢየሱስ ጴጥሮስን ወደ ቀድሞ ቦታው መለሰው

15በልተው ካበቁ በኋላ፣ ኢየሱስ ስምዖን
ጴጥሮስን፣ "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፤
ከእነዚህ አብልጠህ ትወደኛለህን?" አለው።
እርሱም፣ "አዎን፣ ጌታ ሆይ፤
እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ" አለው።
ኢየሱስም፣ "ጠቦቶቼን መግብ" አለው።
16ኢየሱስም ለሁለተኛ ጊዜ፣ "የዮና ልጅ፣
ስም ዖን ሆይ፤ በእውነት ትወደኛለህን?"
አለው።
እርሱም፣ "አዎን፤ ጌታ ሆይ፤
እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ" አለው።

*21፥1 የገሊላ ባሕር ማለት ነው
*21፥8 ዘጠና ሜትር ያህል ነው

**21፥1 ኢየሱስ … እንደ ገና … ታየ፤** ከትንሣኤው በኋላ ክርስቶስ ስለ ታየባቸው ሁኔታዎች ማቴ 28፥9 ይመልከቱ።

**21፥3 ዓሣ ላጠምድ መሄዴ ነው፤** የደቀ መዛሙርቱ ዓሣ ለማጥመድ ማቀድ ለክርስቶስ ከነበራቸው መስጠት ወይም ወንጌልን ከመስበክ ጥሪያቸው አፈገፈጉ ማለት አይደለም። ኢየሱስ ከመቃብር እንደ ተነሣ ያውቃሉ፤ ይሁን እንጂ ከዚያ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸው አልተረዱም፤ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ በኀይል እስከሚመጣ ድረስ በኢየሩሳሌም ቈዩ የሚለውን መመሪያም ገና አልተቀበሉም ነበር (ሐሥ 1፥4-5)። ለራሳቸውና ለቤተሰባቸው አስፈላጊ የሆነውን ማቅረብ ስለነበረባቸው ዓሣ ለማጥመድ መሄድ ለእነርሱ ግዴታ ነበር።

**21፥6 መረባችሁን ከጀልባው በስተቀኝ ጣሉ፤** በምንሠራው ሥራ ሁሉ ከጌታ ምሪትን ማግኘት በጣም አስፈላጊ ነው። የክርስቶስ ሕይወትና ምሪት ሕልውናና የሚመራ እጅ በሌለበት ሁኔታ የምንኖር ከሆነ የምናደርገው ሁሉ ባዶና ከንቱ መባከን ይሆናል።

**21፥15 ትወደኛለህን?** ጴጥሮስ ካጋጠመው ጥያቄ ሁሉ እጅግ ዋነኛና ፈታኝ የሆነው ለጌታው የተሰጠ ፍቅር እንዳለው ወይም እንደሌለው የሚያረጋግጠው ጥያቄ ነበር። (1) እዚህ ላይ ፍቅር ለሚለው ቃል ሁለት የግሪክ ቃላት ተጠቅሰዋል። የመጀመሪያው «አጋፔአ» የሚል ሲሆን፣ ትርጕሙም አስተዋይና ዐላማ ያለው አስተሳሰብንና ፈቃድን ተቀዳሚ የሚያደርግ ፍቅር ነው። «ፊሌኦ» የሚለው ሁለተኛው ሞቅ ያለውን ከተፈጥሮአችን የሚፈልቀው ስሜት አዘል ፍቅር የያዘ በመሆኑ በይበልጥ ግላዊ ስሜትን የሚያሳይ ፍቅር ነው። ኢየሱስ በእነዚህ ሁለት ቃላት እሳቤ አማካይነት የጴጥሮስ ፍቅር ከፈቃድ ብቻ ሳይሆን ከዐላማና ከግል ቅርበትም የሚመነጭ ልባዊ ፍቅር ሊሆን እንደሚገባው አመልክቶታል። (2) ኢየሱስ ለጴጥሮስ ያቀረበለት ጥያቄ ለአማኞች ሁሉ የቀረበ ታላቅ ጥያቄ ነው። እኛ ሁላችን ለኢየሱስ ከልብ የመነጨ ፍቅርና ከልብ የሆነ መሰጠት ሊኖረን ይገባል (14፥15፤ 16፥27፤ ማቴ 10፥37፤ ሉቃ 7፥47፤ 1ቆሮ 16፥22፤ 2ቆሮ 5፥14፤ ገላ 5፥6፤ ኤፌ 6፥24፤ ያዕ 1፥12፤ 1ጴጥ 1፥8፤ ራእ 2፥4)።

**21፥16 በጎቼን ጠብቅ፤** ኢየሱስ አማኞችን እንደ ጠቦቶች (ቍ. 15) እንዲሁም እንደ በጎች (ቍ. 16) መመሰሉ ሦስት ነገሮችን ያስገነዝባል፤ (1) የእረኝነት እንክብካቤ እንደሚያስፈልገን፣ (2) ዘወትር ቃሉን ልንመገብ እንደሚገባን፣ (3) በጎች በቀላሉ ባዝነው ለአደጋ የተጋለጡ እንደሚሆኑ ሁሉ እኛም ያለ ጌታ በቀላሉ ስለምንባዝን ተደጋጋሚ ምሪት፣ ጥበቃና እርምት እንደሚያስፈልገን።

ኢየሱስም፣ "በጎቼን ጠብቅ" አለው።
17ሦስተኛም ጊዜ፣ "የዮና ልጅ፣ ስምዖን
ሆይ፤ ትወደኛለህን?" አለው።
ጴጥሮስም ሦስተኛ ጊዜ ኢየሱስ፣
'ትወደ ኛለህን?' ብሎ ስለ ጠየቀው በዝኖ፣
"ጌታ ሆይ፤ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤
እንደምወድህም ታውቃለህ" አለው።
ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ "በጎቼን
መግብ። 18እውነት እልሃለሁ፤ ወጣት ሳለህ
ልብስህን ራስህ ለብሰህ ወደ ፈለግህበት ትሄድ
ነበር፤ ስትሸመግል ግን እጅህን ትዘረጋለህ፤
ሌላም ሰው ልብስህን አስታጥቆህ ልትሄድ
ወደማ ትፈልግበት ይወስድሃል።" 19ኢየሱስ
ይህን ያለው ጴጥሮስ በምን ዐይነት ሞት
ዕግዚአብሔርን እንደሚያከብረው ለማመልከት
ነው። ከዚህ በኋላም፣ "ተከተለኝ" አለው።
20ጴጥሮስ ወደ ኋላው ዘወር ሲል፣ ኢየሱስ
ይወደው የነበረ ደቀ መዝሙር ሲከተላቸው
አየ፤ ይህም ደቀ መዝሙር ያን ጊዜ ራት
ሲበሉ ወደ ኢየሱስ ደረት ተጠግቶ፣ "ጌታ
ሆይ፤ አሳልፎ የሚሰጥህ ማን ነው?" ያለው
ነበር። 21ጴጥሮስም ባየው ጊዜ፣ "ጌታ ሆይ፤
እርሱስ?" ብሎ ጠየቀ።
22ኢየሱስም፣ "እስክመለስ ድረስ
በሕይወት እንዲኖር ብፈልግ እንኳ አንተን
ምን ቸገረህ? አንተ ራስህ ተከተለኝ" አለው።
23በዚህ ምክንያት ይህ ደቀ መዝሙር
አይሞትም የሚል ወሬ በወንድሞች መካከል
ተሰራጨ። ኢየሱስ ግን፣ "እስክመለስ ድረስ
በሕይወት እንዲኖር ብፈልግ አንተን ምን
ቸገረህ?" አለው እንጂ እንደማይሞት
አልነገረውም።
24ስለ እነዚህ የሚመሰክረውና
ይህን የጻፈው ይኸው ደቀ መዝሙር
ነው፤ ምስክርነቱም እውነት እንደ ሆነ
እናውቃለን።
25ኢየሱስ ያደረጋቸው ሌሎችም ብዙ
ነገሮች አሉ፤ ሁሉም ነገር ቢጻፍ፣ ለተጻፉት
መጻሕፍት ሁሉ ዓለም በቂ ቦታ የሚኖረው
አይመስለኝም።

21፥17 ቀኑ16፣ ዮሐ13፥38፤ 16፥30
21፥19 ማቴ4፥19፤ ዮሐ12፥33፤ 13፥36፤ 18፥32፤ 2ጴጥ1፥14
21፥20 ቀኑ7፤ ዮሐ13፥23፡25
21፥22 ቀኑ19፤ ማቴ4፥19፤ 16፥27
21፥23 ሐሥ1፥16
21፥24 ዮሐ15፥27፤ 19፥35
21፥25 ዮሐ20፥30

21፥17 **ትወደኛለህን ... በጎቼን መግብ፤** ኢየሱስ ፍቅርን ለክርስቲያናዊ አገልግሎት መሠረታዊ የሆነ መመዘኛ አድርጎታል። ሌሎች መመዘኛዎችም እንደተጠበቁ ሆነው (1ጢሞ 3፥1-13)፥ ለክርስቶስና ለሌሎች ያለን ፍቅር አስፈላጊነት እጅግ ከፍተኛ ነው (ከ1ቆሮ 13፥1-3 ጋር ያነጻጽሩ)።
21፥18 **እጅህን ትዘረጋለህ፤** ይህ ሐረግ ጴጥሮስ እንዴት ባለ አሟሟት እግዚአብሔርን ሊያከብር እንዳለው ያመለክታል። ጴጥሮስ በኔሮ ዘመነ መንግሥት ጳውሎስ በተሠዋበት ዘመን አካባቢ (67-68 ዓ.ም. ገደማ) በሮም እንደተሰቀለ የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ያመለክታል። ጌታው በተሰቀለበት ተመሳሳይ ሁኔታ መሰቀል እንደማይገባው በመቃወሙም በራሱ ቁልቁ ተዘቅዝቆ እንደተሰቀለ ትውፊቱ ይገልጻል።

# የኢየሱስ አገልግሎት

## የአገልግሎቱ ጅማሬ ዘመን

| ሁነት | ቦታ | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| ኢየሱስ ተጠመቀ | ዮርዳኖስ ወንዝ | 3፥13-17 | 1፥9-11 | 3፥21-23 | 1፥29-39 |
| ኢየሱስ በሰይጣን ተፈተነ | ምድረ በዳ | 4፥1-11 | 1፥12-13 | 4፥1-13 | |
| የኢየሱስ የመጀመሪያ ታምር | ቃና | | | | 2፥1-11 |
| ኢየሱስና ኒቆዲሞስ | ይሁዳ | | | | 3፥1-21 |
| ኢየሱስ ከአንዲት ሳምራዊት ሴት ጋር ተነጋገረ | ሰማርያ | | | | 4፥5-42 |
| ኢየሱስ የአንድ ባለሥልጣንን ልጅ ፈወሰ | ቃና | | | | 4፥46-54 |
| የናዝሬት ሰዎች ኢየሱስን ለመግደል ሞከሩ | ናዝሬት | | | 4፥16-31 | |

## እውቅናንና ተቀባይነትን የማግኘት ዘመን

| ሁነት | ቦታ | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| ኢየሱስ አራት ዓሣ አጥማጆችን ጠራ | የገሊላ ባሕር | 4፥18-22 | 1፥16-20 | 5፥1-11 | |
| ኢየሱስ የጴጥሮስን አማት ፈወሰ | ቅፍርና-ሆም | 8፥14-17 | 1፥29-34 | 4፥38-41 | |
| ኢየሱስ በገሊላ መስበክ ጀመረ | ገሊላ | 4፥23-25 | 1፥35-39 | 4፥42-44 | |
| ማቴዎስ ኢየሱስን ለመከተል ወሰነ | ቅፍርና-ሆም | 9፥9-13 | 2፥13-17 | 5፥27-32 | |
| ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት መረጠ | ገሊላ | 10፥2-4 | 3፥13-19 | 6፥12-15 | |
| ኢየሱስ "የተራራው ስብከትን" ሰበከ | ገሊላ | 5፥1—7፥29 | | 6፥20-49 | |
| አንዲት ኀጢአተኛ ሴት ኢየሱስን ሽቶ ቀባች | ቅፍር-ናሆም | | | 7፥36-50 | |
| ኢየሱስ በድጋሚ በገሊላ አለፈ | ገሊላ | | | 8፥1-3 | |
| ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት በምሳሌ አስተማረ | ገሊላ | 13፥1-52 | 4፥1-34 | 8፥4-8 | |
| ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አሰኘ | የገሊላ ባሕር | 8፥23-27 | 4፥35-41 | 8፥22-25 | |
| የኢያኢሮስ ልጅ ከሞት ተነሣች | ቅፍርና-ሆም | 9፥18-26 | 5፥21-43 | 8፥40-56 | |
| ኢየሱስ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ላከ | ገሊላ | 9፥35—11፥1 | 6፥6-13 | 9፥1-6 | |

# የኢየሱስ አገልግሎት

የተቃውሞ ዓመት

| ሁነት | ቦታ | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| መጥምቁ ዮሐንስ በሄሮድስ ተገደለ | በይሁዳ በሚገኝ በአንድ ማካኤረስ በተባለ ወህኒ ቤት ውስጥ | 14፥1-12 | 6፥14-29 | 9፥7-9 | |
| ኢየሱስ 5000 ሰዎችን ሕዝብ መገበ | ቤተሳይዳ | 14፥13-21 | 6፥30-44 | 9፥10-17 | 6፥1-14 |
| ኢየሱስ በውሃ ላይ ተራመደ | የገሊላ ባሕር | 14፥22-23 | 6፥45-52 | | 6፥16-21 |
| ኢየሱስ 4000 ሰዎችን መገበ | የገሊላ ባሕር | 15፥32-39 | 8፥1-9 | | |
| ጴጥሮስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መሰከረ | ፊልጶስ ቂሣርያ | 16፥13-20 | 8፥27-30 | 9፥18-21 | |
| ኢየሱስ ስለሞቱ አስቀድሞ ተናገረ | ፊልጶስ ቂሣርያ | 16፥21-26 | 8፥31-37 | 9፥22-25 | |
| ኢየሱስ ተለውጦ በክብር ታየ | የአርሞንዔም ተራራ | 17፥1-13 | 9፥2-13 | 9፥28-36 | |
| ኢየሱስ የራሱን መቅደስ ግብር ከፈለ | ቅፍርናሆም | 17፥24-27 | | | |
| ኢየሱስ በአይሁድ የዳስ በዓል ላይ ተገኘ | ኢየሩሳሌም | | | | 7፥11-52 |
| ኢየሱስ ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የነበረን ሰው ፈወሰ | ኢየሩሳሌም | | | | 9፥1-41 |
| ኢየሱስ ማርያምንና ማርታን ጎበኘ | ቢታንያ | | | 10፥38-42 | |
| ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት አስነሣ | ቢታንያ | | | | 11፥1-44 |
| ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም የመጨረሻ ጉዞ አደረገ | ገሊላ እና ሰማርያን በሚያዋስ-ነው መንገድ ላይ | | | 17፥11 | |
| ኢየሱስ ሕፃናትን ባረከ | በዮርዳኖስ ማዶ | 19፥13-15 | 10፥13-16 | 18፥15-17 | |
| ኢየሱስ ከአንድ ባለጠጋ ሰው ጋር ተነጋገረ | በዮርዳኖስ ማዶ | 19፥16-30 | 10፥17-31 | 18፥18-30 | |
| ኢየሱስ በድጋሚ ስለሞቱ ተነበየ | በዮርዳኖስ አጠገብ | 20፥17-19 | 10፥32-34 | 18፥31-34 | |
| ኢየሱስ ዕውሩ በርጤሜዎስን ፈወሰ | ኢያሪኮ | 20፥29-34 | 10፥46-52 | 18፥35-43 | |

# የኢየሱስ አገልግሎት

## የተቃውሞ አመት (ካለፈው የቀጠለ)

| ሁነት | ቦታ | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| ኢየሱስ ከዘኬዎስ ጋር ተነጋገረ | ኢያሪኮ | | | 19፥1-10 | |
| ኢየሱስ ማርያምና ማርታን በድጋሚ ጎበኘ | ቢታንያ | | | | 11፥55—12፥1 |

## የመጨረሻው ሳምንት

| ሁነት | ቦታ | ዕለት | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የኢየሱስ በታላቅ ክብር ታጅቦ ወደ ከተማ መግባት | ኢየሩሳሌም | እሁድ | 21፥1-11 | 11፥1-10 | 19፥29-44 | 12፥12-19 |
| ኢየሱስ የበለሲቱን ዛፍ ረገመ | ኢየሩሳሌም | ሰኞ | 21፥18-19 | 11፥12-14 | | |
| ኢየሱስ ቤተመቅደሱን ከወንበዴዎች አጸዳ | ኢየሩሳሌም | ሰኞ | 21፥12-13 | 11፥15-18 | 19፥45-48 | |
| ኢየሱስ ሥልጣኑ ከየት እንደ ሆነ ተጠየቀ | ኢየሩሳሌም | ማክሰኞ | 21፥23-27 | 11፥27-33 | 20፥1-8 | |
| ኢየሱስ በቤተመቅደስ አስተማረ | ኢየሩሳሌም | ማክሰኞ | 21፥28—23፥29 | 12፥1-44 | 20፥9—21፥4 | |
| የኢየሱስ እግር በሽቶ ተቀባ | ቢታንያ | ማክሰኞ | 26፥6-13 | 14፥3-9 | | 12፥2-11 |
| በኢየሱስ ላይ የተጠነሰሰው ሴራ | ኢየሩሳሌም | ረቡዕ | 26፥14-16 | 14፥10-11 | 22፥3-6 | |
| የመጨረሻው እራት | ኢየሩሳሌም | ሐሙስ | 26፥17-29 | 14፥12-25 | 22፥7-20 | 13፥1-38 |
| ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን አጽናና | ኢየሩሳሌም | ሐሙስ | | | | 14፥1—16፥33 |
| የኢየሱስ ሊቀ ካህናዊ ጸሎት | ኢየሩሳሌም | ሐሙስ | | | | 17፥1-26 |
| ጌቴሴማኒ | ኢየሩሳሌም | ሐሙስ | 26፥36-46 | 14፥32-42 | 22፥40-46 | |
| ኢየሱስ ታስሮ ፍርድ ሸንጎ ፊት ቀረበ | ኢየሩሳሌም | ዓርብ | 26፥47—27፥26 | 14፥43—15፥15 | 22፥47—23፥25 | 18፥2—19፥16 |
| የኢየሱስ መስቀልና መሞት | ጎልጎታ | ዓርብ | 27፥27-56 | 15፥16-41 | 23፥26-49 | 19፥17-30 |
| የኢየሱስ መቀበር | በአትክልት ቦታ ውስጥ የሚገኝ መቃብር | ዓርብ | 27፥57-66 | 15፥42-47 | 23፥50-56 | 19፥31-42 |

# የኢዩሱስ አገልግሎት

## ከትንሳኤው በኋላ ኢየሱስ መገለጡ

| ሁነት | ቦታ | ዕለት | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ሐዋ ሥራ | 1ቆሮንቶስ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በባዶው መቃብር | ኢየሩሳሌም | የትንሣኤው ዕለት እሑድ | 28፥1-8 | 16፥1-8 | 24፥1-12 | 20፥1-10 | | |
| በአትክልት ስፍራ ውስጥ ለመግደላዋት ማርያም | ኢየሩሳሌም | የትንሣኤው ዕለት እሑድ | | 16፥9-11 | | 20፥11-18 | | |
| ለሌሎች ሴቶች | ኢየሩሳሌም | የትንሣኤው ዕለት እሑድ | 28፥9-10 | | | | | |
| ወደ ኤማሁስ ይጓዙ ለነበሩ ሁለት ሰዎች | ወደ ኤማሁስ በሚወስድ መንገድ ላይ | የትንሣኤው ዕለት እሑድ | | 16፥12-13 | 24፥13-32 | | | |
| ለጴጥሮስ | ኢየሩሳሌም | የትንሣኤው ዕለት እሑድ | | | 24፥34 | | | 15፥5 |
| ለዐሥሩ ደቀ መዛሙርት በቤት ውስጥ | ኢየሩሳሌም | የትንሣኤው ዕለት እሑድ | | | 24፥36-43 | 20፥19-25 | | |
| ለዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት በቤት ውስጥ | ኢየሩሳሌም | የትንሣኤው ዕለት እሑድ | | | 16፥14 | 20፥26-31 | | 15፥5 |
| ዓሣ በማጥመድ ላይ ለነበሩ ሰባት ደቀ መዛሙርት | የገሊላ ባሕር | ከጥቂት ቀናት በኋላ | | | | 21፥1-25 | | |
| ለዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት በተራራ ላይ | ገሊላ | ከጥቂት ቀናት በኋላ | 28፥16-20 | 16፥15-18 | | | | |
| ከአምስት መቶ ለሚበልጡ ሰዎች | አይታወቅም | ከጥቂት ቀናት በኋላ | | | | | | 15፥6 |
| ለያዕቆብ | አይታወቅም | ከጥቂት ቀናት በኋላ | | | | | | 15፥7 |

## ክትንሣኤው ብኋላ ኢየሱስ መገለጡ

| ሁነት | ቦታ | ዕለት | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ሐዋ ሥራ | 1ቆሮንቶስ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|

# የኢየሱስ አገልግሎት

## ከትንሳኤው በኋላ ኢየሱስ መገለጡ

| ሁነት | ቦታ | ዕለት | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ | ሐዋ ሥራ | 1ቆሮንቶስ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወደ ሰማይ ባረገ ዕለት ለደቀ መዛሙርት | ደብረ ዘይት | ከትንሣኤው ከአርባ ቀን በኋላ | | | 24፥44-51 | | 1፥3-9 | 15፥7 |
| ለጳውሎስ | ደማስቆ | ከብዙ ዓመታት በኋላ | | | | | 9፥1-19፤ 22፥3-16፤ 26፥9-18 | 9፥1፤ 15፥8 |

# የኢየሱስ ምሳሌዎች

| ምሳሌ | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ |
|---|---|---|---|
| እንቅብ የተደፋበት መብራት | 5፥14-15 | 4፥21-22 | 8፥16፣ 11፥33 |
| ብልኅና ሞኝ ቤት ሠሪዎች | 7፥24-27 | ... | 6፥47-49 |
| በአረጀ ልብስ ላይ የተጣፈ አዲስ ጨርቅ | 9፥16 | 2፥21 | 5፥36 |
| በአሮጌ አቁማዳ ውስጥ ያለ አዲስ ወይን ጠጅ | 9፥17 | 2፥22 | 5፥37-38 |
| ዘሪና የዐፈር ዐይነቶች | 13፥3-8፡18-23 | 4፥3-8፡14-20 | 8፥5-8፡11-15 |
| ዐረሞች | 13፥24-30፡36-43 | | |
| የሰናፍጭ ዘር | 13፥31-32 | 4፥30-32 | 13፥18-19 |
| እርሾ | 13፥33 | | 13፥20-21 |
| የተሰወረ ሀብት | 13፥44 | | |
| የከበረ ዕንቊ | 13፥45-46 | | |
| መረብ | 13፥47-50 | | |
| የአንድ ቤት ባለቤት | 13፥52 | | |
| የጠፋው በግ | 18፥12-14 | | 15፥4-7 |
| ይቅርታ የማያደርግ አገልጋይ | 18፥23-34 | | |
| የወይኑ አትክልት ሠራተኞች | 20፥1-16 | | |
| ሁለት ወንድ ልጆች | 21፥28-32 | | |
| የወይኑ አትክልት ገበሬዎች | 21፥33-44 | 12፥1-11 | 20፥9-18 |
| የሰርግ ግብዣ | 22፥2-14 | | |
| የበለስ ዛፍ | 24፥32-35 | 13፥28-29 | 21፥29-31 |
| ታማኝና ብልኅ አገልጋይ | 24፥45-51 | | 12፥42-48 |
| ዐሥር ቈነጃጅት | 25፥1-13 | | |
| መክሊቶች | 25፥14-30 | | 19፥12-27 |
| በጎችና ፍየሎች | 25፥31-46 | | |
| የሚያድግ ዘር | | 4፥26-29 | |
| ትጉ አገልጋዮች | | 13፥35-37 | 12፥35-40 |
| ገንዘብ አበዳሪ | | | 7፥41-43 |
| ደጉ ሳምራዊ | | | 10፥30-37 |
| መልካም ወዳጅ | | | 11፥5-8 |
| ሞኝ ሀብታም | | | 12፥16-21 |
| የማታፈራ የበለስ ዛፍ | | | 13፥6-9 |
| ዝቅተኛ መቀመጫ በግብዣ | | | 14፥7-14 |
| ትልቅ ግብዣ | | | 14፥16-24 |

| ምሳሌ | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ |
|---|---|---|---|
| ደቀ መዝሙርነት የሚያስከፍለው ዋጋ | | | 14፥28-33 |
| የጠፋው ገንዘብ | | | 15፥8-10 |
| የጠፋው ልጅ | | | 15፥11-32 |
| ብልኅ መጋቢ | | | 16፥1-8 |
| ሀብታሙ ሰውና አልዓዛር | | | 16፥19-31 |
| አገልጋይና ጌታው | | | 17፥7-10 |
| የማትታክት መበለት | | | 18፥2-8 |
| ፈሪሳዊና ቀረጥ ሰብሳቢው | | | 18፥10-14 |

## የኢየሱስ ታምራት

| | ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|---|
| **የፈውስ ታምራት** | | | | |
| ለምጽ ያለበት ሰው | 8፥2-4 | 1፥40-42 | 5፥12-13 | |
| የሮማዊው መቶ አለቃ አገልጋይ | 8፥5-13 | | 7፥1-10 | |
| የጴጥሮስ አማት | 8፥14-15 | 1፥30-31 | 4፥38-39 | |
| በጌርጌሴኖን የነበሩ ሁለት ሰዎች | 8፥28-34 | 5፥1-15 | 8፥27-35 | |
| ሽባው ሰው | 9፥2-7 | 2፥3-12 | 5፥18-25 | |
| ደም የሚፈሳት ሴት | 9፥20-22 | 5፥25-29 | 8፥43-48 | |
| ሁለት ዐይነስውር ሰዎች | 9፥27-31 | | | |
| በአጋንንት የተያዘ ዲዳ ሰው | 9፥32-33 | | | |
| እጁ የሰለለች ሰው | 12፥10-13 | 3፥1-5 | 6፥6-10 | |
| በአጋንንት የተያዘ ዕውርና ዲዳ ሰው | 12፥22 | | 11፥14 | |
| የአንዲት ከነናዊት ሴት ልጅ | 15፥21-28 | 7፥24-30 | | |
| በአጋንንት የተያዘ ልጅ | 17፥14-18 | 9፥17-29 | 9፥38-43 | |
| ሁለት ዐይነ ስውራን (በርጤሜዎስን ጨምሮ) | 20፥29-34 | 10፥46-52 | 18፥35-43 | |
| ዲዳና ደንቆሮ ሰው | | 7፥31-37 | | |
| በአጋንንት የተያዘ ሰው -በምኩራብ ውስጥ? | | 1፥23-26 | 4፥33-35 | |
| በቤተሳይዳ የነበር አንድ ዐይነስውር | | 8፥22-26 | | |
| ጎባጣ ሴት | | | 13፥11-13 | |
| ሆዱ የተነፋ ሰው | | | 14፥1-4 | |
| ዐሥር ለምጻሞች | | | 17፥11-19 | |
| የሊቀ ካህናቱ አገልጋይ | | | 22፥50-51 | |
| የአንድ ባለሥልጣን ልጅ በቅፍርናሆም | | | | 4፥46-54 |
| በቤተሳይዳ መጠመቂያ የነበረ አንድ ሕመምተኛ ሰው | | | | 5፥1-9 |
| ዐይነስውር ሆኖ የተወለደ ሰው | | | | 9፥1-7 |
| **በተፈጥሮ ላይ የተደረጉ ታምራት** | | | | |
| ማዕበሉን ፀጥ ማሰኘት | 8፥23-27 | 4፥37-41 | 8፥22-25 | |
| በውሃ ላይ መራመድ | 14፥25 | 6፥48-51 | | 6፥19-21 |
| 5000 ሕዝብ መመገብ | 14፥15-21 | 6፥35-44 | 9፥12-17 | 6፥5-13 |
| 4000 ሕዝብ መመገብ | 15፥32-38 | 8፥1-9 | | |
| ከዓሣ ውስጥ የተገኘው ገንዘብ | 17፥24-27 | | | |
| የበለሲቱ ዛፍ መድረቅ | 21፥18-22 | 11፥12-14፡20-25 | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **በተፈጥሮ ላይ የተደረጉ ታምራት (ካለፈው የቀጠለ)** | | | | |
| ብዙ ዓሦችን በአንድ ጊዜ ማጥመድ | | | 5፥4-11 | |
| ውሃን ወደ ወይን ጠጅ መለወጥ | | | | 2፥1-11 |
| በድጋሚ ብዙ ዓሦችን በአንድ ጊዜ ማጥመድ | | | | 21፥1-11 |
| የኢያኢሮስ ሴት ልጅ | 9፥18-19፡ 23-25 | 5፥22-24፡ 38-42 | 8፥41-42፡ 49-56 | |
| በናይን የነበረችው መበለት ወንድ ልጅ | | | 7፥11-15 | |
| አልዓዛር | | | | 11፥1-44 |

## ሐዋርያት ያደርጉዋቸው ታምራት

| ታምር | የሐዋርያት ሥራ |
|---|---|
| በጴጥሮስ የተፈወሰ ሽባ ሰው | 3፥6-9 |
| የሐናንያና ሰጲራ ሞት | 5፥1-10 |
| የሳውል ዐይን መፈወስ | 9፥17-18 |
| የኤንያ መፈወስ | 9፥33-35 |
| የዶርቃ ከሞት መነሣት | 9፥36-41 |
| የኤልማስ መታወር | 13፥8-11 |
| በጳውሎስ የተፈወሰ ሽባ ሰው | 14፥8-10 |
| አጋንንት የወጣላት ልጃገረድ | 16፥16-18 |
| የአውጤኪስ ከሞት መነሣት | 20፥9-10 |
| የጳውሎስ በእፉኝት አለመጐዳት | 28፥3-5 |
| የፑፕልዮስ አባት መፈወስ | 28፥7-9 |